ሕይወተ ማርያም ድንግል

አዘጋጅ፡- ሊቀ ሊቃውንት ስምዐ ኮነ መላክ
በምዕራብ ጎጃም ሀገረ ስብከት የፀዱ ገባኤያት መምህር

፳፻፯ ዓ.ም

ምስጋና

አመስጋኝ ሳይኖር ጥንት በሌለው ባሕርያዊ ምስጋና ሲመሰገን የኖረ፤ ከፍጡራንም መፈጠር በኋላ ያለማቋረጥ የሚያመሰግኑ እላታውያን ፍጥረታትን በሰማይ የሠራ፤ ሥጋዊ ደማዊው ፍጥረት የሚያቀርበውን ምስጋና አርምሞና ፅርዓት በሌለው ልሳን ከቀረበው ከሰማያውያኑ ማኅሌት ይልቅ ወደ የሚቀበል ስለልዕልናው በሰማይ የሚኖር የተባለለት እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ።

ንጹሐት ክቡራት በሆኑ እጆቹ ንጹሕ አድርጎ የሠራት፣ በልጅነት አንደበቴ ‹‹እንተ ይዕቲ ስምዕዩ ማርያም ጽዮን›› ብየ አፈን በስሚ የፈታሁባት፣ በቆሎ ተማሪነቴ ዘመን የኑሮ መሠረቴ፣ በመምህርነቴ ዘመን ሞገሰ ስብከቴ፣ በኂለኛውም ዓለም ተስፋ ድኅነቴ ለሆነችልኝ እስካሁን ባለችው ዘመኔ ሁሉ ምግብ በሆነኝ በታላቁ ስሟ መጽሐፍ እንዳዘጋጅ ለረዳችኝ ለንግሥተ ሰማይ ወምድር ለእመቤቴ ለድንግል ማርያም ምስጋናዬን አቀርባለሁ። ባለማወቅ ያጣመምኩትን በማቃናት፣ በስህተት ያለፍኩትን በማሳየት ከንሥር በተሻለ እይታ መጽሐፉን የፈታተሹልኝ፣ በጣም ጠባብ በሆነች ጊዜአቸው የኔን የታናሹን ልጃቸውን መጽሐፍ ተመልክተው እርማትና ማስተካከያን ላደረጉልኝ ታላቁ አባቴ ለብፁዕ አቡነ አብርሃም ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። ብፁዕ ሆይ! ልጅ አባቱን የሚመርቅ ቢሆን ኖሮ ለዚች ቤተ ክርስቲያን ሲል እግዚአብሔር የማቱሳላን ዕድሜ ይሰጥልኝ ብልዎት ደስ ባለኝ ነበር።

በሁሉም በታና ጊዜ አባት ለልጁ ከሚያደርገው በላይ በሆነ ፍቅር እንክብካቤአቸው ላልተለየኝ እንደ አባትነታቸው በመምከር እንደ መምህርነታቸው በማስተማር ባዶነቴን ለሞሉልኝ ለመላከ ሰላም ኤፍሬም መ·ሱዓለም የምዕ/ጎጃም ሀ/ስ/ ዋና ሥራ አስኪያጅ እና ለታላቁ ሊቅ ለሊቀ ማዕምራን ደጉ ዓለም እግዚአብሔር ረጅም ዕድሜና ጤናን እንዲሰጥልኝ ተመኝቻለሁ።

ፊደላቴን በየቦታቸው ያስቀመጡልኝ መምህር ማዕበል ፈጠነ፤ ቤታቸውን ኮምፒዩተራቸውን ለጽሕፈት አገልግሎት እንድጠቀምበት ሙሉ ፈቃድ የሰጡኝ አቶ ይታያል ዓለሙንና ባለቤቱን ወይዘሮ ጸጋነሽ መኮንን፤ በሌላው ሁሉ የደገፋችሁኝን እግዚአብሔር በሕይወት መጽሐፍ ላይ ስማችሁን ይጸፍልኝ ከማለት በስተቀር ሌላ ምን አላለሁ።

መታሰቢያነቱ

1ኛ በምናኔአቸው ከእንጦንስና ከመቃርስ የሚተካከሉ፤ በሊቅነታቸው በላኤ መጻሕፍት የተባሉ፤ እንደ መምህር እያስተማሩ፣ እንደ መነኮሳት እየጸለዩ እስከ ሕይወታቸው ፍጻሜ ቤተ ክርስቲያኒቱን ላገለገሉት በዚህ ዓለም ላሉ ከእመቤታችን ጋር ቃል በቃል የተነጋገሩ፤ ቤተ ክርስቲያን በማዕከል ደረጃ ለምታዘጋጃቸው መጻሕፍት ተጠያቂ ለነበሩ ንጹሕ ባሕታዊ ለታላቁ ሊቅ መምህረ ሰላም ዲበኩሉ አምባዬ፤

2ኛ እግዚአብሔርን ማወቅ ለጀመርኩባት፣ አስራትና በኩራቷን ተመግቤ ላደግሁባት የትውልድ ስፍራዬ፣ የዕውቀት አቡጊዳዬ ለሆነችው ደብረ መዊዕ አውንት (መንዝ) ቅዱስ ሚካኤል ደብር ትሁንልኝ።



መምህረ ሰላም ዲበኩሉ አምባዬ

ከ _____

ለ _____

መግቢያ

እግዚአብሔር ለፈጠረው ፍጥረት የሰጠውን ጸጋ ተናግሮ መጨረስ አይቻልም ይልቁንም ለሰው ልጅ ያለው ፍቅር ታላቅ ከመሆኑ የተነሣ ከጸጋው አንዳች ሳያሳድል ከሁሉም ፍጥረት በስተመጨረሻ ብቅ እንዲል አደረገው፤ ምንም እንኳን ወደ ኋላ ቢመጣም በክብር ግን የሚቀድመው አንዳች ፍጥረት ሳይገኝ ቀረ፤ ይህ ቀረሀ የማይባል ባለ ሙሉ ጸጋ ሆኖ ተፈጠረ። ዳሩ ግን እንዲህ ሆኖ መቀጠል ባለመቻሉ ወደ ፍዳው ምድር እንዲወርድ ግድ ሆኖበታል፤ ጥላቻ ይጥላል ፍቅር ያነሣልና መውረዱ በጥል ምክንያት ቢሆንም ፍቅር አነሣው፤ ለዚህ ደግሞ ምክንያት እንድትሆን ከራሱ ከአዳም ባሕርይ የተቀዳች እመቤታችን ድንግል ማርያምን ለመረጠው ሥራ ለየለት፤ አዳማዊ በደልና ርኩሰት እንዳይደርስባት ከመጠበቅም በላይ በዚህ ስም የሚጠሩትን እንኳን ይገሥጻቸው ነበር፤ የሙሴ እህት ማርያም ተብላ ብትጠራ በለምጽ ቀጣት፣ ማርያም መግደላዊትን ሰባት አጋንንትን አሳደረባት እንዲህ እያለ ይህን ስም ለእመቤታችን ብቻ ተጠብቆ እንዲኖር ያደርግላት ነበር።

ንጉሥ ለዙፋኑ የክብሩ መገለጫ ነውና እጅግ እንዲቀና ፈጣሪያችን እግዚአብሔርም ዙፋኑ ናትና እጅግ ይቀናላታል። ለዚህ ነው ነቢዩ ሕዝቅኤል ባየው ራእይ ውስጥ አዳራሷን ከበው የቆሙ ቁራዎችን መላክ በሰይፍ እያጨደ ሲጥላቸው የተመለከተው፤ ሕዝ 44÷1 አዳራሷ በአዲስ መቆለፊያ የተቆለፈች አዲስ ናት ነቢዩ ካየው ቀይ ጎልማሳ በስተቀር ሌላ ማንም ወደ ውስጧ እንዳይገባ እግዚአብሔር ከልክሏል፤ ነገር ግን ቁራ ገብቶ ሊያበላሽና ሊያፈርስ ፈለገ መላኩን ልኮ በሰይፍ ቀጣው፤ ይህች አዳራሽ በእውነት ከኖኅ መርከብ ትበልጣለች፤ በኖኅ መርከብማ የሚበሉትም የማይበሉትም ተሰብስበውባታል ኖኅ ብቻ አይደለም ሌሎችም ለባት ሰዎች አብረውት ተጠልለውባታል፤ በዚች አዳራሽ ውስጥ ግን ከኃያላን ጌታ በስተቀር ማንም እንዳይገባ በፅኑዕ መቆለፊያ አትሚታል፤በቁራ የተመሰለው ዲያብሎስ እንዳይቀርባት በሥልጣነ መንፈስቅዱስ አስጠብቋታል፤ የቀደመችውን ገነት እንኳን ሲዘጋ አዳም ተደፋፍሮ ከኃጢአቱ እንዳይገባ ወደ ሕይወት ዛፍ የሚያደርሰውን መንገድ በኪሩብ መላክ እንዲጠበቅ አድርጎት አይደል! ወደሕይወት ዛፍ የምታደርሰው መንገድ እኮ እመቤታችን ናት፤ የሕይወት ዛፍ ልጇ ክርስቶስ ነውና፤ ሁላችን ተመግበነው በሕይወት እንኖር ዘንድ አስጠብቆ እስከ ጊዜው ያቆየልን፤ ጊዜው ሲደርስ ግን እኔ የወይን ግንድ ነኝ ብሎ ዮሐ 15÷1 ራሱን የገለጠልን በኃጢአት ሳሉ ሊመገቡት የማይገባ፣ በኃጢአት ሳሉ ቢመገቡት ፍርድን የሚያመጣ እውነተኛ የጽድቅ ምግብ ነው 1ቆሮ 11÷31

ንግሥቲቱ የወርቅ መጎናፀፊያዋን ለብሳ በቀኝ ትቀመጣለች ብሎ እስኪገልጣት ድረስ የመንፈስቅዱስ ጥበቃ ያልተለያት የዲያብሎስ ሽንገላ ያልተቃወማት ንጽሕት ናትና ከፍጥረት ሁሉ በላይ ክብሯን ከፍ አድርገን እንናገርላታለን፤ የዛሬውን አያድርገውና በሀገራችን የበሉበት እቃ እንኳን ክቡር ነው፤ እመቤታችን ደግሞ ከዚያ በላይ

የሕይወት እንጀራን ያስገኘችልን የኤልያስ መሶብ ወርቅ ናት 1ነገ 19÷5 ስለዚህ እንወዳታለን እናከብራታለን፤ እንዲያውም ክብሯን ለመግለጥ ቢያቅተን እንዲያው ለጥ ብለን እንሰግድላታለን ለፍጡር አይሰገድም የሚለኝ እንዳይኖር፤ እንኳን ማደሪያው ለሆነች እመቤት እግሮቹ ለቆሙበት ሥፍራ እንኳን እንድሰግድ በመጽሐፍ ታዝሜለሁና መዝ131÷7

እንግዲህ ምን እንላለን ሕዝቅኤል ያያትን አዳራሽ ቁራዎች ቢከቧት ምን አደረጉ፤ እንዲያው እነሱ እየታጨዱ ወደቁ እንጅ፤ ዛሬም የእመቤታችንን ክብር ያቃለልን መስሏቸው ተረፈ ቁራዎች ዙሪያዋን ከበው መጽሐፍ ይጽፋሉ፣ንግግር ያደርጋሉ ግን በአዳራሿ ላይ ቅንጣት ታክል ነውር መጨመር እንደማይችሉ የምናገርበት አጋጣሚ ቢሆነኝ ብዬ እኔም አባቶቼ ስለእመቤታችን ከተናገሩት የውዳሴ ውቅያኖስ ቀድቼ እንደ ክብሯ ሳይሆን መንፈስ ቅዱስ በረዳኝ መጠን በማብዛት ያይደለ በማሳነስ፤ በማስረዘም ያይደለ በማሳጠር ጥቂት ቃላትን ተናግሬአለሁና እንድታነቡልኝ ‹‹በእንተ ስማ ለማርያም›› እላለሁ

ሊቀ ሊቃውንት ስምዐ ኮነ መላክ
በምዕራብ ጎጃም ሀገረ ስብከት የፀዩቱ ጉባኤያት መምህር

ማውጫ

ገጽ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ
1. ከዓለም በፊት የነበረ ሌላ ዓለም 6
2. ዓለም ስለ እመቤታችን 14
2.2. ሁለተኛው የሰማይ ክፍል 21
2.3. ጠፈር 26
2.4. የምድር ምሥጢራት 31
2.4.1. ታማኝ 37
2.4.1.2. ምሕረት ለማግለድ 41
2.4.1.3. ወላዲተ አምላክ ማእምንት 44
2.4.2. ሕይወት ያላቸው ፍጥረታት መገኛ መሆኗ 47
2.4.3. በአዲስ ሰማይና በአዲስ ምድር መተካቷ 54
3. ዔደን ገነት 58
3.1. ሁለቱ ጠባቂዎቿ 61
3.2. ሰባቱ የገነት ርስቶች 66
4. ቅድመ ጽንሰታ 73
5. እምፅንሰታ እስከ ልደታ 77
6. የእናት እና አባቷ ቤት 85
7. ከሦስት ዓመት በኋላ 89
8. አስራ አምስተኛው ዓመት 97
8.2. መታጨት 99
8.2.1. ከታጨችበት ጊዜ በኋላም ድንግል ሆና መገኘቷ 101
8.2.2. ዮሴፍ ዕለቱን ንግድ ተሸኝቶ ሚያደሩ 102

8.2.3. ለቅዱስ ገብርኤል በሰጠችው መልስ..... 102
8.2.3.3. ምጽአተ ሰብአ ሰገል ዘምስለ ብዙኅ አምኃ
የሰብአ ሰገል ከብዙ እጅ መንሻ ጋር መምጣት..... 105
8.2.4.በኀቱም ድንግልና ጸንሳ በኀቱም ድንግልና መውለድ..... 109
8.2.5. ብሥራተ መልአክን መስማት..... 111
9. ሞትና ሕይወት በሁለቱም ሔዋኖች.....119
10. የአዲስ ኪዳኑ አገልግሎት መጀመር.....122
11. ሊቃውንት ስለ ማሕጸነ ማርያም..... 123
11.1. ነጻነት.....129
11.2. ጌትነት.....131
12. መንፈስ ቅዱስ ስለ እመቤታችን.....134
12.1. ቅዱስ ገብርኤል.....134
12.2. ተናጋሪው ጽንስ.....137
12.3. በኤልሳቤጥ ቤት.....140
13. ከስድስት ወር በኋላ.....141
14. ሦስት ዓመት ከመንፈቅ.....143
14.1. ምጽአተ ዮሳ ወልደ ዮሴፍ.....146
14.2. ሁለቱ ወንበዴዎች ባገኙት ጊዜ.....147
14.3. ቤተ ኮቲባ..... 148
14.4. የልጇን ጫማ በወሰዱባት ጊዜ.....148
15. እመቤታችን በእለተ ዐርብ.....153
16. እመ አምላክ በቤተ ዮሐንስ 163
17. ጊዜ ዕረፍታ ለሶልያና.....166
18. በሦስተኛው ቀን መነሣቷ የሚያመጣው ችግር.....170
ዋቢ መጻሕፍት 176

ምዕራፍ ፩

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ

ከዓለም በፊት የነበረ ሌላ ዓለም

ዓለም ስንል ሁሉም ፍጥረት ትዝ የሚለው ለሚታየውና ለማይታየው ፍጥረት ማደሪያ የሆኑ ሰማይና ምድር ናቸው። ሰማያውያኑም ሆኑ ምድራውያኑ በእነዚህ የተወሰኑ፣ በእነዚህ ዓለማት የሚያድሩ ናቸው። አንዱ ወደ ሌላው ገብቶ፣ ከተወሰነለት አልፎ እንዳይኖር እግዚአብሔር በልዩ ጥበቡ አትሞታል። እናም፡- ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ከነዚህ አንዱም ስንኳ የሰማዩ ወደ ምድር ወርዶ፣ የምድሩም ወደ ሰማይ ወጥቶ የኖረበት ታሪክ የለውም።

በምድር ላይ ስንኪን የሚኖሩት የባሕሩ በባሕር፣ የየብሱም በየብስ ይኖራሉ እንጂ ከነዚህ ማንም በገዛ ፈቃዱ በወደደው መኖር እንዳይችል ጥበበ እግዚአብሔር ትከለክለዋለች። ብሔሞትና ሌዋታን የራሳቸውን ዓለም ትተው ወደ እኛ ዓለም መጥተው ለመኖር ጥበበ እግዚአብሔር ማኅተም ባይሆንባቸው ኖሮ ማን በፊታቸው ይቆም ነበር።

ነገር ግን አምላካችን ድንቅ ነው! ይዜን ሁሉ ከመሆኑ አስቀድሞ ያውቃልና ሁሉንም ያለ ማኅተም አላኖረውም። እኛም ይህን አይተን በኅብረት ድምፃችንን አንሥተን " ወኵሉ በጥበብ ገበርከ ፤ ሁሉን በጥበብ አዘጋጀህ ብለን ለጥበበኛው ሠራተኛ ዘመርንለት።አንዱ የሚኖርበት ዓለም ለአንዱ የማይመች ወይም የተከለከለ ዓለም ቢሆንም አንዱ ያለ አንዱ ድጋፍ ግን መኖር በፍጹም አይችልም። እኛ በምናውቀውም ሆነ በማናውቀው ሕግ ሥነ ፍጥረታት እርስ በርሳቸው ይደጋገፋሉ፣አንዱ ለአንዱ የሕይወት ስጦታን ይሰጣሉ። ሰው እነርሱን ይጠብቃል ይንከባከባል፣ ያበጃጃል፣ እነርሱም ደግሞ ለሰው በምግብነት፣ ዕውቀት

በመሆን ፣እንዲሁም ሕይወትን በመስጠት ያገለግሉታል። እነዚህ ሁሉ ዓለማት ማለትም በስም የምናውቃቸውም ሆነ የማናውቃቸው፣ የተማርናቸውና ያልተማርናቸው፣ ሕይወት ያለው ፍጥረት ሁሉ የሚርመሰመስባቸው ዓለማት በእግዚአብሔር ፈቃድ የተዘጋጁ ናቸው።

ታዲያ እነዚህ ሁሉ ከመኖራቸው በፊት ምን ነበረ? ከተባለ የነበረው፡- ዓለማት የማያስፈልጉት፣ዓለማት ባይኖሩም ያለ ዓለማት መኖር የሚቻለው ጌታ ነው። እርሱ የዓለማት ዓለማቸው ሲሆን ዓለማትን ይወስናቸዋል እንጂ እርሱን ዓለማት አይወስኑትም። የዓለማት ዓለማቸው ጌታ ከዓለማት መፈጠር፣ ከፀሐይና ከጨረቃ፣ ከክዋክብትም መኖር በፊት ከንጋትና ከማለዳም፣ ከቀንና ከሌሊት፣ ከመላእክት መፈጠርም በፊት እርሱ በመንግሥቱ ነበረ። ተገዥ ሳይኖር ገዥ ሆኖ፣ ያነገሠው ሳይኖር ንጉሥ ሆኖ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ነበረ። ከእዚህ ሁሉ ጋር የአዲሱ ዓለም እናት የታናሹም የታላቁም፣ የሕያዋኑና የሙታኑ፣ የረቂቃኑና የግዙፋኑ ፍጥረታት መኖሪያ የሆነች ከዚህ እስካሁን ስንለው ከነበርነው የተለየች ሌላ ዓለም አለች። ይህ ዓለም ከመታሰቡ አስቀድሞ ሁሉን በማይዘነጋው በአምላክ ህሊና ታስባ ትኖር ነበር። ያረጀውን ዓለም መልሶ ሊያድስባት፣ የጠፋውን ፍጥረት መልሶ ሊፈጥርባት፣ በኃጢአት ምክንያት ለተሰደዱትና መኖሪያ አልባ ለሆኑት መኖሪያ ሊያደርጋት የተዘጋጀች ሌላ ዓለም ናት። ጻድቃን ሰማዕታት፣ ነቢያትና ሐዋርያት የተሰኙት ደናግልና መነኮሳቱ የተገኙባትና ዛሬም ለዘለዓለም የሚኖሩባት፣ እግዚአብሔር ለማረፊያነት የተመኛት ልዩ ዓለም ናት። በእርሷ ዘንድ ሞት የለም፣ ሐዘንና ድካምም አይታይም ምክንያቱም ደስ ብሏቸው የሚኖሩት የቅዱሳን ማደሪያ ሆናለችና። በአምላክ ጎሊና የታሰበች፣ ለዚህ

ዓለም ለመዳኑ ብቻ ሳይሆን ለመፈጠሩም ምክንያት የሆነችው ይህች ዓለም እመቤታችን ድንግል ማርያም ናት።

ይህን የመለኮት ሐሳብ ሲገልጽ የተአምረ ማርያም መቅድም ጸሐፊ የሚከተለውን ተናግሯል። "እግዝእትነ ማርያም ነበረት እምቅድመ ዓለም በጎሊና አምላክ፣ እመቤታችን ማርያም ከዓለም መፈጠር በፊት በአምላክ ጎሊና ታስባ ትኖር ነበር"። ደራሲው በጥቅሉ ዓለም ብሎ የጠራውን በሦስት ከፍለን ልንተረጉመው እንችላለን።

1ኛ ቀደም ሲል እንደገለጽነው የመጀመሪያው የዓለም ትርጉም የሚታየውንና የማይታየውን፣ ማኅደረ ፍጥረት የሆነውን ዓለም የሚያመላክት ነው። ይህ ዓለም ከመፈጠሩም በፊት እርሷ ታስባ ትኖር ነበር ተብሎ መነገሩ ለዓለመ መፈጠር ምክንያት መሆኗን ለመናገር ነው። እንኳን ለዚህኛው ለወዲያኛው ዓለም መሪያችን እርሷ አይደለች እንዴ። ለዚህም እኮ ነው ሊቃውንቱ የስሟን ትርጓሜ ሲናገሩ "ማርያም ብሂል መርሕ ለመንግሥተ ሰማያት፣ ማርያም ማለት መንግሥተ ሰማያት መርታ የምታስገባ ማለት ነው ብለው የተረጐሙት።

በአምላክ ጎሊና መታሰቧ፡- ለዓለማችን መፈጠር፣ መፈጠሯ፡ - መንግሥተ ሰማያት ለተሰኘው ዓለማችን መኖር ቀዳሚ ነው። ምክንያቱም ጌታ ከእርሷ ከተወለደ በኋላ ነውና መንግሥተ ሰማያት የተሰኘው ዓለም መኖሩንና ለኛ የተሰጠን መሆኑን የተነገረን ማቴ 25፥34 ሰማያዊውን ዓለም ለመውረሳችን እመቤታችን ምክንያት ከሆነችን በእውነት እመቤታችን ለዚህ ዓለም መፈጠርም ምክንያት ናት። እመቤታችን እኮ ለበሽተኛው ዓለም መድኃኒት ሆና የተዘጋጀች የአምላክ በጐ ጎሊና ናት።

አምላካችን እንደ በጎ እናት እኛን ከመፍጠሩ አስቀድሞ የሚደርስብንን ያውቃልና ዓለሙን ሲፈጥረው የሚያድንበትን ካዘጋጀ በኋላ ነው የፈጠረው። መልካም እናት በማሕጸኗ ላለ ልጇ ወደ ዓለም ከመምጣቱ በፊት ይህን ለልጇ ብላ ታስብ የለ። ታዲያ በእግዚአብሔር መጽሐፍ ስለ እመቤታችን ሲነገር "በአምላክ ጎሊና ታስባ ትኖር ነበር" ቢባል ምን ይገርማል? ካህኑ ዕዝራ ከዓለም በፊት የነበረውን የአምላክ ሐሳብ ሲገልጽ የላይኛውና የታችኛው ዓለም ከመፈጠሩ አስቀድሞ የአምላካችን ሰው መሆን በአምላክ ጎሊና ታስቦ ነበር ይላል ሱቱ 4÷1 በታላቁ የእግዚአብሔር መጽሐፍ ሰው መሆኑ ከዓለም በፊት ታስቦ የነበረ ከሆነ ሰው ይሆንባት ዘንድ ለተዋሕዶ የመረጣት ድንግል ማርያምም ከዓለም በፊት የተመረጠች መሆኗ አጠራጣሪ ጉዳይ አይደለም።

ሌላው የእግዚአብሔር ነቢይ ቅዱስ ዳዊትም ይህን ሲያረጋግጥልን "ወለድኩከ እምከርሰ እምቅድመ ኮከበ ጽባሕ ፤ ከአጥቢያ ኮከብ አስቀድሞ ከባሕርዬ ወለድኩህ መዝ 109፥ 3 ብሏል፤ በሥጋ ለቀዳማዊ ቃል አባቱ ነውና። ማቴ1÷1፣ዮሐ1÷1በእውነት ነቢዩ ይህንን መናገሩ ከአጥቢያ ኮከብ በፊት ነበርን? ያሉ እንደሆነ እግዚአብሔር ከዓለም መዘጋጀት አስቀድሞ የወሰነለትን መናገሩ እንጂ ከክዋክብት መፈጠር በፊትስ ሰው አልነበረም። ምንም እንኳን የሰው ተፈጥሮ ከክዋክብት በኋላ ቢሆንም ክርስቶስ ወልደ ዳዊት ተብሎ ሲጠራ ከክዋክብት በፊት ለነበረው ጌታ አባት በመሆኑ ከዓለም በፊት የነበረ አድርጎታል። ይህ ሁሉ አስቀድሞ በአምላክ ጎሊና የተዘጋጀ ነበር። እግዚአብሔር ይህን ዓለም ለፍጥረታቱ ሲያዘጋጅ ለክብሩ መገለጫ ትሆን ዘንድ ያዘጋጃት ሌላኛይቱ ዓለም ደግሞ እመቤታችን ድንግል ማርያም ናት። እግዚአብሔር ሕይወት በሌለው ዓለም ውስጥ የሚያድር አይደለም፤

ስለሆነም ሕያው የሆነች ከተማ ድንግልን አዘጋጀ፤ እንዲያውም መጽሐፍ ስለ እርሷ ሲናገር "ይህች ለዘለዓለም ማረፊያዬ ናት" መዝ 131÷14 ነው የሚለው፤ ዓለምነቷ ከዚች ዓለም የተለየች ናት፤ ይህች ዓለም ማረፊያ የሌላት ስለሆነች መቆያ እንጂ ማረፊያ አይደለችም። ይኸውም ጌታ ከዚህ ዓለም የሚለይበት ወርኃ ዕርገት በደረሰ ጊዜ በተናገረው ንግግር ይታወቃል። "ማረፊያ ላዘጋጅላችሁ እሄዳለሁ" ማለቱ ያለንባት ዓለም የምታሳርፍ ዓለም ባለመሆኗ ነው፤ ስለ እመቤታችን ዓለምነት ሲናገር ግን"ማረፊያዬ" ነው ያላት። ለሰው ልጆች ማረፊያ ባልነበረበት ሰዓት እመቤታችን የአምላክ የዘለዓለም ማረፊያ ሆና በመገኘቷ ለሰው ዘር በሙሉ ማረፊያ የሚሆነው ያ ልዩ ዓለም ተዘጋጀ። ለዚያኛው ዓለም መመሥረት መሠረት ከሆነች ለዚህኛውማ ምን ይገርማል።

በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ስለ አዲሱ ዓለም ስለ መንግሥተ ሰማያት ከመስማታችን በፊት በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የሰማነው የሀገረ እግዚአብሔር የእመቤታችን የድንግል ማርያምን ታሪክ ነው። የወዲያኛውን ዓለም ታሪክ የሰማነው ጌታ በዕርገት ወደ ቀደመ አኗኗሩ ሊመለስ በተቃረበበት ሰዓት ሲሆን የእመቤታችን ጉዳይ ግን ወንጌላውያን ለወንጌላቸው መግቢያ ያደረጉት ዐቢይ ጉዳይ ነው። ወንጌል ማለትኮ ተስፋ የምናደርገው ዓለም መንግሥተ ሰማያት ነው መንግሥተ ሰማያት ለምንለው ዓለማችን ለሕገ ወንጌል መግቢያ የሆነው የእርሷ ታሪክ እንደሆነ ሁሉ ለዚህ ግዙፍ ዓለም መፈጠርም እመቤታችን መቅድም ናት።

2ኛዓለም የሚለው ቃል ሁለተኛ ትርጉሙ ሰው ተብሎ ይተረጎማል። አዳሪውን በማደሪያው መጥራት የቅዱሳት መጻሕፍት የተለመደ ጠባያቸው ነው፤ በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ሰዎችን ለመጥራት አሌ

ለኪ ኢየሩሳሌም፣ የኮራዚን ሰዎች ለመጥራት አሌ ለኪ ኮራዚ ማቴ 11÷21 እንደ ማለት በዓለም የሚኖር ሰውንም ለመግለጽ ዓለም ብሎ መጥራት የተለመደ ነው። "እስመ ከመዝ አፍቀሮ እግዚአብሔር ለዓለም - እግዚአብሔር ዓለሙን እንዲሁ ወዶታልና,, ዮሐ 3÷16 አሁን እንዲህ ብሎ ወንጌላዊ ሲናገር እግዚአብሔር የሰማይና የምድር ፍቅር አደረበት ለማለት እንዳልሆነ አዕምሮ ያለው ትውልድ ሁሉ ሊዘነጋው አይችልም። እመቤታችንም "ዓለም ሳይፈጠር በአምላክ ጎሊና ታስባ ትኖር ነበር" ተብሎ ሲነገር በቁመ ዓለሙን ብቻ የሚይሳይ ሳይሆን ከሰው ልጆች መፈጠር በፊት እርሷ በፈጣሪ ዘንድ የታሰበች መሆኑን የሚያሳይ ነው ፤

አበው በታሪክ እንደሚነግሩን ሰው የሚፈጠርባት ዕለተ ዓርብ ከመድረሷ በፊት እግዚአብሔር በመላኩ ቅዱስ ሚካኤል ክንፍ ስሎ እመቤታችንን ለመላእክቱ አሳይቷቸው ነበር፤ በመላእክቱም ዓለም ከአባቷ ከአዳም፣ ከእናቷ ከሔዋን ቀድማ የታወቀች እመቤታችን ድንግል ማርያም ናት።

ተፈጥራ በምድር ላይ መኖር ከጀመረችባቸው ጊዜያት በፊት ለእርሷ ከመላእክት ምስጋና አልታጎለባትም ነበር፤ ለዚህም ነው ኢትዮጵያዊው ቄርሎስ በመባል የሚጠራው አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ‹‹ይዌድስዋ መላእክት ለማርያም በውስተ ውሳጤ መንጦላዕት፤ መላእክት ማርያምን በመንጦላዕት ውስጥ ያመሰግኗታል[3]›› ሲል ያመሰገናት። በመንጦላዕት ውስጥ የተባለው እመቤታችን በሥጋ ያልተገለጠችባቸው ዘመናት ናቸው፤

በተመሳሳይም ሌላኛው የሀገራችን ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ‹‹ሚካኤል መልአክ በክነፍ ጸራ መንጦላዕተ ደመና ሰወራ ፤ሚካኤል በክንፍ

3. መጽሐፈ ሰዓታት

ተሸከማት የደመና መጋረጃንም ጋረደላት[4]›› በማለት በነዚያ እርሷ ባልነበረችባቸው ዘመናት መላእክቱ በዘመን መጋረጃ አሾልከው እየተመለከቱ የሚገባትን የምስጋና እጅ መንሻ ያቀርቡላት እንደነበር ሁለቱም ሊቃውንት ተስማምተውበታል። ቀደም ሲል እንዳየነው እመቤታችን ለዚህ ዓለም መፈጠር ምክንያት ሆናለች የሐዋርያት አለቃ ቅዱስ ጴጥሮስ ለደቀ መዝሙሩ ቀሌምንጦስ እንደነገረው "ሶበሰ ኢኮነት ዛቲ ቅድስት ድንግል እም ኢፈጠርክምሙ ለአዳም ወለሔዋን፤ ድንግል ማርያም በንጽሕና በቅድስና የጸናች ሆና ባትገኝ ኖሮ አዳምና ሔዋንን ባልፈጠርካቸውም ነበር[5] ብሎ ለሰው ዘር ወደ ዓለም መምጣት ምክንያት የሆነች የአምላክ በጎ ጎሊና እንደሆነች ይመሰክራል።

ከኃጢአትም በኋላ ለተደረገው ሁለተኛው የሰው ልጆች መፈጠርስ ታላቋ ምክንያት እርሷ አይደለች?! እርሷ ባትኖር የሰው ልጅ ዳግም ለሕዳሴ ይበቃ ነበርን? አባ ሕርያቆስ እንደመሰከረው የሰው ዳግም ሕዳሴ በእርሷ ተከናወነ። "ወብኪ ተሐደሰ ቀዳሜ ኵሉ ፍጥረት፤ የፍጥረት ሁሉ መጀመሪያ ባንቺ ታደሰ[6]" እንዲል፤ እርጅና እንዳይኖርባት ተደርጋ የተሠራች የሰው ልጆች ስጦታ ናት።

ከሰው ልጆች መፈጠር አምስት ቀናት ቀደም ብሎ በብዙ ምሳሌ በተፈጠሩት ፍጥረታት ውስጥ እርሷ ትታይ ነበር። ይሄውም ሊታወቅ በኋላ የተነሡ ነቢያት፣ ሐዋርያት፣ ሊቃውንት ያመሰገኗት በሥነ ፍጥረት ምሳሌነት ነው። በእውነት እመቤታችን ከሰው ሁሉ ቀድማ የተገኘች ሰው በመሆኗ ነው ከውስጧ ሰው የተወለደው፤ ከዚህም የተነሣ ከሷ በፊትም ሆነ ከሷ በኋላ የተወለደው ትውልድ ሁሉ "እናታችን ጽዮን" ብሎ ያመሰግናታል።ሰሰው ሁሉ እናት ትሆን ዘንድ የተመረጠች ለማለትም ዓለም ሳይፈጠር በአምላክ ጎሊና ታስባ ትኖር

4. ድጓ
5. ቀሌምንጦስ
6. ቅዳሴ ማርያም

ነበር ተባለላት ከሰው መፈጠር በፊት በአምላካዊ ምርጫ የተመረጠች ለማለት ነው።

3ኛ ዘመን፡- ዓለም ሦስተኛ ትርጉሙ ዘመን ማለት ነው ይህን ሲያስረዳ ቅዱስ ያሬድ "በመዳልው ደለወ ዓለመ ፤ዘመንን በመስፈሪያ ሰፈራት[7]" ብሏል። ከዘመናት መቆጠር በፊት ያለውን ቀርቶ የሰው ልጅ ከዘመናት መምጣት በኋላም ቢሆን ያለውን ወቅት ምን አይነትና ስንት እንደሆነ ለማወቅ አልቻለም፤አምላካችን ግን ከወቅቶችም መፈራረቅ በፊት የነበረ ነው፤

ከዘመናት በፊት የነበረው እግዚአብሔር አብ ያለ እናት በቅድምና እግዚአብሔር ወልድን ከአካሉ ከባሕርዩ ባስገኘ ጊዜ የእናትነት ሥልጣኑ በአካል ከመገለጣ በፊት በአምላክ ኅሊና ለእመቤታችን የተሰጠ ነበር፤ የሚያደርገውን እንጂ የማይሆነውን የማያስብ እግዚአብሔር ዘመኑ በደረሰ ጊዜ ከአካሏ አካልን፣ ከባሕርይዋ ባሕርይን ነሥቶ ከእርሷ ተወለደ፤ ዘመናት መቆጠር ፣ዓለማትም በዘመን መሰፈር ከመጀመራቸው በፊት እርሷ በእግዚአብሔር ዘንድ ታስባ ትኖር ነበር። እንዲያውም ቅዱስ ያሬድ ‹‹ዘመንየ አዝማንኪ ፣[8]መጠንየ አምጣንኪ›› በማለት በድንው ያመሰግናታል ሲተረጎምም ዘመኔ ዘመንሽ፣መጠኔም መጠንሽ ነው ማለት ሲሆን ዓለም ከተዘጋጀ ከብዙ ዓመታት በኋላ ጌታ ከእመቤታችን የነሣው ሥጋ ቀዳማዊ መሆኑንና የእመቤታችንም ወላዲተ አምላክነት ከዓለም አስቀድሞ የታሰበ መሆኑን በዝማሬው ያረጋግጥልናል ፤አሮጌው ዘመን አልፎ አዲሱን ዘመን መቁጠር ሲጀመር "ኅሊናሁ ለአብ[9]" ብለን የምንጠራው ጌታ ከእርሷ ተገኘ፤ ፈጣሪያችን ያለጊዜው የሚያደርገው ነገር ባለመኖሩ የሚያደርጋቸውን ነገሮች ዘመን ይቀድማቸዋል እንጂ ሐሳቡን ዘመን ቀድሞት አያውቅም።

7. መርጎ እሙር፣ ጸመ ድጓ ዘቅዱስ ያሬድ
8. ድጓ ዘቅዱስ ያሬድ
9. ትምህርተ ነቢያት

ዓለም ስለ እመቤታችን

ዓለሞት በአራት ዐበይት ክፍሎች የተከፈሉ ናቸው። ከምድር በላይ ያለው ሰማይ ብቻውን በሁለት ይከፈላል፤ የመጀመሪያው መቅደሰ እግዚአብሔር ተብሎ የሚጠራው ክፍል ሲሆን በዚህ ዓለም ውስጥ ሦስት ሰማያት ይገኛሉ። የሁለቱ ሰማያት ጽንፋቸው የማይታወቅ መሆኑን የሥነ ፍጥረቱ መጽሐፍ ይመሰክራል። አንደኛዋ ሰማይ ግን አራት ማዕዘን ሆና በልክ ከላይ እንደ ክዳን ሆና የተሠራች ሰማይ ናት እንጂ እንደ ሁለቱ ሰማያት ዳርቻ የሌላት አይደለችም[10]።

እነዚህን ሦስቱም ሰማያት ማኅደረ እግዚአብሔር በመሆናቸው ፍጡራን ሰግደው ለመመሰስ ካልሆነ መኖር አልተፈቀደላቸውም። እግዚአብሔርም በልዩ ጥበቡ አንዱን መሠረት ፣አንዱን ግድግዳ ፣ሌላውን ጣራ አድርጐ አያይዞታል። እንደ መንበር ሆነው የተሠሩ በመሆናቸው ሁል ጊዜ በኪሩቤል ጀርባ ላይ ጸንተው እንዲኖሩ አድርጓቸዋል። ለወዳጆቹ ሲገለጥ እግዚአብሔር በዚህ ዙፋን ላይ ተቀምጦ ከኪሩቤል ትክሻ ላይ ሆኖ ነው የሚገለጠው ሕዝ 10፥1፣ኢሳ 7÷14

በዚህ ሰማያዊ ዓለም ውስጥ ሁል ጊዜ ቅዳሴ አይቋረጥም፤ ሙሴ በደብረ ሲና ያያቸው ሰባቱ የእሳት መጋረጃዎችም የሚገኙት በዚህ ቅዱስ ቦታ ነው፤ ከዚህ ቤተ መቅደስ በላይ ምንም ነገር የለም ፤የፍጥረት ሁሉ ቁንጮ ነው፤ ይህ ሁሉ ፍጥረት ወደ ዚህ ሰማይ ያንጋጥጣል፤ የፍጥረት ሁሉ የተስፋ ፍጻሜ ከዚህ ሰማይ ይወጣል፤ ምድራውያንን የሚያረካው የምሕረት ጠበል ከዚህ ሰማይ ይመነጫል፤ በአጠቃላይ ለተገፉት ፍትሕ፣ ለግፈኞች ቅጣት የሚወጣው ከዚህ የጽድቅ አዳራሽ ነው ሰማያትን በምጥቀታቸው፣ ምድርን በጥልቀታቸው፣ አየረ

10. አክሲማሮስ ዘእሑድ

አየራትን በንስርነታቸው የፈታተሹት እነዚያ አዕማዶቻችን እንደነገሩን ይህ ሰማይ የእመቤታችንን ምጽአት የሚሰብክ የእመቤታችን ምሳሌ ነበር[11]፤ ከሰማያት በላይ ያለው ይህ ሰማይ ፍጡራን ለሚኖሩባቸው ሰማያት ሁሉ አክሊል ነው። እመቤታችንም አክሊለ ፍጡራን ናት። የቅዱሳን ቁንጮም ናት፤ እንደነዚህ ሰማያትም እመቤታችን መቅደሰ እግዚአብሔር ናት፤ ሌላውን ቅዱስ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ 1ኛ ቆሮ 3፥16 ብንለው እግዚአብሔር በኀድረት፣ በረድኤት ስለተገለጠበት ይሆናል እንጂ እንደ እርሷ በከዊን ተዋሕዶ[12] መች ነውና፤ በእውነት እመቤታችን እግዚአ-ኃያላን የሚኖርባት ከተማ ናትና ፍጥረት ላይኖርባት የተዘጋጀች አማናዊት የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ናት።

አንድ ሊቅም ‹‹መቅደስ አንቲ ዘረሰየኪ ታዕካሁ ፤እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ መመሰገኛ ያደረገሽ አንች ነሽ[13]›› ሲል ያወድሳታል። የመጀመሪያው ዓለም ሲፈጠር የነበረው የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ የነዚህ ሰማያት ኅብረት ነበር፤ ዓለምን በሐዲስ ተፈጥሮ እግዚአብሔር ሊሠራው ባሰበ ጊዜ ግን ሦስቱን ሰማያት በሦስት ነገር በተከበበች ድንግል ለወጠው ማለትም ንጽሐ ሥጋ፣ ንጽሐ ነፍስ፣ ንጽሐ ልቡና በተገኘባት በእመቤታችን ተክቶታል።

ለሐዲሱ ዓለም እመቤታችን የመጀመሪያዋ የምስጋና ሥፍራ ናት። የመጀመሪያው የመላእክቱ ቅዳሴ ፣የትጉሃኑ ሠራዊት ማኅሌት የተቆመው በአርያም ሥርዓት ዝማሬ በምድር ላይ የተንቆረቆረው በእመቤታችን ማሕጸን አይደል?! ሊቃውንቱ በድርሳናቸው እንዳረጋገጡልን ከሆዷ ቅዳሴን ለመስማት አንገቷን ዘንበል ታደርግ ነበር[14]፤ አባቷ ዳዊትም ከሊቃውንቱ በፊት፣ ከእርሷም ወደ ዓለም

11. ሰዓታት ከዘባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ (ኩሶሙ)
12. ተዋሕዶ የከዊንና የኅድረት ተብሎ በሁለት ይከፈላል የኅድረት ተዋሕዶ የምንለው እግዚአብሔር በቅዱሳኑ ላይ አድሮባቸው መኖሩን ነው፤ የከዊን ተዋሕዶ የምንለው ደግሞ ጌታ ከእመቤታችን ነፍስና ሥጋ ነስቶ ማደሩን ነው።

መምጣት አስቀድሞ "ሐነጸ መቅደሶ በአርያም ወሣረራ ውስተ ምድር ዘለዓለም፤ መቅደሱን በአርያም ሠራ በዘለዓለም ምድርም መሠረታት መዝ77÷69 በማለት መቅደስነቷን አስረግጦ ይናገራል ይህች መቅደስ እመ አምላክ እመቤታችን ናት እንጂ ሌላ ማን ይሆናል?

በአርያም ማለቱ ክብሯን፣ ልዕልናዋን ሲያይ እንጂ ቦታውን አይመለከትም፤ አርያም ማለት ልዑል ማለት ስለሆነ። ያማ ባይሆን ኖሮ በዘለዓለማዊት ምድር (በምድር ላይ ለዘለዓለም) መሠረታት ባላለም ነበር፤ ምክንያቱም ለዘለዓለም የምትኖር ምድር የለችምና። ይልቁንም መቅደስ የተባለች እሷ መሆኗ ቀጥሎ ባለው ዐረፍተ ነገር ይታወቃል። ‹‹ባለሟሉ ዳዊትን መረጠ›› በማለት መቅደሲቱ ከዳዊት ቤት የተመረጠች መሆኗን ይመሰክራልና።

ይህ መቅደስ ከኪሩቤል በላይ ነው፤ ኪሩቤል ይሸከሙታል እንጂ አይመረምሩትም እንኳን ሊመረምሩት ከክብሩ ነጸብራቅ የተነሣ በፊቱ መቆም ይቸገራሉ፤ ፊታቸውን በክንፎቻቸው ይጋርዳሉ፤ ሱራፌል አክሊላቸውን አውልቀው ለዚህ መንበር ይሰግዳሉ፤ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ እንደተናገረው "አክሊላቲሆሙ ያወርዱ ቅድመ መንበሩ እንዘ ይሰግዱ ይርዕዱ ወኢይዝበጦሙ ሶበ ይበርቅ ነዱ ፤ በዙፋኑ ፊት እየሰገዱ አክሊላቸውን ከራሳቸው ላይ ያወርዳሉ የእሳተ መለኮቱ ብልጭልጭታ እንዳያቃጥላቸው ይንቀጠቀጣሉ ፈታቸውን ይሸፍናሉ[15]››ይላል።

እመቤታችንም ከኪሩቤል በላይ ያለች መንበረ እግዚአብሔር፣ ከሱራፌል አንደበት ምስጋናና ክብር የሚቀርብባት መቅደስ እግዚአብሔር ናት።

ቅዱስ ኤፍሬም እንደመሰከረው "ይእቲ ተዐቢ እምኪሩቤል

13. መልክአ ውዳሴ
14. አረጋዊ መንፈሳዊ
15. ሰዓታት ዘአባ ጊዮርጊስ

ወትፈደፍድ እምሱራፌል፤ ይህች ከኪሩቤል ትበልጣለች ፤ከሱራፌልም ትከብራለች[16]›› ከነሱ በላይ አድርጎ ነዋ በድንቅ ጥበብ የሠራት፤ በዚያውስ ላይ እነርሱ መንበሩን እንጂ እርሱን ተሸክመው ፤ዙፋኑን እንጂ ፊቱን አይተው አያውቁም፤ እርሷ ግን ፀዋሪተ መንበር ሳትሆን ራሷ መንበር ነች፤ በፊቱ ላይ የተጋረደውን የእሳት መጋረጃ ሳይሆን ፊቱን አይታለች ፤ጉንጩን ዳብሳለች ፤

የደጁ አገልጋዮች፤ የእልፍኙ አሽከሮች እነዚያ ግሩማኑ ባለ ስድስት ክንፎች፤ ባለ ብዙ ዓይኖች ኪሩቤል ሱራፌል ፊቱን አዩ ከተባለ በመጽሐፍ መብረቅ ይሆናል እንጂ ፊት ለፊት አይተውት አያውቁም እመቤታችን ግን እንዲህ አይደለችም ፊት ለፊት አይታዋለች፤ እንዲህ ከሆነ ደግሞ በእውነት እመቤታችን ከኪሩቤል በላይ ያለችው ቤተ መቅደስ ነች፤ አባ ሀርያቆስም ይህንን ሲያረጋግጥልን ‹‹ሰባቱ የእሳት መጋረጃዎች በማሕጸንሽ በስተቀኝ ነው በግራ በወዴት ተዘረጋ[18]›› እያለ ያደንቃል፡፡

ያ! ቤተ መቅደስ የማይደረገው የተደረገበት፤ የማይቻለው የተቻለበት የሰማይ ዓለም ነው፡፡ግድግዳው የእሳት፤ ጣራው የበረድ፤ የውኃ መርገፍ አለው፡፡ እሳቱ ውኃውን ሳያሞቀው፤ ውኃውም እሳቱን ሳያጠፋው፤ እሳቱ በረዱን ሳያቀልጠው፤ በረዱ እሳቱን ሳያጠፋው እሳትና ውኃ በአንድ ተዋሕደው፤ በተዋሕዷቸው ፍጥረትን አስደምመው ሳይነጣጠሉና ሳይቀላቀሉ ለዘለዓለም ጸንተው ይኖራሉ፤ ይህ ለፍጡራን አይመረመራቸውም፤ ምክንያቱም ይህ ነገር በሕገ ተፈጥሮ የማይቻል ስለሆነ ነው፡፡ እርሱ ግን አድርጎታል፤ በእርሱ ዘንድ ሁሉ ይቻላልና፤

17. ውዳሴ ማርያም
18. ቅዳሴ ማርያም

በአማናዊት መቅደስ ድንግል ማርያምም ይህ ሁሉ ሆኗል፤ መለኮትና ትስብእት ልዩ ተዋሕዶ ተዋሕደውባታል ፤መለኮቱ ትስብእቱን ሳያቃጥለው፤ ትስብእቱ መለኮቱን ሳይለውጠው ለዘለዓለም በፍጹም ተዋሕዶ ጸንተው ይኖራሉ፡፡ ከማድነቅ በቀር ፍጡር እንዴት ይኼን የሰማይ ምሥጢር ሊመረምር ይችላል፤ አልመረመራቸው ስላለ አይደል በእርሷ የተደረገውን ነገር አባቶቿ ነቢያት እንዲህ ሲሉ የገለጹት "ነኪር ነገሩ በእንቲአኪ ሀገረ እግዚአብሔር"ሀገረ እግዚአብሔር እመቤታችን ባንቺ የተደረገው ነገር ድንቅ ነው ብለዋታል፡፡

የአምላካችን ልዩ ጥበብ ያረፈባት ቤተ መቅደሳችን በመሆኗ እመቤታችን በእውነት ድንቅ ናት፤ ሁለቱን የተለያዩ አካላት ሥጋና መለኮትን፤ ሁለት የተለያዩ ባሕርያት የሥጋና የመለኮት ባሕርያትን አዋሕዶ አንድ ያደረገ ከእመቤታችን በስተቀር ሌላ ማን አለ? እሳት እና ውኃስ አንድ ማደሪያ ሆነው የተሰሩበት ከላይኛው የአምላካችን ማደሪያ በስተቀር ሌላ ከወዴት ይገኛል፤ በሌላ ሥፍራ ላይደግመው ልዩ ጥበቡን በዚህ ቅዱስ ሥፍራ እግዚአብሔር አሳይቶናል ፤በሌሎች ሴቶችም ላይደግመው ልዩ ምሥጢረ ተዋሕዶውን ከሴቶች ሁሉ ልዩ በሆነች በእመቤታችን አድርጎታል፡፡

ያችኛዋን ዓለም ለእርሱ አሥራት በኩራት አድርጎ ሠርቷታል እንጂ ለፍጡራን ማደሪያነት አታገለግልም፤ ፍጡራን ለአገልግሎት ብቻ ይሰለፉባታል፤

እመቤታችን ድንግል ማርያምም ለእግዚአብሔር አሥራት ሆና ከቀደሙት ከነቢያት፤ከኋለኞቹ ከሐዋርያት የተበረከተች ያለፈውም የሚመጣውም ትውልድ እጅ መንሻ ናት፤ ሰማያውያኑ ፍጥረታት በሰማይ፤ መሬታውያኑም በመሬት ላይ ለአገልግሎት ይሰለፉባታል፤

በላይኛው ትጉሃኑ፣ በታችኛው ቅዱሳኑ ለስሟ ያለማቋረጥ ማኅሌት ይቆማሉ፤ የማይታየውን እግዚአብሔርን በእርሷ ውስጥ እየተመለከቱ ለስሟ ይዘምራሉ፤ እርሷ እኮ! የፊቱ መጋረጃ ነች፤ ማንም ቢሆን የፊቱን መጋረጃ አይቶ ይሰግዳል እንጂ መጋረጃውን ገልጦ ማየት የሚችል የለም። የመቅደሱ ምሥጢር ሊገልጥላቸው ከፈቀደላቸው ከባለሟሎቹ በስተቀር የተሰወረ ነው የእመቤታችንም ክብር እግዚአብሔር ለገለጠላቸው ካልሆነ በስተቀር የተከደነ ነው።

የእርሷ ምስጢርኮ! ወንጌል ነው፤ ወንጌል ደግሞ ለማያምኑት የተከደነ መሆኑን መጽሐፍ ምስክር ነው፤ ከእርሷ የተወለደው ወንጌል ክርስቶስ የተገለጠው መንፈስ ቅዱስ ለረዳቸው ብቻ በመሆኑ የእመቤታችንም ክብር ግራ የሚያጋባቸው ቢኖሩ አይገርመንም ማቴ 11÷25

ያኛው ቤተመቅደስ ነቢዩ ኢሳይያስ እንዳለው በአምላካችን ክብር የተሞላ፣ አደባባዩ በቀሚሱ ዘርፍ የተከደነ፤ ውስጡ ከመላእክቱ ቅዳሴ የተነሣ መድረኩ ብድግ፣ ብድግ እስኪል ድረስ በዝማሬ ማዕበል የተጥለቀለቀ ነበር፤ ይህችኛዋም ቤተ መቅደስ ምልዕተ ጸጋ፤ የአምላካችን የክብሩ መገለጫ ሰገነት ናት፤ የልቡናዋ አደባባይ በንጽሕና በቅድስና የተሞላ ነው፤ የጆሮዎቿ በሮች፣ የአንቀጸ ልቡናዋ መድረኮች ጩኸው ከሚያመሰግኑ ከኃያላኑ ሠራዊት ዜማ የተነሣ በተመስጦ ወደ ሰማይ ይነጠቃል፣ ብድግ ብድግ ይላል፤

የቀደሙን አባቶቻችን ነቢያቱ ይጽናኑ የነበረው በራእይ ባዩትና ከቤተመቅደሱ ይወጣ በነበረው መለኮታዊ ድምፅና የመዳን ተስፋ ነበር፤ በተለይ ይህ ታላቅ ነቢይ ከለምጹ የተፈወሰው ከዚህ ታላቅ ቤተመቅደስ ውስጥ ካለው ከመሠዊያው ሥር ከተገኘው ከእሳቱ የእግዚአብሔር

መላክ ባቀመሰው ጊዜ ነው። ያለዚያ ፍሕም ይህ ነቢይ ምን ዓይነት የመዳን ተስፋ ይኖረው ነበር ብላችሁ ታስባላችሁ?እግዚአብሔርስ ይህን ቤተ መቅደስ በራእይ ነው እንጂ ሌላ እንዴት ሊገልጽለት ይችላል? ጊዜው ገና ነበርና።

ለኛ ግን እንዲህ አይደለም በምሳሌ ሳይሆን ያለ ምሳሌ ያን ታላቅ የእግዚአብሔር ክብር የሞላበት ቤተመቅደስ አየን፤ እንደቀደመው በመላኩ በኩል ሳይሆን በገዛ እጁ ፍሕሙን በጉጠት ያይደለ በሥልጣኑ ከመሠዊያው ሥር ካለው ከፍሕሙ አጎረሰን ማቴ 26÷26 ከሥጋዊ ለምጽ ሳይሆን ከመንፈሳዊ ለምጽለዘለዓለም ፈወሰን፤ ከምድራዊው የእስራኤል ማኅበር ጋር ብቻ ሳይሆን ከሰማያውያኑ የመላእክት ኅብረት ጋርም ቀላቀለን፤ ነቢዩን ከለምጻሞች ሥፍራ አንሥቶ ወደ ነቢያቱ ከተማ እንዳስገባ እኛንም ከለምጻሞች የኢጋንንት ከተማ ለይቶ ወደ ቅዱሳኑ ማደሪያ ወደ ገነት አገባን፤ እንደ ነቢዩ አይተነው በርቀት ብቻ የቀረ አይደለም ፤በረጅሟ ዙፋን በእመቤታችን ላይ ተቀምጦ ስናገኘው አየነው፤ ዳሰስነው፤ ከእርሱ ጋር በላን ጠጣን እንጅ፤ አባቶቻችን ከሩቅ ያዩአት ያች ባለ ግርማ ሞገሷ አማናዊት ቤተ መቅደስ እመቤታችን ድንግል ማርያም ናት።

ለነቢያት ፈውስ ከእርሷ ወጥቷል፤ ያን ጊዜ ከፍ ብላ በርቀት መታየቷ ከፍታዋ፣ ልዕልናዋ፣ ክብሯ ከፍጥረታት የተለየ መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን ርቀቷ ደግሞ በርሷና በነቢዩ መካከል ያለውን የዘመን ርቀት የሚያሳይ ነበር ዘመኑ ሲደርስ፣ የተስፋውም ፍጻሜ ሲቀርብ ግን በመካከላችን ቤተመቅደሷን ሠራልን ልዑል በመካከላችን ሊያድር ቃል ገብቶልን ነበርና።

ሁለተኛው የሰማይ ክፍል

ሕያዋኑ አመስጋኞች ፍጥረታት የሚኖሩበት ዓለም ነው። በዚህ ዓለም ውስጥ በተፈጥሮ መሬታውያን በግብራቸው ግን ሰማያውያን የሆኑ በምድር ላይ ያገለገሉት ቅዱሳን ሰዎችና ሌሊትና ቀን ያለማቋረጥ የሚያገለግሉት ሰማያውያኑ ፍጥረታት መላእክት ይኖሩበታል በነዚህ ከተሞች ሞት የለም የሞትን ጦር የሰባበሩ፣ የመቃብርን አቅም ያዳከሙ ማለፍና መለወጥ እንዳይኖርባቸው ሆነው የተሠሩ፣ ለሞት አገዛዝ የማይመቹ ፍጥረታት የሚኖሩበት ዓለም በመሆኑ ነው። በዚህ ዓለም ውስጥ የሚኖሩ ሥነ ፍጥረታትን ካስቀመጣቸው ፈጣሪ በቀር ማንም የሚያውቃቸው የለም የፈጠራቸው እርሱ ብቻ ግን ይቆጥራቸዋል፣ በየስማቸው ይጠራቸዋል።

እነዚህ የሕያዋን መንደሮች በእውነት እመቤታችንን የሚሰብኩ መምህራን ናቸው ፍጥረታት ሕያዋን መሆን የጀመሩት ከእርሷ በኋላ አይደል? እርሷ የሕይወት መገኛ የሕያዋንም እናት ናት። ቅዱስ ኤፍሬም እንደተናገረው "እሞሙ ለኵሉሙ ሕያዋን፣ የሕያዋን ሁሉ እናት,, ብሎ፤

የሕያዋኑ እናት ብቻም ሳይሆን መሣፈሪያም አድርጎ ነው የሠራት፤ ሕያዋኑ የእግዚአብሔር ወዳጆች ቅዱሳን ከዚህ ሰማይ በስተቀር ሌላ ማደሪያ እንደ ሌላቸው ሁሉ ከድንግል ማርያም የተወለደውንም አምላክ ወልደ አምላክ ለማያምኑ ሰዎች በሕይወት መኖር አይቻልም። ርእሳችን ክርስቶስ የሚኖርባት ብቸኛ ሰማይ አይደለች እመቤታችን? እኛም እኮ አካል ብልቶቹ ነን ራስ ካለበት እጅ እግር ሌሎችም አካላት ይኖራሉ እንጂ ተለይተው መኖር እንዳይችሉ እኛስ ከራሳችን ከክርስቶስ ተለይተን እንዴት እንኖራለን እርሱ ከገባበት ገብተን የምንኖርባት ሰማያችን እመቤታችን ድንግል ማርያም ናት።

ፈጣሪያችን ከገባበት መግባት ነው እንጂ እኛስ ሌላ ምን እንመኛለን?ሐዋርያው የተናገረውን ስናስበው ምንኛ ይደንቃል! በሰማያዊው ሥፍራ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን ኤፌ 2÷7 የቀደሙት ነቢያት አባቶቻችን እንኳን ማደሪያውን ለማግኘት እስኪችሉ ድረስ ለጉንጫቸው ዕረፍትን፣ ለዓይናቸው እንቅልፍን እስከ ማጣት ደርሰው ደጅ ይጠኑ አልነበረምን?

እኛ ግን የያዕቆብን አምላክ ማደሪያ ሳይሆን የምንፈልገው ከማደሪያው ገብተን ለማደር ነው- የምንማጸነው። ሊቁ አባ ሀርያቆስ ቅዳሴ ማርያምን በቀደሰባት በዚያች ቀን ለሕዝቡ ከጸለየላቸው ጸሎቶች በስተመጨረሻ ክፍል ላይ የሚገኘው እንዲህ የሚል ነው "የእሳት ድንኳኖች ወደ ተተከሉበት የካህናት አለቃ ክርስቶስም ወዳለበት ያግባችሁ,, ነው ያላቸው የእሳት ድንኳኖች የተተከሉባት ሰማያችን ድንግል ማርያም ናት በእርሷ ልንኖር ግድ ነው።

ዓለማቱ ከእሳት የተሠሩ አድማሳቸውን ከፈጣሪ በስተቀር የሚያውቀው የሌለ ታላላቅ ሰማያት ናቸው። የእመቤታችንንም የክብሯን አድማስ የሚያውቀው የሌለ የተሰጣትን ጸጋ ሊሰፍረውና ሊናገረው የሚደፍር አንደበት የሌለ ምልዕተ ጸጋ ምልዕተ ክብር ናት።እነዚያ ሰማያት ከእሳት የተሠሩ መሆናቸውን መጻሕፍት ቢመሰክሩልንም እሳቱ ግን ውዕየት (ማቃጠል) የሌለው ልዩ እሳት ነው። እመ አምላክ ድንግልም የእሳት መጋረጃዎች ተዘርግተውላት፣ እሳታዊ ዙፋን ተተክሎባት እሳተ መለኮትን በማሕጸኗ ተሸክማ በጀርባዋ አዝላ መጐናጸፊያው እሳት፣ ቀሚሱ እሳት የሆነውን ጌታ እናት ሆና ሳለ እሳተ መለኮቱ አላቃጠላትም።

ከእሳት ባሕርይ ውዕየትን ለይቶ አስቀርቶ እግዚአብሔር ብሩህነትንና ይቡስነትን ብቻ አድርጎ ነው ሰማያትን የፈጠራቸው፤ ነገር ግን ሰባቱ ዓለመ እሳት ከመባል የከለከላቸው አንዳች ነገር የለም። እመቤታችንንም ሊፈጥራት ከአዳም ባሕርይ ደመ ነፍሳዊ ፍላጎትን ትቶ ነፍስና ሥጋን ነስቶ ነው፤ ቢሆንም ግን ሰው ከመባል የከለከላት አንዳች ነገር የለም። ረቂቅ ባሕርይ ያላቸው ዓለማት መሆናቸው ደግሞ አስገራሚ ነው። በነዚህ ዓለማት በሥጋና በደም መኖር አይቻልም፤ ማግባት መጋባት የለም፤ እመቤታችንም ረቂቅ የእግዚአብሔር የማትመረመር ሐሳቡ እኩ ናት፤ በሥጋና በደም ሊመረመር የማይችል ጽኑዕ ምሥጢር አላት ማቴ 16፥16 ማግባትና መጋባትም በእርሷ ጎሊና ውስጥ ከቶ የሌሉ ተራ ሐሳቦች ናቸው፤ መርከስን ስለሚያስከትሉ ሳይሆን ለሌላ ዓላማ ስለተመረጠች ነው።

ይህች ዓለም /ምድር/ ማግባት መጋባት ቢኖርባትም አንዳንድ ጊዜም ቢሆን ቅድስት ምድር ከመባል የከለከላት የለም ነገር ግን ርኵሰት ይፈራረቅባታል፤ ከሚኖሩባት ፍጡራን የተነሣ ትረክሳለች ዘፍ 6፥3 ዘፀ 3፥5 ወዲያኛው ዓለም ግን ሁል ጊዜ ቅዱስ ነው። የረከሱ እንኳን ቢኖሩበት እነርሱ ሊወጡ ይችላሉ እንጂ በዚያኛው ዓለም መርከስ አይኖርም ሁል ጊዜ በንጽሕናና በቅድስና ይኖራል እንጂ።

ሌሎች ሴቶችም ቅዱሳት ለመባል በቅተዋል።ግን ያለ ነውር የነበሩ አልነበሩም እግዚአብሔር የቀጠረው ቀን ሲደርስ ነውራቸውን አስወገደላቸው እንጂ ሉቃ 1፥23 እመቤታችን ግን ከዚህ ሁሉ በእውነት ልዩ ናት ያለመተዳደፍ፤ ያለመለወጥ እንድትኖር የተፈቀደላት ጽንዕት ናት።

ሰማያቱ- ፍጡራን ከመገረም በቀር ሊለኩት የማይቻላቸውን ያክል ከመሬት ርቀው ተሠርተዋል፤ በአድማስ ግን በጥበበ እግዚአብሔር

ከመሬት ጋር ተጣብቀው አንድ ሆነዋል። እንዲህ ተብሎ እንደተጻፈ "ወአስተጣበቅዎ ዲበ እብነ ኰኩህ[21] በጽኑ ዓለት /የአድማስ ዐለት/ አጣበቅሁት "አበው በጎሊና ሠሌዳ ላይ ስለው ሲያስቀምጡት ምድሩን እንደ መሶብ፣ ሰማዩን እንደ ወዝ ከምባይ አድርገው ይስሉታል በዓይነ ጎሊና ሲመለከቱትም ልባም ሴት የሰፋችው መሶብ ይመስላል። የሰማያቱ ምጥቃቸው፣ ነገር ግን በአድማስ ዙረው ከምድር ጋር መገናኘታቸው የእመቤታችን ክብሯ ከመሬታውያኑ በላይ መሆኑን ይመስክራሉ እውነት ነው እግዚአብሔር ለእመቤታችን የሰጠውን ያህል ጸጋና ክብርን ለማንም አልተሰጠውም እግዚአብሔርን እመቤታችን ያወቀችውን ያክል ማንም አላወቀውም።

ይህን ታላቅነቷን በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ ሰዎች እንዲህ ብለው መሰከሩላት "የዐቢ ክብራ ለማርያም እምኵሉመ ቅዱሳን" ከቅዱሳን ሁሉ ክብር የእመቤታችን ክብር ይበልጣል[22]። የሰማያቱን ምጥቀታቸውን ሊመረምራቸው የሚቻለው አለን? የእመቤታችንንስ ገናንነቷን ክብሯን መናገር የሚቻለው ይኖር ይሆንን? እኔ የሚል እንኳ ቢኖር ሊቁ እንዲህ ሲል ይቃወማል "ዕበያ ለድንግል ኢይትከሀል ለተነግሮ" የድንግል ልዕልናዋ ሊነገር አይችልም ብሎ ዘመናትን አቋርጦ ከኛ በደረሰው ውዳሴው ይከላከልላታል። የእርሷን ነገር የተናገሩ፣ ስለ እርሷ የጻፉም እንኳን ቢኖሩ በማሳነስ እንጂ በማብዛት አይደለም። ለክብሯ እንደሚገባ መጠን አልተናገሩላትምና።

ለፍጡራን መኖሪያ ሊሆን የተሠራው የዚህን የሰማዩን ከፍታ ለመናገር ከከበደን ማኅደረ እግዚአብሔር ሆና የተሠራችውን የዳግማዊት ሰማይ የእመቤታችንን ክብር መናገርማ ምን ያክል ለእኛ ከባድ ይሆን።

21. ሔኖክ
22. ውደ.መር ዘረቡዕ

ሰማይ ከምድር እንደሚርቅ እርሷ በእውነት ከኛ ከመሬታውያኑ ጎሊና በላይ ሆና የተሰቀለች ሰማይ ናት። ከኛ በላይ የሆነች ሰማይ ናት ብንልም ከኛ የተለየች ግን አይደለችም። በአድማስ በኩል ጥበበኛው አምላክ ከመሬት ጋር አገናኝቷታልና።

አያችሁት! የእግዚአብሔርን ሥራ፤ ምንም እንኳን በክብር ከፍ ከፍ ያለች የእርያም ንግሥት ብትሆንም ከመሬታውያኑ ፍጥረታት የተገኘች መሬታዊት ፍጥረት መሆኗን ሲነግረን እኮ ነው። ጸጋዋ ሰማያዊ ነው፤ እርሷ ግን ምድራዊት ናት። አንድ ሊቅ እንዲህ ሲል እንደመሰከረላት "ወሀብተ ሰማያት ለማርያም ድንግል" ሰማያዊ ጸጋ ለድንግል ማርያም ተሰጠ[23] ብሎ። የሌሎችን ቅዱሳን ክብር መዘርዘር ይቻል ይሆናል፣ ለጴጥሮስ የመንግሥተ ሰማያት መክፈቻ፣ ለዮሐንስ ድንግልና፣ ለጳውሎስ ተልዕኮ፣ ለሙሴ ሕገ ኦሪት፣ ለአሮን ክህነትን..... እያሉ የእመቤታችንን ግን ስንቱን ይዘረዝሩታል እሷ እኮ የመለኮታዊው ባሕርይ ምሥጢራዊት ቤተ መዛግብት ናት።

እንዲያው እንደዚያ ብርሃናዊ መላክ በጸጋው የተሞላች የጸጋው ግምጃ ቤት መሆኗን አውቀን " ምልእተ ጸጋ " እንላታለን እንጂ። መላኩስ ቢሆን ከዓለም መፈጠር አስቀድሞ የነበረ ክብረ ድንግልናዋን ለመግለጽ ቢችገርም አይደል "ምልእተ ጸጋ" ሲል የደመደመው። የታላላቅ ባለጠጎችን ሀብትና ንብረት ዘርዝሮ መናገር እንዴት ይከብዳል፤ ከዚያ ይልቅ የሚበዛ የባለጠጋው አምላክ ሀብትና ንብረት የተሰበሰበባት ያችን ድንግልማ ክብሯን እንዴት ይቆጥሩታል? ከሾማት ንጉሥ በስተቀር የእርሷን ጸጋ ቆጥሮ የሚያውቀው እንደሌለ እውነት ብየ እነግራችኋለሁ፤ አብርሃም ያያት ሰፊ ሰማይ እኮ እመቤታችን ናት በሌሊት ከቤቱ ወጥቶ ሽቅብ አንጋጦ በርቀት ካያት ሰማይ ላይ

23. ሥርዓተ ቅዳሴ

ያያቸውን ከዋክብት መቁጠር ተስኖት አይደል አብርሃም ወደ ቤቱ የገባው፤ዘፍ 22

የእመቤታችንንም ክብር ለመመርመር አብርሃም ልቡናቸውን በቀደሙት ዘመን የተነሡት አባቶቻችን ወደ ጥልቁ አውርደውታል፤ ወደ አየር አውጥተውታል፤ አብርሃም ከዋክብቱን መቁጠር አልችል ብሎ እንደተመለሰ አባቶቻችን ቅዱሳኑም ልቡናቸው የእመቤታችን ክብሯን መመርመር አልችል ብሎ መመለሱን ይነግሩናል። ከነሱ አንዱ አባ ሀርያቆስ እንዲህ እንዳለ "ይስእን ወይገብእ ኀበ ዘትካት ህላዌሁ " አልመረመረው ብሎ ወደ አለመመርመሩ ይመለሳል[24] ብሎ።

ማለቂያ የሌለው ይህ ዓለመ- ሰማይ ማለቂያ የሌለውን የድንግል ማርያምን ክብር ሊያስነብበን የተዘረጋ ንጹሕ ብራና ነው። ላለፈውም ለሚመጣውም፣ ለሕያዋኑም ለሙታኑም ማደሪያ ሊሆን የተሠራው ይህ ሰማይ ስንመረምረው ይገርማል። ከዚህ በላይ ያለፈውም የሚመጣውም ትውልድ ብፅዕት የሚላት፣ ለሕያዋኑም ለሙታኑም፣ ለፊተኛውና ለኋለኛው ፍጥረት ማረፊያ ሆና የተሠራች እመቤታችን ደግሞ ትገርማለችና በሰማይ ብንመስላት ሰማይ ቢያንስብን ሁል ጊዜ በምንጸልየው ጸሎታችን "አንቲ ተዐብዩ እምሰማይ " ከሰማይም ይልቅ አንቺ ትበልጫለሽ[25] ብለን እንዘምርላታለን።

ሦስተኛው ክፍል

በሶስተኛነት ተቀምጦ የምናገኘው በዕለተ ሰኑይ እንደተገኘ የሚነገርለትን ጠፈር እየተባለ የሚጠራው ዓለም ነው። ይህ ዓለም የዕለተ ረቡዕ ፍጥረታት ፀሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብትን ሰብስቦ የያዘ ዓለም ነው። ከነዚህ ፍጥረታት በስተቀር በዚህ እንዲኖር የተፈቀደለት ሌላ ፍጥረት የለም፤ ምንም እንኳን ከውኃ ተከፍሎ በቃለ እግዚአብሔር ጽና ተብሎ

24. ቅዳ.ማር
25. ውዳ. ማር

የጸና ውኃ መሆኑን ብናውቅም አንዳንድ ጊዜ ይህን ጠፈር ሰማይ ብሎ መጥራት የተለመደ ነው። ሰማይ ማለት ስዕለ ማይ ማለት በመሆኑ በምሥጢር ተነጥቀው እንጂ አባቶቻችን ሰማይ ብለው የጠሩት፤ እውነት ነው ቁጥሩስ ከሰባቱ ሰማያት ውጭ ነው።

ዓለማችን ከተፈጠረች በሁለተኛው ቀን ይህ ግዙፍ ሆኖ የምንመለከተው ጠፈር ታየ። እስከዚያ ድረስ ታላቁ መጽሐፍ እንደሚነግረን ከዚህ ካለንበት ዓለም አንሥቶ እስከ ብሩህ ሰማይ ድረስ ዓለሚቱ ልክና መጠን በሌለው ውኃ ጢም ብላ ተሞልታ ነበር ሁለተኛው ቀን ግን ለምድር የብስን፣ ለሰማይ ደግሞ ጠፈርን መጋረጃ አድርጎ አስገኘ። በሰማይና በምድር መካከል የጠፈር ግድግዳ ተፈጠረ። በዚህም ምክንያት ከብሩህ ሰማይ የሚፈልቀውን የብርሃን ጠል እንዳትጠጣ ምድር ተከለከለች በአራተኛው ቀን ግን ከመለኮታዊ ብርሃኑ የሰናፍጭ ቅንጣት ታክል የተሳለባቸው ታናሽና ታላቅ ብርሃናት ለምድር ያበሩላት ጀመሩ።

እነዚህን ታላቅና ታናሽ ብርሃን ብዙ የብዙ ብዙ ከሆኑ ከዋክብት ጋር የሚያስተናግደው ዓለም ስሙ ጠፈር ተብሎ በፈጣሪ ተሰይሟል። ጠፈርን በፈጠረው ጊዜ እመቤታችንን በምሳሌ ሲነግረን ነው ይላሉ- አባቶቻችን። በሁለተኛው ቀን መፈጠሩ እመቤታችን በሁለተኛው ክፍለ ዘመን በዘመነ አሪት የምትገኝ መሆኗን አመላካች ነው። ይህን ጠፈር ሲሠራው እግዚአብሔር ከበላዩ ወንዳ ወንድ ውኃ ከበታቹ ደግሞ ሴታ ሴት ውኃን አስቀምጦበታል። በዚህም ድንግል ማርያም በሴትና በወንድ ሩካቤ ከሐናና ከኢያቄም የምትገኝ እንጂ ከሰማይ የምትገኝ ሰማዊያት እንዳልሆነች ተናገረ።

ሔኖ 16÷33 ከበላዩ ያለው ወንዳ ወንዱ ውኃ ሁሌም ሲገማሸር የሚኖር ቁጣ የማይለየው ኃያል ውኃ ሲሆን በኖኅ ዘመን ለተደረገው

ጥፋት የእግዚአብሔር በትር ሆኖ በማገልገሉ ይታወቃል። ወደ ታች ወርዶ ጠፈሩን እንዳያበላሽ አምላካችን ባቢል የሚባል የነፋስ ምሰሶ ተክሎለታል።አባቶቻችን ይህን ውኃ በጥንተ አብሶ ይመስሉታል። ለጠፈሩ ከዚያ ውኃ ጋር አለመገናኘት ከነፋስ በቀር ሌላ ማን የቆመ አለ? ለእመቤታችንም ከጥንተ አብሶ ንጹሕ መሆን በነፋስ ከሚመሰለው ከሥልጣነ እግዚአብሔር በቀር ሌላ ምን አለ! ሥልጣነ እግዚአብሔር ንጹሕ አደረጋት፤ ውኃውን ከላይ፣ ጠፈሩን ከታች አድርጎ ያለ አንዳች መነካካት ቢያኖራቸው ለእግዚአብሔር ምን ይሣነዋል?

ከሰው ልጆችስ እመቤታችንን ለይቶ ከጥንተ አብሶ ንጽሕት ቢያደርጋት ምን ይሳነዋል? ሊምረው የወደደውን ይምረዋል፤ ሊቀጣው የፈለገውን ይቀጣዋል ከፍጥረታት አንዱ ስንኳን ይህን አበጀህ ይህን አከፋህ ብሎ ሊመልስለት አይቻለውም። ከጠፈሩ በላይ ውኃውን በነፋሳት ትክሻ ላይ ሲሰቅለው፤ ከሱም በታች ጠፈሩን በቃሉ ሲያጸና ያማከረው አለ? ብቻውን ድንቅ ማድረግ የሚችለው ጌታ ዓለማችን በተፈጠረች በአራተኛው፤ ጠፈርን ባቆመ በሦስተኛው ቀን ይሄን ምንም ያልነበረውን ጠፈር ከቸርነቱ የተነሣ በፀሐይ፣ በጨረቃና በክዋክብት ልዩ ደም ግባት እንዲያሸበርቅ አደረገው በዚህም በአራተኛው ክፍለ ዘመን፤ ከአራተኛው ትውልድ ከቤተ ይሁዳ ፀሐየ ጽድቅ ኢየሱስ ክርስቶስ ለጨለማው ዓለም የሚወጣባት ፀሐይ መጐናጸፊያዋ፤ ጨረቃም መጫሚያዋ፤ አስራ ሁለቱ ከዋክብት የክብር ዘውድ የሆኑላት አማናዊቷ ጠፈር እመቤታችን መገኘቷን አስቀድሞ በዕለተ ፍጥረት፤ በጥንተ ፍጥረት ነገረን።

የብሩህ ሰማይ ፍንጣቂ ብርሃን ወደ ምድር እንዳይደርስ በመካከሉ ጠፈርና ሐኖስ ከገቡ በኋላ ምድርን ብቻ ሊጐበኝ የመጣው ብርሃን

ጠፈር ላይ ያሉት የፀሐይ፣ የጨረቃና የከዋክብት ብርሃን ነበር። በሰው ልጆች በደል ምክንያት ከሰማይ ወደ ምድር ይመጣ የነበረው ምሕረተ እግዚአብሔር ደግሞ ወደ ምድር የተመለሰው ከጽድቅ ጠፈራችን ከእመቤታችን ነው። ወደ ላይ ቀና ስንል ከሰማይ ቀድመን የምናያት የዓይናችን ማረፊያ ጠፈራችን፣ ከድቅድቅ ጨለማ ወደ ሚደነቅ ብርሃን የወጣንባት የብርሃን ሰሌዳችን እመቤታችን ድንግል ማርያም ናት።

ታላቁ የፀሐይ ጉልበት ጠፈሩን እንዳይፈረካከሰው ከበስተጀርባው ሐኖስን አሳዝሎ ሠርቶታል፤ የፀሐይን ግለት ሐኖስ ያቀዘቅዝለታል፤ ጠፈር ደግሞ በሐኖስ የፀሐይን ጨረር እንዳያርፍበት ይከላከልለታል እመቤታችንም ከአሳተ መለኮቱ የተነሣ እንዳትቃጠል፣ ከግርማ መለኮቱ የተነሣ ደክማ እንዳትዝል መንፈስ ቅዱስ ሞልቶባታል፤ የልዑል ኃይል ጸልሏታል። ከፀሐይ ፊት መቆም የቻለችው፣ ጨረቃን የተጫማችው ብቸኛ ጠፈር እመቤታችን ናት።

ልዩ ልዩ ክብርና መጠን ያላቸውን ከዋክብት በጠፈር ስሎ አስቀምጧቸዋል፤ አንዳንዶቹ ሰሌዳ እንጂ ብርሃን የሌላቸው ሲሆኑ አንዳንዶቹ ግን መጠነኛ ብርሃን ያላቸው ናቸው፤ ሌሎች ደግሞ ሳይታሰቡ ይወረወራሉ፣ በሰፊው ሰማይ ላይ እንደ ንስር ከአድማስ እስከ አድማስ ይወረወራሉ።

በእመቤታችንም ያመኑ ምዕመናን ባለ መቶ፣ ባለስልሳና ባለ ሠላሳ እየሆኑ ገነትን መንግሥተ ሰማያትን ይወርሳሉ። ከከብ ከከከብ እንደሚበልጥ እመቤታችን መሪ በሆነችበት በመንግሥተ ሰማያት መንገድ የሚሄዱ ቅዱሳንም አንዱ ከአንዱ በክብር ይበላለጣሉ። 1ኛ

ቆሮ 15፥47 አንዳንዶቹ በክብር ከፍ ከፍ ከማለታቸውም የተነሣ እንደ ሰማይ መላክ ብር ብር እያሉ ከጽርሐ አርያም እስከ በርባሮስ ከላይኛው ሰማይ እስከ ታችኛው እንጦርጦስ ወደ ወደዱት ይሄዳሉ።

ያለ ከልካይ በተሰጣቸውም ጸጋ በመባርቅት ጀርባ፣ በደመና ሠረገላ፣ በነፋሳት ትክሻ ተጭነው ይመላለሳሉ። አክናፈ ጸጋ ተሰጥቶአቸው ከወዲያ ወዲህ በእግረ መንፈስ፣ በክነፈ ነፋስ ይመላለሳሉ። አንዳንዶቹ ግን ከዚህ ልዩ ናቸው ከሠሌዳ በቀር ብርሃን ያልተሰጣቸዉን ከዋክብት በጠፈር እንደተመለሰትን ሁሉ በእመቤታችን እናትነት፣ በክርስቶስ መሠረትነት ከተገኘው የክርስትና ጠፈር ላይ የተሳሉ ከዋክብት ቢሆኑም ቅሉ ሃይማኖታቸውን በተግባር መግለጥ የተሳናቸው ሰዎችን ይመስላሉ። ክርስቲያን ተብለዋል እንጂ ለዚህ ስማቸው የሚመጥን ስም የሌላቸው ናቸው።

በጠፈር ይህን ሁሉ አየን ይህን ሁሉ ያሳየን ጠፈር በእርጅና አልተለወጠም። ከጥንተ ፍጥረት ጀምሮ እስከ ዛሬ እንዲሁ አለ። እመቤታችንም ከአዳም ጀምሮ እስከ ሐናና ኢያቄም፤ ከዚያም እስከ ዛሬ፤ ከነቢያት እስከ ሐዋርያት፣ ከሐዋርያት እስከ ሊቃውንት ያለና የነበረ ክብሯን ጠብቃ በንጽሕና ስርጉት፣ በድንግልና ጽንዕት ሆና መገኘቷን ያሳያል።

ሊፈጥረውም ጠፈሩን በቀስተ ደመና አምሳል አድርጎ፣ ፊቱን ወደ ምድር መልሶ ከላይ ወደ ታች ምድሩን እስኪነካ ድረስ በጥበብ አቁሞታል። ምድርና በውስጧ ያሉት ሁሉ በዚህ ጠፈር እቅፍ ውስጥ የሚኖሩ የጠፈር ጥገኞች ሆነው ለዘለዓለም ይኖራሉ። በምድራውያኑ ሥርዓት መሬታዊ ሆና ከእናትና ከአባቷ እመቤታችን ተወልዳለች፤ በሰማያውያኑ በመላእክት ሥርዓት ደግሞ እድሜ ዘመኗን ኑራለች።

ምድራዊውን መብል መጠጥ ንቃ ሰማያዊ መብል መጠጥን አስገኝታለች። ከላይ ወደ ታች የተዘረጋውን ጠፈር ተመልክተን እመቤታችን ከጥንት ጀምሮ ለመፈታውያን የተሰጠች የእግዚአብሔር የምሕረት ስጦታ መሆኗን አወቅን።ለዚህ ነው እንዲያውም አባቶቻችን ኪዳነ ምሕረት ሲሉ ስም ያወጡላት። ምድርና በውስጧ ያሉት ሁሉ በምሕረት የሚታሰቡበት ዘመን እደሚመጣ አውቀን፣ ተስፋችንን ሰንቀን እንድንቆይ ምልክት ከሆኑን ነገሮች አንዱ እኮ ይሄ ነው።

ምድርን ያገኘናት ከነጠፈሯ ነው። ምድር ያለ ጠፈር እንዳትኖር የከለከለ አምላክ ምድርን በሠራ ማግስት ጠፈርን ማድረጉ ያለ ወንጌል አረት፣ ያለ ሐዋርያት ነቢያት፣ ያለ እመቤታችንም ክርስትና የለም ሲለን ነው። ክርስትናን ያወቅነው ከእመቤታችን የተወለደው መሲሕ ክርስቶስ የሚል ስም ሲወጣለት ካየን በኋላ ነው። ክርስትናችን የተወለደው ከሷ ሲሆን ሕያው የሆነውና ወደ ዓለም የገባው መለኮት በተዋሐደው የአምላካችን ደም ነው። እናም የክርስትናችን ሐረገ ትውልዱ ሲመዘዝ፣ ታሪኩ ሲነገር መነሻ የሚያደርገው ድንግል ማርያምን ነውና ያለ እርሷ ክርስትናን ማሰብ ያለ ጠፈር የሆነች ምድርን እንደ መፈለግ ቁጥር ነው።

አራተኛው ክፍለ ዓለም

በአራተኛነት የምናገኛት ዓለም ይህች ምድር ናት። የሰው ዘር በጊዜያዊነት፣ እንስሳትና አራዊት በባለቤትነት ይኖሩባታል፣ ምድራውያን የምንላቸው ከሥጋና ከደም የተገኙ ፍጥረታት ሁሉ ከምድር የተገኙ በመሆናቸው እንደገና ተመልሰው ወደ ተገኙበት ምድር እንዲመለሱ ከሰማዩ ንጉሥ ትእዛዝ ተላልፏል።

በመጀመሪያ ከተፈጠረው ከሰማዩ ጋር የተገኘች ብቸኛ ፍጥረት በመሆኗም በመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያው ክፍል፣ የመጀመሪያው ዐረፍተ ነገር ላይ ከእግዚአብሔር ስም ቀጥሎ ስሟ ሊመዘገብ ችሏል። ይህች ምድር ወደ አምስት የሚጠጉ ክፍሎች ያሏት ቢሆንም አንድ መሬት እንጂ አምስት አትባልም። ሐዘን ይበዛባታል፣ ዓመፀኞች ይገዟታል፣ ግፈኞች ይነግሡባታል፣ ኃያላን ቀስታቸውን፣ መኪንኑ ሠራዊታቸውን ለሰልፍ ያስከትቱባታል ከመጀመሪያው በመላእክትና በአጋንንት መካከል ከተካሄደው እስከ መጨረሻው አርማጌዶን ጦርነት ሁሉም ይከናወንባታል፣ ያም ሆኖ ግን ያለ ጊዜዋ እንዳትጠፋ አምላክ በመሐል እጁ ይዟታል።

ሲመሠርታት ቀላል በሆኑትና ጽናት ከሌላቸው ፍጥረታት ከውኃ፣ ከነፋስና ከእሳት ጀርባ ላይ አስቀምጦ ነው፣ ረቂቃን፣ ልህሉሀን ከሆኑት ከነዚህ ፍጥረታት ላይ የተመሠረተች ቢሆንም ቅሉ ሷ ግን ከነሱ ከመሠረቶቿ ተለይታ ጽንዕት ናት። እግዚአብሔር ጥበበኛ ነው! ሁሉን መሸከም የምትችለውን ምድር ምንም መሸከም ከማይቻላቸው ረቂቃን ፍጥረታት አናት ላይ ሲያስቀምጣት በጥንቃቄ ነው። ምንም እንኳ ጽናት ከሌላቸው ከነዚህ ፍጥረታት ላይ ቢያስቀምጣትም እሷን ግን ሁሉን እንድትችል ከሁሉ በላይ አድርጎ ጽናትን አስታጥቆ ፈጠራት። እንደሰው ሰውኛው ቢታሰብማ ኖሮ ጽንዕት ምድር ከሥር፣ እነዚህ ደግሞ ከላይ በሆኑ ነበር፤

አምላካችን ሁሉን ቻይ ነውና ከሰው አዕምሮ በላይ የሆነውን ሥራ ሠርቶ ምድሪቱን አጸናት። ከሥር ያሉት በተለይም እሳትና ነፋስ ቀላሎች እንደመሆናቸው መጠን ሽቅብ ወደ ላይ እንውጣ ይላሉ፤ ምድርና ውኃ ከላይ ሆነው ወደታች ሲገፏቸው ይኖራሉ። እናም አሁን ስለምድር

26. ዘፍ 1፡2

ስናነሣ ቀላሎችን ፍጥረታት እሳትና ነፋስን የተሸከመች እርሷ ነች እንጂ ምንም በላያቸው ብትሆንም እነርሱ የተሸከሚት አይደሉም። ከሥራ የሚገኙ እነዚህ እሳት፣ ውኃና ነፋስ ከላይዋ ቢፈለጉም አይታጡም ሁሉን የተሸከመች ሥጋዊና ደማዊ ፍጥረታት የተወሰኑባት ይህች ምድር እመቤታችን ድንግል ማርያም ናት። ሰው ከምድር አፈር ተበጅቶ ምድርን በልቶ፣ ምድርን ለብሶ በምድር ላይ ይኖራል- ከአርጊቷ ምድር ወደ አዲሲቷ ምድር እስኪሸጋገር ድረስ። ታላቁ መጽሐፍ ከፍጥረታት ሁሉ ታላቅ የሆነውን የሰውን ተፈጥሮ ሲናገር ከምድር አፈር የተበጀ መለኮታዊ ሸክላ እንደሆነ ይመሰክራል። ዘፍ1÷27 ይህች ምድር የመጀመሪያውን ሰው አዳምን ከባሕርይዋ ያለ ዘርና ሩካቤ በእግዚአብሔር ቃል ብቻ አስገኘች። ከዚህ ተያይዞ ፍጥረት ሁሉ ከእርሷ ማሕጸን የወጣ መሬታዊ ሆነ። ሁለተኛይቱ ምድር ድንግል ማርያም ደግሞ የአዲሱ ፍጥረት አባት የሆነውን አዲሱን ሰው ኢየሱስ ክርስቶስን አስገኝታለች። በማሕጸኗ ስታሳድረው እንደ ፍጥረት ልማድ ዘር ምክንያት አልሆናትም። ገዥዋ፣ አለቃዋ፣ ጠባቂዋ፣ ተንከባካቢዋ አዳምን ምድር እንዳስገኘች ሁሉ እመቤታችን ድንግል ማርያምም ፈጣሪዋን ወለደችው፣ ገዥዋን፣ አስገኝዋን አስገኘችው፣ የቀደማት እርሱን ቀደመችው።

ከእርሱ ተያይዞ ከማይሞትና ከማይጠፋ ዘር የሚወለዱት ምእመናን የዘር ሐረግ ሳይቋረጥ መቆጠር ጀመረ። ታላቁ መጽሐፍ ዓለማችን ህልውናዋ ከተረጋገጠ በኋላ በመጀመሪያውና በሁለተኛው ቀን የነበረውን ትዕይንት በተናገረበት አንቀጹ ስለ ምድር የተናገረው እጅግ አስደናቂ ነገር ነው። " ወምድርኒ ሀለወት እራቃ ወኢታስተርኢ " ምድርም ባዶዋን ነበረች አትታይምም ነበር ዘፍ 1÷2 ይላል።

ምድርም ባዶ ነበረች ስትል ቅድስት አሪት መናገሯ ስለዚህ ግዙፍ ምድር አይደለም ምክንያቱም በዚያ ወቅት ባዶውን አልነበረምና። ከዚህ እስከ ብሩህ ሰማይ ውኃ ሞልቶ ይዞት ነበር እንጂ። ይልቁንም ቅድስት አሪት ዳግማዊት ምድር እመቤታችን ከኃጢአት ከርዙሰት የተለየች መሆኗን ለመግለጽ " ምድርም ባዶ ነበረች " አለች እንጂ። ከዚያው በማያያዝ "አትታይም ነበር" ማለቱስ ያን ጊዜ ያልተፈጠረች በአምላክ ኅሊና ታስባ፣ ተሰውራ ትኖር የነበረች መሆኗን የሚገልጽ ነው እንጂ ሌላ ምንድነው።

የእግዚአብሔር መንፈስ ገና ከመታሰቧ ጀምሮ የመረጣትና ያልተለያት መሆኑንም ሲገልጽልን "ወመንፈሰ እግዚአብሔር ይጼልል መልዕልተ ውእቱ ማይ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ በውኃው ላይ ሰፎ ይኖር ነበር ብሏል።

ስለ ሰማይ ሲናገር ይህን አልተናገረም፣ ምድሪቱን ጽንፍ እስከ ጽንፍ ስለ ከደነው ውኃ ሲናገር ግን የእግዚአብሔር መንፈስ በላይዋ ላይ ሰፍፎ የነበረ መሆኑን ይናገራል። አባቶቻችንም ስለ እመቤታችን ሲናገሩ ‹‹መንፈስ ቅዱስ ዐቀባ እምከርሠ እማ ፣ከእናቷ ከሔዋን ባሕርይ ጀምሮ መንፈስ ቅዱስ ጠበቃት›› ብለው መናገራቸው ለዚህ ነው። ከጥንት ከመሠረት ጀምሮ ሰማያውያኑን መላእክት ሳይባርካቸው ፣ምድራውያኑን ጻድቃንም ሳይመርጣቸው ጀምሮ የጌታ መንፈስ ተለይቷት የማያውቅ ማኅደረ መንፈስ ቅዱስ ናት።

አንድም:- መንፈስ የሚለው ቃል ፈቃደ እግዚአብሔር ተብሎ ይተረጐማል።[27]" የእግዚአብሔር መንፈስ በላይዋ ሰፍፎ ይኖር ነበር" ማለቱ ከመጀመሪያው ጀምሮ የጌታ እናት ለመሆን ከለማያዊው አምላክ ፈቃድ የተሰጣት መሆኑን የሚያስረግጥ ቃል ነው።

27. ዮሐንስ አፈወርቅ

ፈቃዱማ ቢሆን ነው ከእናት ከአባቷ ቤት ለይቶ ጎብስት ለማያዊ ፣ጽዋዕ ለማያዊ መግቦ አሳድጐ ካደገችም በኋላ ከአይሁድ ሴራ ሰውሮ ፣መጥቁል የተባለው ጠንቋይ ከበረሐ ወርዶ ከጠራቸው 373 አጋንንት አድኖ እናቱ ያደረጋት ፈቃዱ ቢሆንም አይደል?።

አስቀድመን እንደተናገርነው እርሷ ከዓለም በፊት የነበረች ሌላ ዓለም፣ ከመገለጧም በፊት በአምላክ ጎሊና ታስባ ትኖር የነበረች ናት። ይህን ያሰበ ጊዜ ሙሴ የተናገረው ነገር ምንኛ ድንቅ ነው "ምድርም እራቁቷን ነበረች አትታይምም ነበር" ዘፍ 1፥2 ራቁቷን ሆና ነገር ግን የማትታይ ምድር ነበረች ለምን ከተባለ ሊቀ ነቢያት ሙሴ መልስ አለው "ወኢኮነት ድሉተ የተዘጋጀች አልነበረችም።

በአምላክ ጎሊና የተገለጠች መሆኗ ዕራቁቷን ነበረች አሰኝቷታል ገና በእዝነ አዳምም ያልተሰማች ልዩ የእግዚአብሔር ምሥጢር በመሆኗ ደግሞ አትታይምም ነበር ተባለላት ታሰበች እንጂ አልተፈጠረችም ነበርና። ይልቁንም በሥራው ድንቅ የሆነው አምላክ ከዳር እስከ ዳር በውኃ መልቷት የነበረ መሆኑ በሥነ ፍጥረታት ታሪክ የተረጋገጠ ነው፡ እስከ ሁለተኛው ቀን ድረስ በውኃው ላይ የእግዚአብሔር መንፈስ ሰፍፎ ይዞት ምድሪቱ ፊቷ እንዳይታይ አድርጓት ነበር።

ሁሉን የሚያዘጋጀው እግዚአብሔር እስኪያዘጋጀው ድረስ ምድሪቱን ሸፍኖ የነበረው ውኃ እመቤታችን ድንግል ማርያም እስከተገለጠችበት ጊዜ የነበረውን ዘመን ያመላክታል ይህን ውኃ አምላክ በቃሉ ከፈለው በሁለተኛይቱ ቀን ከሦስት ቦታ ላይ እንዲሰበሰብ ተወስኖበት ውኃው እንደተከፈለ ለዓመተ ፍዳ ለዓመተ ኩነኔ ሁለተኛ በሆነች ዓመተ ምሕረት በተሰኘው ዘመን ጌታን በድንግልና ጸንሳ በትንቢተ ነቢያት የተዘጋጀች ሆና እስከተገለጠችበት ጊዜ የነበረውን ዘመን ለሦስት ይከፈላል ዘመነ አበው፣ ዘመነ መሳፍንት፣ ዘመነ ነገሥት ተብሎ፤

በነዚህ በሦስቱም ክፍላተ አዝማን መንፈስ ቅዱስ በላይዋ ላይ ሰፍፎ እስከ ዳግመኛው የምሕረት ዓመት ድረስ የማትታይ ምድር እደረጋት በእውነት ይህ የእግዚአብሔር ሐሳብ ስለ እመቤታችን ባይሆንማ ኖሮ ሊቀ ነቢያት ሙሴን በውኃ ላይ በረቂቅ ሰፍፎ ስለነበረው የእግዚአብሔር መንፈስ እንዲናገር ምን አስገደደው፤ ምክንያቱም በእያንዳንዱ ፍጥረት ላይ የእግዚአብሔር መንፈስ የማይለይ ሆኖ ሳለ ከዚህ ሲደርስ ለይቶ አስቦታልና እስከ ሁለተኛው ቀን ድረስ በመንፈስ ቅዱስ ጥላ ሥር የምታርፍ መሆኗን ውኃውም ተዘጋጅቶ ሲያልቅ የምትገለጥ መሆኗን አሳየን።

ውኃ ብለን የጠራነው ዘመን ሲፈጸም ያለ ገበሬ ድካም፣ ያለተክልና ያለዘር ማፍራትና ማለምለም የሚቻላት የተዘጋጀችዋ ምድር እግዚአብሔር የቀጠረው ቀን ሲደርስ ተገለጠች ዓለማችን በጥንተ ተፈጥሮዋ ከእግዚአብሔር በሆነ ብርሃን ስትመራ የቀናቱ ሁሉ መካከለኛ በሆነው በዕለተ ረቡዕ ፀሐይ እንደተገለጠች ክብሯ ከፀሐይ ይልቅ የሚያበራው እመቤታችንም የዘመናት ማዕከል ላይ ማለትም በዓመተ ፍዳ መካተቻ በዓመተ ምሕረት መባቻ ላይ ተገለጠች በጣም የሚገርመው ፀሐይ በአራተኛው ቀን በከዋክብት ተከባ እንደታየች እመቤታችንም ከአራተኛው ትውልድ ከቤተ ይሁዳ ነው የተወለደችው አስራ ሁለቱን ነገደ እስራኤል ከሮቤል ጀምረን ስንቆጥር ይሁዳ አራተኛ ስለሚሆን ነው። የዓለም ብርሃን ክርስቶስ ከእርሷ ይወጣ ዘንድ የጽድቅ ፀሐይ እመቤታችን ከአራተኛው ትውልድ ወጣች ያውም በከዋክብቱ በነቢያት በካህናት ታጅባ ዮሐ 8፥12 ከድቅድቅ ጨለማ ወደ ሚደነቅ ብርሃን ሰው እንዲወጣ የአማናዊው ብርሃን ሰሌዳ ድንግል በሰማይ ሰሌዳ ላይ ተቀረጸች።

ሦስቱ ነገሮች ለዚች ምድር መሠረት ሆነዋታል፣ በላይዋም እነርሱ ያድሩባታል። በምድር ላይ የሚርመሰመሰው ማንኛውም ፍጥረት ቢሆንም ከነዚህ በምንም ያልተለየ የነዚህ ነገሮች ውሕድ ውጤት ነው። ያለ እነርሱም ምድር ባዶ ናት እመቤታችንም መሠረቷ ሥሉስ ቅዱስ የሆነላት ንጽሕት አዳራሽ ናት። ጉልላቷም እግዚአብሔር ነው በውስጧም የሞላው እርሱ ነው፤ እርሷ ለእርሱ ማደሪያነት ተዘጋጅታለች እንጂ ሌላ ምን አላት፤ ከእርሱም በቀር ሌላ ቢፈለግ በውስጧ ምንም የለም፤ ለእርሱ ብቻ የተሠራች ምሥራቃዊት አዳራሽ ናትና። ወደእርሷ ተልኮ የመጣውም መላክ ያረጋገጠላት እውነት ይህ ነው- የሦስቱ አካላት ማኅደር መሆኗን። በውኃ ላይ ተመሥርታ፤ በእሳትና በነፋስ ላይ ጸንታ የምትኖረው ምድራችን ቢያንስ በሦስት ታላላቅ ቁም ነገሮች ተለይታ ስትመሰገን ትኖራለች።

ታማኝ፡- የሚያምነው ቢታጣ እንኳን ታማኝ ሆኖ ለዘለዓለም የሚኖረው ንጉሣችን እግዚአብሔር ብቻ ነው። መታመን የባሕርይ ገንዘቡ በመሆኑ የሚያምኑ ፍጥረታት ከመኖራቸው በፊትም እርሱ የታመነ ነበርና። ፍጥረታት ግን ሲሞላ ሲጐድል ነው ማመንና መታመን ክዳትና ሽንገላ ይፈራረቁባቸዋል።

ከፍጥረታት ሁሉ እንደ ምድር በታማኝነቱ የተመሰከረለት ደግሞ ማንም የለም። ምድራውያን ሁሉ የአንድ ነገር ጥገኞች ናቸው- የምድር። የሥጋ ለባሹ ኑሮ በሁሉም መንገድ ከምድር ጋር የተያያዘ ነው። ሁሉም በእርሷ እንጂ ያለ እርሷ መኖር የማይችል መሆኑ ቢታወቅም ምድራቱን ሁልጊዜም በታማኝነት ገበሬው ከጐታው፣ ከጐተራው እያወጣ ያለውን የሚበትነው በምድር ላይ ነው። ከምድር የሰበሰበውን መልሶ በምድር ላይ ሲበትነው ያለ አንዳች መጠራጠር ነው። ንጉሥ

በመካንንቱ፣ በሠራዊቱ፣ ጳጳሱ በሊቃውንቱ፣ መምህር በአርድእቱ ታማኝነትን አጥቶ ተስፋ በቆረጠበት በዚህ ዘመን በምድርና በገበሬው መካከል ግን ዛሬም መተማመን አለ፤ እርሷ ለዘለዓለም ታማኝ ናትና።

እመቤታችን ድንግል ማርያምም በሦስቱ ነገሮች ለዘለዓለም የታመነች ናት።

ሀ/ በድንግልና፡-

እንከን የሌለው የውስጥና የውጭ ድንግልናን መኖር የቻለች እመቤታችን ድንግል ማርያም ብቻ ናት። ድንግል የተባሉ በዚች ዓለም ብዙዎች ቢሆኑም በድንግልናቸው ጥያቄ ያልተነሣባቸው ግን የሉም። በዚያውም ላይ የውስጥና የውጭ ድንግልናቸውን ጠብቆ በመቆየት ለነፍሳቸውም ለሥጋቸውም ድንግልና ታማኞች አይደሉም፤ እመቤታችን ብቻ በዚህ የታመነች ናት። ድንግል ከተባለች በኋላ ተፈትሆ የለባትም፤ ድንግልናዋን በጎልዮ ሳይቀር ላለማርከስ የታመነች ናት።

ለዚህ ድንግልና ካላት መታመን የተነሣ ትወልጃለሽ ብሎ ለነገራት የእግዚአብሔር መላክ "እፎኑ ይከውነኒ ዝንቱ እንዘ ኢየአምር ብእሴ" ወንድ ሳላውቅ ይህ እንደምን ይሆንልኛል ብላው ነበር። ለድንግልናዋ ታማኝ መሆኗ ይህን አናግሯታል እንጂ ሌላ ምን ይሆናል። ገና የ15 ዓመት ብላቴና ብትሆንም ለዘለዓለም በልቧ ድንግል ነበረችና ይህን ተናገረች ::ቅዱስ ኤፍሬምም "ድንግል ማእምንት፤ በድንግልና የታመነች" ብሎ ያመሰገናት በዚህ ምክንያት ነው።

ዛሬም ከክርስትናው ወዲያ ማዶ ባሉት በመሐመዳውያን ዘንድ ሳይቀር የእርሷ ድንግልናዋ ያለ ጥያቄ የተረጋገጠ ነው። ይችኛዋ ምድር ገበሬው ሳይወጣባት ሳይወርድባት ነበር ቀዳሜ ፍጥረታት አዳምን ያስገኘችው፣ ሁለተኛይቱ ምድር ድንግል ማርያምም ዘርዐ ብእሲ በሥጋዋ፣ ኃጢአተ አዳም በነፍሷ፣ ምክረ ሰይጣን በልቧ ሳይገኝባት

በድንግልና ሆና በኵረ ፍጥረታት ዳግማዊ አዳም ኢየሱስ ክርስቶስን ወለደችልን።

ቀዳሜ ፍጥረት ከቀዳሚት ምድር፣ በኵረ ፍጥረታት ከዳግሚት ምድር ተገኘልን።ከመጀመሪያ የሆነችው ምድር ሕያው ነፍስ ያለው ሰውን፣ ሁለተኛይቱ ምድር ደግሞ ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ የሆነውን ሰው አስገኘችልን።

ከታተመው ዓለት ላይ ውኃን አፍልቆ የእስራኤልን ስለ ውኃ ጥማት የተጮኽ ጩኽት ያስወገደ ጌታ በሲኦል በረሐ ጽምዐ ነፍስ ደርሶባቸው ይጪጪሁ ለነበሩ ነፍሳት ጩኽታቸውን ሰምቶ የሕይወት ውኃን ያፈለቀው ከታተመችው ዓለት ከእመቤታችን ነው። እነሱ የሚያውቁት ያንኑ ነበርና ‹‹ብፁዕ ዘይሰቲ እማየ አይጋቲሃ ለግብፅ፤ ከግብጽ ምንጮች ውኃን የሚጠጣ ብፁዕ ነው›› እያሉ የምድረ በዳ ኑሮአቸውን ያማርሩ በነበሩበት በዚያ ሰዓት ከግብጽ ምንጮች የተሻለ ጥሩ ምንጭ ያለው መሆኑን ለሕዝቡ እግዚአብሔር ያስታወቀባት እስከ ዛሬም ድረስ "ዘአንቅዐ ማየ እምኰኵህ እስመ ለዓለም ምሕረቱ" ከዓለት ውኃን ያፈለቀው እርሱ ምሕረቱ ለዘለዓለም ነውና" መዝ 135÷... ተብሎ የተመሰገነባት ያች ዓለት ከዓለቶች ሁሉ ተለይታ የታተመች ዓለት ናት።

እስኪ አስቡት! በዚያም ዘመን በሲኦል የነበሩ ነፍሳት ከመዳን ቀን በፊት ከመከራው ብዛት የተነሣ " አብርሃም አባት ሆይ ማረኝ በዚህ ነበልባል እሰቃያለሁና የጣቱን ጫፍ በውኃ ነክሮ ጉሮሮዬን ያርስልኝ ዘንድ አልዓዛርን እንድትሰድልኝ እለምንህለሁ ሉቃ 16÷24 እያሉ ይጮሁ የነበረበት ዘመን ነበርክ፤ ለተጠማው ዓለም ዘለዓለማዊት ጽምዐ ነፍስን ያስወገደለት የሕይወት ውኃችን ክርስቶስ የፈለቀው ከመንፈሳዊቷ ዓለት ከእመቤታችን ነው"። መጠማታችንን አይቶ

ነው "የተጠማ ሁሉ ወደ እኔ ይምጣ ይጠጣም" ዮሐ 6÷... ሲል በመካከላችን የሰበከው።

ስድስት መቶ ሺህ ሕዝብን ከታተመው ዓለት ውኃን አፍልቆ መመገብ የቻለ ጌታ በድንግልና ከታተመ ማሕጸን የሕይወትን ውኃ አፍልቆ አስራኤል ዘነፍስ እኛን ከዘለዓለማዊ ጥማት ቢታደገን ምን ይላነዋል። አስራኤል የጠጡላት ዓለት እስከ ኢያሪኮ ድረስ ይዘዋት ተጉዘዋል፤ ዮርዳኖስን ከፍለው ሲሻገሩም አብራ ተሻግራለች፤ የኢያሪኮን ቅጥር አፍርሰው የተስፋይቱን ምድር ከወረሱም በኋላ አልተዋትም። ዛሬ የሚኖሩት በኢያሪኮ ውኃ ቢሆንም ከበረሐው ቢያመልጡም ዓለቲቱን ግን በክብር ተቀምጣ በታላቂቱ የኢየሩሳሌም ከተማ ትኖር ነበር። ጌታ ወደ መቃብር በወረደባት በዚያች ቀን ለመቃብሩ ክዳን ያደረጓት እርሷ ነች።

አያችሁ! እስከ ክርስቶስ መምጣት ከሺህ ዓመት በላይ የታተመች ዓለት ነበረች ማለት ነው። የታተመች ሆና ለዘመን ዘመናት እንድትኖር ካደረጋት እመቤታችን ድንግል ማርያም በድንግልና የታመነች ሆና እንድትኖር ቢያደርጋት ከባድ ነው?

የተስፋይቱን ምድር እስክንወርስ የሰይጣንን ቅጥር አፍርሰን እስክናልፍ ድረስ በልቡናችን ትክሻ ላይ ተሸክመናት የምንዞር ዓለታችን ናት። ምድረ ርስታችንን መንግሥተ ሰማያትን እስክንወርስ ድረስ ሕይወታችንን ያቆየልን የሕይወት ውኃን ያፈለቀችልን በመሆኗ ሊቃውንቱ ሲያወድሷት "ንቅዐ ፈልፈለ ማየ ሕይወት፤ የሕይወት ምንጭ የኢየሱስ ክርስቶስ መገኛ›› ብለዋታል። ሌላውም ሊቅ በቅዳሴው እመቤታችንን ሲገልጻት "የሚበላውን የሚጠጣውን ያስገኘሽልን ብለው ክርስቶስን ያየንባት መንፈላዊት ዓለታችን መሆኗን መስክረውልናል። በሌላ በኩል ካየነው ለይስሐቅ ቤዛ የሆነው በግ ከጎቱም ግንድ የተገኘ

ነው፤ በጉን አግኝቶ መሥዋዕት ማቅረቡን እንጂ አብርሃም ሌላ ምን ያውቃል "በጉንማ እግዚአብሔር ያዘጋጃል" ማለቱስ ለዚህ አይደል፤ የበጉ መገኘት ድንቅ ነው። ከጉንዱ ላይ ተገኘ እንጂ ከጉንዱ ከወዴት በኩል እንደወጣ ግን የሚታወቅ ነገር በአብርሃም ዘንድ የለም። በኋለኛው ዘመን ለሰው ሁሉ ቤዛ ስለሚሆነው በግ እንጂ ሲያሳየው የነበረው ስለ አንዱ ጊዜያዊና ምድራዊ በግ አልነበረምና። ይህን ታላቅ ምሥጢር ከሰው አዕምሮ በላይ መሆኑን ለመግለጽ ከአብርሃም እውቅና ውጭ አደረገው።

ለይስሐቅ የወረደው በግ በማይመረመር ግብር ከተገኘ ያንን በግ ያስገኘችው ዕፀ ሳቤቅ ከዚያ በኋላ ተፈትሆ ተገኝባት አልተባለችም እመቤታችንም እንዲሁ ናት ለዘለዓለም በማይመረመር ድንግልና ጎትምት ናት እኛም እንደ ቅዱስ ኤፍሬም "ድንግል ማእምንት" ስንላት ለዘለዓለም እንኖራለን።

ለ/ <u>ምሕረት ለማግኘት</u>:- አምነው የሚልኩት ታማኝ መልእክተኛ ማግኘት የነገር ፍጻሜ መቅድም ነው። በዚህ ዓለም ላይ አስቸጋሪው ነገርም እሱ ሳይሆን አይቀርም፤ ቀዳሜ ፍጥረታት አዳም ለእግዚአብሔር ታማኝ አልሆን ብሎ መታመን ከምድር ላይ መጉደል ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ብዙ መልእክተኞች በምድር ላይ የኖሩ ቢሆንም ተልእኮአቸው ግን ጉዳይ ፈጻሚ አልነበረም። በእግዚአብሔር ፊት ያለ ነውር የሚመላለስ ንጹሕና ያለ ነውር የሆነ ጻድቅ መልእክተኛ በምድር ላይ አልተገኘም ነበርና።
ከአቤል እስከ ዘካርያስ በገዛ ደማቸው መፍሰስ ሳይቀር ለማገልገል የወሰኑ ሰዎች የነበሩ ቢሆንም ምን አልባት ስማቸውን በታሪክ መጽሐፍ ላይ አለመዘግበው ይሆናል እንጂ ሌላ ምን ጠቅመውናል። ምሕረት ለማግለድ

ያለ ነውር የቆሙ ታማኝ አገልጋዮች አልነበሩምና። እመቤታችን ድንግል ማርያም ግን ከዚህ ሁሉ ተለይታ ምሕረት ለማግለድ የታመነች ናት፤ እግዚአብሔር ዓለሙን ኃጢአት በወለደው ንፍር ውኃ ሲያጠፋ ሸሽጎ ያስቀራት ንጽሕት ርግብ ናትና። በመጀመሪያ በኖኅ ፊት ለመልእክተኝነት ከሌላው ፍጥረት ሁሉ ተለይቶ ሞገስን ያገኘው ቁራ ነበር፤ ኖኅ መረጠው እንጂ እሱ ግን መመረጥ የማይገባው ፍጥረት ነበር።

ምንም ከመርከብ ሲወጣ ንጹሕ ሆኖ የወጣ ቢሆንም ከመርከቧ ውጪ ባለው የዓለም ርኩሰት ላለመተዳደፍ የማይለወጥ ጎሊና የነበረው ፍጥረት ግን አልነበረም። ይህም ማለት ፍጥረት ሁሉ በእግዚአብሔር ሥልጣን ያለ ነውር ንጹሕ ሆኖ የተፈጠረ ቢሆንም ወደ ዓለም ከመጣ በኋላ ግን ያለ ኃጢአት እና ያለ ርኩሰት መኖር የቻለ አልነበረም። ቁራ ታማኝ ሆኖ ሊያገለግል በኖኅ ፊት ቃል ገብቶ የወጣ ቢሆንም ወደ ዓለም ሲመጣ የገጠመውን የሥጋ ፈተና አሸንፎ፤ ለተመረጠለት ዓላማ ታማኝ ሆኖ፤ ለተጨነቀው የመርከቧ ውስጥ ነዋሪ እግዚአብሔር ምድርን ይቅር እንዳላት ለመግለጽ አልተቻለውም።

ርግብ እስከወጣችበት ጊዜ ድረስ የእግዚአብሔር ምሕረት ለመርከቧ ነዋሪዎች አልታወቀላቸውም ነበር፤ ይልቁንም በመፍራትና በመንቀጥቀጥ ነበሩ እንጂ። የሞት ጥላ በጣለበት ዓለም ውስጥ እየኖሩ እንዴት ብሎ ጎሊናቸው ዕረፍት ያገኛል። የሞት ጥላ ከምድር መወገዱን፤ በምድር ሰላም መሰበኩን ርግብ ካልተመለሰች በስተቀር በምን እርግጠኛ ይሆናሉ፤ ስትጠበቅ የነበረችው የሰላም ርግብ ስትመለስ ግን የእግዚአብሔር ምሕረት ለፍጥረት ታወቀ። ቁራውን ያባበለች ዓለም፤ ለቁራ ወደ መርከብ አለመመለስ ምክንያት የሆነ

የዓለም ርኩሰት ታማኝነቷን ሳያጐድልባት ታምና የተኘች አማናዊቷ ርግባችን እመቤታችንም በእኛ በመርከቧ ውስጥ በምንኖር ትውልዶች እና ፍጥረቶች ዘንድ ምሕረትን ለማማለድ የታመነች ናት።

የዓለም ርኩሰት፣ የሰው ልጆች የኃጢአት ብዛት ሊለውጠው የማይችል ጽኑዕ የምሕረት ቃል ኪዳን አላትና ለዚህ ደግሞ ብቁ ያደረጋት በዓለም ውስጥ ያለው ምኞትና ክፋት የማይለውጣት ጽንዕት በመሆኗ ነው። ይህን የተረዳው የሀገራችን ሕዝብ ዛሬም ድረስ ሲጨንቀው መርከቧ ውስጥ ሆኖ የተቃጣለትን የእግዚአብሔር ምሕረት ለማወቅ ስሟን ጠርቶ የሰላሟን ርግብ እመቤታችንን ወደ እግዚአብሔር ይልካል። ከጠባቧ መርከብ ወደ ሰፊው ዓለም ኖኅና ቤተሰቡ የወጡት ከርግቧ በተረዱት የእግዚአብሔር ሰላም እንደሆነ ሁሉ ዛሬም በምጥ፣ በጣርና በጭንቀት የሚኖሩ የቅዱሳን ነፍሳት ከጠባቡ የሥጋ ኑሮ ወደ ሰፊው የነፍሳት መኖሪያ ዓለም ለመሸጋገር ለመንፈሳዊት ርግብ ድንግል ማርያም የተሰጠውን የማማለድ ሥልጣን ተስፋ ያደርጋሉ። በዚህ ዓለም ስንኖር "አ! መስተምሕርት አስተምሕሪ ኀበ ወልድኪ ከመ ያዕርፍ ነፍሰ ኵሎሙ ጻድላት ...." አማላጅት ሆይ! የጻድላትን ..... ነፍስ ይቅር ይል ዘንድ ከልጅሽ ዘንድ አሳስቢ" እያልን ላለፈውም ለሚመጣውም ለሙታንም ለሕያዋንም የታመነ የምሕረት ቃል ኪዳኗን እንማጸናለን። በአጸደ ሥጋ፣ በአጸደ ነፍስ፣ በገነት በመንግሥተ ሰማያት ለምንኖር ለሁላችንም ምሕረት ለማማለድ የታመነች በመሆኗ "ሰዓሊተ ምሕረት[29] ማእምንት" ብለን እናወድሳታለን።

ሐ/ <u>ወላዲተ አምላክ ማእምንት</u>:- ቀዳሚ አዳምን ለማስገኘት ባሕር አልተመረጠችም፣ ሰማይ እድሉን አላገኘችም፣ ይህች ያለንባት ምድር ብቻ በፈጣሪ የታደለች ሆነች እንጂ። የምድር እናትነት

ለአዳም የታመነች ናት፣ እንደዚሁ ዳግማዊ አዳም ኢየሱስ ክርስቶስን ለማስገኘት እመቤታችን የታመነች ናት። በሚያስደንቅ ተአምራት የሚያስደንቅ ጸጋ የተሰጣቸው ልጆችን ለመውለድ የታደሉ ብዙዎች ናቸው። አምላክን ለመውለድ ግን አልታደሉም፣ ለዚህ የታመኑ አልነበሩምና። እመቤታችን ብቻ ለዚህ የታመነች ናት፣ ለትንቢተ ነቢያት፣ ለሱባዔ አበው ቀደምት የታመነ ከእርሷ በቀር በምድር ላይ ማንም አልተገኘም ነበርና። ለመመረጧ ምክንያት የሆናትም የታመነች ሆና መገኘቷ ነበር፣ የሰማዩን ምሥጢር ለመስማት ከርሷ በቀር ማን ብቃት ነበረው፣ በሰማይ የሚኖሩ አልሰሙትም፣ ለዚህ የታደሉ አልነበሩምና።

ምሥጢሩ ታላቅ በመሆኑ ከፍጡራን ሁሉ ታላቅ ለሆነችው ለእመቤታችን ካልሆነ ለሌላ ለማን ይነገራል፣ በሰማይ በእግዚአብሔር ዘንድ የተመከረውን የሥጋዌ ምሥጢር የሰማዩ መላእክት የሰሙት እርሷ ከሰማችው ከ33 ዓመት በኋላ ነው። እርሷ ግን ከባለሟሎቹ ይልቅ ባለሟል፣ ከወዳጆቹም በላይ ወዳጅ ናትና አስቀድማ ብትሰማም በልብዋ ጠብቃ ትኖር ነበር ብሎ ታላቁ መጽሐፍ ነግሮናል "ማርያምም በልብዋ ትጠብቀው ነበር" ሉቃ 2÷51እንዲል።

ለዚህ ሁሉ ጸጋ የተመረጠች ቢሆንም ብዙዎች ግን ወላዲተ አምላክ በመሆኗ ላይ ብዙ ብለዋል እነ ንስጥሮስ ወላዲተ ሰብእ እንጂ ወላዲተ አምላክ ልትባል አይገባም ሲሉ አይሁድና ፈረሳውያን ደግሞ እርሷ የወለደችው አምላክን አይደለም የአምላክ እናት ማርያም ገና አልመጣችም በማለት በነቢያት የተነገረላት ወላዲተ አምላክ እሷ ለመሆኗ ጥያቄን ያነሣሉ፣ እነ ሣምሳጢ ጳውሎስ የአምላክ ማደሪያ ለመሆን የተመረጠውን ኢየሱስ የተባለውን ሰው ወለደች፣ እርሷ

በወለደቸውም አምላክ አደረበት በማለት የእመቤታችንን ክብር ብቻ ሳይሆን የክርስቶስንም የባሕርይ አምላክነት ይክዳሉ። በዚህ በከፋው የክህደት መርዛቸው የዋሃን ምእመናንን ይዋጋሉ።

እንደ እውነቱ ከሆነ የእመቤታችንን ወላዲተ አምላክነት ሰይጣን ራሱ እንኳን አይክድም። ምክንያቱም እነሱ ይህን መሰል ትምህርት ከማስተማራቸው በፊት ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲናገር "የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ" ሲል ተሰምቷልና። ማቴ 8፥29 ሉቃ 4፥3 መንፈስ ቅዱስ በተለያዩ ሰዎች ላይ አድሮ ሲናገር እንደሰማነው ግን እመቤታችን ወላዲተ አምላክ ለመሆኗ ምንም የሚያጠራጥር ነገር አላየንም። ከብርሃናዊው መላክ ከቅዱስ ገብርኤል ጀምሮ ስለ እርሷ የተናገሩ ሰዎች ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም እንደተናገረው ድንቅ ድንቅ ነገርን ተናግረውላታል። በሰማይ የሚኖሩ ሦስቱ አካላት ወደ አዲሲቷ ሰማይ ድንግል ማርያም የሚመጡና የሚያድሩ መሆናቸውን መላኩ ካበሠራት በኋላ ከእመቤታችን ጋር ለመገናኘት የታደለችው ኤልሳቤጥም የጌታችን እናት መሆኗን ያለ ፍርሀት መስክራለች። ሉቃ 1፥35 ይህ ቀዳሚው ምስክርነት ነው- ስለ እመቤታችን ወላዲተ አምላክነት። ከዚያ በኋላማ ከሐዋርያት ዛሬ እስከተነሡ ሊቃውንት፣ ትናንት ከነበሩ ቅዱሳን ዛሬ እስከምናቃውቸው መምህራን የእርሷን ወላዲተ አምላክነት ያለ ማቋረጥ በንባብ፣ በዜማ ለዘመን ዘመናት ያውጃሉ።

በተለይም ከሦስተኛው እስከ አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በሀገራችንም ሆነ በሌላው ዓለም የተነሡ አባቶቻችን ወላዲተ አምላክ ብለው መንፈስ ቅዱስ በሚመራው በኤፌሶኑ ጉባዔያቸው ወስነው ተነሡ ከዚያ በፊት ከዚያም በኋላ የነበሩ ቅዱሳን ሁሉ ዘመንን ተሻግሮ በሚመጣው ድርሳናቸው ለዘለዓለም ወላዲተ አምላክ ብለው አተሙት። ይህ

ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ሐሳብ መሆኑን አስቀድሞ በኤልሳቤጥ ንግግር እንደተረዳነው በኋላም በኤፌሶኑ ጉባኤም መቅደንዮስን በመቅጣት ወላዲተ አምላክ መባል የሚገባት መሆኑን አስረዳ። ከሰማይ እስከ ምድር በተዘረጋው የሥነ ፍጥረት ሥርዓት የፍጡራን አንደበት ሁሉ ወላዲተ አምላክ ብለው ይጣራሉ። ስዕሏን የሚስሉ ሰዓልያን ይህንን ለማስረዳት አምላክን በግራ እጇ አስይዘው ይስላሉ፤ ስሟን በሚጠሩበት ቦታ ሁሉ ወላዲተ አምላክ የሚል ቅጽል ያስቀምጣሉ፤ ከሌሎች ማርያሞች ለመለየት ሁል ጊዜ ይህን መግለጫ ይጠቀማሉ።

ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ እስከዛሬ፣ ከዛሬም እስከ ዘለዓለም የአምላክን ሰው መሆን በሚያምኑት ሁሉ ዘንድ አምላክን ለመውለድ እርሷ የታመነች ናት። እምኀበ አልቦ ኀበ ቦ /ካለመኖር ወደ መኖር/ የመጣችው መሬት ቀዳሚ አዳምን እንዳስገኘች መካኒቱ የሐና ፍሬ እመቤታችንም የአዳም ሁለተኛ ኢየሱስ ክርስቶስን ማስገኘቷ የቀደመውን የአዳምን ተፈጥሮ እንድናስታውስ አድርጎናል።

የመጀመሪያይቱ ምድር በፍጡራን ፍላጎት የተገኘች ሳትሆን በፈቃደ እግዚአብሔር ጊዜዋ ሲደርስ ካለመኖር ወደ መኖር የመጣች ናት፤ ሊቁ ቅዱስ ያሬድ ይህን ሲያስረዳ "እመ ይፈጥራ እግዚአብሔር ለምድር ኢዜነም ለሰማይ ወኢተማከረ ምስለ መላእክቲሁ" እግዚአብሔር ምድርን ሲፈጥራት ለሰማይ አልተናገረም፤ ከመላእክት ጋር አልተማከረም ይላል።

አሁን እንዲህ ማለቱ ሰማይ ቀድሞ ተፈጥሮ መላእክቱም ከምድር በፊት ኑረው አይደለም፤ ምክንያቱም ታላቁ መጽሐፍ በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን እንደፈጠረ ነግሮናልና። ዘፍ 1፥1 ሊቁ በመንፈስ ቅዱስ በተቃኘው አንደበቱ ሲናገር የፈለገው ስለ ዳግማዊት ምድር ስለ እመቤታችን መሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም። ከሰማይ

መዘርጋት ከመላእክትም ሥርዓት በኋላ የተፈጠረች ምድር የለችምና፤ እንዲያም ከተባለ ድህረ ዓለም የተፈጠረች ምድር እመቤታችን ናትና፤ እርሷንም ሲፈጥራት ከሰማያውያኑ መላእክት ከምድራውያኑም የአዳም ዘሮች ጋር አልተማከረም እሱ በፈቀደ ጊዜ ፈጥሮአታል እንጂ። እርሷ ምድር ተብላ መጠራቷም ለክርስቶስ አዳም ተብሎ መጠራት ምክንያት ሆኖታል። ያለ ዘር፣ ያለ ሩካቤ ፍጥረትን ማስገኘት የቻለ በጥንት ዘመን ከምድር በቀር ሌላ ነበርን? በኋለኛውም ዘመን ያለ ወንድ ዘር ሰውን ያስገኘች ከእመቤታችን በቀር ሌላ ሴት የሌለች መሆኗ እርሷን ከምድር ጋር እንድናመሳስላት ያስገድደናል። በእውነት አምላክን በመውለድ ጸንታ የተገኘች ብቸኛ ምድር።

2ኛ ሕይወት ያላቸው ፍጥረታት መገኛ መሆኗ፦ ዘፍ 1፥27

ይህች ምድር ዛሬ እንደምናያት የለቅሶ ድምፅ የሚሰማባት፣ የሐዘን መሸሻ የሚገጠምባት፣ የሐዘንተኞች መቀመጫ ድንኳን ሆና የተሠራች አልነበረችም። ይልቁንም ሕይወት ያላቸው ነገሮች መገኛ፣ ያለ አንዳች ሐዘንና ሰቆቃ ፍጥረት እንዲኖርባት እግዚአብሔር መልካም እንደሆነች አይቶ የፈጠራት ዓለም ናት እንጂ። ከተፈጠረች በኋላ ሦስት ታላላቅ ነገሮችን አድርጎላታል።

የመጀመሪያው ከዚህ እስከ ሰማይ ድረስ በላይዋ ላይ ነግሦ ይኖር የነበረውን ውኃ ከሦስት ከፍሎ የየብስ ፊት እንዲኖራት፣ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ከሰሜን እስከ ደቡብ ተዘርግታ ፍጥረት ሁሉ እንዲመለከታት አደረገላት፤ ይህን ባደረገበት በሦስተኛው ቀን ደግሞ ሌላ አዲስ ነገር አደረገላት፤ በእርአያውና በአምሳሉ የፈጠረውን የሰው ልጅን ገዥ አድርጎ ሾመላት፤ በተራ ፍጡር ሳይሆን የፍጥረት ሁሉ በኩር የሆነው አዳም እንዲመራት እንዲያደራጃትና እንዲንከባከባት

ተሾመላት። ከብዙ ጸጋዎቿ እነዚህ ዋና ዋናዎቹ ናቸው። እስከዚህ ጊዜ ድረስ የሞት እግር አልረገጣትም፤ ዓይኖቹም አልተመለከቷትም እንዲያውም ሕያዋን የሆኑ ፍጥረታትን እንድታስገኝ በመታዘዟ በሕያዋን የተሞላች የሕያዋን መንደር ሆና ቆይታለች። ሙታን ከእርሷ የተገኙ በመሆናቸው ተመልሰው ወደ እርሷ እንዲገቡ ቢወሰንም እሷ ግን ሕያዋኑን እንጂ ሙታንን አላስገኘችም።

ሙታን ከራሳቸው ሞትን እስኪያስገኙ ድረስ ሕያው የሆነ ፍጥረት ብቻ ይወጣባታል ይወርድባታል። ለመጀመሪያ ጊዜ ምድራችንን የጐበኘው ብቸኛው ሬሳ ያ ከሰማይ ወደ ምድር የተጣለው በኋለኛው የግብር ስሙ ሰይጣን ተብሎ የተጠራው ፍጡር ነው። እሱም ቢሆን በሰማይ ሥፍራ ስላልተገኘለት ወደዚች ምድር ተጥሎአል እንጂ ከመሬት የተገኘ መሬታዊ ፍጡር አይደለም። ነገር ግን ሊቃውንት እንዳስተማሩን ዓለም በተፈጠረ በአራተኛው ቀን ክፉው ጠላታችን ከሰማይ ወደዚች ምድር ደረሰ፡21፡ ራዕ 12፥7

እስከዚህ ጊዜ ድረስ ሕያዋን ሰልጥነውባት ትኖር የነበረችው ምድራችን ለሕያዋን መገኛም ብቻ ሳይሆን ለሕያዋን ምኞት ያላት የመኖሪያ መንደርም ነበረች። ከሰው እስከ እንስሳ ፣ከአራዊት እስከ ሰማይ አንስርት በሕይወት የተገኙ ፍጥረታት በሙሉ ከምድር የተገኙ ብቻም ሳይሆኑ በመሬት የሚኖሩባትም ጭምር ናት። አስገራሚው ነገር ወደ ሰማይ ወጥቶ፣ ወደ አየር መጥቆ የሚበረው ንስር ሳይቀር ተመልሶ ወደ መሬት መምጣቱ አይቀርም። ከርሷ በቀር ሌላ ምን ማረፊያ ኖሮት ወደ ሌላ ይሔዳል?

ሰማያት በዙሪያ ብዙ ሲሆኑ ፍጥረተ መላእክትን ብቻ ይዘው ይኖራሉ። ይህች ያለንባት ምድር ግን አንዲት ሆና ሳለ የልዩ ልዩ ነገድና

ሕዝብ መኖሪያ፣ የሚታዩትና የማይታዩት ሥነ ፍጥረታት መናኸሪያ አድርጓታል። ነባብያንና ኢነባብያን ፍጥረታት ይኖሩባታል። ምድራችን አንዲት ስትሆን ከሰማይ ትበዛለች፤ ጠባብ ስትሆን ከሰፊው የሰማይ ዓለም ትሰፋለች። በዚህና በሌሎች ነገሮች ምድር እመቤታችንን ትመስላለችና ብለው የቤተክርስቲያናችን ሊቃውንት ዳግማዊት ምድር ብለው ይጠሯታል። ስለ ምድር የተነገረውን ሁሉ ለእመቤታችን ሰጥተው ይተረጉማሉ።

ምድርን የሕያዋን እናት ብለን እንደምንጠራት ዘፍ 1÷24 ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያምንም እሞሙ ለኵሉሙ ሕያዋን ብለን እንጠራታለን። የቀደመው ሰው ከምድር አፈር ተበጅቶ ሕያው ሆኖ ለዘለዓለም እንዲኖር ተወስኖለት የእግዚአብሔርን ሕያው እስትንፋስ አግኝቶ ሕያው ሆኖ ይኖር ነበር። ይህን የሕይወት ጉዞ ሞት ሲያደናቅፈው፣ ዳግመኛ ሕያው ፍጥረት ማስገኘት ምድራችን ሲሳናት ሌላ ሕያው ሰው ያስገኘችልን ሁለተኛዋ ምድር እመቤታችን ናት። በአንዱ በአዳም ምክንያት ሁሉም ሞቶ ነበርና በሁለተኛው አዳም ፍጥረት ሁሉ ዳግም በሕይወት ሲፈጠር በሁለተኛው ጊዜ ሕያዋን ፍጥረታት የተገኙባት እመቤታችን ድንግል ማርያምን እሞሙ ለኵሉሙ ሕያዋን ብለን መጥራታችን ተገቢነት አለው።

የመጀመሪያው ሕያው ፍጥረት ሲገኝ "ወነፍሐ ውስተ ገጹ ለአዳም መንፈስ ሕይወት፤ በአዳም ላይ የሕይወትን እስትንፋስ እፍ አለበት ዘፍ 2÷7 ተባለ። ስለ ሁለተኛው ሰው ሕይወት ግን የተነገረው ነገር ድንቅ ነው። "መንፈሰ እግዚአብሔር ቅዱስ ይመጽእ ላዕሌኪ፤ ቅዱስ የሆነው የእግዚአብሔር መንፈስ ወደ አንች ይመጣል ሉቃ 1÷28 የሚል ነው። የመጀመሪያው ከአፉ በተቀዳ የጸጋ ሕይወት የከበረ ሕያው

ፍጥረት ሲሆን ከሁለተኛይቱ ምድር የተገኘው ሁለተኛው ሕያው ሰው ግን በባሕርይ ሕይወቱ በመንፈስ ቅዱስ ሕያው የሆነ መሆኑን ያሳያል። ከመጀመሪያይቱ ምድር የተገኙት ሕያዋን ፍጥረታት በነፍስ ሕያዋን የሚሆኑ ሲሆን ከሁለተኛይቱ ምድር የተገኙት ግን በመንፈስ ቅዱስ ሕያዋን ሆነው ይኖራሉ። የመጀመሪያው (የነፍስ)ሕያውነት በተፈጥሮ የሚሰጥ ነው፤ ሁለተኛው ሕያውነት (ክርስትና) ደግሞ በፈቃድ የሚሰጥ ነው።

ሰው ከመጀመሪያይቱ ምድር የተገኘ መሬታዊ ፍጡር መሆኑን አምኖ በጥንተ ተፈጥሮው "እኔ አመድ እና ትቢያ ነኝ" አለ። ከሁለተኛይቱ ምድር የተገኘ ዳግማይ አዳም ክርስቶስ ከማይሞትና ከማይጠፋ ዘር ወልዶኛል ብሎ ከአመነ በኋላ በሐዲስ ተፈጥሮ ከአባቱ ዳዊት ጋር "ኢይመውት ዘእንበለ ዘአሐዩ በሕይወት እኖራለሁ እንጅ አልሞትም" መዝ 117÷17 እያለ አብሮ ይዘምራል።

ይህች ያለንባት መሬት እንኳን ማለፍ፣ መለወጥ ማርጀት የሚስማማት ሲሆን በውስጧ የሚኖሩት ፍጥረታትን የምታድስበት ጊዜ አላት። እንደ እባብ ያሉ ሥነ ፍጥረታት በልባቸው ተስበው አመድና ትቢያን ምግብ አድርገው የሚኖሩ ሲሆን የሕይወት ዋስትናቸው የእርጅና መከላከያቸው መሬት እንደሆነች የታመነ ነው።

እንደ እባብ ሁሉ የቀደመውን የመርገም ጽዋ የጨለጠው የቀደመው ሰው አዳምም የታደሰው እርጅናውን ያስወገደው ከዳግማዊት ምድር ከእመቤታችን ነው። ዳግመኛ ላያረጅ አዳም አዲስ ሰው ሆኗል። ለዚህ ነው መንፈስ ቅዱስ አባ ሕርያቆስን እዲህ ብሎ ያናገረው ".... ወበኪ ተሐደሰ ቀዳሜ ኵሉ ፍጥረት የፍጥረት ሁሉ መጀመሪያ በአንቺ ታደሰ" ከመጀመሪያይቱ ምድር ለተገኙት ሰዎች እንዲህ ተብሎ ተነግሮላቸው

ነበር። "በእድሜአቸው ፈጽመው ሽምግለው አርጅተውም ነበር" ዘፍ 18፥11 ሉቃ 1፥18 ከሰው ልጆች ነውርን ያስወግድ ዘንድ ባረጀውና በሸመገለው ዓለም ውስጥ ከአዲሲቱ ምድር አዲስ ሰው ተወለደና አሮጌውን አስወገደ። እንዲያውም ሁሉን አዲስ አደረገ 1ኛ ቆሮ 5፥17 አዲስነቱ ደግሞ ለጊዜው አዲስ ሆኖ ቆይቶ የሚያረጅ እንዳይሆን ባለመለወጥ አጸናው። ከዚያም አያይዞ ለሰው ዘለዓለማዊነት ተሰጠው። ሞት ሲገዛው ለነበረው የሰው ልጅ ባሕርይ "ወተውህበ ሎቱ ሥልጣን ወምኵናን ዘለዓለም፤ የዘለዓለም ግዛት ተሰጠው" ዳን 7፥17 ተብሎ ተነገረለት። በዘመናት ተወስኖ ይኖር የበረው የሰው ልጅ ዘመናትን አልፎ የሚቀር ክብርና ጌትነትን ተቀበለ። ወደ ኋላም ወደ ፊትም ቢሆን የሌለበት ጊዜ የሌለና የማይኖርበት ጊዜ የማይኖር ሆነ።

ይህ ሁሉ በአዲሲቱ ምድር በእመቤታችን ላይ የተከናወነ ጣፋጭ የሰው ልጆች ታሪካችን ነው። ይህች ምድር ካስገኘቻቸው ልጆቿ ዳግማዊቷ ምድር እመቤታችን ያስገኘቻቸው ይበዛሉ። የዚች ምድር ልጆቿን ሞት ቀምቷታል፤ ከእመቤታችን የተገኙት ግን ሁሉም በሕይወት ያሉ ናቸው። እንዲያው ለዘለዓለም ምድራቸውን ወርሰዋት ሊኖሩ ከአምላካችን ጋር ቃል ኪዳን አላቸው እንጂ ኢሳ 60፥22

ለዚችኛዋ ምድር ጥሩ ምሳሌ ይሆን ዘንድ ያችኛዋ ምድር በልብ የሚሳቡትን፣ በእግር የሚሽከረክሩትን፣ በክንፍ የሚበሩትን፣ በደመ ነፍስ ሕያዋን ሆነው ጸንተው የሚኖሩትን ሦስት ሕያዋን ፍጥረታት እንድታስገኝ ታዝዛ ነበር። እንደ እግዚአብሔር ቃል ሁሉም ፍጥረታት ከመሬት የተገኙ ናቸው። ምድራችን በራሷ ሕይወት ሳትሆን ሁሉን በቃሉ የሚያኖረውነው እግዚአብሔር ሕያውት ላላቸው ነገሮች መገኘት ምክንያት አድርጓታልና ሕይወት ያላቸው ነገሮች ሁሉ ከርሷ የተገኙ ናቸው።

በዚህም እመቤታችን የሦስት ነገሮች እናት መሆኗ ታወቀ ተረዳ፡- የሰብአ ዓለም፣ የባሕታውያን የሰማዕታት ፤ከዚህ ዓለም እስከ ታላቁ ዓለም መንግሥተ ሰማይ ድረስ የሚኖሩ ጻድቃን በነዚህ ሦስት ሰዎች የተጠቃለሉ ናቸው። በክንፍ የሚበሩ በሰማዕታት ይመሰላሉ። እንደ ሰማይ ንስር ከሚያውቁት ዓለም ወደ ማያውቁት ዓለም በተመሥጦ ስለሚነጠቁና ሽቅብ ወደ ጽርሐ አርያም ወጥተው ይህን ዓለምና ክብሩን ንቀው አጥቅተው ቁልቁል ስለሚመለከቱ ነው።

በልብ የሚሳቡ በዚህ ዓለም በፈቃዳቸው በሕጋዊ ጋብቻ ተወስነው በሚኖሩ ጻድቃን ልጆቿ ይመሰላሉ። እነዚህ በልብ የሚሳቡ እንስሳት በምድር ላይ ሲርመሰመሱ የሚኖሩ ቢሆንም አንዳንድ ጊዜ ቀና ብለው ከዕፀዋት ፍሬን ለቅመው ወደ መሬት መመለሳቸው የማይቀር የተፈጥሮ ተግባራቸው ነው።

ሰብአ ዓለምም ሰባት ጊዜ ወድቀው፣ ሰባት ጊዜ ተነሥተው በሚያደርጉት መንፈሳዊ ጉዟቸው የጽድቅ ፍሬን የሚቀምሱ ሲሆን አብዛኛውን ጊዜ ግን በመሬታዊ ግብር ሲርመሰመሱ የሚኖሩ መሆናቸውን የሚያመላክት ነው። ሰብአ ዓለም ፣ባሕታውያን፣ ሰማዕታት ደጅ የሚጠኗትን፣ የሚጋደሉላትን መንግሥተ ሰማያትን ያስገኘችላቸው እናት እመቤታችን ድንግል ማርያም ናት። ቅዱስ ኤፍሬም በውዳሴው ሊቃነ ጳጳሳት የጵጵስናቸውን ዋጋ፣ ነቢያት የትንቢታቸውን፣ ሐዋርያት የስብከታቸውን፣ ሰማዕታት የተጋድሎአቸውን ዋጋ ለማግኘት ደጅ የሚጠኑት ክርስቶስን ወለደችላቸው[32] ብሎ አመስግኗታል።

ከሷ በፊት የነበሩ ነቢያትና ጻድቃን ጽድቃቸው እንደመርገም ጨርቅ የተናቀ ሆኖ እንደነበር ታላቁ መጽሐፍ የሚነግረን እውነታ ነው። ኢሳ 64፥6 ዛሬ ግን ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው መጠን ይከፍል ዘንድ

የሰው ልጆች ዋጋ በእጁ የተያዘለት ጌታ ከእመቤታችን ተወልዷልና። እንዲያውም በጥላ ቡተረዳ ነገር እንሰት፣ አራዊት፣ አዕዋፍ የተሰኙ ፍጥረታትን አንድ አድርጉ በመያዝ የቀደመችው ምድር እመቤታችንን መሰለች።

እኛ በልማዳችን እንስሳት የምንላቸው ሣር ነጭተው ውኃ ተጎንጭተው የሚኖሩትን ሲሆን አራዊት የምንላቸው ደግሞ ሥጋ ነጭተው ደም እንደ ውኃ ተጐንጭተው የሚኖሩትን ነው። በሌላም መንገድ የሚበሉትን እንስሳት የማይበሉትን አራዊት እንላቸዋለን። እነዚህ ሁሉ ፍጥረታት በምድር ላይ ሲኖሩ አንድም ቀን የፍቅር ታሪክ ሳያስመዘግቡ አንዱ አንዱን ሲያሳድደው በጠላትነት ይኖራሉ። አዳም ከፈጣሪው ከተጣላበት ቀን ጀምሮ እስከአሁን ድረስ በዚህ ሕግ ጸንተው ይኖራሉ፤ ከዚያ በፊት ግን ይህ እንዳልነበረባቸው ግልጽ ነው።

እመቤታችንም ከአዳም ርኩሰት አስቀድሞ የነበረችው ሰላማዊ ምድር ናትና እንስሳት፣ አራዊት፣ አዕዋፍ የተሰኙ እስራኤልን፣ ካህናተ እስራኤልንና አሕዛብን በፍቅር መረብ አስተሳስራ አንድ መንጋ አድርጋለች። የቀደመ ታሪካቸውን ስናይ ጦርነት ነው፤ እስራኤል ምድረ ርስትን ሲወርሱ አሕዛብን አሳደው ነበር ኢያ 6÷21 ዛሬ ግን ነገሩ እንዲህ አይደለም፤ ዘለዓለማዊቷን ምድር መንግሥተ ሰማያትን አብረው ለመውረስ ኑ ወደ እግዚአብሔር ቤት ተራራ ወደ ያዕቆብ አምላክ ቤት እንውጣ ተብሎ ጥሪው ተላልፏል። ኢሳ 2÷3 የቀደመውን የዕርቅ ዘመን የመለሰች የመጀመሪያውን የሰላም ኑሮ ያስታወሰች ከጥንተ አብሶ በፊት የነበረችዋ ንጽሕት ምድር በእውነት እመቤታችን ናት። ለጴጥሮስ እውነቱን ሊመሰክር የመጣው የእግዚአብሔር መላክስ ቢሆን ያስረዳው ነገር ቢኖር ይህን አይደል?

32. ሙዳ.ዘሐመስ

ከዚህ በኋላ ንጹሕ እንጂ ርኩስ ፍጥረት የሌለ መሆኑን ጥንቱንም ኃጢአት እንጅ ያረከሰው በባሕርዩ ርኩሰት ኖሮበት የተፈጠረ አንዳች ፍጥረት የሌለ መሆኑን የሥነ ፍጥረቱ መጽሐፍ የሚነግረን እውነት ነው። አሁንም ኃጢአታችንን አጥፍቶ፣ የቀደመ ኑሮአችንን መልሶ የሚያኖረን ጌታ ከእመቤታችን ከተወለደልን በኋላ ሁሉም ንጹሕ ሆኖአል። ባንድ መዝገብ ውስጥ የሚኖሩ የእግዚአብሔር የክብር እቃዎች ናቸው። የሐዋ 10÷15 ሕዝቡንና አሕዛቡን አንድ አድርጎ እግዚአብሔር ያኖረባት መሬት በእውነት እመቤታችን ናት። ሁሉም ዳግም አሁን ንጹሓን ሆነዋል። አንዳች እንኳን የቆሸሸ ቢኖር ወደ ውጭ ይጣል እንጂ በእርሷ አይኖርምና ሁሉም ስለ ራሱ ይጠንቀቅ ማቴ 22÷13

3ኛ በአዲስ ሰማይና በአዲስ ምድር መተካቷ

አሮጌውን አሮጌ ማለት የሚቻለው አዲስ ነገር ሲኖር ብቻ ነው። አዲሱን ኪዳን ከእግዚአብሔር ስንቀበል የቀደመውን ኪዳን አሮጌ ብለነዋል። ይህችን ምድርና ይህችን ሰማይ አሮጌ ብለን በአዲስ ሰማይ እና በአዲስ ምድር የምንተካበት ጊዜ ሊመጣ እንደሚችል ደግሞ ዮሐንስ ወንጌላዊ በራእይ ይመሰክራል። ራዕ 21÷1 ዘመንን ዘመን ሲተካው አዲስ ብለን የተቀበልነውን ዓመት ጥቂት ወራትን ካሳለፍን በኋላ አሮጌ ብለን ስንሸኘው መኖራችን የተለመደ ተግባር ነው። ሌላው ቀርቶ ሰውን ያህል ታላቅ ፍጡር እንኳን ሰው የሚተካው በመሆኑ ሣገርጀት አንዱ የሰው ልጆች ጠባይ መገለጫ ሆኗል። ሦስት ነገሮች ብቻ በእርጅና ሳይለወጡ ጸንተው ይኖራሉ።

- ❖ ለባሕርዩ እርጅና የማይስማማው አምላካችን
- ❖ ሰባቱ ሰማያትና
- ❖ ቅዱሳን መላእክት

❖ዘመን የማይቆጠርለትና ከዘመናት በፊት የ ነበረው ኃያሉ አምላካችን እ ግዚአብሔር ዘመናትን የሚያስረጅ እንጂ ዘመናት የሚያስረጁት አይደለም በምንም ሆነ በማንም አይተካም፣ አይለወጥምም፣ ሁል ጊዜ አዲስ ሆኖ ይኖራል እንጂ:: ታላቁ የእግዚአብሔር ሰው ይህን ታላቅ ጌታ የገለጸበት ቃል ምንኛ ድንቅ ነው:: "አንተ ግን ያው አንተ ነህ ዘመኖችህም አያልቁም" መዝ 101፥26-27 ነበር ያለው:: ሁሉን አሳልፎ እሱ ግን ብቻውን ለዘለዓለም አዲስ ሆኖ ይኖራል:: ከሁሉም በፊት እርሱ ነበረ፣የዛሬ ታላቅነቱ በትናንት ታናሽነት የተጀመረ አይደለምና ሁልጊዜ ‹‹ዐቢይ እግዚአብሔር›› ተብሎ ሲመሰገን ይኖራል::

❖ ሰባቱ ሰማያትና ቅዱሳን መላእክት ምንም እንኳን ከዘመናት መፈጠር በኋላ የተገኙ ፍጥረታት ቢሆኑም ከሌሎቹ ፍጥረታት ልዩ የሚያደርጋቸው ጸጋን የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር አጐናጽፏቸዋል:: እርሱም የማያረጁና ኃይላቸው በድካም የማይለወጥ መሆኑ ነው:: የዚህም ምሥጢሩ በመላእክት ዘንድ እና በከተሞቻቸው ውስጥ ዘመን የማይቆጠር መሆኑ ነው::

ሁል ጊዜ በሰማይ ዛሬ እንጂ ትናንት እና ነገ የሉም:: እድሜአቸው፣ ቀናቸው የሚለካው ጨለማ በማይፈራረቀው ፀሐይ በኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑ ነው:: እኛም ከመሠረት ጀምሮ ለዘለዓለም እንዲኖሩ እንጂ ከንቱነት የሚሰማቸው ፍጥረታት ጋር የምንስማማ ፍጡራን ሆነን ባለመፈጠራችን በቀደመው የሰው ልጆች ስሕተት የተነሣ በከንቱ ዓለም ውስጥ የምንኖር ፍጡራን ለመሆን የተገደደን ቢሆንም ተስፋ አለን:: ለዘለዓለም መለወጥ በሌለበት ዓለም ውስጥ የምንኖርና

ዛሬ የቅዱሳን ብርሃን ብለን የምንጠራው ፀሐየ ጽድቅ ክርስቶስን እየሞቅን የምንኖርበት ዘመን ይመጣል::

እሱም ይህ አሮጌው ምድርና ሰማይ አልፎ አዲሱ ሰማይና አዲሱ ምድር ሲመጣ ነው:: የሚመጣውም አዲሱ ሰማይና ምድር አሮጌውን እንደለወጠው ሁሉ እመቤታችንም ሁሉን አዲስ ለማድረግ እግዚአብሔር ያዘጋጃት አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ናት:: ይህ የተሰፋ ዓለም ይህን ዓለም ተክቶ ለሰው ልጆች ከመሰጠቱ በፊት ስለዚህ ዓለም የተነገረው ሁሉ በእመቤታችን ተደርጓልና::

ይህ ዓለም ከመጣ በኋላ በነጭ ዙፋኑ ላይ የተቀመጠው ጌታ የተናገረውን በጥቂቱ ለማሳያነት ብንመለከት "እኔ ለተጠማው ሁሉ ይጠጣ ዘንድ ከሕይወት ውኃ ምንጭ ያለዋጋ እሰጣለሁ ድል የነሣም ይህን ይወርሳል እኔ አምላክ እሆነዋለሁ፣ እሱም ልጅ ይሆነኛል" ራዕ 21፥6 አቡቀለምሲስ ዮሐንስ ይህንን ሲናገር ስለ አዲሱ ሰማይና ስለ አዲሲቷም ምድር መናገሩ ነው:: ነገር ግን ይህ ሁሉ አስቀድሞ በእመቤታችን አልሆነልንም ? የሕይወት ውኃ ወንጌልን፣ ልጅነትን ከሷ ከተገኘ አንድ ልጇ ያለ ዋጋ አገኘነው::ከቃሉም "ዘጸምአ ይምጻእ ኀቤየ ወይስተይ የተጠማ ሁሉ ወደ እኔ ይምጣ ያለ ዋጋም ይጠጣ" ዮሐ 4፥14 ሲል ሰማነው::

ሰው የእግዚአብሔር ልጅ የሆነውስ ጌታ ከእመቤታችን ከተወለደ በኋላ አይደለምን? አዲሲቷ ምድር እመቤታችን ያስገኘችልን ዳግማዊ አዳም ከቀዳማዊው አዳም ይልቅ ለፍጥረት ሁሉ የበኩራት ዓይነት እንድንሆን በቅዱስ ቃሉ አስቦ ወለደን::ይህን አባትነቱንም ያረጋገጥነው ከዚህ ዓለም ወደ ወዲያኛው ዓለም ከመሄዳችን አስቀድም "አቡነ ዘበሰማያት" ብላችሁ ጥሩኝ ሲለን ነው::

ወገኖቹ ያልነበርን እኛን ወገኖቹ ያደረገን፣ ርቀን የነበረውን ያቀረበን አዲሲቱ ምድር እመቤታችን ከመጣች በኋላ ነው ያዕ 1፥18 1ጴጥ 2፥10 ያችኛዋ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ስትመጣ የሚሰጠንን አዲሱን የጽድቅ ፀሐይ ኢየሱስ ክርስቶስን ያስገኘችልንስ እርሷ እመቤታችን አይደለች? አባ ኤፍሬም በውዳሴው እንደመሰከረው:: "ሠረቀ ለነ እምኔኪ ፀሐየ ጽድቅ፤ የእውነት ፀሐይ ክርስቶስ ካንቺ ተወለደልን›› ይላታል:: አሁን የምናውቀው ሰማይ ካስገኘልን ከምናውቀው ፀሐይ የተለየ ፀሐይ መሆኑን ለመግለጽ ነው-የእውነት ፀሐይ ሲል የገለጠው::

ሁሉን ነገር በመታደስ የሚያጸና አዲስ ፀሐይ ነው- ኢየሱስ ክርስቶስ ፤እሱም ከአዲስ ሰማይ የተገኘ እንጂ ጎልፈት ውላጤ ከሚስማማው ከዚህ ሰማይ የተገኘ አይደለም:: ይህ ያሁኑ ሰማይ ሕይወት ከክንፎቿ በታች የሆነላት ፀሐይን አስገኝቶ ያውቃልን? አዲሲቱ ሰማይ ያስገኘችው ፀሐይ ግን "ያን ጊዜ የእውነት ፀሐይ ይወጣላችኋል ሕይወትም ከክንፎቿ በታች ነው›› ሚል 4፥5 የተባለለት ፀሐይ ነው:: ፍጡራንን በመውለዷ የሕያዋን እናት ተብላ የምትጠራ ይህችን ምድር የምትመጣይቱ ምድር እንደምትተካት ሁሉ ሕይወታቸው ክርስቶስ የሆነላቸው ምዕመናንን በማስገኘቷ "እሞሙ ለኵሉሙ ሕያዋን" ተብላ የምትጠራይቱ ዳግማዊት ምድር እመቤታችንም ምድራዊና ጊዜያዊ ሕያውነት የተሰጣቸው ፍጡራንን የምታስገኝ የፍጥረታት እናት ቀዳሚት ሔዋንን ትተካለች:: አዲስ ሰማይ፣ አዲስ ምድር ማለቱ እመቤታችን ገረድነቷንና እመቤትነቷን አስተባብራ ይዛ መገኘቷን የሚያመለክት ሲሆን ይህም በሌሎች ሴቶች የማይደገም ታሪክ በመሆኑ ሁል ጊዜ አዲስ እንድትሆን ያደርጋታል::ገረድነትን ከእመቤትነት ጋር፣እናትነትን ከድንግልና ጋር አስተባብሮ ይዞ መገኘት

የሚቻላት ሴት አትገኝምና:: እናቱን የፈጠረ ልጅ እርሱ የድንግል ማርያም ልጅ ክርስቶስ ብቻ ሲሆን ፈጣሪዋንም የወለደች ብቸኛ እናት እርሷ እመቤታችን ድንግል ማርያም ብቻ ናት፤ይሄን ታሪክ ሊያስረጅ የሚችል ሌላ አዲስ ታሪክ ብትፈልጉ ታገኛላችሁ?::

ገነት:-

ይህን ቃል ቀጥታ ወደ አማርኛ ብንለውጠው የአትክልት ቦታ ተብሎ የሚተረጐም ሲሆን የታጠረና የተቀጠረ አዕምሮን ሁሉ መማረክ የሚችል ምድረ በዳ ያልሆነ ልዩ የአትክልትን ቦታ ያመለክታል:: አስካሁን ስናነሣት የነበረችው ምድራችን በአምስት ክፍል ተከፍላ አምስቱ ዓለማተ መሬት ተብለው ይጠራሉ፤ ከነዚያ አምስት ዓለማት አንዱ ገነት ሲሆን ስለክብሩ ብቻውን አድርገን ልናየው ግድ ይለናል:: ገነት ከሰው ልጅ በቀር ማንም ላይኖርባት ውሳኔ ከእግዚአብሔር ተሰጥቶባታል:: ዘፍ 2፥8 የህልውናዋን ዜና ታላቁ መጽሐፍ የመዘገበላት ፍጥረት ሁሉ ተደራጅቶ አልቆ በመጨረሻ ስለተፈጠረው የሰው ልጆች አባት ሲናገር በምሥራቅ በኩል ሌላ ዓለም ተተክለች፤ እሷም ዔደን ገነት ናት ብሎ ነው::

ከሰማይ በታች ከሚገኙ ክፍላተ መሬት ውስጥ እጅግ ከፍ ያለች እና የከበረች ምድር ናት:: ምክንያቱም ንጉሠ ምድር አዳም የሚኖርባት የንጉሥ ምድር ናትና:: መላውን ዓለም እንዲያጠጡ የተመረጡት አራቱ አፍላጋትም እንዲወጡ የተደረጉት ከዚህች ልዩ ስፍራ ነው:: ይህን ሰፊ ዓለም ዞረው ያጠጣሉ:: ያለ አንዳች አድሎ ሌሊት እና ቀን በአራቱ ማእዘናት ይፈሳሉ:: በሚፈሱባቸውም ቦታዎች ሁሉ የደረቀውን ያለመልማሉ ከአበባ ወደ ፍሬ ያደርሳሉ:: ለዓለም የሚበቃ ልዩ ልዩ ገጸ

በረከቶችን የተሞላች ሀገር ናት። ገነት ለሰው የሚሆኑ ውድ የሕይወት ስጦታቸውን አሟልታ ይዛ ነበር። ሁሉንም ማወቅ ከሚያስችለው ዛፍ ጀምሮ ለዘለዓለም በሕይወት መኖር እስከሚያስችለው የሕይወት ዛፍ ድረስ በውስጧ አሉ።

በመጀመሪያ ወደ ሰው ልጆች ጆሮ የደረሰው መለኮታዊ ትእዛዝስ ቢሆን መጀመሪያ የተላለፈው በዚህች ምድር አይደል? ሰው መጠበቅ ባይችልም መጀመሪያ ቃለ እግዚአብሔርን የሰማባት ቦታ ናት፤ ሰውና እግዚአብሔር አብረው ይኖሩ የነበረው ሰው በገነት በኖረባቸው ጊዜያት ሲሆን በኋላም ጊዜው ሲደርስ በዓለም መለያየቱ ጠፍቶ አንድነቱ ጸንቶ ሰውና እግዚአብሔር በአንድነት መኖር የጀመሩት በገነት ነበር። ሉቃ 23፥43

አባታችን አዳም በሠራው ስሕተት የጀመረው ኑዛዜ በገነት ውስጥ በነበረ ጊዜ ፍጻሜውን አላገኘም ነበር። ጀምሮ ሳይጨርስ ነበርና የተወው አዳም ኑዛዜውን እስከ ደመደመበት ዕለት ድረስ ከእግዚአብሔር ተለይቶ ከገነት ወጥቶ መኖር ግድ ብሎታል። እርቁ የተፈጸመበት ዕለተ ዓርብ አዳምም የመደምደሚያውን የኑዛዜ ቃልና የመማጸኛ ንግግር ያደረገባት ዕለትና ሰዓት ይህች ዕለት ዓርብ ናት።

ከሞት ጋር ተፋጦ ፈያታዊ ዘየማን ያደረጋት ንግግርኮ አዳም በገነት ጀምሮ የተወውን ንግግር ለመደምደም የተነገረች ንግግር ናት። የነገር ሁሉ መደምደሚያ መንግሥተ እግዚአብሔር ናትና ለአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ለተደረገው ጸሎት መሪና ፈታውራሪ ሆኖ ገነትን ያስከፈተው ይህ አጭር ጸሎት ጥንት የተጀመረው የአባቶቻችን ጸሎት ፍጻሜ እንጂ ዛሬ የተጀመረ አይደለም። አጭር በሚመስለው በዚህ ጸሎት የሰው ልጆች ገነትን መውረሳቸው ተረጋግጧል። በዚህም

እመቤታችን ድንግል ማርያም የአበው ነቢያት የጸሎታቸው ፍጻሜ መሆኗ ታወቀ ተረዳ።

በዱሩና በገደሉ፣ በዋሻና በፍርኩታ በቤተ መንግሥትና በቤተ ክህነትም ስለ እርሷ ብዙዎች ከለቅሶ እና ከብርቱ ጩኽት ጋር ምልጃ እና ጸሎትን አቅርበው ነበር። ያለ እርሷ እንዳይባረኩ እግዚአብሔር ከልክሏቸዋልና።

ሰው ከእግዚአብሔር ጋር መኖር የጀመረባት አማናዊቷ ገነትስ እመቤታችን አይደለች! "ዛሬ በገነት ከኔ ጋር ትሆናለህ" ሲል አዲስ ነገር እንዳይመስልህ ሰው እና እግዚአብሔር መጀመሪያ የተገናኙባት ገነታችን እመቤታችን ናት። "ዛሬ በገነት....." ከሚለው ቃል "ስሙንም አማኑኤል ትለዋለች" የሚለው ስም አይቀድምምን? አማኑኤል ማለትስ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ሆነ ማለትም አይደል ማቴ 1፥23 ስለዚህ በገነት ከእግዚአብሔር ጋር መኖር ከጀመርን ቆይተናል ማለት ነው። ይህች ጌታ የተጸነሰባት ዕለትና ሰዓት ሰውና እግዚአብሔር በገነት ኅብረት የፈጠሩባት ሰዓት ናት። መለያየቱ በተፈጠረበት ዕለትም ወደ ሰው ልጅ የሄደው እግዚአብሔር ነበር። አንድነቱ ሲፈጠርም የመጣው እግዚአብሔር ነው።

ከፈጣሪያችን ጋር አንድ ሆነን የምንኖርባት ይህች ገነት በምሥራቅ በኩል መተከሏም እመቤታችን ከምሥራቃዊቷ የዓለማችን ክፍል የተገኘች መሆኗን ያሳያል። ገነት ውስጥ አንድ አዳም ብቻ እንጂ ልጆቹም ሆኑ የልጅ ልጆቹ ከበደል በፊት ገነትን አላወቋትም ነበር። ይህም እመቤታችን ከዳግማይ አዳም ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር በውስጧ ሌላ ሰው ያልተጸነሰ መሆኑን ያሳያል። የመጀመሪያዋ ገነት ከመጀመሪያው አዳም በኋላ ሌላ ሰው በውስጧ መመላለስ አለመቻሉን ከተስማማን

ከእመቤታችንም ማሕጸን የወጣ ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር ሌላ አንዳች ፍጥረት የለም ብንል አልተሳሳትንም። ከዳግማይ አዳም ከኢየሱስ ክርስቶስ በኋላ ለዘለዓለም ተዘግታ ትኖራለች። ነቢዩ እንደመሰከረው ሕዝ 44፥2 በመላእክቱ እንድትጠበቅ ያደረገውስ ለዚህ አይደል፤

ሁለቱ ጠባቂዎቿ

ስለ ገነቲቱ ክብር የሚናገረው ታላቁ ቅዱስ መጽሐፍ ለገነት ሁለት ጠባቂዎችን ያኖረላት መሆኑን ይመስክራል። እነሱም የምትገለባበጥ የእሳት ሰይፍ እና ኪሩብ መላክ ናቸው።እግዚአብሔር አዳም ከወጣበት ቅፅበት ጀምሮ ገነትን ያለጠባቂ የተወበት ጊዜ የለም ይጠብቃት ዘንድ የተተወችለት አዳም ታማኝ ሆኖ ባለመገኘቱ ሌሎች ጠባቂዎችን አዘጋጀ። ገነትን መጠበቅ ያስፈለገው አዳም በድፍረት እንዳይገባ ለማድረግ ነበር አሮጌውን አዳም በሐዲሲቷ ምድር በገነት ሊያኖረው አልፈቀደምና።

በዚህም ነገር እመቤታችንን እግዚአብሔር ያለ መንፈስ ቅዱስ ጥበቃ የተወበት ጊዜ እንደሌለ አስረዳን። በበደል ውስጥ የነበረው ሰው ተደፋፍሮ እንዳይገባ በምትገለባበጥ የእሳት ሰይፍ ማጠሩ የአጋንንትን ሥልጣን መቆራረጥ በሚችለው የመንፈስ ቅዱስ ሥልጣን ከበደለኛው ሰው ከአዳም በደል የተነሣ መተዳደፍ እንዳይኖርባት ከእናቷ ከሔዋን ማሕጸን ከአባቷም ከአዳም አብራክ ከመከፈሏ አስቀድሞ ሲጠብቃት የነበረ መሆኑን የሚያስረዳ ነው። አባቶቻችን ዐቀባ መንፈስ ቅዱስ እምከርሠ እማ ከእናቷ ማሕጸን ጀምሮ መንፈስ ቅዱስ ጠበቃት በማለታቸው ከእናቷ ከሔዋን ጀምሮ በመንፈስ ቅዱስ ጥበቃ ከበደለኛው ከአዳም ርኵሰት እንደለያት ነግረውናል።

በኪሩብ መላክ እንድትጠበቅ መደረጓም ቅዱስ ኤፍሬም ነባቢት ገነት ብሎ የሚጠራት የምትናገረዋ ገነት እመቤታችን እንደ ኪሩቤል ሁሉ የአምላካችን መቀመጫ ዙፋን መሆኗን ያስተምረናል። ለቀደሙት አባቶቻችን በኪሩቤል ላይ ተቀምጦ ከፀሐይ መውጫ እስከ መግቢያ ድረስ ይገለጥ ነበር። ሕዝ 10፥1 በሐዲስ ኪዳን ከኪሩቤል በምትበልጠውና በምትሻለው ዙፋን በእመቤታችን ላይ ለፍጥረት ሁሉ ተገልጦ እንደ ቀድሞ በሕልም ዘፍ 28፥10 በራእይ ኢሳ 6፥1 ያይደለ ለሰማያውያኑ እና ለምድራውያኑ ፍጥረታት በሥጋ ተገልጦ 1ጢሞ 3፥16 ከዙፋኑም ከፍታ የተነሣ ለሁሉም ፍጥረት ታየ ፤

ከቀደመው ዙፋኑ ከኪሩቤል ይልቅ ያሁኗ ዙፋን እመቤታችን ትበልጣለችና ለሁሉ ግልጥ አደረገችው በክብርና በልዕልና ከኪሩቤል የምትበልጥ ኪሩባዊት ብቻ ሳትሆን ኪሩብ መላክ ሊጠብቃት የኖረች ሌላ ኪሩብ ናት። እመቤታችን በምትገለባበጥ ሰይፍና በኪሩብ መላክ እንድትጠበቅ ያደረጋት በውስጧ ለዘለዓለማዊው የሰው ልጆች የሕይወት ዋስትናነት የተተከለው ለዓለሙ ሁሉ ሕይወትን ያድል ዘንድ ከእመቤታችን የተወለደው ክርስቶስ ነው እንጂ።"ሌላ ምንድን ነው፤ መጽሐፍ "ወደ ሕይወት ዛፍ የሚወስደውን መንገድ ይጠብቁ ዘንድ ኪሩቤልን አዘዘ" ሲል በቁሙ ስለ አንድ ዛፍ የተናገረ ይመስልሀል? ስለ እርሱ በተናገረ ጊዜ " እኔ የወይን ግንድ ነኝ" ዮሐ 14፥1 ሲል ስለሰማነው የሕይወት ዛፍ ስለክርስቶስ ነው እንጂ። ያማ ባይሆን ኖሮ መጀመሪያ ላይ ከፍተኛ ጥበቃ ስለተደረገለት የሕይወት ዛፍ የነገረን መጽሐፍ በኋላም መዳረሻውን በነገረን ነበር።

አዳም ከገነት ሲወጣ በገነት ውስጥ የሕይወት ዛፍ መኖሩ ተነግሮን ነበር ዳግመኛ ወደ ገነት በተመለሰ ጊዜ ግን በምድራዊቷ ገነት መካከል

የተተከለ የሕይወት ዛፍ የነበረ መሆኑን አንመለከትም። ነገር ግን በአማናዊቷ ነባቢት ገነት በእመቤታችን ውስጥ ለሚበላው ሁሉ የዘለዓለም ሕይወትን የሚሰጥ የሕይወት እንጀራ መኖሩ ተጽፏል። ዮሐ 6፥31 ለተዳደፉት እጃቸውን ሰደው እንዳይነኩት የተከለከልነው በዘፍጥረት 3፥24 የተመዘገበው የሕይወት ዛፍ በሕያውነቱ ሕይወትን በሰጠን በክርስቶስ ይተረጐማል። የማይገባቸው ሰዎች በኃጢአት ተዳድፈው ሊመገቡት የማይቻላቸው የሕይወት ምግብ ክክርስቶስ በቀር ሌላ አለን? "ሳይሻው ይሆን ጉበኑት የበላ ይሆንም ጽዋ የጠጣ የጌታችን የኢየሱክ ክርስቶስ ሥጋና ደም ዕዳ አለበት እንዲል 1ቆሮ 11፥32

አባቶቻችንም መንፈስ ቅዱስ የነገራቸውን ሲነግሩን ይህ የሕይወት ዛፍ ክርስቶስ እንደሆነ ነግረውናል። ‹‹ዳግመኛ ከዕፀ ሕይወት እንበላ ዘንድ አደለን ይሄውም ሥጋና ደሙ ነው›› እያሉ፤

በጣም የሚገርመውና ይህን ቃላችንን የሚያስረዳልን ደግሞ ከዛፉ ሥር የሚፈልቁት አራቱ አፍላጋት ናቸው። እነዚህ አራቱም ወንዞች ከአንዱ ዛፍ ሥር ይመነጫሉ፤ መጀመሪያ ገነትን ከዚያም በአራቱ የዓለም ማእዘናት እየዞሩ መላውን ዓለም ያጠጣሉ፤ የደረቀውን ያለመልማሉ፤ ለፍሬም ያደርሳሉ፤ እነዚህ አፍላጋት የማይከቡት ምድር የለም፤ ቅድስት አሪት ይህን ስትናገር ዘፍ 2÷9-15 ቅድስት ወንጌል ደግሞ የዚህን ምሥጢራዊ ትርጓሜ ትናገራለች እንዲህም ስትል ታስረዳለች "የሕይወት ምንጭ ውኃ ከሆዱ የሚፈልቅ ዮሐ 4፥14 የሕይወት ምንጭ ክርስቶስ ሲሆን ውኃው ደግሞ ከሆዱ ማለትም ከባሕርዩ የሚፈልቀው ቅዱስ ቃሉ ነው። እሱም በአራቱ ወንጌላውያን በኩል የደረሰን ነው። በገነት መካከል የበቀለው የሕይወት ዛፍ ከበታቹ አራቱን አፍላጋትን እንዳፈለቀ ጌታችንም አራቱን ወንጌላውያን

33. ውዳ.ዘሐመ.ስ

አሥነስቶ ወንጌልን አራት ክፍል አድርጐ የማዳኑን ምሥጢር የሚገልጽ ነው። መጀመሪያ ኢየሩሳሌም ለአንድ ዓመት ከሌላው ዓለም ተለይታ በዚህ ቃል መንፈሳዊ ልምላሜን እንድታገኝ የተደረገ መሆኑን ታሪክ የሚነግረን እውነት ነው።

ምን አልባት የበዓለ ሃምሳ ቀን ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ሲቀበሉ "በዓለ ሠዊትን" ለማክበር ከተሰበሰበው ልዩ ልዩ ሕዝብና ነገድ በስተቀርና እግዚአብሔር የመረጣቸው እንደ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ያሉ ሰዎች ካልሆኑ በስተቀር በዚያች አንድ ዓመት ውስጥ ወንጌልን ሰምቶ ያመነና የተጠመቀ ፍጡር በምድር ላይ አልነበረም።የሐ ሥራ 2፥1 8፥27 ለአንድ ዓመት በጎብረት ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ የአራቱንም ወንጌላውያን ቃል በኢየሩሳሌም ብቻ ይሰብኩ ዘንድ ታዘዋልና። ከዕፀ ሕይወት ሥር የሚመነጩት አራቱ ወንዞችስ በጎብረት ሆነው ገነትን ዞረው ካጠጡ በኋላ አይደል ወደ ሌላው ዓለም የሚወጡት፤

ከወጡ በኋላ ግን አራቱም ወንዞች ዓለምን ለአራት ተካፍለው ያለ ከልካይ ይፈሳሉ፤ የደረቀውን ይህን ዓለም ያለመልማሉ፤ ወንጌልና ወንጌላውያንም ከኢየሩሳሌም በኋላ ዓለምን ተካፍለው መጥተው ሲሰብኩ በመላው ዓለም ያልደረሱበት የለም፤ ያለ ከልካይ እንደሚፈስ ውኃ ከዓለም ዳርቻ እስከ ሌላው ዳርቻዋ ተጉዘዋል። እንዲያውም ነቢዩ ይህን ሲገልጽ "ውስተ ኵሉ ምድር ወጽአ ነገሮሙ ወእስከ አጽናፈ ዓለም በጽሐ ነቢቦሙ" ሲል ዜና ስብከታቸው ያልደረሰበት ዓለም የሌለ መሆኑን ተናገረ። መዝ 19፥7

እንዲያውም በገነት ያሉት አራቱ አፍላጋት ከምድራዊው የሕይወት ዛፍ ሥር የሚመነጩ መሬታውያን በመሆናቸው ወደ ምድር እንጂ ወደ ሰማይ የፈሰሱበት ጊዜ የለም። የአራቱ ወንጌላውያን ትምህርት

ግን ከሰማያዊው የሕይወት ዛፍ ከክርስቶስ የፈለቁ ሰማያውያን ትምህርቶች እንደመሆናቸው ወደ ሰማይ ሲፈሱ ተመልክተናል። ለአራቱ ወንጌላውያን ገልጾላቸው ያጻፈውን ወንጌል በሰማይም ለነበሩ የመላእክት ማኅበር ከዕርገት እስከ ጰራቅሊጦስ ባሉት አስር ቀናት የሰበከው መሆኑን አባቶቻችን በታሪክ አስተምረውናልና ነው። ወደላይ ወደሰማይ፣ በታችም በምድር ላይ ከመፍሰሱም አልፎ በመቃብር ውስጥ ያሉትን የደረቁ አጥንቶች ሁሉ ማለምለም የቻለ እውነተኛ የሕይወት ምንጭ ውኃ ነው።

በእውነት እግዚአብሔር አራቱንም ከአንድ ምንጭ እንዲወጡ ካደረገ በኋላ ከአራት የከፈላቸው በአራቱም የዓለም ማእዘናት እንዲፈሱ መደረጉ ለምን ይመስልሃል? ከአንድ ጥሩ ምንጭ ከክርስቶስ አንድ ሆና የወጣች ጥሩ ውኃ ሕገ ወንጌልን አንድ አድርጎ የሠራት ሆኖ ሳለ ከአራት ከፍሎ በመላው ዓለም የሚያስነግራት መሆኑን ለመግለጽ ነው እንጅ ነው እንጅ ሌላ ምንድነው። ከነዚህ አራት ወንዞች የተነሣ ለሰው ልጆች የሚበላውና የሚጠጣው ነገር በገነት መካከል ተዘጋጅቷል። ተበልተው የማይጠገቡ ለዓይን የሚያስጐመጁ ዕፀዋትን ከነፍሪያቸው ገነት ከማስገኘት አልተከለከለችም። እመቤታችን ድንግል ማርያምም የሚበላውና የሚጠጣው የተገኘባት እውነተኛ ገነት ናት። በአራቱ ወንጌላውያን ስብከት ላመኑት ሁሉ መብልና መጠጥ ከእርሷ ነው የወጣው፤ ለዚህ ነው ቅዱስ ኤፍሬም "ተፈሥሒ አ! ቤተልሔም" ብሎ ያመሰገናት፤ ቤተ ልሔም ማለት ቤተ ኅብስት (የእንጀራ ቤት)ማለት ነውና።

የብሕንሳው ሐዋርያ አባ ሕርያቆስም "አ!ድንግል መፍርዩት ለእንተ ይትበላዕ ወመንቅዒት ለእንተ ይሰተይ፤ ድንግል ሆይ የሚበላውን

የሚጠጣውን ያስገኘሽልን›› ሲል በቅዳሴው ያወድሳታል።ሊቁ አትናቴዎስም በቅዳሴው እንደነገረን በገነት መካከል ያሉ ዕፀዋት የሚያስገኙልን ፍሬ አንዱ ሲያልቅ ሌላው እየተተካ የሚኖር ሲሆን ከእመቤታችን የሚገኘው የሕይወት ፍሬ ግን መተኪያ የሌለው የዘለዓለም ስንቅ ነው። ከዚህ በቀር ሌላ ምግብ እንዳይመገብ ለፍጥረት ሁሉ "እንኩ ብሉ" ማቴ 26፥2 ተብሎ አዋጅ ተላልፏል።

ሰባቱ የገነት ርስቶች

ከዚህም በተጨማሪ የመጀመሪያዋ ምሥራቃዊት ምድር ገነት በሰባት የምትከፈል ባለ ሰባት ክፍል የሰው ልጅ ርስት መሆኗን አባቶቻችን ነግረውናል። ይህም የነቢያት፣ የሐዋርያት፣ የሰማዕታት፣ የመነኮሳት፣ የካህናት፣ የፍጹማን ምእመናን፣ የደናግል፣ የሕጻናት ርስት ተብሎ ይከፈላል። እነዚህ ባጠቃላይ ማኅበረ ቅዱሳን፣ ማኅበረ ጻድቃን ተብለው ይጠራሉ። እነዚህን ሁሉ በአንድ ላይ አጠቃሎ የሚይዝ የወይኑን ቦታ የሚያበላሹ ጥቃቅን ቀበሮዎች ያልተሰማሩባት ሰፊ ርስት ያላት ቦታ ገነት ናት።

ርስት ማለት በገንዘብ የማይሸጥ የማይለወጥ ከአባትና ከእናት የሚወረስ ለልጅ ልጅም የሚተላለፍ እስከ ሞት ድረስ የሚጋደሉለት ነው። 1 ነገ 20፥1 ጌታ እስራኤልን ርስቱ ሲል ይጠራቸው ነበር እስከ ሞት ድረስ የሚወዳቸው ውድ ገንዘቡ ናቸው ማለቱ ነው። እግዚአብሔርም ለሰው ልጆች ርስትና ዕድል ፈንታ ነው። "እግዚአብሔር ዕድል ፈንታዬና ጽዋ ተርታዬ ነው" መዝ 15፥5 ሰማዕታት፣ ሐዋርያት እስከ ሞት ድረስ የተጋደሉለት ርስታችን ነውና። ራእ 2፥10 ነቢዩ ይህን ካለ በኋላ የተናገረው ትንቢታዊ ቃል ደግሞ አስገራሚ ነው። "አንተ

ውእቱ ዘታገብእ ሊተ ርስትየ፤ ርስቴን የምትመልስልኝ አንተነህ›› ብሎ የተናገረውን አባ ሕርያቆስ "..... ርስት አንቲ....[25]" ብሎ እግዚአብሔር ለሰው ዘሮች የመለሳት ርስት እመቤታችን መሆኗን ይመሰክራል።

ሰይጣን በክፉ ግብሩ ያስነጠቀን በክርስቶስ ደም የተመለሰችልን ርስታችን ገነት ባለሰባት ክፍል ናት ተብሎ መነገሩ የሚበላውን የሚጠጣውን ያስገኝችልን አማናዊት ርስታችን እመቤታችን ድንግል ማርያምም ለእርሷ ብቻ የተሰጡ ለሌሎች የአዳም ዘሮች ያልተሰጡ ሰባት ታላላቅ ነገሮች በውስጧ ያሉ መሆኑን አመላካች ናቸው።

እነርሱም ሦስቱ ድንግልናዎቿ ማለትም በሥጋ፣ በነፍስና ጎሊና የተሰጧት ሲሆኑ ሌሎችም፡- ድንግል ወእም ማለትም እናትነትን ከድንግልና፣ ድንግልናን ከእናት ጋር አስተባብራ ይዛ መገኘቷ ከድንግልናዋ ቀጥሎ አራተኛ ሆኖ የሚቆጠር ሲሆን እናት ከሆኑ በኋላ ድንግል፣ ድንግልም ከሆኑ እናት መሆን ለሰው የማይቻል የተፈጥሮ ሕግ ሆኖ ሳለ በእርሷ ዘንድ ግን ሲደረግ እንመለከተዋለን። አምስተኛው ገረድነት ሲሆን ስድስተኛው እመቤትነት ነው ለእግዚአብሔር ምንም እንኳን በሥጋ እናቱ ብትሆንም በመለኮቱ ግን ገረዱ፣ አገልጋዩ፣ ናት ለዚህም ነው የመውለዷን ነገር ሲነግራት ለነበረው መላክ እንዲህ ስትል የመለሰችለት "ነየ አመቱ ለእግዚአአብሔር ፤ እነሆ የእግዚአብሔር ገረዱ›› ሉቃ 1፥38

ትሕትናዋን ልብ በሉላት! ካንቺ ይወለዳል ብሎ እየነገራት እርሷ አሁንም ጌታዬ ትለዋለች፣ ገረዱ አገልጋዩ እንደሆነች ትናገራለች። በመላእክት እና በሰዎችም ዘንድ ደግሞ እመቤት ናትና እመቤታችን ብለን እንጠራታለን። የንጉሥ እናት ናትና ይገባታል እንዲያውም

ኢትዮጵያዊው ጻድቅ አጼ ዘርዐ ያዕቆብ መልክአ ማርያም በተሰኘው ድርሰታቸው እመቤታችንን ሲያመሰግኑ "... ማርያም ድንግል እግዝእተ መላእክት ወሰብእ..." ብለዋታል። ሰማያውያንና መሬታውያን ተስማምተው ንግሥትነቷን የሚገልጹላት የንጉሥ እናት ናትና አባቶቿ ነቢያትም ስለ ንግሥትነቷ ሲናገሩ በእግዚአብሔር ቀኝ ለመቆም ሥልጣን የተሰጣት መሆኑን ተናግረውላታል።

ለክብሯ የማይገዛ ሕዝብና መንግሥትም እድል ፈንታው ጽዋ ተርታው እንደሰዶምና ገሞራ በእሳት፣ እንደ ሰብአ ትካት በንፍር ውኃ መቃጠል ነው። ሲሉ አስጠንቅቀዋል መዝ 44፥10፣ ኢሳ 60፥12 ሰባተኛውና የመጨረሻው ለዚህ ሁሉ ጸጋ መሠረት የሆናት "እመ እግዚአብሔር" መሆኗ ነው ከመጀመሪያይቱ ሴት ከሔዋን ጀምረን ብንቆጥር በሰው ልጆች የትውልድ ሐረግ ውስጥ ብዙ እናቶችን እናገኛለን።

ከእነርሱ አንዲቱ ስንኳን "እመ እግዚአብሔር " ተብላ ለመጠራት የታደለች አንዳችም ሴት የለችም ባጠቃላይ እነዚህን ሰባት ነገሮች ይዛ የተገኘች ከእመቤታችን በቀር ሌላ ሴት በምድር ላይ አትገኝም። በነዚህም ሰባት ነገሮች እመቤታችን ገነትን ትመስላለችና ብለው ሊቃውንት ገነት ብለው ይጠሯታል። እነዚህን ጸጋዎቿን መተርጉም የሚቻለው ሊቅ መተርጉም የሚቻለውስ ምን አንደበት ነው፤ እመቤት ሆኖ ገረድ መሆን፣ ድንግልም ሆኖ እናት መሆን በዚያውም ላይ ሰማይና ምድር ለማይችሉት ንጉሥ እናት ሆኖ መገኘት ያልገረመ ምን ይግረም?

ንዋይ ጎሩይ ተብሎ የሚጠራው ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ገነት ሲናገር "... በዚያም ሊናገሩት የማይቻለውን ምሥጢር አየሁ...."

2 ቆሮ 12፥2 ብሎ ነበር ስለ እመቤታችንም የተናገሩት ሊቃውንት "አይ ልቡና ወአይ ነቢብ ዘይክል አዕምሮ ዝንቱ ምሥጢር" በእርሷ የተደረገውን ይህን ድንቅ ምሥጢር መናገር የሚቻለው አንደበት፣ ማሰብ የሚቻለው አዕምሮ እንደምን ያለ ነው? ብለዋል። አባታ ዳዊትም የእርሷን ጸጋ መተርጉም የማይቻል መሆኑን ይስማማል እንዲህም ይላል። "የእግዚአብሔር ሀገር ሆይ ስላንቺ የተነገረው ነገር ድንቅ ነው። ይላታል

በድንቅ ምሥጢር የተከበበች፣ በመንፈስ ቅዱስ የታተመች ባልተገዘረ አንደበት የማትተረጉም መጽሐፍ ናትና- እመቤታችን ጠንቅቀው ሊማሩዋት ይገባል። ከነቢያት እስከ ሐዋርያት ከዚያም እስከ ዘመነ ሊቃውንት እስካሁንም በተነሡ መምህራን ያልተገለጠ መልክና ውበት ያላት ገነታችን ናት- እመቤታችን ድንግል ማርያም።

ከወላጅ አባቶቿ መካከል በጥበቡና በአስተዋይነቱ የተመሰከረለት ንጉሥ ሰሎሞን የተዘጋች ገነት መኃ 4፥12 ብሎ ለአዳማዊ ርኩስትና ለምድራዊ ሐሳብ የተዘጋች ገነት መሆኗን ሲገልጥ በሌላው ስፍራ ደግሞ "ወልድ እጉየ ወረደ ውስተ ገነቱ" በማለት ከሦስቱ አካላት አንዱ ወልድ በተለየ አካሉ ሥጋዋና ነፍስዋን ነሥቶ ሰው የሆነ መሆኑን ይመሰክራል መኃ 5፥2

እንግዲህ ምን እንላለን መንፈስ ቅዱስ ከጥንት ጀምሮ በድንቃ ድንቅ ምሥጢር የከበባት ስለ ክብሯ ገና ሳትወለድ ብዙ ነገርን ያናገረላት ንጽሕት የተክል ቦታ ናት እመቤታችን፤ በዚህች የተክል ቦታ ከቦታዎች ሁሉ ተለይታ መቃብር አይቆፍሩባትም ሬሳ አይጥሉባትም ስለምን ያሉ እንደሆነ የሰው ደምና አጥንት ተክል ያደርቃል፣ ፍሬ ይቀንሳል ብለው ነው በዕብራውያን ባህል በአትክልት ስፍራ ሬሳ አያስቀምጡም

መድኃኒታችን ክርስቶስ ብቻ በአትክልት ስፍራ ከባሕላቸው ውጭ ተቀብሯል በሌላ ቦታ ተቀብሮ ቢሆን ኖሮ እንደ ኤልሳዕ ያለ ገባሬ ተአምራት ነቢይ በተቀበረበት ቦታ ቢቀብሩት ተነሥቷል እንጂ በገዛ ሥልጣኑ ኢይሖም ብሎው ኢይሁድ ምክንያት እንዳያፈጥሩ ነው። 2 ነገ 13፥21 ስለዚህም ሰው ተቀብሮበት በማያውቅ የአትክልት ስፍራ ቀበሩት የአትክልት ስፍራ ለመቃብርነት እንደማያገለግል ሁሉ በእመቤታችንም ምዉት ግብር በውስጧ የማይገኝባት መሆኑን ያሳያል። በእርሷ ዘንድ ሰውን ሁሉ ለሞት ያበቃው ምዉት ኀሊና ስንኳን በፍጹም አይገኝባትም ለዚህ ነው ‹‹ንጽሕት በድንግልና አልባቲ ሙስና›› ብለን የምንጠራት እንጂ ምዉት ኀሊና ባላቸው ሰዎች ዘንድማ እንደምን ሆኖ ያለ ርኩሰትና ያለ በደል መገኘት ይቻላል? ከሰማይ ተልከ የመጣው መላክ ላቀረበላት ሰላምታ ስትመልስ "እፎኑ ከመዝኑ እንጋ አምኃ ይትአመኑ " እንደምን ያለ እጅ መንሻ ይደረግልኛል ?ሉቃ 1፥27 ብላ መናገሩዋ። እንደ መጀመሪያይቱ እናታችን የሞተ ኀሊና ባይኖራት እኮ ነው፤ እንኳን ለሞተ ነገር ለራሱ ለሞት ሳይቀር የማትመች ልዩ የተክል ቦታ ናት- እመቤታችን።

ወደ መዳን እንዲደርሱ የተጠሩት ሁሉ እውነተኛውን የወይን ግንድ ያገኙባት በኦሪትና በነቢያት በሐዋርያትና በሊቃውንት እስከ አለተ ምጽአትም ባሉት ዓመታት የሚነሡት ሁሉ ቅርንጫፍ የሚሆኑበት የወይን ግንድ ነው። ይህ ከእርሷ የተገኘ የክርስትናችን የወይን ሐረግ ቢመዘዝ ሥሩ የሚገኘው ከዚች የተክል ቦታ ነው እርሱ ደግሞ ንጉሡ እንደ መሰከረው መድኃኒት ነው፤

በእሊህና መሰል ነገሮች ገነት ብለናታል የዕረፍት ቦታ ናትና። በገነት ያሉ ነፍሳት በተድላ በደስታ ይኖራሉ ኃጥአን ከቦታቸው ሆነው አሻቅበው እያዩ የተሰጣቸውን ጸጋ ያደንቃሉ ሉቃ 16፥19 እመቤታችንም ለኛ ለኃጥአን ዕረፍትን ያስገኘች ገነት ናት። ወደኔ ኑ አሳርፋችኋለሁ" ማቴ 11፥28 የሚለው ጌታ የተወለደው ከርሷ ነውና። ይሄን ማን ብሎ ያውቃል? "እንዲህ የበዙት ብታሳርፏዋቸው አይደለምን?አታሳርፏቸው" ዘጸ 5፥5 እንባል በነበረባት ምድር "እንግዲህስ ዕረፉ የሚለውን ድምፅ ለዘለዓለም ዕረፍት ሊሆነን የሰማነው ከዚች ገነት ከተገኘው ጌታ ነውና መካነ ዕረፍታችን ናት።

ልጇ መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ በሞት ከዚህ ዓለም የተወሰዱትን "ዛሬ በገነት ከኔ ጋር ትሆናለህ" ሉቃ 23፥43 ብሎ ቃል ሲገባለቸው በአጸደ ሥጋ የሚኖሩ ምእመናንንም በሜዳ አልነበረም የተዋቸው፤ ወደ አማናዊት ገነት "እነኋት እናትህ" ዮሐ 19፥27 ብሎ አስጠግቶአቸው ነበር እንጂ፤ ይህን ስላልን ግን መቼም ምሳሌ የሚሆን ነገር ሁሉ አማናዊውን ነገር አይወክልም በገነትና እመቤታችን መካከልም ልዩነት መኖሩ የተገለጠ ነው።

ያችኛዋ ገነት የምታልፍ ዓለም ስትሆን በእመቤታችን ግን ማለፍ የለባትም፤ የሰው ልጆች ጠብን ከእግዚአብሔር ጋር የጀመሩት መርገምም ወደ ሰው ልጆች የመጣው በየት ሆነና! በገነት አይደል?እመቤታችንን ያየን እንደሆነ በየትኛውም ዘመን ያልተደረገው ወደ ፊትም የማይደረገው ባዕድ መለኮት ከባዕድ ሥጋ ጋር የተዋሐዱባት፣ ሰውና እግዚአብሔር የዕርቅ ሰነድ የተፈራረሙባት፣ መርገም ቀርቶ ለሰው ልጆች በረከት የታደለባት ገነት ናት። በዚያኛችኛዋ ገነት ስንኳን የሰው ዘር ከሰው ተግባር የተነሣ "ርግምት ትኩን ምድር በተግባርከ፤ከሥራህ

የተነሣ ምድር የተረገመች ትሁን›› ዘፍ 3፥17 ተብሎ ነበር፤ በዚችኛዋ ገነት ደግሞ "ወቡሩክ ፍሬ ከርሥኪ" ሉቃ 1፥59 ሲባል ሰማን።

እናም ሌላ ምሳሌ ቢያጡላት አበው ገነት ብለውታል እንጂ ገነት በራሱ ለክብሯ ሙሉ በሙሉ የሚመጥን ምሳሌ አይደለም ሁሉንም ፍጥረት አይተው እንደ ክብሯ ምሳሌ ሆኖ የሚገልጽላቸው ቢያጡም አይደል "በመኑ በአምሳለ መኑ ናስተማስለኪ " በማን እና በምን እንመስልሻለን ብለው ያመሰገኗት። የተመሰለለትን አካል ከምሳሌው እንደሚበልጥ ከተስማማን መቀጠል እንችላለን አንዳንድ ሰዎች በብዙ ምሳሌ ሲነገርላት ሲሰሙ የሚከፋቸው እንዳሉ ስለማውቅ ነው።

አልችል ብለን ነው እንጂ ከዚህም በላይ የምናውቀው ዓለም ቢኖርና ብንመስልላት እንወድ ነበር፤ የኛ ቤተክርስቲያን ጉባኤያት ሁሉ ከጌታችን ቀጥለው ስለ እርሷ ገነትነት አስረድተዋል የንጹሐን፣ የደናግል፣ የመነኮሳት፣ የሰማዕታት ሁሉ ማደሪያ የሚሆን ጌታ የተገኘው ከእርሷ ነውና። ቅዱስ ኤፍሬም ይህን ሲያረጋግጥልን "እስመ ኮንኪ አንቲ ማኅደረ ለፍሡሓን፤ አንቺ ደስ ብሏቸው የሚኖሩ የቅዱሳን የማደሪያቸው ማደሪያን ሆነሻልና ይላታል፤

እንዲያው ይሄ ሁሉ ምስክር ለምን ያስፈልገናል እግዚአብሔር እንኳን ለማረፊያነት የመረጣት ንጽሕት የሴም ድንኳን አይደለችምን?ለጊዜው ያይደለ ለዘለዓለም ማረፊያው ገነት እመቤታችን ናት። ስለ እርሷ በመጽሐፍ የተባለው ምንኛ ድንቅ ነው? "ማረፊያው ልትሆን መርጧታል ለዘለዓለም ማረፊያዬ ናት መርጫታለሁና በእርሷ ውስጥ አድራለሁ" መዝ 131፥14 ዘፍ 9፥27 ይህንንም ቅዱስ ገብርኤል ሲተረጉመው "መንፈስ ቅዱስ ያድርብሻል" ብሎ በመናገሩ ለዘለዓለም የተዘጋጀች የአምላክ ማረፊያ ድንግል ማርያም እንደሆነች ታወቀ ተረዳ።

ምዕራፍ ፪

ቅድመ ጽንሰታ

እግዚአብሔር ለሚሠራው ሥራ ሁሉ ጊዜ አለው፤ ውብ አድርጎ የሠራቸው ነገሮችን በጊዜውና በፈቀደው ሰዓት አድርጓቸዋል። በምድር ላይ ከሠራቸው ውብ ነገሮች አንዷ እመቤታችን ናትና በፍጥረታት ልማድ ከእናትና ከአባቷ በሥጋና በደም ተከፍላ፣ በነባቢት ነፍስ ሕያው ሆና፣ በደማዊት ነፍስ ከብራ ከመገለጧ በፊት ለማኅበረ መላእክት በታላቁ መላክ በቅዱስ ሚካኤል ክንፍ ላይ ስሎ አሳይቷቸዋል።

ይህንም ቅዱስ ያሬድ በዜማው ሲገልጽ "ሚካኤል መልአክ በክንፉ ተሸከማት የደመና መጋረጃም ጋረደላት ይላል[37]›› የደመና መጋረጃ ብሎ የገለጸው በደመና የተሸፈነ እንዳይታይ በአካል አልታየችም ማለቱ ነው። ለማኅበረ መላእክት በዚሁ መልኩ እንደገለጻት ለሰው ዘር ደግሞ በተለያየ መልክ የገለጻት ቢሆንም አዳም ከገነት በወጣ ጊዜ ኃጢአት ባወየበው ባሕርዩ ውስጥ እድፈት እና ርኩሰት የሌለባት ሆና በተስፋ ተገልጻ ነበር ፤

በጭቃ ውስጥ የወደቀ ወርቅ ከጭቃው ጋር ምንም አይነት ዝምድና እንደማይኖረው ሁሉ በበደሉ እና በመተላለፉ ሳትተባበር በአዳም ባሕርይ ውስጥ እንደ ነጭ ዕንቊ ታበራ የነበረች ንጽሕት ደም ነበረች እና በዚች ንጽሕት ባሕርይ የሚያድነው መሆኑን ገልጾለታል። ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ በአንድ ቦታ በተናገረው "ማርያምሰ ተንቱ ውስተ ከርሱ ለአዳም ከመ ባሕርይ ፀዓዳ፤ ማርያም ግን እንደ ነጭ ዕንቊ በአዳም ገላ ውስጥ ታበራ ነበር[38]" ብሎ።

37. ዋዜማ ዘታህሳስ ገብርኤል

ለአዳምም ትልቅ ተስፋ የሆነው ይህ እንደሆነ በአባ ሕርያቆስ በኩል መንፈስ ቅዱስ ተናገረን "አንቲ ውእቱ ተስፋሁ ለአዳም አመ ይሰደድ እምገነት" አዳም ከገነት በወጣ ጊዜ አለኝታ ስንቁ አንቺ ነሽ ብሎ።
በዚህም ሆነ በሌላ ምሳሌ ለፍጥረት የተገለጠችው ድንግል እመቤታችን የእግዚአብሔር የምሥጢር ሐሳብ ናትና በትንቢትና በምሳሌ እንጂ በአካል ሳትገለጥ ዘመናት ነጐዱ፤ዓመታት ዓመታትን ወለዱ፤ ዕለታት ከወራት ጋር ተዋሐዱ፤እመቤታችን ግን በእግዚአብሔር ኅሊና ተጠብቃ ለረጅም ዘመናት ተቀመጠች እንጂ አልተገለጠችም ፤ሊደርሱባት ፈልገው አንዳንዶቹ በፍናተ አዕምሮ ተጉዘው ፈለጓት፤ እነ ሙሴ እነ አሮን ለአርባ ዓመታት በባሕርና በየብስ ሌሊትና ቀን ተጓዙ፤ አሻግረው አዩአት እንጂ ወደ እርሷ ገብተው ማረፍ ክፍሬዋም መብላት ግን አልተቻላቸውም፤ ሞት ከልክሎአቸዋልና። ባለተስፋዎቹ አባቶቻችን ሁሉ የተሰጣቸውን ተስፋ እየጠበቁ ሳሉ አንቀላፉ፤የተስፋይቱን ምድር ዜና ከመልእክተኞች ብቻ እንደሰሙ፤ የስንዴና የወይን ምድር መሆኗን እንደተረዱ ሳይወርሷት አለፉ፤ ዘኁ 13፥27

ሙሴ የተስፋይቱን ምድር እንዲሰልሉ የላካቸው መልእክተኞች የነቢያት ምሳሌዎች ናቸው እንጂ ሌላ ምንድን ነው? በዚያ ዘመን የነበረው ትውልድ ቃልን ከነቢያት ይሰማ ነበር እንጂ ሌላ ከየት ይሰማል፤ የምድሪቱን ፍሬም አየት እንጂ አልበሏትም ነበር፤ ዘኁ 13÷26 ጊዜው ገና ነበርና። በነዚህ ረጅም ዓመታት ረጅም የትውልድ ጅረት ከሩቅ አይቶ ተሳለማት፤ እጅ ነሣት፤ ከመጻሕፍት በአንድ ሥፍራ "እምርሑቅሰ ርእይዋ ወተአምኅዋ፤ ከሩቅ አይተው ተሳለሟት " ተብሎ እንደተጻፈ ከአጠገቧ ደርሶ ከፍሬዋም ቀምሶ እንዲኖር ለተፈቀደለት ሕዝብ መንገዱን እየመሩ እነርሱ ግን ካሰቡት ሳይደርሱ

28. ጸመ ድን

ቀሩ፤ ዘዳ 34÷4 የተፈቀደለት ትውልድ ብቻ በዙሪያዋ ሰፍሮ፣ ሱባዔ ቆጥሮ ቅጥሩ ከፈረሰለት በኋላ ምድሪቱን ወረሰ፣ አባቶቹ በዓይናቸው አይተው ያልቀመሱትን የምድሪቱን ፍሬ ቀመሰ።

ልብ በሉ! የተስፋይቱን ምድር ለመውረስ የተፈቀደለት ትውልድ ማለት ባሕታውያኑ፣ መነኮሳቱ፣ መናንያኑ በአጠቃላይ ማኅበረ ምእመናን ናቸው። እነዚህ ሁሉ በዮርዳኖስ በኩል ማለትም በጥምቀት ተሻግረው በጾም እና በጸሎት የኃጢአት ቅጥርን አፍርሰው ወርሰዋት ይኖራሉ።የአማናዊቷ ከነዓን የድንግል ማርያም ፍሬ የሆነውን ቅዱስ ቍርባንን ተመግበው ይኖራሉ፤ መናንያኑ በዋሻ ውስጥ ገብተው በበረሐ ወድቀው ሌሊት እና ቀን በስሟ ይጽናናሉ፤ ምእመናኑ በረከተ ቃል ኪዳኗን ተስፋ ያደርጋሉ፤ በሰማይና በምድር እርሷን ወርሰው ይኖራሉ።

ይህ ከመሆኑ አስቀድሞ ወደ ተስፋይቱ ምድር የተደረገው ጉዞ ምን ያህል ከባድ ነበር፤ እርሷን ፍለጋ ብዙዎች በመንገድ ሳሉ አስትንፋሳቸው ተቆረጠች፤ አርባ ዓመታትን ከቤተሰቦቻቸው ወጥተው በድንኳን ኖሩ፤ በበረሐ ከአራዊት ጋር አደሩ፤ ይህም ሆኖ ግን ከነርሱ ብዙዎቹ ሳይደርሱ ቀሩ።

ይህ ሁሉ አሰቃቂ ጉዞ ለምን ይመስልሀል? እግዚአብሔር በአንድ ቀን ማውረስ እየቻለ አርባ ዘመን ሁሉ ለምን ይሄን አደረገ? ለአርባ ዓመታት መና ከደመና ከማውረድ፣ ውኃ ከዓለት ላይ ከማፍለቅ ምድሪቱን ማውረስ አይቀልም ነበርን? ውሳኔው አርባ ዓመት ለጸኑት ብቻ ከምድሪቱ ፍሬ የተፈቀደ ነበር፤ አለበለዚያ ከመናው ብቻ እንደተመገቡ መሞት የግድ ነበር፤

ይገርማል! አማናዊቷን የቃል ኪዳን ምድር እመቤታችንን የገለጸበት መንገድ። ከእመቤታችን የተገኘው የሕይወት ፍሬ ክርስቶስ በአርባ ቀን ለተጠመቁት ብቻ የተሰጠ ነው፤ ላልተጠመቁት እኮ የምድሪቱን በረከት ሥጋውና ደሙን መብላት አይቻልም። በልተውት ከሞት የማያድነውን መና ይበላሉ እንጂ፤ እርሱም የዚህ ዓለም ሀብትና ንብረት ነው፡1 ቆሮ 10÷4 ዮሐ 6÷49 እስራኤል የሰለቹትን የተበላሸውን ያን መና ያመለጥንባት ፣ከአንድ ቀን በላይ አድሜ የሌለውን መና በዘለዓለማዊው መና የተካንባት የቃል ኪዳን ምድራችን ድንግል ማርያም ናት። ዘፀ 16÷19

ቅድስት አሪት እንደመሰከረች ለአባታችን አብርሃም ከሰማይ ከዋክብት ለሚበዙ ልጆቹ እንደሚያወርሳት ሲናገር ስለ ምድራዊው ነገር የሚናገር ይመስልሃል? ስለ እመቤታችን እንጂ፤ ለአንድ አድርጎ "ለዘርህ እሰጣታለሁ" አለ እንጂ ለብዙ እንደሚሰጣት ለዘሮችህ አላለም። እርሷ ለአንዱ የአብርሃም ዘር ለክርስቶስ እናትነት የተመረጠች ናትና ገላ 3÷16፣ ማቴ 1÷1

አብርሃምም በሕይወቱ የመጀመሪያውን መሠዊያ የሠራው ስመ እግዚአብሔርንም መጥራት የጀመረው በዚች ቦታ ነው። ዘፍ 12÷7 ይሄውም ልብ ላለው ሰው የሐዲስ ኪዳኑ የእግዚአብሔር ሕዝብ የአምልኮ መጀመሪያ መሆኗን ያሳያል። የሰማይ መላእክት በሆዷ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን የምስጋና መሥዕዋት ያቀረቡባት መሠዊያ ፣ ቅዱስ ዮሐንስ በማሕጸን ሳለ የሰገደባት መስገጃ እና ቅድስት ኤልሳቤጥ የጸለየችባት በመንፈስ ቅዱስ የተዘጋጀች ቤተ ጸሎት ናት፤ በእውነት ያለሐሰት የምድር አሕዛብ ሁሉ ስመ እግዚአብሔርን መጥራት የተለማመዱባት የሰው ዘር ቋንቋ ናት።

በአንድ ስፍራ ስለ እርሷ "ለሥላሴ ስግደትን የምታስተምሪላቸው አንች ነሽ" ተብሎ ተነግሮላታል። የእግዚአብሔር ሦስት አካሉ፣ የማይከፈል አንድ ባሕርዩ የተገለጠው ከእመቤታችን በኋላ ነውና። በዚህ ሁሉ ትውልድ ደጅ ጥናት የመጣችው እመቤታችን ድንግል ማርያም የተገኘችው ከደጅ ጠኝው ትውልድ መካከል ነው። በአባቷ በኩል የታላላቁ ነገሥታት አባት ይሁዳ፣ በእናቷም በኩል የመገናኛው ድንኳን አገልጋይ ካህናትን የወለደው ሌዊ እንደሚወልዷት ታሪኳን የሚናገሩ ድርሳናትም ምስክር ናቸው። እስከወዲያኛው ያየን እንደሆነ ዳዊት ፣ሰሎሞን፣ አሮን፣ አልዓዛር ወላጆቿ ናቸው ማለት ነው። ለዚህ አይደል አባቷ ዳዊትስ መሠረቶቿ የተቀደሱ ተራሮች ናቸው። መዝ 86፥1 በማለት እንደ ተራራ የገዘፈ ክብርና ሞገስ ካላቸው ነገሥታትና ሊቃነ ካህናት መገኘቷን የገለጸው።

እምፅንሰታ እስከ ልደታ

በዚህ ሁሉ ትውልድ ደጅ የተጠናችው እመቤታችን የተጸነሰችው ለምሕረት ዓመት 15 ዓመት ሲቀረው በ5485 ዓመተ ዓለም በዓመተ ምሕረት ዋዜማ ላይ ነበር። እግዚአብሔር ሕዝቡን ይቅር ሊለው ዘመኑ ሲቃረብ የሰላሟ ርግብ የጥፋቱን መቆም ልታበሥር ወደ ዚህች ምድር ብቅ አለች።

ያኔ! ዓለም የመኑታን መንደር በሆነችበት ሰሞን በምድር ላይ የነበረ ሥጋዊና ደማዊ ፍጥረት ሁሉ ወደ ሬሳነት የተቀየረ ጊዜ ፣ውኃው ከታላላቁ ተራሮች ከነ አራራት ከነ ቀርዱ በላይ ሆኖ ለአስራ አምስት ክንድ ወደ ላይ ወጥቶ ይታይ ነበር፤ ይህ የጥፋት ውኃ ደግሞ ለመጕደሉ መልስ የሰጠች የሰላሟ መልእክተኛ ርግብ እንደነበረች ሊቀ ነቢያት መሴ ምስክር ነው። ዘፍ 7፥19

አስተውል! ያ ወደላይ ለ15 ክንድ ከፍ ብሎ የታየውና ምድሪቱን የከደነው ውኃ ከአዳም እስከ ክርስቶስ መምጣት በምድራውያን ላይ ሠልጥኖ የነበረውን ኃጢአት ይመስላል። በዚያ ዘመን የወረደው ውኃ ፍጥረትን ሁሉ ጐድቷል፤ ሰውን ብቻም አይደል፤ በምድር ላይ የሚርመሰመስ ሥጋዊ ደማዊ ፍጥረት ሁሉ ተጐድቶበታል፤ ከአዳም የወጣው ኃጢአትም ሰውን ብቻ ሳይሆን እንስሳትንም አራዊትንም ጐድቷል፤ እንኳን ምድራውያኑን ሰማያውያኑን መላእክትም ሳይቀር ጐድቷል።

ቅዱሳን መላእክት በክብር ላይ ክብር ተጨምሮላቸው የሚኖሩት ከእግዚአብሔር ወደ ሰው፣ ከሰው ወደ እግዚአብሔር በሚያደርጉት አገልግሎታቸው ጭምር ነበርና ይህን አስቀርቶባቸዋል። በዕለተ ልደቱ ከሰው ይልቅ እየዞሩ የምሥራቹን ያሰሙ የነበረውስ ለዚህ አይደል ሉቃ 2፥8-12 ይሄ ፍጥረታትን በሙሉ አንድ አድርጎ የገዳው ኃጢአት ሁላችንንም ሙታን ባደረገበት ዘመን ሊጐል አስራ አምስት ዓመት ሲቀረው ከሞት ላመለጠው ትውልድ ማለትም ለሐዲስ ኪዳኑ ትውልድ ሰላምን ልታበሥር ርግቧ ብቅ አለች፤

በእናቷ በኩል ከካህናት፣ በአባቷም በኩል ከነገሥታት ወገን የተገኘች ናት። ከነገሥታት ዳዊት ሰሎሞን፣ ከካህናትም ታላቁ አሮን አባቶቿ ናቸው። ከነዚህ የተወለዱት ሐናና ኢያቄም በዘመናቸው ታላቅ የሆነ ችግር ደርሶባቸዋል፤ መካኖች በመሆናቸው ያሸማጥጧቸዋል፣ ይዝቱባቸዋል፤ ወደ ቤተ እግዚአብሔር መባዕ እንዳያገቡ ይከለክሏቸዋል፤ ምክነት(መካንነት) የኃጢአት ውጤት ነው ብለው ያምኑ ነበርና።

ትዝ አልላቸው ብሎ እንጂ እግዚአብሔር ከብዙ መካናት እናቶች ታላላቅ ሥራ የሠሩ ሰዎችን አሥነሥቷል፤ ከሣራ ይስሐቅን፣

ከኤልሳቤጥ ዮሐንስን፣ ከስምዖንና አቅሌስያ ገብረ መንፈስ ቅዱስን[39] አስገኝቷል።

እመቤታችንም ከእነዚያ አንዷ ናትና ከመካኖቹ እናትና አባቷ ተወልዳ በጐ ነገር መውለድ በተሳናት ዓለም ውስጥ የተገኘች መሆኗን ለማመልከት ከመካኖች ተገኘች፤ ልጅ የበረከት ምልክት ነውና። 127 ÷3 ዛፍ ካላፈራ ቅጠሉ ቢያምር ቁመቱስ ቢያድግ ምን ይጠቅማል?ከምንም በላይ የእግዚአብሔር ሐሳብ እንደ ሰው አይደለምና ሐናና ኢያቄም ልጅ በማጣት በሚገቡት ሱባዔ በሚያለቅሱት ለቅሶ ከአዳም እስከ እርሷ መገኘት ድረስ አባቶቻችን የገቡትን ሱባዔ ያለቀሱትን ለቅሶ ለመፈጸም ለመደምደም ነው። እነ ሙሴ፣ እነ ኤልያስ ለአርባ ቀናት ያለ አንዳች መብልና መጠጥ የጾሙት ዘዳግ 9÷9፣ 1 ነገ 19÷5 እነ ዳንኤል ዝለው እስከ ሚወድቁ ድረስ የተጋደሉት ዳን 10÷1 አባቷ ዳዊት ለዓይናቹ እንቅልፍን፣ ለሽፋሽፍቶቹ መኝታን፣ ለጕንጮቹ ዕረፍትን ላይሰጥ የማለው የያዕቆብ አምላክ ማደሪያ እመቤታችንን ለማግኘትም ነው።

በእውነት ብዙ ነቢያት ሱባዔን አውጀዋል ፣ጸምን ቀድሰዋል ፣እነ ኤርምያስ በዕለት፣ ሰባቱን ቀን አንድ እያሉ ፣ እነ ዳንኤል ሰባቱን ሳምንት አንድ ሱባዔ እያሉ፣ እነ ሔኖክ በትውልድ ሰባቱን ትውልድ እንደ አንድ ሱባዔ እየቆጠሩ ብዙ ትንቢትን ተናገሩ ::የሁሉም ሐሳብ ግን አንድ ነው ፤ከድንግሊቱ ዘመን ለመድረስ ፤የነዚህ ሁሉ ጩኾት በሐናና ኢያቄም ጩኸት ተደመደመ፤

እነዚህ ሰዎች ለመሥዋዕት የማይሆነውን ምግብ ሁሉ ከመብላት ተከልክለው በብርቱ ፍለጋ ልጅ ይፈልጉ ነበሩ፤ ከነርሱ በኋላ እውነተኛ መሥዋዕት ክርስቶስን የምታስገኝ እመቤታችን ከእነርሱ የምትወጣ ናትና። የሚመገቡትን ብቻም ሳይሆን የሚወልዱትንም

39. ገድለ ገብረመንፈስ ቅዱስ

ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርገው ሊሰጡ ተሳሉ[40]። የአባቶቻቸው የእነ ያዕቆብ ስዕለት እንዲፈጸም የተደረገ ስዕለት ነው። ዘፍ 28÷21-23 የኃጢአት ውጤት ነው ተብሎ የሚነገርለት መካንነት እንደ ነውር ሆኖ በእነርሱ ተጣብቆ ያ እስኪወገድላቸው ብርቱ ጩኸትን ጮሁ፤ ታላቅ ለቅሶን አለቀሱ፤ በሕዝቡ ሁሉ ላይ የሆነውን ነውር እግዚአብሔር ከሕዝቡ እስኪያስወግድ ድረስ ይህ ሁሉ በእነርሱ ሆነ። የቀደሙት ወላጆቻችን ከኃጢአት በኋላ ያቀረቡት መሥዋዕታቸው ፣የጸለዩት ጸሎታቸው ችግር የማይፈታ መሆኑን ለመግለጽ እግዚአብሔር በምሥጢር ካህናቱ መሥዋዕታቸውን እንዳይቀበሏቸው ከለከለ። የላይኛው ቤተ መቅደስ አገልጋዮች ቅዱሳን መላእክት የሰውን መሥዋዕት ተቀብለው ወደ ሰማዩ ቤተ መቅደስ የሚያሳርጉበት ጊዜ ገና ነበርና ሐናና ኢያቄምም መሥዋዕት እንዳያስገቡ በምድራዊቷ ቤተ መቅደስ አገልጋዮች ተከለከሉ።

በሕይወታቸው ረጅሙን ዓመት በነውር አሳለፉ። በተለይም ውበት፣ ሙቀትና ልምላሜ የማይታጣበትን በጕውን የልጅነት እድሜአቸውን በለቅሶ ጨረሱ፤ ይህች ዓለምም እንደወጣትነት የሚቆጠር እድሜዋን በኃጢአት ጨርሳ 5500 ዘመናት ተቆጥረውላት መሸምገል ከጀመረች በኋላ መሥዋዕቷን እግዚአብሔር ተቀበላት። የታችኛዋ ቤተመቅደስ አገልጋዮች የአረጋውያኑን መሥዋዕት እንደተቀበሉ የላይኛዋም ቤተመቅደስ አገልጋዮች የአሮጌይቱን ዓለም ልጆች መሥዋዕት ተቀብለው ማሳረግ ጀመሩ። ራዕ 8÷3

ያረጁ ሆነው ሳሉ እናት እና አባቷ ተስፋ ሳይቆርጡ ለመኑ፤ በእድሜ ለገፉት ዓለማችን የተሰጠች ብቸኛዋን የተስፋ ፍጻሜ እስኪያገኙ በተስፋ ጸኑ። አንድ ቀን እግዚአብሔር በሌላ በኩልም አይደል በማሕጸናቸው

40. ተአምረ ማርያም

ፍሬ ነውራቸውን ከላያቸው እንደሚያንከባልል በማመን ተማጸኑ። ይሄ ደጅ ጥናታቸው በሰማይና በምድር፣ በሲኦል እና በመቃብር ለነበሩ ነፍሳት ሁሉ መልስ አስገኝቷል።

እኒህ ፍጡራን ለብዙ ዘመናት ደጅ የጠኑትን ጌታ የምትወልድላቸው አምላያ የሌላት አንዲቷን ድንግል በነሐሴ በሰባት ቀን እንደ ምትጸነስ በሱባዔያቸው ወቅት ራእይ አይተው ነበር፤ ፀዓዳ ርግብ ሰባቱን ሰማያት ሰንጥቃ መጥታ በሐና ማሕጸን ስትቀመጥ ለእርሷ ኢያቄም ራእይ አይቶላት ነበር፤ ይህም ኃጢአት ላመከነው ዓለም እመቤታችን እግዚአብሔራዊ ስጦታ ሆና የተሰጠች መሆኗን ያሳያል። ሰማያዊ ምሥጢር የሚገልጥባት ናትና ከሰባቱ ሰማያት ስትመጣ በራእይ ታየች በሌላ መንገድ በተፈጥሮዋ ምድራዊት ሴት ብትሆንም በክብር ከሁሉ የተለየች መሆኗን የሚገልጽ ራእይ ነው በእናቷ በሐና ዘንድም በራእይ ከደጃቸው ሎሚ ለምልማ አብባ አፍርታ ታይታለች፤ በዚያችው ሌሊት ለፍጥረት ሁሉ መንፈሳዊ ምግብ የሚሆን የሕይወት ፍሬ የኢየሱስ ክርስቶስ እናት የጽድቅ ተክል እመቤታችን በብሥራተ መልአክ ተጸነሰች[41]፤ ለእስራኤል የሚበላውን የሚጠጣውን ያስገኘችው ምድራዊት ርስት ሊያወርሳቸው በመላኩ መሪነት ነበር ዛሬ ደግሞ ለእስራኤል ዘነፍስ ለእኛ የሚበላውን የሚጠጣውን ያስገኘችልን እመቤታችን በመላኩ ብሥራት ተጸነሰች። እናት እና አባቷ መንፈሳዊ ተድላ ደስታን አደረጉ። ከቀደመው ይልቅ አብዝተው ጾሙ ጸለዩ፤ ድሃች ሳሉ አልናቃቸውምና የልባቸውንም መሻት ፈጽሚልና።

ከሰው ዘር ብትወለድም በሕገ መላእክት የምትኖር እኅተ መላእክት እመቤታችንን በጾም እና በጸሎት ተቀበሏት። የእመቤታችን ምሳሌ የሆነችው አሪትን ሲቀበል ሙሴ በዚህ ዓይነት ሥርዓት መቀበሉን

41. ገድለ ሐና

የዲያቆናት አለቃ እስጢፋኖስ ይመሰክራል፡ ሥራ 7፥53 አማናዊቷ የእግዚአብሔር ሕግ የተጻፈባት የኪዳን ጽላት እመቤታችንም በሕገ መላእክት፣ በሰማያዊ ሥርዓት ወደ ዓለም መጣች ፤

ከተቀደሰው ጋብቻ የተገኘችው የሐናና የኢያቄም ፍሬ በማሕጸንም ሳለች ታላቅነቷን የሚመሰክሩ ታላላቅ ሥራዎችን ሠርታለች። ለዕውራን ብርሃንን የሰጠችው፣ ለሰለሉ እጆች ብርታትን ያደለችው ገና በማሕጸን ሳለች ነው። ገና ስትጸነስ ጀምሮ ቅድስት መሆኗን ልብ ይሏል፤ ከዚያም አልፋ ሐና እርሷን በማሕጸኗ ተሸክማ ጥላዋን ከጣለችባቸው መታን ሳይቀር ይነሣሉ[42]፤

የሞተውን ዓለም ሞትን ገድሎ ከሞት ግዞት ነጻ የሚያወጣን ጌታ ከእርሷ የሚወለድ ነውና መታንን በማሕጸን ሳለች ታነሣ ነበር። የሰው ልጆች የትንሣኤ ዘመን የደረሰ መሆኑን ለመመስከር ነው ስትሄድ ሞት ከመታን ተለይቶ ይሸሸላታል፤ መታን ከእንቅልፍ እንደሚነቃ ነቅተው በማሕጸን- ሐና ሳለች ያወድሷታል፤ ይሄን የተመለከተው ሰይጣን ግን ዝም አላለም፤ መቼ እንደሆነ ጊዜውን አያውቅም እንጂ የሚረታበት ጊዜ መኖሩን ያውቃልና ገና ሳትወለድ ይሄን ካደረገች ስትወለድስ ምን ትሆን? ብሎ በመሰጋት ሰልፍ ጀመረ፤ ሠራዊቱን አይሁድን ለሰልፍ አስከትቶ በእናትና በአባቷ ላይ ጠላትነትን አስነሣ ፤ ገና በማሕጸን ሆና ለሰይጣን አልተመቸችውም፤ ገና ወደ ዓለም ሳትመጣ አስደነገጠችው፤ እውነት ነው! ይሄ ከፍጡራን ለማን ተደርጐለታል በታላቁ መጽሐፍ እንደተነገረ ከማሕጸን ሳሉ የተመረጡ ነበሩ ኤር 1፥5 በማሕጸን ሳሉ በሞት የተከደኑ ዓይኖችን የከፈቱ፣ በሞት የታሰረ አንደበትን ያናገሩ ሰዎች ግን የሉም ፤የዛሬው ጽንስ ሰይጣንን ያስደነገጠው በዚህ ነው፤ ገና በማሕጸን የሚሳነው ነገር

42. ዝኒ ከማሁ

የሌለ ፤ከሙታን አንደበት ዝማሬን የተቀበለ ይህ ጽንስ እንደምን ያለ ነው?

የመጀመሪያው ሰው በእናት ማሕጸን በምትመሰለው በገነት ውስጥ ሲኖር ሳለ ነበር የሰይጣን ዓይኖች በክፋት ወደ እርሱ የተወረወሩት፤ በገነት በነበረው ሰው ውጤትን እንዳገኘ በዚህም የሚያገኝ ስለመሰለው ሰይጣን ጦሩን ሰበቀ፤ የክፋት ዓይኑን አጮረጠረጠ፤ የሁላችንን አባት በእባብ አድሮ እንደተዋጋው የጦር መላውን ቀይሮ በሰዎች ልቡና አድሮ የሁላችንን እናት ዳግማዊት ሔዋን ድንግልን መዋጋት ጀመረ፤ ግን አልቻለም።

መጀመሪያም በክንፉ ላይ ስሎ ለመላእክት ሲገልጣት የጠባቂነት መዓርግን መስጠቱ ነበርና ከማሕጸን ጀምሮ እንዲጠብቃት አደራ በተሰጠው መላክ በኩል እንደተናገረው በዘመድ የከበሩ ቢሆኑም ቅሉ ለምትወለደዋ ሕጻን ዘመዶቿ የሰማይ መላእክት ናቸውና በእነርሱ ተከባ ወደ ምትወለድበት ስፍራ እንዲሄዱ ተነገራቸው፤

እርሷ ከዓለም አይደለችምና በመወለዷ በቤት ውስጥ የነበሩ ሰዎች ዓለማዊ ተድላ ደስታን እንዳያደርጉ በመንፈሳውያን ዘመዶቿ በመላእክት ታጅባ ከቤት ወጣች። ከቤቱ ወጥቶ፤ ሕገ እግዚአብሔርን ስቶ የነበረ አዳምን የሚፈልግ ጌታ እናቱ ናትና ከቤት ወጥታ ቀድሞ አባቶቿ ነቢያት እሷን በራእይ ወደ ተመለከቱበት ታላቅ ስፍራ ወደ ሊባኖስ ተራራ ተጓዘች። በሊባኖስ ተራሮች ጉያ ሥር በአንበሶች ጉድጓድ እንደምትወለድ ትንቢት የተነገረላት የሊባኖስ ሙሽራ እርሷ ናትና።

ከግሩማኑ አንብስት ከነዳዊት ከነሰሎሞን ፤ከታላላቁ ተራሮች ከነ አብርሃም ፤ይስሐቅ፤ ያዕቆብ አብራክ የተገኘችው እመቤታችን በዚህ

ሰው በማይኖርበት ስፍራ ልትወለድ ተወሰነ። በዚያው ሳሉ ክብሯ ከአድባራት ሁሉ በላይ የሆነ ከቀደሙትም ከኋለኞችም በላይ ስሟ የገነነ፤ ከፀሐይ ይልቅ የምትደምቅ እመቤታችን በግንቦት አንድ ቀን ተወለደች ፤

እሷ የሁሉም ፍጥረት ናት እንጅ የሐናና የኢያቄም ብቻ ባለመሆኗ በአንድ ሰው ቤት ውስጥ እንዳትወለድ መንፈስ ቅዱስ ከለከለ፤ በዚህ ዕለት ታዲያ ዕፀዋት ያለ ጊዜአቸው ለምልመዋል አፍርተዋል። ድንጋዮች ጎብስት ሆነዋል የክረምቱ ወራት አልፎ የበረከቱ ዘመን ቀርቦ የሰው ዘሮች የጽድቅ ፍሬ የሚያፈሩበት፤ ክርስቶስ ጎብስት ሰማያዊ ሆኖ ለዓለም የሚሰጥበት ዘመን ደርሷልና ይሄ ምልክት ታየ፤ ከሰማይ ልደቷን ለማክበር ብዙ የሰማይ ሠራዊት ተልከው ወደ ምድር መጥተው ነበርና አካባቢው በበጎ መዓዛ ተሞላ፤ የምድር መዓዛ በሰማያውያን መዓዛ ተተካ፤ አዲሲቷ ሕፃን ድንግል ማርያም አባቷ ኢያቄም ከሠራው ዳስ መሳይ ነገር በላይ የመላከ ውቃቤዋ የቅዱስ ሚካኤል፤ የመላከ ብሥራቷ የቅዱስ ገብርኤል ክንፍ በላይዋ ላይ ተዘርግቶላት ነበር የተወለደችው ።

የስደተኛ ስንቁ ይህ ነውና ለአራሲቱ ሐና የቀረበላት ምግብ ንፍሮ ነበርና ዛሬም በሀገራችን በዚህች ቀን ምእመናኑ ንፍሮ አቅርበው ፤ከቤት ወጥተው በዓለ ልደቷን ያከብራሉ።

የእናት እና አባት ቤት

እግዚአብሔር ለወዳጆቹ ምድረ በዳውንም ለመጠለያነት እንደሚያውለው በእመቤታችን ልደት ተረጋግጧል። ከስደቶች ሁሉ አስከፊው ስደት የትኛው ነው ካላችሁኝ የነፍስ ጡሮችና የሚያጠቡ ሴቶች ስደት ነው።
ማቴ 24÷19

በእመቤታችን እናት እና አባት ላይ የደረሰውም የስደት ዓይነት ይሄው ነበር፤ እነርሱ ግን በእርሷ መወለድ ነውራቸው ተወግዷልና ሁሉን ረስተው በሊባኖስ ተራሮች ጉያ ውስጥ ሆነው ፈጣሪያቸውን አመሰገኑ፤ የፍጥረት ሁሉ ሐዘን የሚወገድባት አንዲቷ የማሕጸናቸው ፍሬ ሐዘናቸውን አስረሳችላቸው፤ የትውልዱ እንባ የሚታበስባት እርሷ እንባቸውን ከዓይናቸው አበሰችላቸው ፤

ለእስራኤል በሥጋ የመዳን ምክንያት የሆነው ታላቁ ሙሴ የተወለደበትን ዘመን ስንመለከተው ከእመቤታችን ጋር በጥቂቱም ቢሆን ይገናኛል። ያኛው የልደት ዘመን እጅግ የመከራ ዘመን ነበር ዘፀ 1÷22 ለእስራኤል ዘነፍስ ለእኛ የድኅነት ምክንያት የሆነችው እመቤታችንም በተወለደችበት ዘመን ከቤት ውጭ እስከ መጣል ደርሳ የምናየው ታላቅ ፈተና አለባት። እግዚአብሔር ግን ይሄን ለበጎ አድርጐታል ፤እርሷ ስደተኞቹ አዳም እና ሔዋን ሊድኑባት የተዘጋጀች የእግዚአብሔር መሳሪያ ናትና ከቤት ውጭ እንድትወለድ አደረጋት፤ የመጀመሪያዎቹ እናት እና አባቷ በምድረ በዳ ተጥለዋልና ሐናና ኢያቄምም ይዘዋት ተሰደዱ፤ አዳምና ሔዋን በተስፋ ፤ ኢያቄምና ሐና ግን በይፋ ሁለቱም ከቤታቸው ሲወጡ እርሷን ይዘው ወጡ፤በእርሷ ምክንያት ሐዘናቸውን ረሱ፤

በዚህም የቅዱሳን ማደሪያቸው ከእርሷ የሚወለደው አምላክ እንጂ ሌላ ማደሪያ እንደሌላቸው ታወቀ ተረዳ፤ ይህንንም ይዘው ከእርሷ በኋላ የተነሡ ባሕታውያን በእርሱ ይኖራሉ፤ ለሚጠይቋቸው ሁሉ "ኢትሕዝን ኦ! እጉየ በእንተ ዘአልብክ ቤት ወምጽላል" ወንድሜ! የምጠጋበት ቤት ስለሌለኝ ብለህ አትዘን ሲሉ ይመልሳሉ። ፍጥረትን አንድ አድርጎ የሚይዝ ነገር ግን በሰው እጅ ያልተሠራ ቤት ነው

እግዚአብሔር። በበረሐ ያሉ ወዳጆቹ በእርሱ ተጠልለው ይኖራሉ፤ ለእመቤታችንም የተደረገላት ይሄው ነው።

ሰው ቤት ከሚለው የተለየ ሰውን እንደ ቤት ገመናውን ሸፍኖ ፤ከቶ የሚያኖር ሌላ ቤት ያለ መሆኑን በመወለጃዋ ቀን አስረድታለች ፤ይሄ ተደርጎ ስድስት ቀን ሲሆናት በእናቷ ጀርባ ሆና ወደ እናትና አባቷ ቤት ተመለሰች፤ በማሕጸን ሳለች ተሰደደች፤ በእናቷ ጀርባ ሆና በስድስተኛው ቀን ደግሞ ወደ ቤት ተመለሰች።

አባታችን አዳም በገነት ሲኖር በማሕጸን እንደተወሰነ ሕጻን ነበር፤ በዚያውም ሳለ ስደት ደረሰበት። እግዚአብሔር የቀጠረውን ቀን ደርሶ በስድስተኛው ምዕተ ዓመት ዳግም እንደገና ‹‹አንተ አቡነ ወአንተ እምነ›› በሚባለው ጌታ ትክሻ ላይ ሆኖ ወደ ቀደመ ቦታውና ክብሩ ተመለሰ።

የሚገርመው ነገር ከመወለዷ አስቀድሞ ነፍስ እና ሥጋን የሚለይ ጩኸት እየጮሁ በድንጋይ ሊወግሯት፤ በእሳትም ሊያቃጥሏት የነበሩ ክፋዎች አይሁድ ወደ ቤት በእናቷ እቅፍ ስትገባ የተናገረ አልነበረም። እንዲያውም የቅርብ ዘመዶቻቸውና የሚያውቋአቸው ሰዎች በደስታ ተቀበሏቸው። በእርጅና ዘመናቸው ልጅ አግኝተዋልና ብለው፤
ሲጀመርም የአይሁድን ቁጣ የቀሰቀሰው እግዚአብሔር የነቢያት ትንቢታቸው እንዲፈጽምላቸው እንጂ እንዲያው በከንቱ ነውን?በምድረ በዳ በመወለዷ የዓለምን ምድረ በዳነት፤ ማረፊያ በሌለው ቦታ ተወልዳ የዓለማችንን ማረፊያ የሌላት መሆኑን እግዚአብሔር በድንግሊቱ ልደት ሊገልጠው ወዶ የአይሁድን ቁጣ ቀስቅሶታል፤ እውነት ነው !

የብርሃን እናቱ እመቤታችን የብርሃን ድንኳን ተተክሎላት የሚያንጸባርቅ የእሳት ዛኒጋባ ተጥሎላት ትወለዳለች እንጂ ሰው በሠራው ቤት እንደምን ትወለድ? ይህ እግዚአብሔር ብቻ የሚያውቀው ልዩ ምሥጢር ነበር፤ ይህ እስኪፈጸም እንደ ጢስ ምድርን የከደነው የአይሁድ ቍጣ ሁሉም የእግዚአብሔር ፈቃድ ከተፈጸመ በኋላ ግን ፀሐይ እንደተቆጣው ቅቤ የደረሰበት ጠፋ፤

እናትና አባቷ እርሷን በመውለዳቸው ከእርጅናቸው ታድሰው፣ ወደ ወጣትነት እድሜአቸው ተመልሰው፣ ዳግም እርሷን ከበው ተመለሱ አባ ሕርያቆስ በቅዳሴው እንደተናገረው ከፍጥረታት በፊት የተፈጠረው አባታችንን ጨምሮ ሁሉም የሰው ዘር የሚታደስባት የአሮጌው ዓለም መታደሻ ናትና ጌታ ከእርሷ የነሣውን ሥጋና ደም ተቀብለን፣ በልባችን መታደስ እየተለወጥን አዲስ ፍጥረት የምንሆነው፣ ወደ እመቤታችን ገነትነት የምንገባው በእርሷ በኩል በሚፈጸመው ምሥጢረ- ተዋሕዶ ነውና አስቀድማ በተወለደችበት ዕለት የእናት እና አባቷን እርጅና አስወገደች፤ በድካም፣ በምሬትና በሐዘን፣ በብዙ የአይሁድ ማስፈራራትና ግፊት ከቤታቸው ወጡ፣ አሁን ግን ሲመለሱ በብርታት፣ በመታደስ፣ በሞገስ በብዙ ተድላ ደስታ ነው።

ቀደምቶቹ እናትና አባቷ አዳም እና ሔዋንም ከቤታቸው ገነት ሲወጡ በድካም፣ በመሪር ሐዘን እንደ ሳማ በሚለበልብ ቍጡ እንባ፣ ከግሩማን መላእክት ቅያሞት የተነሣ በተመዘዘውም የቍጣ ሰይፍ ጽኑ ፍርሀትና መንቀጥቀጥ ደርሶባቸው ነበር። በእርሷ ላይ ከተደረገውም የማይመረመር የማስታረቅ ምሥጢር ምክንያት በለቅሶ የዘሩትን በደስታ አጭደውታል። በፍርሀትና በምሬት የተሰናበቱት ገነት ቤታቸውን በደስታ ተመልሰውበታል ፣እየገፉ፣ እየተቆጡ ያስወጧቸው

መላእክት እያጨበጨቡ ተቀበሏቸው፤ ይሄ ሁሉ ትዕይንት ግን አስቀድሞ በልደቷ ተደረገ።

እንግዲህ ከዚህች ቀን ጀምራ መንፈስ ቅዱስ ለተለየችለት ሥራ ወደ ቤተ- መቅደስ እስከ ወሰዳት ቀን ድረስ በእናት እና በአባቷ ቤት ተቀመጠች። በየቀኑ ብዙ የሰማይ ሠራዊት መጥተው ይጐበኙት እንደ ነበርም የልደቷን ዜና የሚናገሩ መጻሕፍት ምስክሮቻችን ናቸው። አንዳንድ ቀን መላእክት በክንፎቻቸው ጋርደው ወደ ላይ ነጥቀው ያጫውቷት ስለ ነበር ከፊቷ ስለምትሰወርባት እናቷ ሐና ትጨነቅ ነበር፤ የእርሷ እንዳልሆነች ፣የእግዚአብሔር ገንዘብ እንደሆነች ጠንቅቃ ብታውቅም ለዘመናት የነበረባት የልጅ ፍቅር እስኪወገድላት ለፍቅሯ ትሳሳ ነበርና ካይኗ ስትሰወር ትጨነቃለች።

በዚህ ወራት ነው እግዲህ የመወለዷን ዜና የሰሙ ሁሉ እየመጡ ከደም ግባቷ የተነሣ የተደነቁባት፤ በስተ እርጅና ለወለደችው ሐናም ዘመዶቿ ሁሉ ከቅርብና ከሩቅ እየመጡ የመውለጃሽ ወራት ካለፈ በኋላ ባንቺ የተደረገ ይህ ነገር ምንድን ነው? እያሉ ይጠይቋት ነበር፤ በዘመናቸው የነበሩት ሁሉ ዘር ካጡ፣ ተስፋ ከቆረጡ በኋላ እግዚአብሔር ለሰው ዘርን መስጠት የሚችል አምላክ መሆኑን አወቁ፤ ለብዙዎች የመዳን ተስፋን ፈነጠቀላቸው፤ በእጇ ታምራት ይደረግ ነበርና ፤

እግዚአብሔር ፈጽሞ እንዳልተለያቸው ተረድተው ስለ እርሷ አመሰገኑ ከሐና ማሕጸን ከሚፈልቀው መድኃኒት የተነሣ ሕመማቸው ተፈወሰ፤ ይሄ ሁሉ ሲሆን ግን በነቢያት ትንቢት የተነገረላት እርሷ መሆኗን ከመንፈስ ቅዱስ በቀር ያወቀ አልነበረም፤ ይህ ምሥጢር ለሰው የሚገለጥበት ዘመን ገና ነበርና። አስቀድሞ ተገልጦ ቢሆንስ ኖሮ

ዲያብሎስ እጅግ አድርጎ በተዋጋቸው፣ ከሀገር ወደ ሀገር ባሳደዳቸውም ነበርና ስለ ዲያብሎስ ሲባል ምሥጢሩ ከሰው ልጆች የተሰወረ ሆነ፤ እስከ ሦስት ዓመታት ድረስ እንዲህ ተደረገ።

ከሦስት ዓመት በኃላ

ይህ ጊዜ ለሕፃናት የተለየ የሽግግር ወቅት መሆኑን የሚከራከረኝ የለም። ሕፃናት የእናት ጡት የሚተውበት፣ ከሌላ መብል ጋር የሚለማመዱበት፣ በኮልታፋ አንደበት አበ፣ እመ እያሉ ለእናት እና አባት ደስታን የሚፈጥሩበት ልዩ ዘመን ነው። በሕገ ተፈጥሮ ለእመቤታችንም ይህ ሊደረግላት ባለበት ዘመን አፏ እህል ሳይለምድ፣ ሆዷም ዘመድ ሳይወድ ከመጸነሷ በፊት በገቡት ቃል መሠረት ወስደው ለቤተ እግዚአብሔር ሰጡ፤ ምግቧ ሰማያዊ፣ ዘመዶቿም ሰማያውያን መላእክት ናቸውና ብለው ምድራዊ መብል መጠጥ ከሚቀርብበት፣ ምድራውያን ወገኖቿ ከሚገኙበት ምድራዊ ቤት አውጥተው ለሰማያዊ አምላክ ቤት አደራ ሰጧት።

እኅትና ወንድም አልነበራትም፤ ዓለማችን እሷን የሚመስል በጐ ፍጥረት ማስገኘት የማትችል መካን ሴት ናትና ከፍጥረት ሁሉ ተለይታ ንጹሕ ዘርን በምድር ላይ ለማባዛት የተፈጠረች ብቸኛ ዘር ናትና ተለይታ ተቀመጠች። አመስጋኞች እነ ቅዱስ ኤፍሬም " ወአልቦ ዘይመስል ኪያኪ." አንቺን የሚመስል የለም ማለታቸውም ለዚህ ነው። ሐናና ኢያቄም አንድ ሆና ሳለ የፍጥረት ሁሉ እናት የሆነች እርሷን ከመውለዳቸው አስቀድሞ፣ ከወለዷትም በኋላ ሌላ አልወለዱም፤ መንፈስ ቅዱስ ስለ እርሷ በነቢያት የተናገረው እንዲፈጸም ይህ ሆነ፣ ተደረገ " አሐቲ ይእቲ ለእማ ወጎሪት ይእቲ ለእንተ ወለደታ

ለእናቷ አንዲት ናት ለወለደቻትም የተመረጠች ናት፡መኃ 6፥9 ተብሎ የተነገረው ስለ እርሷ ነውና። ለእናቷ ሲል እናቷ የተባለች ሔዋን፣ ለወለደቻት ሲልም ስለ ሐና መናገሩን ልብ ይሏል፤

እመቤታችን አንዲትነቷ ለሔዋን ነው፤ ከወለደቻቸው ልጆቿ ሁሉ የጌታችን እናት ሆና የተገኘች እና የሔዋን መድኃኒት የተሰኘች ከእመቤታችን በቀር ሌላ ሴት አትገኝምና፤ እስካሁንም ሆነ ከዚህ በኋላ ብቻዋን አንዲት ሆና ለዘለዓለም ጸንታ ትኖራለች፤

በዘመናት ሂደት እንደተመለከትነው መንታ- መንታውን እያደረጉ ብዙ ቁጥር ያላቸውን ልጆች የወለዱ ሴቶች ትናንትና በምድራችን ላይ ነበሩ፤ ምድር እንድትሞላ በፍጥረት ከድነዋታል እንጅ እንደ እመቤታችን የከበረ ፍጥረት ማስገኘት አልቻሉም፤ ስለዚህም በየጊዜው የሚነሣው ትውልድ ሁሉ እርሷን ብቻ ብፅዕት ሲል ይኖራል።

ሰው እንደ ሃይማኖቱ ነው እንጂ ብዙ ወልደው ያልተባረከላቸው ፣አንድ ወልደው ደግሞ እንዲህ የተደረገላቸውን ስንመለከት እግዚአብሔር ካልባረከው የሚጠቅም ነገር እንደሌለ እንመለከታለን።

ሰው ሆይ! እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር ያለ አንዳች ጸጋ አይፈጥረውምና ብዙ ጸጋ እንዲሰጥህ ከምትለምን የሰጠህን አንዱን እንዲባርክልህ ብትጸልይ ይሻልሃል። ብዙ ጸጋ የነበራቸው ነገር ግን አልባረክላቸው ብሎ ብዙ ጸጋቸውን ብዙው ነውራቸው የሸፈነባቸው ሰዎች ብዙ ናቸውና። *ይህችን ዓለም በተባረከ ነገር እንጅ በብዙ ነገር ማሸነፍ እንደማይቻል ከነዳዊት፣ ከነጌዖን የጦርነት ታሪክ መረዳት የሚቻል ይመስለኛል።* መሳ 7፥71 ሳሙ 17፥49 በጠላት

ሰልፍ ይዘናት የምንሰለፍ የጦር ዕቃችን፣ ጎልያድ ዲያብሎስን የምንገድልበትን ድንጋይ ይዛ የተገኘችልን አንዲቷና አማናዊቷ የዳዊት ወንጭፍ እመቤታችን አንዲት ብትሆንም ለዛሬው ሰልፍ በቂ ናት። የተወለደችው ፍጥረት ሁሉ ሊደሰትባት እንጂ ለአንድ ቤተሰብ ለዳዊት ቤት ብቻ አልነበረምና የሁሉ ወደሆነው ወደ እግዚአብሔር ቤት እንዲወስዷት መንፈስ ቅዱስ አሳሰባቸው።

ከላይም እንደጠቀስነው ዘመኑ ከተወለደች ሦስተኛ ዓመቷ እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ይናገራሉ። ይህ ሦስት ዓመት በሦስቱ ክፍላተ አዝማን ይመሰላል። በዘመነ ሕገ ልቡና፣ በዘመነ አሪት እና በዘመነ ወንጌል። እመቤታችን በሦስተኛው ዓመት ወደ ቤተ መቅደስ መምጣቷ ታዲያ ሦስተኛው ክፍለ ዘመን ዘመነ ሕገ ወንጌል የሚባለው ዘመን ሰው የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ሆኖ የሚሠራበት ዘመን ነውና፣ ሰውና እግዚአብሔር አብረው የሚኖሩበት መልካም ዘመን የደረሰ መሆኑን ለመግለጽ፣ የመጀመሪያዋም የሐዲስ ኪዳኑን ቍርባን ይዛ የተገኘች ቤተመቅደስ እርሷ በመሆኗ አስቀድማ በዚህ እድሜዋ ወደ ቤተ መቅደስ ገባች።

ከእርሷ በፊት ወደ ቤተ መቅደስ የገቡ ሰዎች መኖራቸው አይዘነጋም 1 ሳሙ 1፥28 ያና ይሄ ግን በእጅጉ የተለያየ ነበር። የእመቤታችን ወደ ቤተ መቅደስ መግባትኮ የፍጥረትን ሁሉ ወደ ሰማይ ቤተ መቅደስ መግባት የሚያመለክት በመሆኑ በወቅቱ የነበሩ ሰዎችን ሁሉ ያስጨነቀ ጉዳይ ነበር። ከሊቀ ካህን እስከ ደብተራ አሪት ሌዋውያን፣ ከአዕሩገ እስራኤል እስከ ወራዙተ እስራኤል የነበሩ ሁሉ የምግቧን ነገር ሲማከሩ መገኘታቸው ለዚህ ማሳያ ነው።

በዚህ የካህናትና ሽማግሌዎች ጉባኤ በእውነት መንፈስ ቅዱስ ምን ሊናገር የፈለገ ይመስልሃል? እነዚህ ካህናት ስለ አንዲቷ ብላቴና ምድራዊ መብል እና መጠጥ የሚነጋገሩ ይመስልሃልን? አይደለም። ለፍጥረት ሁሉ ስለሚያስፈልገው፣ ዘለዓለማዊ ረሐብን ከሰው ሊያስወግድ ስለሚችለው ሰማያዊ መብልና መጠጥ ተነጋግረዋል እንጂ። ስለ እርሷማ ቢሆን ኖሮ ጭንቀታቸው፣ ከዚህ ሁሉ ሳይደርሱ የሦስት ዓመት ብላቴና ናትና ያለ እናት እንዴት እናኖራታለን? የሚለው የመጀመሪያው ጥያቄ ባልሆነ ነበርን? እኒህ ሰዎች ብላቴናዋን እግዚአብሔር ያለ እናት ያኖራታል ብለው ካመኑ በምግቧ ጉዳይ እንደምን አላመኑ?

እናምናለን! ስለ ዘለዓለማዊው መብል እና መጠጥ ለራሳቸው መክረዋል፣ ወዲያው ለጉባኤው አስቸኳይ መልስ ከሰማዩ አባት ተሰጠ፣ ሰማያዊው መብልና መጠጥ ከእርሷ የሚገኝ መሆኑን ጠቀሜሞ እንደማሳየት መላኩ ፋኑኤል ሰማያዊ መብል እና መጠጥ ይዞ በሰማይ ላይ ረቦ ታየ። ፋኑኤል ማለት ፀዋሬ መና ማለት ሲሆን እመቤታችንም ፀዋሪተ መና ሰማያዊ መሆኗን ለማመልከት በዚህ መላክ በኩል እግዚአብሔር መናውን እንደላከላት ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን ያመሠጥራሉ።

መላኩም መናውን ይዞ፣ እንደ ደመና ረቦ ታየ እንጂ ለጊዜው ወደ ምድር አላወረደውም ነበር። ምክንያቱም ሰማያዊው መና ክርስቶስ ለዓለም የሚሰጥበት ጊዜው ቀርቧል እንጂ አልደረሰምና፣ መና ከሰማይ ሲወርድ በምድራችን ላይ የመጀመሪያው እንዳልሆነ መጻሕፍትን የሚያገላብጡ አዕምሮ ያላቸው ሰዎች ያውቁታል። በቀደመው ዘመን ከግብጽ ለኮበለለው ታላቅ ሕዝብ ይህ ተደርጐለታልና። ዘፀ 16፥15 ይሄ ግን ከዚያ ልዩ ነው፣ ያኛው በቀን ያይደለ በማታ፣ በኢየሩሳሌም

ያይደለ በምድረ በዳ፣ አመጣጡ ከወዴት እንደሆነ ሳይታወቅ በማለዳ ከፀሐይ መውጣት በፊት የሚለቀም፣ በሁሉም እስራኤላዊ ድንኳን ደጃፍ ላይ የሚገኝ የሰማይ ፍርፋሪ ነበር፤ ይሄኛው ግን በመላኩ እጅ ከሰማይ ሲወርድ የታየ፣ ከእርሷ በስተቀር ማንም ሊቀምሰው ያልተፈቀደለት ስለ ክብረ ድንግል በንጹሕ መሶብ- ወርቅና በንጹሕ ጽዋ ተዘጋጅቶ የመጣ ነው።

ክብሯ ልዩ ነው፤ ሲል ከሰው ለይቶ፣ ወደ ሰማይ አውጥቶ፣ በምድርና በሰማይ መካከል አድርጐ፣ በክንፍ ጋርዶ መግቧት አርጓል። ለጊዜው የምግቧን ሰማያዊነት መናገሩ ሲሆን ፍጻሜው ግን ምድራዊው ሰማያዊ፣ ሰማያዊውም ምድራዊ የሚሆነው ባንቺ ነው ሲላት ነው፤ ይህንን የመላኩን ሐሳብ መንፈስ ቅዱስ ሲገልጸው "ሰማይኒ ኮነ ዓለመ-ወዓለምኒ ኮነ ሰማየ፤ ሰማይ ምድርን ሆነ ምድርም ሰማይን ሆነ[44]" ብሎ አናግሮታል ይህም ማለት አምላክ ሰው ሆነ፣ ሰው አምላክ ሆነ ማለት ነው። የዚህ ምሥጢር ፍጻሜ ከመታየቱ አስቀድሞ መላኩን ልኮ ሰማያዊ መብልና መጠጥን ማዕከለ ሰማይ ወምድር አድርጐ መገባት።

ከዚህች ጊዜ ጀምሮ ምድራዊ መብል መጠጥን እየተመገበች ያደገች አይደለችም ሰማያዊ መብልና መጠጥን ተመገበች እንጂ። ሊቁ አባ ሕርያቆስ እንደተናገረው " አ!ድንግል አኮ ጎበስተ ምድራዌ ዘተሴሰይኪ አላ ጎበስተ ሰማያዌ እምሰማየ ሰማያት ዘበሰለ አ! ድንግል አኮ ስቴ ምድራዌ ዘሰተይኪ አላ ስቴ ሰማያዌ እምሰማየ ሰማያት ዘተቀድሐ ፣ድንግል ምድራዊ መብል መጠጥን እየተመገብሽ ያደግሽ አይደለሽም ሰማያዊ መብል መጠጥን ተመገብሽ እንጂ›› ሲል ይቀኝላታል፤

44. ሃዶ አባ ዘዘርዝርዮስ

በሌላ በኩል ኢትዮጵያዊው ሊቅ ‹‹የምታውቀው ሳይሆን የማታውቀው ሌላ መላክ መጣ፤ ቀኝ ክንፉን ቢባርከው ጎብስት ሆነ፤ ግራ ክንፉን ቢባርከው ወይን ሆነ ›› በማለት መላክ የተባለው ቅዱስ ፋኑኤል ሳይሆን ክርስቶስ እንደሆነ ይተረጉማል።(ዝማሬ)

ከዚህ በኋላ እናትና አባቷ፣ ካህናቱና ሽማግሌዎችም ጭምር ተለይተዋት ሄዱ፤ በዚህ ጊዜ አባቷ ዲዊት ከአንድ ሺህ ዓመት በፊት የመከራትን በጐ ምክር ተግባራዊ አደረገች፤ ንጉሡ ዳዊት ይህን ቀን አስቀድሞ አይቶት ኖሮ ለሦስት ዓመታ ብሉቴና ምክርን ይለግሳታል። "ስምዒ ወለትየ ወርእዪ ወአጽምኢ እዝነኪ ርስኢ ሕዝበኪ ወቤተ አቡኪ እስመ ፈተወ ንጉሥ ሥነኪ " ልጀ ሆይ ስሚኝ፣ አድምጭኝም፣ የአባትሽን ቤትና ወገኖችሽንም እርሺ ንጉሥ ውበትሽን ወዷልና መዝ 44፥10

በዚች ዕለት ለቤተ እግዚአብሔር ሰጥተዋት ሲሄዱ እናትና አባቷን፣ ምድራውያን ዘመዶቿንም ሁሉ ተወች፤ እናትና አባት እግዚአብሔርን፣ ዘመድ እና ወገን መላእክትን አድርጋለችና። እናትና አባቷም ለእግዚአብሔር ሰጥተዋታልና እንደ ሳሙኤል እናት ሐና በየዓመቱ አልጐበኟትም አባ ሕርያቆስ እንደተናገረው መላእክት እና ሊቃነ መላእክት፣ ካህናት እና ሊቃነ ካህናት ጐበኙት እንጂ።

እንዲህ ሆና ከዓለም ርኩሰት ተሰውራ፣ የሚያታልሉ የጕልማሶችን ድምፅ ሳትሰማ በመላእክቱና በካህናቱ ዜማ እየተጽናናች አደገች፤ ዋዛና ፈዛዛ ፣ሳቅና ጨዋታ፣ ዘፈን እና እስክስታ ያልተቀላቀለበት አስተዳደግ አደገች። አስቀድሞ በትንቢት እንደተነገረላት ለአስራ ሁለት ዓመት በቤተ መቅደስ ኖረች፤ የአሮን በትር ለአስራ ሁለት ሰዓት በቤተ መቅደስ መቆየቷ፣ ሳይተክሏትና ውኃ ሳያጠጧት ለምልማ፣ አብባ፣

አፍርታ መገኘቷ እመቤታችን በቤተ መቅደስ አስራ ሁለት ዓመት ለመኖሯ ማሳያ ሆኖ አስቀድሞ በምሳሌአዊ ድርጊት ነበር፤ አማናዊቷ በትረ አሮን ያለዘርዐ ብእሲ በጎቱም ድንግልና ጌታን የወለደችው፣ ለአስራ ሁለት ዓመት በቤተ መቅደስ የቆየችው እመቤታችን ድንግል ማርያም ናት።

በዚያችኛዋ በትረ አሮን፡- አሮንና ወገኖቹ ከሞት እንደዳኑባት በእመቤታችንም ፍጥረትን ሁሉ ከሞት የሚያድነው ፍሬ ሕይወት ጌታ ተገኝቷልና ሊቃውንት እመቤታችንን ሲያመሰግኗት "በትረ አሮን እንተ ሠረፀት ..... " ብለው ያመሰግኗታል። ለጊዜው ይህ ሆኖ ሳለ ፍጻሜውና አማናዊው ምሥጢር ግን ያችኛዋ ለ12ቱ ነገደ እስራኤል ምልክት ሆና ለዘለዓለም በቤተ መቅደስ እንድትኖር እንደተደረገች እመቤታችንም ለ12ቱ ሐዋርያት ምልክታቸው ናት። ነቢዩም ስለ እርሷ ሲናገር " እርሱ እግዚአብሔር ምልክትን ይሰጣችኋል ብሎ የሐዲስ ኪዳኑ ታላቅ ሕዝብ ምልክት እመቤታችን እንደሆነች ይመሰክራል። ኢሳ 7፥14 ዘኍል 21፥1

አስራ ሁለቱ ዓመት ሕገ መላእክትን፣ ሥርዓተ ሰማያዊትን ያጠናችበት፣ ትንቢተ ነቢያትን ያወቀችበት፣ የብዙ መጻሕፍትን ትንቢታዊ ቃል ያነበበችበት ወቅት ነው። በአጠቃላይ ጥበብ ሥጋዊን፣ ጥበብ መንፈሳዊን የተማረችበት ወቅት ይህ ነው ማለት ነው።
ጥበብ ሥጋዊ ማለት ወርቅና ሐር እያስማሙ መፍተል፣ ያን የፈተሉትን ምንጣፍ፣ መጋረጃ አድርጐ ለቤተ እግዚአብሔር መስጠት ነው። ይህ ከቤተ እግዚአብሔር ደጅ ተሰብስበው እግዚአብሔርን ከሚያገለግሉ ከደናግለ እስራኤል የተማረችው ጥበብ ነው።

ጥበብ መንፈሳዊ ማለት ትንቢተ ነቢያትን ፣ምሥጢረ መጻሕፍትን መመርመር ፣ትንቢት የተነገረለት፣ ሱባዔ የተቆጠረለት መሲሕ መጣ ቀረ ብሎ ማውጣት ማውረድ ሲሆን ይሄን ከካህናት አለቆች፣ ከቤተ መቅደሱ አገልጋዮች ተምራለች። ከዚህም ጋር ከሰማያውያኑ መላእክት ቅዳሴን፣ ዝማሬን የተማረችበት ወቅት ነበር፤ ይህም በቀጣይ ሕይወቷ ይታወቃል፤ በጸሎትና በዝማሬ ያሳለፈችው ጊዜ እንደሚበዛ ታሪክ ያስረዳናልና።

በመሆኑም በሕይወቷ ውስጥ ይሄ ዘመን ልዩ ነው። ከእናት እና አባቷ ቤት ከቆየችው ሦስት ዓመት ጋር ሲደመር የአስራ አምስት ዓመት ብላቴና አድርጓታል።

ምዕራፍ ፫

15ኛው ዓመት

በሕግ ጠባይዓዊ በየጥቂቱ ማደግ ግዴታ ነውና በልማደ ፍጥረት እመቤታችን ድንግል ማርያምም አንድ ሁለት ..... እያለች አስራ አምስተኛው ዓመት ላይ ደረሰች፤ የሴቶች ትክክለኛ ጊዜ ማለት ይህ ዘመን ነው፤ ዐቅመ ሔዋን የሚያደርሱበት፣ የሚታጨበት፣ በኋለኛውም ዘመን ከትንሣኤ ሙታን በኋላ በመንግሥተ ሰማያት የሚኖሩበት፣ ለእግዚአብሔር ማደሪያነት የሚታጨበት፣ ከሰማያዊው ንጉሥ ጋር የሚዋሐዱበት ዘመን ነው። እመቤታችንም በዚህ ዘመን ሦስት ዐበይት ቁም ነገሮችን አከናውናለች።

1. ከጠላት ጋር መዋጋት

እስከዚህ ዓመት ድረስ በእመቤታችን ሕይወት ውስጥ የተመዘገበ ከፍተኛ የጦርነት ወቅት የለም፤ አሁን ግን እናቷ ሔዋንን ስታክል ጦርነቱ ተጀመረ፤ ሰይጣን ከሔዋን ጋር ጦርነትን የጀመረው በዚህ እድሜዋ ላይ ሳለች ነበርና። ቀዳሚት ሔዋን በዚህ እድሜዋ ድል እንደተነሣችለት ዳግማዊት ሔዋን እመቤታችንም ድል የምትነሣ መስሎት ጦርነቱን ጀመረው፤

የሁሉ እናት ሔዋንን ራሱን በእባብ ሰውሮ እንደተዋጋት እመቤታችንንም የተዋጋት በካህናተ-አይሁድ፣ በሕዝቡ-አይሁድ ላይ ሆኖ ነበር፤ የመጀመሪያይቱ ሔዋን ጦርነት የተጀመረው በገነት መካከል በቅዱስ ስፍራ ሲሆን፣ ዳግማዊት እመ ሕያዋን ድንግል ማርያምንም ሰይጣን ጦሩን ያነሣባት ገና በመሠዊያው ስፍራ፣ በተቀደሰው ተራራ በቤተ መቅደስ ሳለች ነው።

ምናምንቴ ሰዎችን አሥነሥቶ፣ ከቤተ መቅደስ የመውጣቷን ጉዳይ ለማስፈጸም ደፋ ቀና ማለት የጀመረው ሰይጣን በገነት የነበረችውን ሔዋን ለመጣል የተጨነቀውን ያክል ተጨንቋል፤ በሕዝቡ ጩኸት፣ በካህናቱ ክፋት፣ በጠንቋዮች አስማትና ምትሐት በእግዚአብሔር እጅ የተያዘች ክብርት ሕይወቷን ለማጥፋት በቅጠል ቀዳዳ እየተመለከተ ይከታተላት ነበር።

በ12 ዓመት የቤተ መቅደስ ቆይታዋ ከመላክቱ በሰማችው ስመ እግዚአብሔር ብቻ መጥቁል የተባለውን ጠንቋይ ከተከታዮቹ ሦስት መቶ ሰባ የሚጠጉ አጋንንት ጋር ከምድር በታች እንዲሆኑ ያደረገች መሆኗን በታላቁ ነገረ ማርያም መጽሐፍ ተመዝግቧል።

ሰውን ወደ መቃብር ማውረድን በሴቶች በኩል የጀመረው ጠላታችን ሰይጣን በዛሬዋ ሴት በኩል ደግሞ ራሱ ወደ መቃብር ወረደ፤ በመላእክት ሰይፍ እየታጨዱ የጠፉ አጋንንትም ብዙ ናቸው፤ በታላላቅ ጦርነቶች ድልን የተጐናጸፉ እንደነ ዳቦራ ያሉ ታላላቅ ሴቶችን ታላቁ መጽሐፍ የመዘገበልን ሲሆን መሳ 4፥1 እና 5፥1 በረቂቃኑ የክፋት ሠራዊት ላይ ድልን በመጐናጸፍ ግን እንደ እመቤታችን የተሳካለት የለም፤ ሁሉንም የማሸነፏ ምሥጢር ግን ትዕግሥት ነው፤ በሕማሙ ሁሉ የማይናገረው የትዕግሥት እናቱ ትዕግሥት ድንግል ማርያም ሰይጣንን ያሸነፈችበት መሳሪያ ትዕግሥት ነው።

የቀደመችው ሴት በሰይጣን ለመሸነፏ ምክንያቱ ትዕግሥት አልባነቷ ነበር፤ አዲሲቷ ሔዋን ግን ትዕግሥትን የተጐናጸፈች የትዕግሥት እናት ናትና በሔዋን መቸኮል ምክንያት የተወለደውን ሞት ክንፉን የሚሰብር የዘለዓለም ሕይወትን ወለደች፤ በሕይወት መኖር ለሚታገሡ ሰዎች የተሰጠ ጸጋ ነው።

የሰው ትዕግሥት የሚገለጠው በፈተና ውስጥ ማለፍ ሲችል ነው። የእመቤታችንም ትዕግሥት እስከ ወዲያኛው ለዓለም የተገለጠ ይሆን ዘንድ ሰይጣን በፈተና ላይ ፈተናን እየደራረበ ከቤተ መቅደስ እስኪያስወጣት ደርሶ ተፈታተናት፤ ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ በእርሷ ላይ ሥልጣን የሌለው መሆኑ ይታወቅ ዘንድ ብዙ ጊዜ ጥፋት ያላደረሰባት ቢሆንም ከቤተ መቅደስ ልትወጣ ከሰማይ አምላክ ተወሰነ፤ ከቤተ መቅደስ ስትወጣ እርሷን ግን አማናዊት ቤተ መቅደስ አደረጋት፤ ሰዎቹ የሰው ልጅ የሠራውን ቤተ መቅደስ ሲከለክሏት እግዚአብሔር ግን የማትፈርስ ቤተ መቅደስ አድርጎ ለዘለዓለም ማረፊያ ልትሆነው ሃያውን ዓለማት ፣ሃያ ሁለቱን ሥነ ፍጥረት በሠራባቸው ቅዱሳት እጆቹ ሠራት ፤ያን ጊዜ በነቢይ ስለ እርሷ የተባለው ተፈጸመ "ልዑል ማደሪያውን ቀደሰ፤ እግዚአብሔር በመካከሏ ነውና አትታወክም።

2. <u>መታጨት</u>

ማጨት የነገሮች ሁሉ መቅድም ነው፤ አዳም ሚስቱ ሔዋንን ሚስት ከማድረጉ አስቀድሞ አጫት። "ይህች አጥንት ከአጥንቴ፤ ሥጋዋም ከሥጋዬ ነው፤ ሚስት ትሁነኝ" ዘፍ 2፥23 ዳግማዊ አዳም ኢየሱስ ክርስቶስም ቤተ ክርስቲያንን አካሉ ከማድረጉ በፊት አጫት፤ ለማጫዋ የሚሆን፣ ለክብሯ የሚመጥን ሌላ ዋጋ ባያገኝ የገዛ ደሙን ማጫ አድርጎ ከፈለ። አካሉ ልትሆን በተወሰነበት በዕለተ ስቅለት ዋዜማ ሥጋውን ቆርሶ፤ ደሙን አፍስሶ መስጠቱ ማጨት መቅድመ ነገር በመሆኑ ነው፤

ሙሽራዋ ክርስቶስ ሐዋርያትን ሾማግሌ አድርጎ የማጫ ዋጋውን ሥጋና ደሙን ካቀረበ በኋላ ነው ሙሽራይቱ ቤተ ክርስቲያንን አካሉ

ሊያደርጋት የሚችለውን ማየ-ገቦውን ያፈሰሰላት፤ ከዚህ በኋላ እርሱም " መርዓዊሃ ለቤተ ክርስቲያን" ተብሎ ተጠራ ቤተክርስቲያንም "እርሷም ሁሉን በሁሉ የሚሞላ የእርሱ አካሉና ሙላቱ ናት" ኤፌ 1፥23 ተብላ ተጠርታለች አሁን ቤተክርስቲያን የክርስቶስ ናት፤ ክርስቶስም የቤተ ክርስቲያን ነው።

በዚህ ልማድ እመቤታችን ድንግል ማርያምም በዮሴፍ በኩል ለእግዚአብሔር ማደሪያነት ታጨች፤ ቀደም አድርገን እንደተናገርነው እናቷ ሔዋን የታጨችውና በቀዳማይ አዳም ዘንድ ሞገስን ያገኘችው በዚህ በአስራ አምስተኛው ዓመት እድሜ ላይ ነበር፤ እመቤታችንም የቀና መልክ ከደም ግባት አስተባብራ ይዛ የተገኘች ፍጽምት ሔዋን መሆኗን ለመግለጽ በዚህ እድሜዋ ታጨች፤ በዳግማይ አዳም በክርስቶስ ዘንድ ሞገስን አገኘች።

በዚህ ምክንያት በሥላሴ ዘንድ መወደዷን አወቅን፤ መታጨት አንዱ የመወደድ ምልክት ነውና። ከዚያም ባሻገር ባትታጭ ኖሮ ከሰማይ የወረደች አርያማዊት ኃይል ላለመሆኗ ምን ማስረጃ ይኖረን ነበር?ከእኛ ይልቅ በቀደመው ዘመን ከሰማይ ሥጋን ለብሶ ወረደ እንጂ የኛን ምድራዊ ሥጋ አልተዋሐደም ለሚሉት ሰዎች በተመቻቸው ነበር ፤አሁን ግን ከዳዊት ወገን ለሆነው ለዮሴፍ ስትታጭ በማየታቸው ከአብርሃም ዘር የተወለደች ምድራዊት ሴት እንጂ ሰማያዊ መላክ እንዳልሆነች ታወቀ ተረዳ ማቴ 1፥18 ዕብ 2፥16

ለዮሴፍ መታጨቷ በብዙዎች ዘንድ የመሰናክል ዓለት ሆኖባቸዋል፤ እርሷ ግን በዮሴፍ በኩል የታጨች የእግዚአብሔር ሙሽራ እንጂ፣

ለዮሴፍ የታጨች የዮሴፍ ሙሽራ እንዳልነበረች በዙሪያችን እንደ ደመና የከበቡን ብዙ ምስክሮች አሉን ማኅቶተ- ቤተክርስቲያን ቅዱስ ጳውሎስ በአንድ ወቅት በቆሮንቶስ ላሉ ደቀ መዛሙርቱ ሲጽፍላቸው "እንደ ንጽሕት ድንግል ላንዱ ንጹሕ ሙሽራ አጭቻችኋለሁ" 2 ቆሮ 11፥2 ብሎ እንደተናገረ ዮሴፍም እመቤታችንን ለፈጣሪ ሰማያት ወምድር ለኢየሱስ ክርስቶስ ማደሪያ ትሆን ዘንድ አጫት እንጂ ለተቃርቦ ብእሲ ወብእሲት እንዳልሆነ በጥቂቱ በሚከተሉት ነገሮች መመልከት ይቻላል።

ሀ/ <u>ከታጨችበት ጊዜ በኋላም ድንግል ሆና መገኘቷ</u>

ከደናግለ እስራኤል ሁሉ ልዩ የሆነችው እመቤታችን ነቢይ እንደመሰከረላት ለዘለዓለም በሦስቱም ድንግልናዎቿ ታትማ ትኖራለች እንጂ አትከፈትም ሕዝ 44፥1 ለዮሴፍ ከመታጨቷ በፊት እንደነበረው ሁሉ ከታጨች በኋላም እንዲሁ ነበረች፤ ለዮሴፍ ከታጨች ከዘጠኝ ወር በኋላ ስለ ተደረገው ነገር ወንጌላውያን ሲመዘግቡ የተናገሩት ለዚህ በቂ ምስክር ነው። "እናቱ ማርያምም ለዮሴፍ በታጨች ጊዜ ሳይገናኙ ጸንሳ ተገኘች" ማቴ 1፥18 ብለውናል ።

ለዮሴፍ መጨነቅስ ምክንያት የሆነው ምን ሆነና ነው፤ በድንግልና ሳለች የጸነሰች ሴት ከዚህ አስቀድሞ ባለመኖሯና በድንግልና የጸነሰች መሆኗን ለልቡናው የሚያስረዳበት መንገድ ባለማግኘቱም አይደል?መላክ እስከሚነግረው ድረስ እርሱ በታላቅ ጭንቀት ውስጥ ነበር። በተለይም ከካህናት የተቀበላት ሊጠብቃት እንጂ ለሌላ አልነበረምና በመንፈስ ቅዱስ የጸነሰች መሆኗን እስከሰማበት ጊዜ ድረስ ከመጨነቅ አላቋረጠም። ሊቃነ ካህናቱ በመንፈስ ቅዱስ ያስጠበቁት አደራው ናትና። ወንጌላዊው ሉቃስም የእርሷን ነገር ሲናገር ከታጨች በኋላ

ድንግል በሚለው ስም ጠርቷት እናገኘዋለን ሉቃ 1፥26 መንፈስ ቅዱስ በወንጌላውያን በኩል ባወጣው ስም ቤተ ክርስቲያናችን ለዘለዓለም ስትጠራት ትኖራለች "ቅድስት፣ ድንግል"

ለ/ <u>ዮሴፍ ዕለቱን ንግድ ተሸኝቶ ማደሩ</u>

የእመቤታችን ዜና መዋዕል በተጻፈባቸው መጻሕፍት ሁሉ እንደተመለከትነው የታጨችለት ሰው ዮሴፍ እርሷን ከተቀበለበት ዕለት ጀምሮ ወደ ንግድ ለመሄድ ተሸኝቶ ማደሩ ተመዝግቧል። በዘመናቸው የነበረው ንግድ የሁለት፣ የሦስት ወር መንገድ ተጉዞ የሚነገድ በመሆኑ እመቤታችንን ተቀብሎ ዕለቱን ወደ ንግድ ነው የሄደው ፤ዓለም ሁሉ ወደ ገዛ መንገዱ አዘንብሎ የነበረ መሆኑን ያመላክታል፤ ጠባቂዋ ቅዱስ ሚካኤል እንጂ ዮሴፍ አይደለምና ጠበቅሁ ብሎ እንዳይኩራራ ነው፤

ምሥጢሩ ይህ ሆኖ ሳለ ዮሴፍ ለሚስትነት የታጨችለት ቢሆን ኖሮ ዕለቱን ንግድ ለመሄድ ተሸኝቶ ያድር ነበርን? የአዲስ ሙሽራ ሥርዓት ያለው አይደለምን? በመጽሐፍ እንደተመዘገበው አዲስ ሚስት ያለችው እርሱ ቢጠሩት እንኳን አቤት አይልም ሉቃ 14፥18 የዮሴፍ ግን ከዚህ ልዩ ነውና ከሥርዓተ መራዊ ውጭ ወደ ንግድ ከመሄድ አልተከለከለም።

ሐ/ <u>ለቅዱስ ገብርኤል በሰጠችው መልስ</u>

ቅዱስ ገብርኤል ወደ እመቤታችን ገብቶ በምስጋና የተሞላ ሰላምታን ካቀረበ በኋላ የመጣበትን ዓላማ ሲገልፅ የጀመረው "ትጸንሲ" በማለት ነው እመቤታችን ግን ይህን ስትሰማ ዝም አላለችም "ምድር ያለ ዘር፣ ሴት ያለ ወንድ እንዴት ሆኖ! ትጸንሻለሽ ትለኝ አለህ" ብላዋለች ሉቃ 1፥34 ይህ ቃል ባል የታጨላት ሴት ቃል ይመስላልን? ለሚስትነት

የታጨች ሴት እውነቱን ነው ባል ያገባሁ ለዚህ አይደል፤ ትላለች እንጂ ‹‹እኔ ወንድ ሳላውቅ›› መቼ ብላ ታውቃለች?

በቀደመው ዘመን የእግዚአብሔር መላክ የመጽነሷን ነገር የነገራት አንዲት ሴት እንደነበረች በመሳፍንቱ መጽሐፍ ተጽፏል፤ ወንድ ልጅ ትወልጃለሽ ሲላት እንድወልድ በምን አውቃለሁ ብላ ምልክቱን ጠይቃለች እንጂ እንደ እመቤታችን “ይህ እንዴት ይሆናል” ብላ አልተገረመችም። በነቢይ የተነገራት ሌላይቱም ሴት የደገመችው ይህንኑ ነው ለመውለድ ከነበራት መሻት የተነሣ “ባሪያህን እንዳትዋሻት” አለችው እንጂ ይህ እንዴት ይሆናል አላለችውም 2 ነገ 4፥16 መሳ 13፥3

የእመቤታችን ግን ከዚህ ልዩ ነው፤ ለዘለዓለም እንደማታደርገው አውቃ ‹‹ወንድ ስለማላውቅ›› አለች፤ ይሄን ቃል ሊቃውንት ሲተረጉሙላት “ዘንተ ትቤ ድንግል በእንተ ዘኢዐርገ ጎሊና እገለ እመሕያው ውስተ ልባ፤ ድንግል ይህን የተናገረችው የሰው ልጆች ሐሳብ ማግባት መጋባት በልቡናዋ ስለሌለ ነው ብለው ተርጉመውታል።

የመላኩም መልስ ቢሆን የሚያመለክተው ንጽሕናዋን ነው “እኔ ወንድ ሳላውቅ ....” ብላ ስትጠይቀው የመለሰላት ምነው ለዮሴፍ የታጨሽ አይደለምን? ብሎ አይደለም እውነትሽን ነው! ያንቺማ ጽንስ መቼ እንደሌሎች ሴቶች ጽንስ ነው፤ መንፈስ ቅዱስ ያድርብሻል፣ የልዑል ኃይልም ይጸልልሻል..... ብሎ መልሶላታል፤ ለሰማያዊቷ ሙሽራ ትክክለኛው መልስ ይህ ነበርና።

ከዚህ በመነሣት ዛሬም ካህናት በቤተ መቅደስ ሲያመሰግኗት “አ!ድንግል አኮ ለዮሴፍ ዘተፍሕርኪ ለተቃርቦ አላ ከመ ይዕቀብኪ ንፁሐ፤ ድንግል

ሆይ ለዮሴፍ የታጨሽው እንደ ሰው ባለ ልማድ አይደለም ንጹሕ ሆኖ ሊጠብቅሽ ነው እንጂ” ይሏታል፤

ወንጌላዊው ማቴዎስም ንጽሕናዋን ሲገልጽላት “ሊገልጽባት አልወደደም” በማለት ዮሴፍ ለእመቤታችን የነበረውን ጥንቃቄ ይገልጽለታል ማቴ 1፥19 መንፈስ ቅዱስ ባወቀ ዮሴፍ ጻድቅ በመሆኑ በቅድስና ሊጠብቃት የተሰጠችው የመንፈስ ቅዱስ አደራ ናትና እጅግ ተጠነቀቀላት፤ የበኵር ልጇንም እስከወለደችበት ጊዜ ድረስ በነቢያት ትንቢት የተነገረላት ድንግል እርሷ እንደሆነች አላወቀም በመጨረሻም ጌታ በተወለደባት የቤተልሔም ዋሻ አምስት ምስክሮችን አይቶ እስኪረዳ ወላዲተ አምላክነቷንና በመንፈስ ቅዱስ የጸነሰች መሆኗን አላወቀም።

✞ ሥርቀተ ስብሐተ- እግዚአብሔር ዐቢይ፦ታላቅ የሆነ የእግዚአብሔር ክብር መገለጥ፤ ማለትም የቤተልሔም ዋሻ በዕለተ ልደት በታላቅ የእግዚአብሔር ክብር ተሞልቶ አድሮ ነበር ከዚያም አልፎ እረኞች እስከ ነበሩበት ድረስ እንደ ክረምት ጎርፍ ታላቅ ሰማያዊ ብርሃን በአካባቢው ይጥለቀለቅ እንደነበር በቅዱስ ሉቃስ አመዘጋገብ ይታወቃል ሉቃ 2፥8

✞ ሑረተ ኮከብ በካልእ ፍኖ፦የኮከብ ባልተለመደ መንገድ መሄድ፤ ኮከብ ዓለማችን ከተፈጠረበት ከአራተኛው ዕለት ጀምሮ ከታላቁ የሰማይ ሠሌዳ ላይ ኮከብን መመልከት የተለመደ ቢሆንም የዛሬው ኮከብ ግን ከዚያ ልዩ ነው። በነቢያት “ከያዕቆብ ኮከብ ይወጣል ከእስራኤልም ኃጢአትን ያስወግዳል” ዘኁ 24፥12 የተባለለት የአጥቢያ ኮከብ ክርስቶስ መወለዱን ለማብሠር ሐዋርያ ሆኖ ከፋርስ ባቢሎን እስከ ኢየሩሳሌም፣ በሌሊት እንደተለመደው ሳይሆን ባልተለመደው ሰዓት በቀን፤ ከመጀመሪያዋ የሥነ ፍጥረት ዕለት ጀምሮ እንደምናውቀው በሩቅ ሆኖ ማንም በማይሰፍረው የሰማይ ርዝመት ልክ ብሩህ መልኩን

እያሳየ ሳይሆን በሰው ቁመት ልክ ሆኖ መንዙና በጌታችን የልደት ስፍራ በበረት ላይ ሰፈፍ ብሎ መታየቱ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ በጉልህ ላልተረዳው ዮሴፍ ጠቁሞ የሚያሳይ ምልክት ነበር ከሰው ልጆች ተለይቶ ማደሪያውን ሩቅ አድርጎ በጽርሐ አርያም ይኖር የነበረ ጌታ ማደሪያውን በሰው መካከል ሲያደርግ፣ በሩቅ ይታይ የነበረው ሰማያዊው ኮከብ በበረቱ ላይ ሆኖ ብርሃኑን ሲነዛ ከዮሴፍ እስከ ሰብአ ሰገል ሃይማኖታቸውን አጽንቶላቸው ለባሕርዩ የሚገባ ስግደትን ሰግደውለታል።

✞ ምጽአተ ሰብአ ሰገል ዘምስለ ብዙኅ አምኃ፡- የሰብአ ሰገል ከብዙ እጅ መንሻ ጋር መምጣት፤

ሰብአ ሰገል ሲመጡ ይሄን ሁለት ዓመት የፈጀውን መንገድ በብዙ ሠራዊት ተከበው፣ ብዙ እጅ መንሻ ተሸክመው እንደመጡ ቅዱስ ወንጌል ምስክር ነው። ማቴ 2፥11 ከሩቅ ምሥራቅ እስከ ቤተልሔም ተሸክመው ያመጡትን እጅ መንሻ ሲያቀርቡ ሲመለከት ዮሴፍ በልቡናው ሁለት ነገሮችን ያወርድና ያወጣ ነበር።

1ኛ እልፍ ሠራዊት የተከተላቸው እነዚህ ታላላቅ ነገሥታት ዘውዳቸውን እያወረዱ ክብራቸውን ትተው የሚሰግዱለት አርሱ በእውነት አምላክ ቢሆን አይደለምን?

2ኛ ነቢያት የተናገሩት ስለዚህ ሕፃን ነው? ሲል በልቡናው ያመላልሳል፤ በገጸ ልቡናው ቆሞ ነቢዩ ዳዊት አሥር አውታር ባለው በገና "ነገሥተ ተርሴስ ወደሰያት አምኃ ያበውኡ ነገሥተ ሳባ ወዐረብ ጋዳ ያመጽኡ ወይሰግዱ ሎቱ ኵሎሙ ነገሥተ ምድር፣ የተርሴስና የደሰያት

ነገሥታት እጅ መንሻ ያቀርባሉ የሳባና የዐረብ ነገሥታትም ስጦታን ያመጣሉ፣ የምድር ነገሥታትም በፊቱ ይሰግዳሉ" መዝ 71፥10 እያለ ይዘምራል፤ ይህን ሁሉ ከዮሴፍ ጋር እመቤታችንም በልብዋ ትይዘው ትጠብቀውም ነበር፤ የአባቶቿ ነቢያት የትንቢታቸው ፍጻሜ ነውና ሉቃ 2፥19

✞ ፍርሀተ ኖሎት፡-የእረኞች ፍርሀት

በቤተልሔም ምድር መንጋቸውን በትጋት ሲጠብቁ ያደሩ እረኞች እግዚአብሔር ከበረከተ ልደቱ ሊያሳትፋቸው ያዘጋጃቸው ፍጡራን ናቸው። የተሰለፉበት ዓላማ ይሄ ባይሆንም ሰውን ለልዩ ልዩ በረከት የሚጠራ አምላክ ሳአልን ከአህያ ፍለጋ፣ ዳዊትን ከበግ መንጋ፣ ሙሴ ጸሊምን ከውንብድና፣ ጢሞቴዎስን ከምንዝርና[45] ጠርቶ እንደባረከ እነዚህንም ሳያስቡት አስቦ ጠርቶ ባረካቸው። መላክ አይተው፣ በመለኮታዊ ብርሃንም ተጐብኝተው አያውቁም ነበርና እንደ መብረቅ ጆሮን ጭው የሚያደርግ ድንጋጤን ደነገጡ። የሰማዩ መላክ ቅዱስ ገብርኤል ፍርሀታቸውን እንዲያስወግዱ አጥብቆ የመከራቸው ቢሆንም እነሱ ግን እስከ ቤተልሔም ፍርሀታቸው አልተወገደላቸውም ነበር፤ ዮሴፍ ይህን ሲመለከት ወላዲተ አምላክ እንደሆነች፣ እርሱም በነቢያት ደጅ ሲጠና የነበረው ጌታ መሆኑን አወቀ። ምክንያቱም እንደ ሰው ሰውኛ በጨርቅ ተጠቅሎ፣ በግርግም ተጥሎ ያለው ይህ ሕጻን ምኑ ያስፈራል? አምላክ ቢሆን ነው እንጅ፤ በባሕርየ መለኮቱ መላእክት የሚፈሩት፣ ኃያላኑ የሚንቀጠቀጡለት ነውና።

45. ንክሳር

ቅዳሴ መላእክት፡-የመላእክት ምስጋና፤

ይሄ ቀን ለፍጥረት ሁሉ አዲስ ቀን ነው፤ ሰው የመላእክቱን ዝማሬ የሰማበት ቀን፤ አምላክ በሰማይ ማደሪያውን የሚመሰገነውን ምስጋና ከምድራውያን ፍጥረታት መካከል ማን ያውቃል? በወዲያው የመላእክት ዓለም በሰማይ እንጂ በወዲሁ የሰው ልጆች ዓለም በመሬትስ መቼ ተዘምሮ ያውቃል፤ ዛሬ ግን እንደዚያ አይደለም፤ ሊቁ በሃይማኖተ- አበው እንደተናገረው "ዓለምኒ ኮነ ሰማየ ወሰማይኒ ኮነ ዓለመ" ዓለም ሰማይ ሆነ፣ ሰማይም ዓለም ሆነ፤ ያ ማለት ሰማያዊው መለኮት ምድራዊ ሰውን ሆነ ምድራዊው ሰውም ሰማያዊ መለኮትን ሆነ ማለት ነው። ስለዚህም ለሰማያዊው አምላክ የሚገባው ሰማያዊ ዝማሬ ለመሬታዊው ሰው በተደረገለት ጊዜ የሰማያውያኑ መላእክት ዜማ እንደ ማለዳ ውርጭ ወርዶ ፣ወርዶ በቤተልሔም ዙሪያ ተነጠፈ።

ከዚያም በነቢይ የተባለው እንዲፈጸም እግዚአብሔር የሰማዩን መስኮት ከፈተ፤ ይበሉት ዘንድ ለሰው ልጆች የሰማዩን እንጀራ አዘነበላቸው፤ የመላእክቱንም እንጀራ ሰው በላ መዝ 77፥23-25። የዝማሬን ጣዕም ቀምሰው፣ መዓዛውን አሽተው አያውቁ የነበሩት እረኞች ሳይቀር ከመላእክት ዝማሬን ተምረው ዘምረዋል። በሰማይም በምድርም የሚኖሩ በልሳነ ሰብእ፣ በነገረ እንስሳት የሚነጋገሩ ፤በሕገ ጣዖት፣ በሕገ አሪት የሚኖሩ፤ በዙፋን ከሚቀመጠው ንጉሥ በአደባባይ እስከ ሚቀመጠው ጽኑስ፤ በብርሃናውያኑ የሰማይ ከተሞች ከሚኖሩ መላእክት፣ በበረሐ እስከ ሚኖሩ እንስሳትና አራዊት ሁሉም አንድ ሆነው ሊዘምሩለት ሲመለከት ዮሴፍ አምላክነቱን ተረዳ፤ እርሷም ወላዲተ አምላክ እንደሆነች አወቀ፤

ወደ ኋላ ተመልሶ አባቶቹ ነቢያት በትንቢት የተናገሩትን ሲመረምር ነቢዩ ኢሳይያስ አለቅነት በጫንቃው ላይ ነው ስሙም ድንቅ መካር ኃያል አምላክ፣ የዘለዓለም አባት፣ የሰላም አለቃ" ኢሳ 9፥6 ብሎ ሲጠራው አገኘውና ነገሥታቱ፣ ሊቃነ መላእክቱም ሊሰግዱለት እንዲገባው አመነ ስለ እናቱም "እነሆ ድንግል በድንግልና ጸንሳ ትወልዳለች" ሲል ሰማውና "እምነ መኑ ጸነስኪ" ባላት ጊዜ " እመንፈስ ቅዱስ" ብላ ስትነግረው አዕምሮው አልቀበልለት ብሎ የነበረውን ከዘጠኝ ወር በኋላ ከአዕምሮው በላይ የሆነውን ሐሳብ በፍጹም ልቡናው አምኖ ተቀበለ። ራሱን ያለ ምስክር ያልተወው ጌታችን ለዮሴፍ የተገለጠው በእነዚህ አምስት ምልክቶች ነው፤ ወላዲተ አምላክ መሆኗን የተረዳው ዮሴፍ የንጉሥ እናት መሆኗን በመረዳቱ በአረጋዊነት ጉልበቱ እስከ ደኃሪት እስትንፋስ አገልጋይዋ ሆኖ ሊኖር ወደደ፤ ስለዚህም ከሩቅ ምሥራቅ እስከ ምድረ አፍሪቃ፣ ከእስክንድርያ እስከ ኢትዮጵያ በመንገዷ ሁሉ አገለገላት። የመታጨቷ አንዱ አላማም ይህ ነበርና፤ በሄደችበት ሄዶ ሊያገለግላት፤ እሱም ራሱ ለዚህ ዓላማ የታጨ፣ ከመከራዋ እንዲሳተፍ የተፈቀደለት ታላቅ ባለ ትዕግሥት ሰማዕት ነው።

እመቤታችን ለዚህና መሰል ተግባራት የታጨች የሰማዩ የአምላክ ሙሽራ ስለሆነች ለዮሴፍ የታጨችበትን ነገር አጣመው ከሚተረጉሙ የሰይጣን ደቀ መዛሙርት፣ ሥጋ ለበስ አጋንንት መጠንቀቅ መልካም ነው፤ እስኪ ፍረዱ! ንጉሥ ሳለ በዙፋኑ ሌላ ንጉሥ ይቀመጣል? ንጉሡ ከሞተ በኋላ ዙፋኑ የሚወረስ አይደለምን? የድንግል ማሕጸንም እኮ የጌታ ዙፋን ነው ከጌታ መጸነስ በኋላ በማሕጸኑ- ማርያም ፍጡር ተጸነሰ ብሎ ማውራት የፈጣሪን ዙፋን ማውረስኮ ነው።

ይሄ ደግሞ እንዳይሆን መላኩ ቅዱስ ገብርኤል ‹‹ወይሁቦ እግዚአብሔር አምላክ መንበረ ዳዊት አቡሁ፤ እግዚአብሔር አምላክም የዳዊትን የአባቱን ዙፋን ይሰጠዋል›› ሉቃ 1፥32 በማለት የዳዊት ዙፋን ተብላ በተጠራችው በማሕጸነ ማርያም ለዘለዓለም ነግሦ እንደሚኖር ተናግሮታል፤ ሞት የማይሽረው የዘለዓለም ንጉሥ መሆኑንም በተከታዩ ቃል "ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም" በማለት ዙፋኑ ለዘለዓለም የጸና እንደሆነ ይመሰክራል። እንግዲያውስ እመቤታችን ጌታችን ከወለደች በኋላ ሌሎች ልጆችን ወለደች ማለትህ ወንድሜ ሆይ! በመንግሥቱ ሽረት የሌለበትን ንጉሥ ዙፋኑን ለሌላ ለባዕድ መስጠትህ ነውና ተመለስ፤ እንደ አባትህ እንደ ዳዊት " አቤቱ ዙፋንህ ለዘለዓለም ነው" መዝ 44፥6 ብለህ ዘምር።

መ/ <u>በኅቱም ድንግልና ጸንሳ በኅቱም ድንግልና መውለድ</u>

እናታችን ሔዋን የመጀመሪያ ልጇን ቃኤልንና መንትያውን ሉድን ከወለደችበት ጀምሮ ጸንሳ የምትወልድ ሴት በዓለማችን አለች፤ በኅቱም ድንግልና ጸንሳ፣ በኅቱም ድንግልና ወልዳ አስደናቂ ታሪክ ያስመዘገበች ሴት ግን መኖሯን ታሪክ አይነግረንም፤ ታላላቅ ታምራት ያደረጉ፣ ታላላቅ የእግዚአብሔር ሰዎችን የወለዱ ቅዱሳት አንስት ሳይቀሩ በተፈትሆ ማሕጸን ጸንሰው እንደወለዱ ምስክር የማያሻው ሀቅ ነው።

ምን አልባት ከኅቱም ምድር የተገኘ ሰው፣ ከኅቱም ጎን የተገኘች ሴት፣ ከኅቱም ግንድ የተገኘ በግ ሊኖር ይችል ይሆናል ዘፍ 2፥7 ፣ 2፥21-22 በኅቱም ድንግልና ተጸንሶ የተወለደ የመጀመሪያው ሰው ክርስቶስ ሲሆን በኅቱም ድንግልና ጸንሳ የወለደች የመጀመሪያዋ ሴት ደግሞ እመ ብዙኃን ድንግል ማርያም ናት።

46. አካል የሚባለው ከራስ ፀጉር እስከ እግር ጥፍር ያለው የመልኮቻችን ስብስብ ሲሆን መልክ የምንለው ደግሞ ዐይን፣ እጅ እግር እየተባሉ የሚጠሩ የአካል ብልቶቻችንን ነው። በዚህ መሠረት አካል የመልእክት ማህደር ነው ማለት ነው።

በሕገ ፍጥረት እንደለመድነው ሰው መጀመሪያ ከአባቱ ዘር፣ ከእናቱ ደም ተከፍሎ በአርባኛው ቀን በሚፈጸምለት ተስዕሎተ መልክእ[46] (ሙሉ አካል ማግኘት) ፍጹም ሰው ይሆናል፤ ይሄኛው ልደት ግን ከዚያኛው ልደት በእጅጉ የተለየ ምሥጢር አለው፤ በዘር በሩካቤ የሚደረግ ልደት ከዚህ አስቀድሞ ህልውና የሌለው፣ ከዚህ በኋላ ሊኖር የሚችል ሰውን የሚያስገኝ ልደት ነው። በእመቤታችን የተደረገው ልደት ግን አወጣጡ ከጥንት የነበረውን አካል ያየንበት ልደት ነው መክ 5፥2 በዚህም ቀዳማዊ ልደቱን አወቅነው፤ ታላላቁ ሊቃውንት ሃይማኖታቸውን በገለጹበት መጽሐፍ እንደተነገረው "ልደት ቀዳማዊ ተዐውቀ በደኃራዊ ልደት፤የመጀመሪያው ልደት በሁለተኛው ልደት ተገለጠ ።

ከድንግሊቱ የተወለደበት አንዱ ምክንያትስ ምን ሆነና ነው፤ ቅድመ ዓለም በቀዳማዊ ልደቱ የወለደው አባት መኖሩን ለማስረዳትም አይደል፤ ምክንያቱም ለአንድ ሰው በግብር፣ በቃል የሚወልደው ብዙ እናት እና አባት ሊኖረው ይችል ይሆናል እንጅ በባሕርይ አስመስሎ፣ በአካል አስተካክሎ የሚወልደው ከአንድ እናት፣ ከአንድ አባት በቀር ሌላ አያስፈልገውም፤

ስለዚህም በምድር አባት፣ በሰማይ ደግሞ እናት የሌለው መሆኑን አወቅን፤ በአባቱ ሰማያዊ፣ በእናቱ መሬታዊ በመሆኑ ሰማያውያንና መሬታውያንን አስታረቀ፤ በአስራ አምስት ዓመቷ ቆንጆ በቀዳማዊቷ ሔዋን የተፈጠረው ጠብና መለያየት እንደገና በአስራ አምስት ዓመቷ ብላቴና በዳግማዊት ሔዋን በእመቤታችን ተመልሶ ጥልና መለያየቱ ተደመሰሰ፤ ከቀደመችው ሔዋን ይልቅ አዲሲቷ ሔዋን በክብር፣ በባለሟልነት፣ በጸጋ፣ በሞገስ በሥላሴ ዘንድ የተሻለች ናትና ተዋሕዶውን ከፍ አደረገችው።

የቀደመው የሰው እና የእግዚአብሔር ተዋሕዶ በጎድሬት ነበር። የአሁኑ የሰው እና የእግዚአብሔር ተዋሕዶ ግን በክዊን ነው። ያ ማለት ዛሬ በመላእክት አድሮባቸው ለቅዳሴ ሲያተጋቸው እንደሚኖር በሰውም ላይ እንዲህ አድሮ ይኖር ነበር፤ ዛሬ ግን ሰው እግዚአብሔር፣ እግዚአብሔርም ሰው ሆኖ በመገለጡ ዝምድናችንን ከፍ አድርጎታል። ይሄን ጸጋ ከማግኘታችን አስቀድሞ የተከናወኑ ነገሮችን በቅደም ተከተል ለማየት ያክል፦

ብሥራተ መልአክን መስማት

ለመጀመሪያይቱ ሔዋን ከመጣው ከመጀመሪያው መላክ የተለየ መሆኑን ለመግለጽ ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ ወደ እመቤታችን የመጣውን መላክ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደተላከ ይናገራል። ሉቃ 1፥26 የመጀመሪያው ጠላታችን እርሱም ዲያብሎስ ሳይላክ ሥጋችንን ለሞት አጨ፤ ሁለተኛው መላክ ግን ከሙሽራው ከእግዚአብሔር ዘንድ ተልኮ ሥጋችንን ለሕይወት አጨ።

ያን ጊዜ ገና በገነት ቤታችን ባለጠጎች በነበርንበት ጊዜ ደሀው ሞት በእግዚአብሔር ጸጋ የበለጸገ ሰውነታችንን አጨው ፤ዛሬ ግን ድሆች ሆነን ሳለ ባዶውን ባሕርያችንን ሕይወት ክርስቶስ አጨው ፤

ድሀም ቢሆን ክርስቶስ ለተዋሐደው የሥጋ ባሕርይ ከደጅ ድረስ መልክተኛ ተላከበት፤ ጥንት በአባቶቻችን ዘመን ከምድረ አሕዛብ ሁሉ ተለይቶ እንደ አብርሃም የከበረ ፍጡር አልነበረም። በሕይወት ሳለ ፈጣሪውን ያየ፣ ቃል በቃል ከፈጣሪው ጋር ጥያቄና መልስ ያደረገ፣ የፈጣሪውን እግር ያጠበ፣ ከፈጣሪው ፊት ማዕድ አቅርቦ በማዕድ ያገለገለ ፤እንዲያው በሁሉ ዘንድ ጌታ የሆነ እንደ አብርሃም ማን ነበረ? ለልጁ ለይስሐቅ ሚስት በፈለገ ጊዜ ግን ወደ ድሀይቱ ወደ

ርብቃ ቤት መልእክተኛውን ኢያውብርን መላኩ ዛሬ ወደ እመቤታችን ቅዱስ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ዘንድ ለመላኩ አምሳልና ጥላ ነበር ርብቃ የእመ ብርሃን ድንግል ምሳሌ ናትና።

ርብቃ ምንም እንኳን ባይስማሙ የሁለቱ ሕዝቦች መገኛ ናት፤ እመቤታችንም የሁለቱ ወገኖች የሕዝብ እና የአሕዛብ እናት ናትና ዘፍ 23፥5 ፤ 24፥10 ፤ 25፥22 ርብቃ የአስራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል በሥጋ አባት የሆነውን ያዕቆብን እንደወለደች እመቤታችንም የአስራ ሁለቱ ሐዋርያት መምህርና አባት የሚሆነውን ንጉሥ ክርስቶስን ወልዳለችና።

መላኩ ወደ እመቤታችን የተላከበትን ቀን ሊቃውንተ- ቤተክርስቲያን ሲናገሩ መጋቢት 29 ቀን ከረፋዱ ሦስት ሰዓት፤ ዕለቱ ዕለተ እሁድ፤ ዘመኑ ዘመነ ዮሐንስ፤ የአምስት ሺ አምስት መቶ ዓመተ ፍዳ መካተቻ፤ የዓመተ ምሕረት መባቻ ላይ ነበር፤ ይሄን ደግሞ ወደ ኋላ መለስ ብለን ታሪክ እናጥና ከተባለ ቀኑ ዓለም የተፈጠረበት፤ ሰዓቱም የመጀመሪያው ሰው የተገኘበት፤ ጌታም ዳግም ዓለምን ለማሳለፍ የሚመጣበት ወቅት ነው፤

ቀድሞ ሰውን በሠራበት ሰዓት ዳግም ሰውን ሊሠራ ወደ ዓለም መጣ። ሰማያዊው የንጉሥ መልእክተኛ ታላቁን ምሥጢራዊ መልእክት ይዞ ከሰማይ ወደ ምድር በወረደ ጊዜ ክንፉን ሲያማታው እመቤታችን እስከተወለደችበት እስከ አድባረ ሊባኖስ ድምፁ ይሰማ ነበር፤ በኋለኛው ምጽአቱ በነጋሪት ድምፅ፣ በመላእክት አለቃ አዋጅ ነጋሪነት የሚመጣ ነውና 1 ተስ 4፥15

የእግዚአብሔር ጸጋ የመጣላት እመቤታችን ግን በዚህ ሰዓት የነበረችው ከውሃው ምንጭ አጠገብ ከእስራኤል ሴቶች ጋር ውኃ ስትቀዳ ነው የተገለጠላት፤ እንደምትጸንስ የነገራትም ሦስት ጊዜ ሲሆን ለመጀመሪያ ጊዜ ያገኛት በዚሁ ሥፍራ በውኃው ምንጭ አጠገብ ነበር። እጅግም ሽማግሌ እጅግም ወጣት ሳይሆን በመካከለኛ ሰው መልክ ተገለጠላት።

እርሷ ወደ ውኃው ምንጭ አጠገብ የወረደችው እኮ እናት ላልነበራቸው ለዮሴፍ ልጆች እናት ልትሆናቸው፤ ውኃ ልትቀዳላቸው ነው። ለዮሴፍ የታጨችበት አንዱ ዓላማ ይህ ነበርና ።ለሙት ልጆች እናት ልትሆን።

እግዚአብሔር ልዩ ዓላማ በእርሷ በኩል ነበረውና እናት ለሌለውና የሙት ልጅ ለሆነው ዓለም እናት እንድትሆን፤ የሕይወትን ውኃ አጥቶ ለተጠማው ዓለም የሕይወትን ውኃ እንድትቀዳ አደረጋት እናታችን ሔዋንን በሞት ስንነጠቅ የሙት ልጆች ሆነን ነበር እናት አልባ ለሆነው ዓለም እናት እስክትሆን ድረስ እናትነትን በዮሴፍ ቤት ጀመረችው ልጁ ክርስቶስ በዚህ ዓለም ሳለ ያለውን ነገር እናስታውሰዋለን፤ ‹‹የሙት ልጆች ትሆኑ ዘንድ አልተዋችሁም››ዮሐ16÷12 ይህ ቃል ኪዳን የተፈጸመው በመስቀል ላይ እነኋት እናትህ ባለ ጊዜ ነው።

ወደዚህ የውኃ ምንጭ አጠገብ እንድትወርድ የተደረገበት ምክንያት አንዱ ይሄ ሆኖ ሳለ በተጨማሪም የቀደሙት እናቶቿ እነ ሲፓራ፤ ርብቃ የታጩት በውኃ ምንጭ አጠገብ ነበርና በዚያ ልማድ እርሷንም እንደ እናቶቿ ከውኃ ምንጭ አጠገብ አጫት ዘፍ 24÷12፤ 29÷10 ምሥጢሩ ግን ቤተ ክርስቲያንን በማየ ገቦ የሚያጭበት ጊዜው የደረሰ መሆኑን አመላካች ነው።

የምሥራችን ይዞ ለመጣው ለዚህ ታላቅ መላክ እመቤታችን ፈጥና እሽ በጀ ያለችው አይደለችም ይልቁንም “ተፈሥሒ አ ምልዕተ ጸጋ .....” እያለ ሊያመሰግናት የቀደመችው ሔዋንን “ሰላም ለኪ አ! ሔዋን ንግሥተ ሰማይ ወምድር” በሚለው የከንቱ ውዳሴ ንግግሩ ድል የነሣት ሰይጣን መሰላትና ወደ ፈጣሪዋ መጸለይን አበዛች።

ከእናቷ ከሔዋን ልዩ ናትና በቀረበላት ምስጋና ደስ አልተሰኘችም በቤተ መቅደስ ቅዱሳት መጽሐፍትን ስትመለከት ያደገች በመሆኗ ለቀረበላት ምስጋና “እፎኑ ከመዝኑ እንጋ አምኃ ይትአመኑ “ እንደዚህ ያለ እጅ መንሻ እንደምን ይደረግልኛል” የሚል መልስ ሰጠች እንጅ ወደ ልቧ አላስገባችውም። ቤተክርስቲያናችን እመቤታችንን ስታመሰግን “ድንግል በኀሊናኪ” የምትለውም ከዚህ የተነሣ ነው ኀሊናዋ ለምንም አይነት ኃጢአት የተቆለፈ ነበርና።

ምን ጊዜም ቢሆን የደስታ መግቢያው መከራ ነውና እመቤታችን ይህን የምሥራች ከመስማቷ በፊት ከውኃው ምንጭ አጠገብ የተቀመጡ የሰይጣን ውጥን ጨራሽ ሥራ ፈት ሴቶችን ሽሙጥ ስትሰማ ነበር። የተጠማ ውሻ ማጠጣቷን ተከትሎ በኑ ነገርን የማይሻው ሰይጣን ተቃውሞውን አሰምቷል።

ምን አልባት በነቢያት የተነገረላት ማርያም የሚሉሽ አንቺ ትሆኝ ይሆንን? ብለው ተቀላለዱባት። አውቆ አያደርገውም እንጅ ሳያውቀው አንዳንድ ጊዜ ሰይጣንም እውነት ይናገራል ወቅቱ አባቷ አዳም እናቷም ሔዋን የሰይጣንን ተግዳሮት በሲኦል የሚሰሙበት ወቅት ነውና በእርሷም ላይ ይህ ተደረገ መከራውን የታገሰችው ድንግል እንደ ጭንቁር የሚባላውን ንግግራቸውን እልፍ ብላ በትዕግስት ባለፈችበት

ጊዜ የደስታው መላክ ቅዱስ ገብርኤል አጥንትን የሚያለመልመውን የምስጋና ቃል ይዞ መጣ። ክፉውን በዝምታ አልፋ የመላኩን ውዳሴ ግን ተቃወመችው፤ የእግዚአብሔር ሰዎች ስድብ የሚያስደስታቸውን ያህል መወደስ አያስደስታቸውም፤ ምክንያቱም በነቀፋ ከወደቁት በውዳሴ የወደቁት ይበዛሉና። ሲጀመር ጀምሮ ሔዋን ኃጢአትን አሜን ብላ የተቀበለችው ከንቱ ውዳሴ በተባለ የሐር ግምጃ ስለተጠቀለለ ነው። ኃጢአት በዚህ የስጦታ ዕቃ መጠቅለያ ተጠቅልሎ ነው ለሰው ልጆች መታደል የጀመረው።

ይህን የመሰለ ተንኮል የሚሠራ ጠላት እንዳላቸው ሳያውቁ የሚጓዙ አገልጋዮች ፈንጅ በተቀበረበት የጦር ቀጠና እንደ ልብ የሚንቀሳቀሱ ሞኞች ናቸው እመቤታችን ግን ነገሩን አልተቀበለችውም፤ የሴቶችን ተግዳሮት በሰማች ጊዜ የነበራት ትዕግስት አሁን የላትም፤ እንዴት ያለ ተግዳሮት ነው አላለችም አሁን ግን እንዴት ያለ እጅ መንሻ ነው አለች።

የአምላክ እናት በመሆኗ ክብርን የሰጣት የእግዚአብሔር መላክም እንደ ዘካርያስ አላስደነገጣትም እመቤቱ፤ የፈጣሪው እናት ናትና። አልፎ ሄዶ ከዮሴፍ ቤት ገብታ ውኃ የያዘችበትን እንስራ ስታወርድ እንደገና ለሁለተኛ ጊዜ የቀደመውን ቃል በመድገም "ትጸንሲ›› አላት በዚህ ጊዜ ይሄስ ከእግዚአብሔር ነው መሰለኝ የሰይጣንማ ቢሆን ቃሉን ይለውጥ ነበር እንጅ አንድ ቃል ይናገር ነበር? አለች።

ይህንስ ከቤተ እግዚአብሔር ሂደው ሊረዱት ይገባል ብላ ከቤቷ ወጥታ ወደ ቤተ እግዚአብሔር ሄደች፤ ከቤተ እግዚአብሔር ወጥቶ፤ ልጅነትን አጥቶ የነበረ የሰው ልጆችን ባሕርይ ልታስባርክ መሆኑ ነው። የቀደመችው የ15 ዓመቷ ብላቴና ሔዋን በተቀደሰው ቦታ

በገነት ከሠይጣን ጋር ተዋውላ ባመጣችው ፍዳ የተያዘ የሰው ልጅ ነጻነትን ያገኝ ዘንድ ዳግመኛ የሞቱን ቃል ኪዳን ወደ ዘለዓለማዊ የሕይወት ቃል ኪዳን ለመለወጥ ዳግማዊት ሔዋን ድንግል ማርያም ወደ ቤተ መቅደስ አቀናች።

የአባቶቿ የነቢያት የዘመናት ጥሪ ነበር ከኢየሩሳሌም እስከ ስምንቱ አጽናፈ ዓለም ሲሰማ የኖረ፤ ለትውልድ የተነገረ ጥሪ ነው፤ እርሱ በዚህ ጊዜ ተከናወነ " ኑ ወደ ያዕቆብ አምላክ ወደ እግዚአብሔር ቤት እንውጣ ....." ኢሳ 2፥3 ሚክ 4፥2 *ያችኛዋ ሔዋን ያስከበለችውን ትውልድ ይህችኛዋ ሔዋን ፊቱን ወደ እግዚአብሔር መለሰችው* እርሷም እንደ አባቶቿ ኑ ወደ ያዕቆብ አምላክ ወደ እግዚአብሔር ቤት እንውጣ ....." ብላ ተጣራች በመዝሙር እንደተነገረው "በኋላዋ ደናግሉን ለንጉሥ ይወስዳሉ ..... ወደ ንጉሥ እልፍኝም ያገባሉ" መዝ 44፥14-15 እንደተባለ ሔዋንን ተከትለን ከቅድስቷ ምድር ወጣን፤ ዳግመኛ ሔዋንን ተከትለን ወደ ገነት ተመለስን።

በሐዲችበትም ጊዜ እመቤታችን የተቀላቀለችው በቤተ መቅደሱ ዙሪያ ከተሰበሰቡ ደናግለ እስራኤል ጋር ነው። እነርሱ እንደሚያደርጉት ሁሉ ልታደርግ ከደናግለ እስራኤል ተካፍላ ወርቅ እና ሐሩን እያስማማች መፍተል ጀመረች[37]። በእስራኤል ልማድ መጋረጃ፤ ልብሰ ተክህኖ የሚሆነው ደናግሉ የሚፈትሉት ነው ። ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ እንደተናገረን ወርቅ እና ሐሩን እያስማማች ስትፈትል ቅዱስ ገብርኤል በድንገት ተገልጦ ያንኑ ቃል ለ3ኛ ጊዜ ደገመላት። "ትጸንሲ" ወርቅ እና ሐር በሊቃውንቱ ሲተረጐም ሃይማኖትን በወርቅ በጐ ምግባርን በሐር መስለው ምግባርና ሃይማኖትን አስተባብራ ይዛ ሳለ ገብርኤል ወደ እርሷ ተላከ ማለት ነው ብለውታል

47. ዚቅ ታህሳስ ገብርኤል

አንድም፡- ወርቅ የመለኮት፣ ሐር የትስብዕት ምሳሌ ነውና ብለው፣ መለኮትና ወርቅ የወንጌል ሀሩ የአሪት ምሳሌ በመሆኑ እመቤታችን ወርቅና ሐርን ስታስማማ ብሎ ሊቁ መናገሩ። ድንግል ማርያም የብሉይ ኪዳን ፍጻሜ የሐዲስ ኪዳን የወንጌል መግቢያ በር መሆኗን መንፈስ ቅዱስ ገልጸለት ተናግሮታል ብለው ተርጉመውታል።

ወርቅ እና ሐሩን እያስማማች ማለት በልቧ የነቢያትን ትንቢት እየመረመረች ሳለ መላኩ መጥቶ ለ3ኛ ጊዜ ቃሉን ሳይለውጥ ሲነግራት እንደ ብልህ ደቀ መዝሙር የጽንሱን ነገር ለመረዳት ትጠይቀው ጀመር "እኔ ወንድ ሳላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል" አለችው ምንም እንኳን የ15 ዓመት ብላቴና ብትሆንም ታገባለች ተብሎ አትጠረጠርምና መላኩም ለዘካርያስ በተገለጠበት የሚያስፈራ ክብር የተገለጠላት አይደለም፣ በትህትና ነው እንጅ። ወንጌላዊውም ሲመዘግብ "መላኩም ወደ እርሷ ገባ" ሉቃ 1፥27 ብሎ መናገሩ የቦታ አይደለም በባሕርይ እርሷን መሰለ ማለቱ ነው እንጅ።

ሞት በሔዋን ልቡና ሲጸነስ አብሣሪ የነበረው መልአከ ሞት ሰይጣን ጋር እናቷ ሔዋንም ስህተት በተጀመረባት በዚያች አለት ተከራክራ ነበር ጽድቅ በተጀመረችበት በዚህችኛዋ ቀንም አዲሲቷ ሔዋን እመቤታችን ሕይወት እንዲጸነስ ከመልአከ ብሥራቷ ጋር ተከራከረች።

ለመጀመሪያይቱ ሔዋን አምላክ እንደምትሆን ሲነግራት ለዚህችኛዋ ሔዋን ግን አምላክን እንደምትወልድ ተነገራት። አምላክን መውለድ ምንም እንኳን የማይቻልና ከባድ ቢሆንም አምላካዊ ባሕርይን፣ እግዚአብሔራዊ ጌትነትን የባሕርይ ገንዘብ ማድረግ ደግሞ ፈጽሞ የማይቻል ጉዳይ ነው። ውሸት የማይሳነው ጥንተ ጠላታችን ይህን ተናገረ።

- ከፊቷም ቆሞ ደጅ የሚጠናት ቅዱስ ገብርኤል ለጠየቀችው ጥያቄ ሦስት ምስክሮችን አምጥቶ ነገሩን አስረድቷታል
- መንፈስ ቅዱስ ያድርብሻል የልዑል ኃይልም ይጸልልብሻል ይህ የሚወለደውም ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል የሚለው አንዱ ሲሆን

- እነሆ ዘመድሽ ኤልሳቤጥ ስንኪን ዘሯ ካለቀ ደሟ ከደረቀ በኋላ በእርጅና ወራት ትሞታለች እንጅ ትወልዳለች የሚላት ባልነበረበት ሰዓት ጸንሳለች። ብሎ ምንም ዘካርያስ ምክንያት ቢኖራት እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ አምላክ ስለሆነ እንጅ የማይቻል መሆኑን ከመግለጽ ጋር አብሮ ምንም ምክንያት የሚሆን ወንድ ባይኖራትም ያለ ወንድ ዘር መጽነስ እንደምትችል አስረድቷል።

- በመጨረሻም የነገር ሁሉ መደምደሚያ የሆነውን ዐረፍተ ነገር አስቀመጠላት "ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም" አላት ሉቃስ 1፥35-38

በእዚህ ሦስት ምስክሮች ተረድታ ነው እመቤታችን "እነሆ የጌታ ባሪያ እንደ ቃልህ ይደረግልኝ" አለችው።

በሰውነቱ እናቱ እንድትሆን የተመረጠች ቢሆንም በአምላክነቱ ደግሞ ጌታዋ ነውና ራሷን የጌታ ባሪያ ብላ ትጣራለች፣ በዚህም አነጋገሯ ከቀደመችው ሔዋን የተለየ ቅድስና ተገኘባት። ሔዋን ኃጢአትን ወደ ዓለም ያስገባችው በክፉ መሻትና በመጐምጀት እንዲሁም በትዕቢት ነበር እመቤታችን ግን ያን ክፉ መሻት አርቃ፣ ትዕቢትን አስወግዳ እናትነት ተሰጥቷት ሳለ በትሕትና በትዕግስት ገረድነትን ተመኘች

ይሄ ትሕትናዋ ሁለቱን ተቃራኒ ነገሮች እናትነትን እና ግርድናን አስተባብራ የያዘች ልዩ ሴት አድርጓት ይኖራል።

ሞትና ሕይወት በሁለቱም ሔዋኖች

ድንግል በፈጣሪዋ የመመስገኛ ስፍራ በመሠዊያው ፊት ለፊት ቆማ ይህን ቃል ስትናገር ከዓለም መፈጠር አስቀድሞ ለእናትነት ያጫት እግዚአብሔር በማይነገር ቅጽበት ተዋሐዳት። ከነፍሷ ነፍስን፣ ከሥጋዋ ሥጋን ነስቶ በማሕጸኗ ተቀረፀ። ፍጡራን ሊያውቁት ሊመረምሩት በማይችሉት ሁኔታ ልዑል የነበረ ትሑት ሆነ። ጌታ የነበረው እናቱ "እነሆ የጌታ ገረዱ" ብላ ስትናገር እርሱም የባሪያውን መልክ ያዘ።

ከፈጣሪ በቀር ሥጋንና ነፍስን ከፍሎ ሲዋሐድ ከፍጡራን መካከል ያወቀ የለም እንኳን ሌላው ቀርቶ መላክ ብሥራቷ ቅዱስ ገብርኤልም ቢሆን ለዚህ የበቃ አልነበረም። የሠራዊት ጌታ በአንዲት ድሃ ቤት ሲያድር፣ ሰማይና ምድር የማይወስኑት አምላክ በአንዲት ገሊላዊት ታናሽ ብላቴና ማሕጸን ሲወሰን፣ ሰባቱ የእሳት ከተሞች ከክብሩ ውበት የተነሣ ከፊቱ ጸንተው መቆም የማይቻላቸው በሰው መካከል ሲያድር ማየት ከፍጡራን አዕምሮ በላይ ነውና በጥበቡ ሰወረው።

በዚያውስ ላይ ሞት በሔዋን ልቡና ሲጸነስ ከፍጡራን መካከል ያወቀው አለን? ሳይታወቅ በአንዲት ሴት ምክንያት ሞት ወደ ዓለም የገባ አይደለም? በወቅቱ የነበሩ ፍጡራንም ቢሆን ከሰው እስከ መላእክት ሞትን ያዩትና ያወቁት ተሰውሮ ወደ ዓለም ከገባ በኋላ ነበር። በተለይም መርገም በሰው ልጆች ላይ ከተላለፈ በኋላ ለጌታ ወደ ዓለም መምጣት

ትንቢት እንደተነገረለት ሞትም ትእዛዙን ለሚጥሱ የሚመጣባቸው መሆኑ አስቀድሞ ተነግሮ ነበር፤ ከሆነ በኋላ እንጅ ሲሆን ማንም አላየውም፤ ጌታም በማይመረመር ግብር ሰው ሆነ።

ደራሲው እንደገለጸው ቅዱስ ሚካኤል እስከ አምስተኛው ሰማይ ድረስ ተከትሎት ነበር፤ ከዚያ በኋላ ግን መንገዱን ሰወረበት እና ወዴት እንደገባ አላወቀም። ያውም ቢሆን በአምሳለ ዐቢይ ሊቀ ካህናት አክሊል ደፍቶ፣ ካባ ላንቃ ደርቦ የወርቅ ዘንግ ጨብጦ ሲወርድ ሲመለከተው ደግሞ ከኔ የሚበልጥ ሊቀ ካህናት ከወዴት መጣ ብሎ አዲስ ቢሆንበት ገርሞት ይከተለዋል እንጅ ጌታ መሆኑን አውቆ የተከተለው አይደለም [48]።

ሔዋን ከዲያብሎስ ሽንገላ የተሞላበት ቃልን ሰምታ ሞትን ወለደች፤ የብርሃን እናቱ እመቤታችን ግን ሕይወትን ጸነሰች። ከአበው ነቢያት ቃለ ትንቢትን፣ ከቅዱስ ገብርኤል ምስጋና የተሞላበት ቃልን ሰምታ በጐ ምኞትን ወለደች "አባታ ኢሳይያስ እነሆ ድንግል ትጸንሳለች ልጅንም ትወልዳለች" ያለውን ሰምታ ምነው ይህ ትንቢት ከተነገረላት ሴትስ ከዘመኗ ደርሼ ወጥቼ ወር ባገለገልኳት አለች እንጅ ምነው እኔን ባደረገኝ አላለችም። ድንግል ሆና ለእራሷ አልተመኘችም። እርሷም እንደ ነቢዩ ድንግሊቱን ትፈልጋለች እንጅ።

ይሄ በጐ ምኞታ ሕይወት ክርስቶስን እንድትጸንስ አደረጋት፤ የጸነሰችው የወለደችውም እንደ ሔዋን ሞት የሚበረታታበት መቅበዝበዝ እና መኮብለል የጸናበት ቃልን አይደለም ሞትን ድል አድርጐ መቃብር እና ሲኦልን ጠራርጐ ባዶ አድርጐ ማስቀረት የሚቻለው የሞትና የሲኦል መክፈቻ በእጁ ተይዞ ወንጌላዊ ዮሐንስ የተመለከተውን ክርስቶስን ነው።

48. ትም. ነቡ. ትር

የሞት ሰባኪ በሆነው ጥንተ ጠላታችን ሰይጣን የተሰበከችው ሔዋን የሰባኪውን ድምፅ ሰምታ ነፍሰ ገዳዩን ቃኤልን ጸነሰችው። ሰባኪው በራሱ ነፍሰ ገዳይ ነበርና ዮሐ 8፥44 በሰባኪነቱ በመላእክት ከተማ የሚታወቀው በመላእክት ዓለም የመጀመሪያው ሰባኪ ፣የተዋሕዶ ሃይማኖትም የመጀመሪያው ሰባኪ ማለትም ቤተክርስቲያን ከጥላ ወደ አካልነት ስትለወጥ ከሰባኪዎች ሁሉ አስቀድሞ ከምዕመናን ሁሉ ለከበረችው እመቤት ያስተዋወቀው ሰባኪያችን፣ በስብከቱ ዓለመ መላእክት የተረጋጋበት፣ ለብዙ መላእክት በሕይወት መኖር ስብከቱ ምክንያት የሆነለት፣ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት የሚቆመው የእግዚአብሔር አገልጋይ ቅዱስ መላክ የሰበከላት ድንግል ማርያም ግን የሞት መድኃኒት የሆነ፣ ስለ ሰው የሚሞት እንጅ ሰውን የማይገድል ንጹሐ ባሕርይ ክርስቶስን ወለደች።

መጽሐፍ እንደተናገረ ለእግዚአብሔር አምላክነት የማይገባ ሆኖ በመገኘቱ ከሥላሴ መንግሥት የተወገደው ሰይጣን በእርሱ ፋንታ አመስጋኝ ሆኖ ሰው በመፈጠሩ በወሰደው የበቀል እርምጃ ዕፀ በለስን አብልቶ ከክብሩ ከማዕረጉ አዋርዶታል። 3ኛ መቃ 9፥1 በበቀል ፈንታ ፍቅርን ሲመልስ ራሱን አሳልፎ የሚሰጥልን አምላክ ተወለደ።

በቀል የፍቅርን ያክል ጉልበት የለውም። 15ኛው ዓመት በመጀመሪያይቱም ሆነ በሁለተኛይቱ ሔዋን እንዲህ ዓይነት አስገራሚ ነገሮች የተከናወኑበት ወቅት ሲሆን የመጀመሪያይቱ ሔዋን ከገነት የወጣችበት፣ ሁለተኛይቱም መንግሥተ ሰማያትን ክርስቶስን የጸነሰችበት፣ ከዚህ በኋላም ቢሆን ለሴቶች ባለውለታ የሆነ እድሜ ነው የማያልፈውን ዓለም መንግሥተ ሰማያትን ወርሰው የሚኖሩበት እድሜ ነውና

በአጠቃላይ ስንመለከተው ሔዋን በ15 ዓመት እድሜዋ የዓመተ ፍዳ ምክንያት ስትሆን እመ ብዙሃን ድንግል ማርያም በ15 ዓመቷ የምህረት ዓመት መጀመርን አበሠረች በኋለኛውም ዘመን በትንሣኤ ሙታን ሴቶች የ15 ዓመት ቆነጃጅት ሆነው ተነሥተው በአዲስ እና በማያልፍ ቀን ዳግም መኖር ይጀምራሉ።

የአዲስ ኪዳኑ አገልግሎት መጀመር

አሮጌ ኪዳን አለና የሚመጣውን አዲስ ኪዳን ማለታችን የግድ ነው። አሮጌው ኪዳን የሞትን መልእክት ማራቅ ያልቻለ ስለ ምድራዊ ርስት የተማለ ካንድ ሕዝብ ጋር ብቻ የተደረገ መሐላ ነበር አዲሲቷን ሰማይ እና አዲሲቷን ምድር መሠረት ያደረገው ሐዲሱ ኪዳን ሲመጣ ግን አሮጌውን አስረጀው።

አዲስ ኪዳን ማለት የሞት አገልግሎት ከተፈጸመ በኋላ የመጣ የሕይወት አገልግሎት ነው። አገልጋዩ በራሱ ሞት የማይገዛው የዘለዓለሙ ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በሕያውና በተቀደሰው መሥዋዕት በተደጋጋሚ ሳይሆን አንድ ጊዜ ፈጽሞ የሚገባባት ቅድስት ይህችውም ሥጋው የዘለዓለም የአገልግሎት ስፍራችን ናት።

የስምንቱ ብሔረ ኦሪት ምግብና አልቆ የሐዲስ ኪዳኑ አገልግሎት በደመ ክርስቶስ ጸድቆ በዐዋጅ ሥራ የጀመረው በምሴተ ሐሙስ በተደረገው የእራት ግብዣ ላይ ቢሆንም ማቴ 26፥26 የዕዳ ቅነሳ ለሰው ልጆች የተጀመረው ግን በማሕጸነ ማርያም ነው።ይሄውም ቁራኝነት ነው።

ሊቃውንት ስለ ማሕጸነ ማርያም

የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ስለ ማሕጸነ ማርያም መናገር በጀመሩ ጊዜ በመገረም ይመሠጣሉ- የሚሉትን ያጣሉ። ከሊቃውንት አንዱ የሶርያው መምህር ቅዱስ ኤፍሬም ‹‹ገበሬ ሳይደክምበት ዘር ሳይወድቅበት ለመሥዋዕትነት የተዘጋጀውን ስንዴ ያበቀለ ንጹሕ የስንዴ ማሳ›› በማለት ያደንቃል እውነት ነው ያለድካም እንደምን ፍሬ ይገኛል? ያለ ዘርስ እንዴት ይበቅላል "ሴት ያለ ወንድ ምድር ያለ ዘር" እንዲሉ። ምን ይዜ ብቻ ይላል ቅዱስ ኤፍሬም በጭንቅ በጸዕር ትወልድ ዘንድ የፈረደባት ማሕጸን ነበረች በእመቤታችን ግን ይህ መርገም የለምና የፈለፈለ ሕይወት የኢየሱስ ክርስቶስ መገኛ ሆነች።

ሰው ከዚህ አስቀድሞ መራር ሕይወትን ይዞ የሚወለደው ከእናቱ ማሕጸን ጀምሮ ነበር፤ በሔዋን ምክንያት የሴቶች ሁሉ ማሕጸን መራርነትን የተሞላ ምድር ሆኖ ነበርና ከዚህ ምድር የሚመነጩ የሰው ዘሮች በሙሉ መርገም የተላለፈባቸው ናቸው። በኢያሪኮ እንደነበረው ውኃ ፈውስን የሚሹ፤ ነገር ግን ፈዋሽ በማጣታቸው ክፉዎች ሆነው የቆዩ ሲሆኑ ከእነርሱ የተነሣ ምድሪቱም ትጨነግፋለች፤ ፍሬ አልባ ትሆናለች። በኤልያስ ኃይል እና በመንፈስ ቅዱስ የተሞላው ታላቁ ሰው ኤልሳዕ ማሰሮውን ከነጨዉ ይዞ ካልመጣ ምድሪቱም ፍሬዋን መጨነገፏን ውኃውም ምሬቱን እና ክፋቱን መቀጣላቸው አይቀርም። የውኃው መሬት ያልነካት ሰዎች ያልተገለገሉባት አዲስ ማሰሮ ለውኃው መፈወስ ታስፈልግ ነበር መራራውን ውኃ ማጣፈጥ የሚቻለውን ጨው ይዞ መገኘት የሚችል የለምና። ይህችውም እመቤታችን ናት።

በመሬት የተመሰለው መርገም ሥጋ መርገመ ነፍስ ያልተገኘባት ዕድፈት እና ርኩሰትም የሌለባት አዲስ ማሰሮ፤ በመራራው ውኃ መካከልም ሞትንና ጭንገፋን ለማስቀረት ጨውን በውስጧ ይዛ የተገኘች የውኃው ሕይወት ናት።

ውኃው በጥንተ አብሶ ይመሰላል ከውኃው የተነሣ ምድሪቱም ፍሬዋን እንደጨነገፈች በጥንተ አብሶ ምክንያት ምድራችን አንድ ስንኳን ኪኅኪኦት ንጹሕ የሆነ ሰውን ማስገኘት እንዳልቻለች ያሣያል። ከአቤል እስከ ዘካርያስ ደማቸውን ያፈሰሱ፤ በየዋህነት የተገደሉ ልጆች ቢኖሯትም አንዱም እንኳን በጽድቁ ሊያጸድቃት፤ በቅድስናው ሊፈውሳት አልቻለም እንዲያውም እነሳቸውም ቢሆኑ ከመራራው የኢያሪኮ ውኃ ጠጥተዋልና ሞት እና ጭንገፋ ታይቶባቸዋል።

ከዚህ ሁሉ ነጻ የሆነች አዲስ ማሰሮ ጨው ይዛ መገኘቷ ለፈውስ ሥራ እጅግ አስፈላጊ ነው። አለበለዚያማ ፈውስ እዴት ይመጣል?ኢትዮጵያዊው ቄርሎስ የተሰኘው የጋስጫው ክስብ አባ ጊዮርጊስ፡- ጨው ተብሎ የተጠራው አልጫውን ዓለም ያጣፈጠው የድንግሊቱ የማሕጸን ፍሬ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው[49] ሲል አዲሲቷን ማሰሮ ደግሞ እመቤታችን መሆኗን የሶርያው ሊቅ ቅዱስ ኤፍሬም "ልሕኩት ንጽሕት" ንጽሕት ማሰሮ ሲል ይመሰክርላታል።

እውነት ነው! መርገም ባመረረው ዓለም ውስጥ የዓለም ምሬት እስኪጠፋ ድረስ ይህን የሚያደርገውን ጌታ በማሕጸኗ ተሸክማ በዓለም ውስጥ ኖረች እንጅ ወደተቀደሰው የመላእክት ከተማ ሄዳ አልወለደችውም[50]። ወደ ጽርሐ አርያም አልወጣችም፤ የረከሰው ዓለም ይቀደስ ዘንድ በዚህ ዓለም ወለደችው እንጂ። እናም የአዲሲቷ

49. ሰዓታት
50. መ.ምሥጢር

ማሰሮ ጨውን በውስጧ ይዛ በመራራው ውኃ ውስጥ መገኘት ለውኃው ፈውስ ነው እመቤታችንም በዚህ ክፉ ዓለም ክርስቶስን ጸንሳ መገኘቷ እርሷን በሔዋን መርገም አያስጠረጥራትም መራርነትን የሚያስወግደው ጨው መገኛ ናትና።

ለዚህ ነው ከላይ ስሙን የጠራነው ሊቅ "በጻዕር እና በጭንቅ ትወልድ ዘንድ የፈረደባት ማሕጸን ነበረች ዛሬ ግን የሕይወት ውኃ የክርስቶስ መገኛ ሆነች" ሲል የሚገረመው። እንዲገረም ያደረገው እኮ እስከዚች ቀን ድረስ ከዓለም ርኩሰት ነጻ የሆነ ሰው ተጸንሶ አያውቅም ነበር። ስትጸንስ ያለ ወንድ ዘር የጸነሰች ስትወልድም ያለምጥ እና ያለ ጻዕር የወለደችም ሌት ከሔዋን ጀምሮ በምድራችን አልነበረችም። ዛሬ ግን ተገኘች፣ ይህችውም እመቤታችን ድንግል ማርያም ናት።

እመኑኝ ሰዎች! ከእንግዲህ በኋላ ሞት እና ጭንገፋ አይኖርም። አዲሲቷ ማሰሮ ምሬታችንን ያጠፋውን ጨው ይዛ አሁን በመካከላችን ናትና ሞት በመሸነፍ ተውጧል። መቃብርም አሁን ባዶውን ቀርቷል ኤልሳዕ ሕገ ወንጌልም "ፈቅጃለሁ ንጻ" ብሎ በውኃው ለተመሰለ ባሕርያችን ተናግሯል ማቴ 8፥3

ባሕርያችን አሁን ከምሬቱ ማለትም ከፍዳው እና ከመርገሙ ተለይቶ ንጹሕ ሆኗል። "ሁሉም በደሉ አብረውም ረከሱ አንድ ስንኳ በጐ ነገርን የሚያደርጋት የለም" መዝ 52፥3 ተብሎ በተነገረለት ዓለም ውስጥ "ኃጢአትን አላደረገም በአንደበቱም ሐሰት የለበትም" ኢሳ 53፥9 ተብሎ ተነገረለት። ይህ ለተደረገበት ማሕጸን አንክሮ ይገባል።

የሰው ልጆች የዕርቅ መሠረት የተጣለበት የዕርቅ ሰነድም ነው- ማሕጸነ ማርያም። ዕርቁ በሰው እና በእግዚአብሔር መካከል የተፈጸመ ነው። ቅድስት አሪት እንደተናገረች ያለ ደም ስርየት ባለመኖሩ ዕርቁ ውጤት ያመጣው እና ድኅነቱ ፍጹም የሆነው በጌታ ደም መፍሰስ በዕለተ ዓርብ ቢሆንም መሠረቱ ማሕጸነ ማርያም ለመሆኑ ግን አሌ የማይባል ሀቅ ነው።

ምክንያቱም እግዚአብሔር ራሱ ረግሞ ከገነት ያባረረውን የሰው ልጆች ባሕርይ ወርሶታልና ነው። አይገርማችሁም! ማደሪያውን ገነትን አስለቅቆ በግድ ከማደሪያው እንዲወጣ ያደረገውን ሥጋ ዛሬ ግን እንደታረቀው ለማጠየቅ ሲያድርበት ሊዋሐደው በድንግሊቱ በኩል አማላጅ ላከባት እኮ! ድንግሊቱም እሽ ብላ ታዘዘችለት፤ እርሱም ወዶ ፈቅዶ ሥጋን ተዋሕዶ መታየቱ የዕርቅ ምልክት እንጅ ሌላ ምን ይባላል።

የሰው እና የእግዚአብሔር ጠብና መለያየት የተጀመረው እኮ ሔዋን ምክረ ሰይጣንን ሰምታ ዕፀ በለስን ከበላችበት ጊዜ ጀምሮ ነው እንጅ እግዚአብሔር በሠርክ መጥቶ አዳም እና ሔዋንን ባሰናበተበት ጊዜ አይደለም በመካከሉ ከአምስት ሰዓት ያላነሰ ከስድስት ሰዓት ያልበለጠ ጊዜ ሰላለ ማለት ነው። የዕርቁም ጉዳይ ደርሶ በአንድ ጊዜ በዕለተ ዓርብ የተፈጸመ አይደለም በዕለተ ጽንስ ተጀምሮ በዕለተ ዓርብ ተፈጽሟል እንጅ።

እስኪ አስቡት! ምን ያህል አስደናቂ ምሥጢር እንደሆነ፤ ሰው ከጸጋው ተራቁቶ፣ በፈጣሪው ፊት ለብሶት የሚቆመው አጥቶ ከፊቱ ለመሸሽ ይሽሎጠጐጥ በነበረበት ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት የሚታይ ጸጋን ይዞ መገኘት አምላክ በላከው መልክተኛም "..... ምልዕተ ጸጋ" ተብሎ መመስገን አያስደንቃችሁም?

ከዚያ በላይ በደለኛው ፍጥረት ወደ በደለው አካል መሄድ ሲገባው የተበደለው መላክ መምጣቱ።

ለነገሩ በመጀመሪያይቱ ሔዋን ዕራቁታቸውን በመሆናቸውና አፍረው የማያውቁትን በማፈራቸው አንገት ለአንገት ተናንቀው ሲላቀሱ ወደ እነርሱ ቀርቦ ኑሃዜአቸውን የተቀበላቸው ራሱ ጌታ ወደ እነርሱ መጥቶ እንጅ እነርሱ ወደ እርሱ ሄደው አይደለም፤ በዚህም ዓለም የሚድነው በእርሱ ወደ ዓለም መምጣት እንጅ በሰው ልጆች መባና መሥዋዕት አለመሆኑን አስረድቶናል።

የፍጥረት አለቆች አዳም እና ሔዋን በፊቱ መቆም ያልቻሉትን የአዳም እና የሔዋን ልጅ ድንግል ማርያም እንደምን ወሰነችው? ሰማይ እና ምድር አይወስኑትም እኮ! ቅዱስ ኤፍሬንዮስ በቅዳሴው እንደተናገረው ዓሣዎች የማይዋኙት ጥልቅ ነው፤ ንስሮች የማይበሩት ምጡቅ ነው፤ ኪሩቤል የማያዩት ረቂቅ ነው፤ ነፋሳት ሩጠው የማይደርሱበት ሰፊ ነው፤ አሳታውያኑ ኪሩቤል ሊነኩት የማይቻል አሳት ነው፤ ከአርያም በላይ የሚገኝ ልዑል፤ ከበርባሮስም በታች ያለ እረጅም ነው፤ ከዚያም በላይ ነው ነገር ግን ለመለኮት ነውና ላይገርመን ይችላል መለኮት ሁሉን ይችላል እና። በጣም የሚገርመው በአንዲት የ15 ዓመት ብላቴና ማሕጸን ሲወሰን ከሚያንጸባርቀው ዙፋኑ ከሚወጣ ብርሃናዊ ክብሩ የተነሣ ፊቱን ለማየት ብርሃናውያኑ ፍጡራን ፊታቸውን በክንፎቻቸው የሚጋርዱለት እርሱን በማሕጸኗ ተሸከመችው።

እነርሱ ዙፋኑን እንኳን እንዳያዩ ነው የሚለው አባ ጊዮርጊስ ፊታቸውን ይሸፍናሉ እርሷ ግን ዙፋን ሆነችው ሦስት ክንድ ከስንዝር ሆና ሳለ የማይወሰነውን ወሰነችው፤ ጠባብ ሆና ሳለ ሰባቱ የአሳት

መጋረጃዎች በማሕጸኗ ተዘረጉ የሚይስደነግጠው እና የሚያስፈራው ኪሩቤል የሚሸከሙት ዙፋን በማሕጸኗ ተዘጋጀ።

እንዲያውም አባ ሀርያቆስ ገርሞት በልቡናው ይህን እያሰበ እመቤታችንን በመንፈስ ቅዱስ ይጠይቃታል። "ኪሩቤል የሚሸከሙት ዙፋን በማሕጸንሽ በወዴት በኩል ተዘጋጀ በቀኝ ነውን በግራ? ሙሴ በደብረ ሲና ያያቸው ሰባቱ የአሳት መጋረጃወችስ በወዴት በኩል ተዘረጉ ጥበትን ከስፋት ጋር እንደምን አስተባብረሽ ያዝሽ? "እያለ በቅዳሴው አግራሞቱን ገልጿል።

ነገሩ የሚገርም ነውና አነሣው እንጅ ልመርምረውስ ቢል እንደምን ይመረመራል፤ ልቡናዬ በነፋሳት ጀርባ ላይ ይጫናል፤ ወደ ቀኝም ወደ ግራም፤ ወደ ላይም ወደ ታችም ይሄዳል፤ በነፋስ ፍጥነት ብሮጥም ደርሽበት ልመረምረው አልቻልኩም ብሎ ነው የማሕጸኗ ሥራ አስደናቂ መሆኑን የተናገረው።

አባ ሀርያቆስ በመንፈስ ቅዱስ ክንፍ በተጫነ ልቡና መርምሮ አልመረመረው ቢል ወደ አለማወቁ ተመለስኩ ብሎ ተናገረ፤ መንፈስ ቅዱስ ሰፊ ሥራ የሠራበት ማሕጸን አይደል! እንደምን ይመረመራል? መንፈስ ቅዱስ በኤልሳቤጥ ማሕጸን አድሮ የስድስት ወር ጽንስ አናግሯል ከተባለ፤ ከዚህ በላይ በሕድረት ያይደለ በኩነት አካላዊ ቃል ወልደ እግዚአብሔር የተገለጠበት ቅዱስ ሥፍራ ነው።

እንዲያው የእግዚአብሔር ጥበቡ ሁል ጊዜም ድንቅ ነው፤ ከባዱን የውቅያኖስ ውኃ ወደ ላይ ያወጣል አይደል? ነፋሳትን በዘመኑ ሁሉ ውኃውን ከጥልቁ እየተሸከሙ ለመላው የምድር ገጽ በየጥቂቱ ምድር እስክትረካ ድረስ እንዲያጠጣት ያዝዛቸው የለ? እኔም እላችኋለሁ "ለእግዚአብሔር የሚሣነው ነገር የለም"።

ነጻነት

ከኃጢአት በኋላ ለኃጢአተኛው ሰው ምን አይነት ነጻነት አለው? ኃጢአት በራሱ ባርነት ሲሆን ሲኦል ደግሞ የኃጢአተኞች እስር ቤት ነው። ነጻነቱ ነጻነትን አሳጥቶት ለባርነት አሳልፎ ሰጠው። ነጻነት የሌለው ሰው ሁል ጊዜም ተሰውሮ መኖርን ይመርጣልና ከነጻነት የተለየው ሰው አዳም በዚያች ዕለት ያከናወነው የመሰወር ፍላጐት ከዚህ የመነጨ ነው። ፍርሀት፣ ጭንቀትና ድንጋጼ እነዚህ ሁሉ ተሰብስበው ነጻነቱን ገፈፉት።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ኃጢአት ተጣብቶት ከእርሱ ወደ ልጆቹ መተላለፍ ጀመረ። እሱም ቁራኝነትን አስከተለ፤ ያም ማለት ሰይጣን በእባብ አድሮ ሰውን አስቶ ፈቃዱን ከፈጸመበት በኋላ የሰው ልጆችን ባሕርይ ተቆራኝቶ ነው የኖረው።

በ5500 ዓመታት የዓለም ታሪክ ውስጥ ከቁራኝነት ነጻ ሆኖ መወለድ የተቻለው አንዳችም ሰው ለዚህች ዓለም የላትም። ሁሉንም ሰይጣን ከማሕጸን ጀምሮ ተቆራኝቷቸው ይኖራል እንጂ። ከሞትም በኋላም ቆራኝነቱ አይቋረጥም፤ ሥጋቸውን በመቃብር ተቆራኝቶ፣ ነፍሳቸውንም ሲኦል አግቶ ይኖር ነበር። በአጸደ ሥጋ ሲኖሩ ኃጢአት ያሠራቸዋል። ጣዖት ያስመልካቸዋል።

ክፉ ዛፍ መልካም ፍሬን ማፍራት አይችልምና አዳም እና ሔዋን በጥንተ- አብሶ በተለወጠ ኃጢአተኛ ባሕርያቸው ንጹሕ ሰውን ከአባት አብራክ፣ ከእናትም ማሕጸን ማስገኘት አልተቻላቸውም። የተወለደው ሁሉ ከአባት እና ከእናቱ የኃጢአት ውርስ ተካፍሎ ወደ እዚህች ዓለም ይመጣና እርሱም ከማሕጸን ጀምሮ በወረሰው ጥንተ አብሶ

መሠረት ላይ ተነስቶ ሌሎች የኃጢአት ሕንጻዎችን እየገነባ ዓለምን በምልዐተ ኃጢአት ሲያጥለቀልቃት ይኖራል።

ታዲያ አምላካችን ክርስቶስ ይህን ሊያፈርስ ያለ ኃጢአት በነጻነት ወደዚህ ዓለም መጥቶ በማሕጸነ ማርያም ሲያድር ቁራኝነት ከሰው ዘር ተወገደ። በዓለማችን በረጅሙ የዓመታት ታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ ከቁራኝነት ነጻ የሆነ አዲስ ሰው ተጸነሰ።

ከመጀመሪያው ሰው ከአዳም በቀር ይህ የተደረገለት ከኃጢአት እርሾ ነጻ የሆነ ከሰው ልጆች ማንም አልነበረም። እሱም ቢሆን ኃጢአት አስረጅቶታል ፤ይህን ያስወግድ ዘንድ ሰው እንደሆነ ለማጠየቅ አባ ሀርያቆስ በቅዳሴ ማርያም "ወብኪ ተሐደሰ ቀዳሜ ኩሉ ፍጥረት፤ የፍጥረት ሁሉ መጀመሪያ ባንቺ ታደሰ" ሲል ከድንግል የተጸነሰው ያለ ኃጢአት የሆነ ንጹሐ- ባሕርይ አዳም መሆኑን ይመሰክራል። እናም ማሕጸነ ማርያም ማለት የፍጥረት ሁሉ መታደስ የተረጋገጠበት፣ የሰው ልጆች ነጻነት የተጻፈበት የነጻነት ሠሌዳ ነው። አንድ ሊቅ በሃይማኖተ አበው "አ! ማሕጸን እንተ ባቲ ተጽሕፈ መጽሐፈ ግዕዛንነ፤ የነጻነታችን ደብዳቤ የተጻፈበት ማሕጸን እንደምን ያለ ነው! ብሎ ያደንቃል።

ከምጥ፣ ከጻዕር፣ ከጋዕር ተለይታ የወለደች ማሕጸን፤ ከርስሐት፣ ከልማደ አንስት፣ ከዘርዐ ወራዙት ተለይታ የጸነሰች ማሕጸንም የለችም፤ እመቤታችን ግን ከዚህ ሁሉ ነጻ ሆና ቀጣዩን ትውልድም ከጥንተ አብሶ ነጻ አደረገችው። ከዚያ በኋላ የተነሣው ትውልድም "በነጻነት ልንኖር ክርስቶስ ነጻነት አወጣን" ገላ 4÷31 ብሎ ለመናገር በቃ።

ጌትነት

አዳም ሲፈጠር ጀምሮ ከወረሳቸው ጸጋዎች መካከል አንዱ ጌትነት ነው። በመጽሐፍ ስለ እርሱ መንፈስ ቅዱስ የተናገረው ነገር ምንኛ ድንቅ ነው! "ምድርን ሙሉአት ግዙአትም የባሕር ዓሣዎችንና የሰማይ ወፎችንም ግዙአቸው" ዘፍ 1፥28 ብሎ እግዚአብሔር ባረካቸው በማለት የሰው ልጅ ለምድር እና በውስጧም ላሉት ጌታ ሆኖ መፈጠሩን ያስረዳል። ከዚያ ሁሉ በላይ ደግሞ ክብርት ሕይወቱን እንዲጠብቅ በእጁ አደራ የሰጠው ታላቅ ፍጥረት ነው። ሌሎች ፍጥረታት በተፈጥሮ የእግዚአብሔር ገንዘቦች ሲሆኑ የሰው ልጅ ግን ልጁ ነው።

ከዚህ ክብሩ የተነሣ የእግዚአብሔርን ጌትነቱን በጸጋ ወርሶ የመለኮት ባሕርዩ ተካፋይ የሆነ ብቸኛ ፍጥረት ነው። ራሱን መግዛት ሲያቆም ጌትነቱ በቅፅበት ተወሰደበት። የጌትነት መሠረቱ ራስን መግዛት ነው። ይህን ማድረግ ባለመቻሉ ከእንስሳት እንደ አንዱ ሆኖ ተቆጠረ፤ ከቅዱሳን አንዱ በመጽሐፍ "ሰውስ ክቡር ሲሆን አላወቀም አዕምሮ እንደሌላቸው እንደ እንስሳትም ሆነ" መዝ 48፥10 ብሎ እንደተናገረ። እንዲያውም የሥነ ፍጥረት ምሁራን እንደሚናገሩት ከሌሎች ፍጥረታት ተለይቶ ቆሞ የሚሄድ መሆኑ ገዥነቱን የሚያመላክት ሲሆን ሌሎች ፍጥረታት እንስሳት አራዊት ዝቅ ብለው ምድር ምድር እየተመለከቱ እንዲሄዱ ሁነው መፈጠራቸው የተገዥነታቸው ማሳያ ነው ብለውናል።
ምንም እንኳን በጌትነት የተፈጠረ ልዑል ፍጥረት ቢሆንም ከዚህ ጌትነቱ ጋር አብሮ መቆየት አልተቻለውም፤ በኃጢአት ምክንያት ወደ ባርነት ተለወጠ፤ የጌትነቱን መልክ አጥቶ የባሪያ መልክ ያዘ፤ እርሱ

በኃጢአት ላይ ነገሠ፤ ኃጢአትም በእርሱ ላይ ነገሠች፤ ኃጢአትን የሚያደርግ ሁሉ የኃጢአት ባሪያ እንደመሆኑ የኃጢአት ባሪያ ሆነ ዮሐ 8፥34

በእርሱ ፈንታ ዓለማችን በሌላ ገዥ እጅ ወደቀች፤ እውነተኛውን ፍርድ ከፈጣሪው አግኝቶ ወደ ውጭ እስከተጣለበት ጊዜ ድረስ ከአዳም በላይ የጌትነት እድሜ ተሰጥቶት ዓለምን ገዛ።

ጌትነትን በጸጋ እግዚአብሔር የተቀበለው አዳም ደግሞ በተቃራኒው "አዳም ገብሩ ለዲያብሎስ፤ ሔዋን አመቱ ለዲያብሎስ" ተብለው ተጠሩ፤ ባርነቱ ጌትነቱን ብቻም ሳይሆን ልጅነቱንም አስነጠቀውና ለልጅ እንጅ ለባሪያ ከማይገባው ከአባቱ ከእግዚአብሔር ከተማ ከገነት አስወጣው።

ምክንያቱም ቅድስት ወንጌል እንደተናገረች ባሪያ ለዘለዓለም በቤት አይኖርምና ዮሐ 8÷35 ከቤት ውጭ ሥጋው በመቃብር ነፍሱ ደግሞ በሲኦል እንዲኖር ግድ ሆነ። እንዲህ ሆኖ ዘመናት አለፉ፤ ለአዳም ራሱን የገዛ ልጅ፤ ከኃጢአትም ንጹሕ የሆነ ሰው ሊገኝለት አልቻለምና። እንዲያውም ታላላቅ ሥራዎችን የሠሩ ቅዱሳን ልጆቹ ሳይቀር በቁጭት ቃል "ሞት እስከዚህ ቀን ድረስ ገዛን" ሮሜ 5፥14 ሲሉ እንደነበር የክርስቶስ ሐዋርያ ይናገርላቸዋል።

ዛሬ ግን የድንግል ማርያም ልጅ ሰይጣን ባልጠረጠረው ጥበቡ በማሕጸነ ማርያም ተሰውሮ፤ ኃይለኛውን አስሮ ከሥልጣኑ ሻረው። በመጽሐፈ ኪዳን እንደተነገረው ራሱ ሞት "ሥጋን ለብሶ ከሥልጣኔ የሻረኝ ይህ ማን ነው?" እያለ በዐውደ መስቀል ይናዘዝ ነበር፤ ጦረኛው ሞት ተረታ፤ ብዙዎችን የማረከው ዲያብሎስ ተማረከ፤ ይህ የሹም ሽር ሥርዓት የተጀመረው ደግሞ በማሕጸነ ማርያም ነው።

መላኩ ገብርኤል እንደተናገረው በማሕጸነ ማርያም የነገሠው ክርስቶስ እግዚአብሔር አምላክ የዳዊትን የአባቱን ዙፋን የሚሰጠው ለመንግሥቱም ፍጻሜ የሌለው ንጉሠ ነገሥት ነውና። በዚህም የአዳም ባሕርይ ከቀደመው ይልቅ ወደ ተሻለ ጌትነት እንደመጣ እናምናለን። እግዚአብሔር እንደተናገረ "አዳም ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ"ብሎ ዘፍ 3፥22 አዳም ከሦስቱ አካላት እንደ አንዱ ሆኖ በማይቋረጠው ምስጋና የተመሰገነበት ዘመን ነው። የጸጋ የነበረው ምስጋና ለአዳም ባሕርይ የሚስማማ የባሕርዩ ሆነ፤ የክርስቶስ ባሕርይ የአዳም ባሕርይ ነውና።

አሁን የሰው ልጅ የባርነቱ ደብዳቤ ተቀዶ፣ ነጻነቱ ታውጆ በሥልጣን እንዲኖር ተፈቅዶለታል፤ ያውም ከሥልጣን ሁሉ አንቀጥቅጦ በገዛን ጥንተ ጠላታችን ላይ መሾም እጅግ ደስ የሚያሰኝ ሥልጣን ነው። ለሰው ልጆችም የተሰጠው ሥልጣን ይሄው ነው ማቴ 10፥1 ከዚህ በኋላ ከእርሱ መከራን ከተቀበልን ከእርሱ ጋር አብረን እንነግሣለን።

እንዲያውም "ባሪያዎች ሠልጥነውብናል ከእጃቸውም የሚታደገን የለም..... የልባችን ደስታ ቀርቷል አክሊል ከራሳችን ወድቋል" ሰቆ ኤር 5፥18፤15 ብሎ ይናገር የነበረው የሰው ልጅ ዛሬ ግን እንዲህ አይናገርም። ከፍ ካለ ተራራ ላይ ቆሞ "ተውህበ ሊተ ኵነኔ ሰማይ ወምድር፤ በሰማይ እና በምድር ሥልጣን ተሰጠኝ ማቴ 28፥18 ብሎ ይናገራል እንጅ። ክብሩን አጥቶ ለተለያዩ ጣዖታት እንዳልሰገደ ዛሬ ግን ፍጥረት ሁሉ ይሰግድለታል ፊል 2፥10

ይህ ሁሉ የሆነው በ15 ዓመቷ ብላቴና በእመቤታችን ማሕጸን ነው። ከመጀመሪያይቱ ሔዋን የኃጢአት ባሪያ ቃኤል ማሕጸኗን የሚፈታ በዙር ሆኖ ተወለደ፤ ከሁለተኛይቱ ሔዋን ደግሞ ለጌትነቱ መጨረሻ የሌለው ጻድቁ ባሕርይ ክርስቶስ ማሕጸኗን ሳይፈታ የበዙር ልጇ ሆነ።

ገና በአባታችን በአዳም ወገብ በእናታችንም በሔዋን ማሕጸን በነበርን ጊዜ ያጣነውን ጌትነት ደግሞ በማሕጸነ ማርያም አገኘነው።

አሁን ግን በክርስቶስ በኩል ባገኘነው ድል ሐዋርያው እንደተናገረው "ጠላቶቹን ሁሉ ከእግሩ በታች እስከሚያደርግ ድረስ ሊነግሥ ይገባዋል" 1ቆሮ 15፥25

መንፈስ ቅዱስ ስለ እመቤታችን

ስንኳን የሰው ቅድስናና ንጽሕና የእግዚአብሔርም የማያጠራጥረው ጌትነቱ ያለምስክር ሊረዳ፣ ሊረጋገጥ ስለማይችል የእመቤታችንም ቅድስናዋንና ባለሟልነቷን ያረጋገጥነው መንፈስ ቅዱስን ምስክር አድርገን ነው። መንፈስ ቅዱስ ለሰው የሚመሰክረው በተለያየ መንገድ ነው፤ በተአምራት፣ ደጋግ ሰዎችን በማሥነሣት፣ ግዕዛን ባላቸው እና በሌላቸውም ሥነ - ፍጥረታት ላይ በማደር ከተፈጥሮአቸው ውጪ ታላላቅ ነገሮችን እንዲያደርጉ በማድረግ ሊሆን ይችላል።

ለእመቤታችንም ፈጥኖ በተደረገ ሦስት ምስክር ወላዲተ አምላክ መሆኗን መሰከረላት።

1ኛ ቅዱስ ገብርኤል

ይህ መላክ ቀደም ሲል እንዳነሣነው ከእግዚአብሔር የተላከ መሆኑን በብዙ መንገድ የገለጸ ሲሆን ከዚያ በመቀጠል የእመቤታችንን ክብር በሰፊው ይገልጻል። ለክብሯ እንደሚገባ ሦስት ጊዜ ስግደትን ካቀረበ በኋላ የንጉሥ ማደሪያ ናትና የሚያምረውን ውዳሴ ልብን በሚመስጥ ድምፀ ቃና ለክብሯ እንደ ሚገባ አድርጐ አቅርቦላታል፤ ከዚህም የተነሣ የመጀመሪያው ውዳሴ ማርያም ደጋሚ መላክ ብለው ይጠሩታል፤

በዚህም መንፈስ ቅዱስ እመቤታችን ከፍጥረት ሁሉ የከበረች ቅድስት መሆኗን አስመሰከረ።

እናታችን ሔዋን ዕፀ በለስን በልታ ባደረገችው ዓመፃ በሰው ዘር ላይ በአጋንንት ይደርስ የነበረው ሽሙጥ እና እንግልት የሚያልቅበት ዘመን እንደደረሰ ለማጠየቅ በፊቷ ቆሞ ውዳሴን ያቀርብላታል። ለቀደመችው ሔዋን ሰይፍን መዝዘው ግሩማን ሆነው ከታዩት መላእክት አንዱ ቅዱስ ገብርኤል ነበር፤ ዛሬ ግን ከፊቱ ለተቀመጠችው ሔዋን ሰይፍን አይደለም፣ የምስጋና እጅ መንሻን ይዞ ቀረበ። ያችኛዋ እኩ የቃኤል እናት ናት ምን ብሎ ያመስግናት፤ ይህችኛዋ ደግሞ የንጉሥ ክርስቶስ እናት ናት፤ ክብራቸው ልዩ ልዩ ነው።

የመከራው ዘመን ማብቃቱን፣ የምሕረት ዓመት መጀመሩን መንፈስ ቅዱስ መጀመሪያ የገለጸው ለእመቤታችን ነው። "ተፈሥሒ ፍሥሕት" ማለቱ መርገም እንደተወገደ፣ መዓዛ ንጽሕናዋ በእግዚአብሔር ዘንድ እንደተወደደ የሚያመላክት ቃል ነው። የመጀመሪያይቱ ሔዋን ከገነት ስትባረር "በሕማም በጭንቅ ትወልጃለሽ" የሚለውን የመርገም ቃል ሰምታ ነበር- የወጣችው፤ እመቤታችን ግን የስደተኞች ማረፊያ ገነት ክርስቶስን ስትጸንስ ከመጽነሷ አስቀድሞ በጆሮዎቿ የምስጋናን ቃል ሰማች ::

ከዚያ አያይዞም በክብር የሚተካከላት የሌለ መሆኑን ጨምሮ ሲገልጽ "አ! ምዕልተ ጸጋ" አላት። እስከ ዚህች ቀን ድረስ ጸጋው በመላት የተሰጠው ሰው ከሴቶችም ከወንዶችም መኖሩን መጽሐፍ አይነግረንም፤ ስለ እመቤታችን ግን ይሄ ቃል በእውነት ተነግሯል። እንዲያውም ሊቁ ቅዱስ ባስልዮስ እመቤታችንን ሲያመሰግናት "ወሀብተ ሰማያት

ለማርያም ድንግል፤ ሰማያዊ ሀብት ለድንግል ማርያም ተሰጣት" ሲል በሥርዓተ ቅዳሴ ያመሰግናታል።

ሊቁ እንደተናገረው ለሚካኤል ምሕረት፣ ለገብርኤልም ብሥራት፣ ለሙሴ ሕግ፣ ለአሮን ክህነት በማለት ለእያንዳንዱ ፍጥረት ጥቂት ጸጋ እንደተሰጠው ከተነገረ በኋላ ስለ እመቤታችን ክብር ሰማያዊነት የማያጠራጥር ምስክርነቱን ሰጥቷል። በእውነት ይህ ነገር ምንኛ ድንቅ ነው! ሰማያውያኑን አልፎ ለምድራዊቷ ታናሽ ብላቴና እንዲህ ያለ ጸጋ መስጠት አስደናቂ ነው።

ቅዱስ ባስልዮስ በዚህ አንቀጽ ውስጥ መግለጽ የፈለገው ነገር ጸጋው ከሰማይ የመጣ የሰማያዊው አምላክ ስጦታ መሆኑን ብቻ ሳይሆን ጸጋዋ ከሁሉም በላይ መሆኑን የሚገልጽ ሀሳብ ነው- ያለው። ሰማይ ከሁሉ በላይ የተቀመጠ፣ ከእግዚአብሔር በቀር ከእርሱ በላይ ሌላ ፍጥረት የሌለ ታላቅ እና ሉዓላዊ ፍጡር ነው፤ እመቤታችንም ከፈጣሪ በቀር በክብር የሚተካከላት የሌለ መልዕልተ ፍጡራን ናትና።

እንደዚያማ ባይሆን ኖሮ የሌሎችስ ጸጋ ከሰማይ ነው እንጅ ከምድር የተገኘ ነውን? በጎ ስጦታዎች በሙሉ ከሰማይ አባት የሚሰጡ አይደሉምን? መንፈስ ቅዱስ በቅዱስ ገብርኤል በኩል የገለጸውን ታላቅነቷን ነው በቅዱስ ባስልዮስም በኩል የገለጸው፤ ትውልድ ሁሉ በአጸደ ሥጋ፣ በአጸደ ነፍስ ብፅዕት እስኪላት ድረስ በቀደመችው ሔዋን ምክንያት በሴቶች ላይ የነበረ ጥላቻም እስኪወገድ ከሩቅ የሚጣራ ሕያው የምስጋና ቃል ነው።

2ኛ ተናጋሪው ጽንስ

ዕለቷቱ ከዕለታት ሁሉ የተለየች ናት። ሰማይ፣ ከሰማይ በላይ ያለው ሰማይ ከተሸከሙት የሚበልጥ የሆነ ሌላ ምሥጢር በምድራችን ላይ የተገለጠባት ዕለት። ስለዚህ ምሥጢር ታላቅነት ሲናገር አንዱ በመጽሐፍ የተናገረው የሚገርም ነው። "ይህ ምሥጢር ታላቅ ነው" ኤፌ 5፥32 ብሎ ነበር። የልዑሉ ትሑት መሆን፣ የኃያሉ አምላክ መድከም፣ ከብርሃን የተገኘው ብርሃን ሰው ሲሆን፣ ቤተክርስቲያንም የመለኮትን ባሕርይ በጸጋ ተካፍላ አካሉ ስትሆን ከማየት በላይ ሌላ ምን ይገርማል።

ታዲያ በዚህ ዘመን ከሰማይ መላእክት በማሕጸን እስካለ ፍጥረት መናገር የጀመረበት ጊዜ ነው። ስሕተት በተጀመረባት በዚያች ቀን ከመጀመሪያዋ ቀን ፍጥረታት ከቅዱሳን መላእክት ጀምሮ በስድስተኛዋ ቀን እስከተፈጠረው የሰው ልጅ ድረስ አርምሞ የነገሠበት፣ ከሰማይ እስከ ምድር ሁሉም ፍጥረት ዝም ብሎ የዋለባት ዕለት ነበረች።

ያ የሚያበራው የአጥቢያ ኮከብ ሲጨልም፣ ተወርዋሪው ኮከብ ጉዞውን ሲያቆም የሁሉን አንደበት ዘጋ፤ ራሱም እንኳን የሰው ልጆች አባት አዳም በመገረም ተዋጠ። እንደ ፀሐይ ጸዳል የሚያበራው ፊቱ ተለወጠ። የኃጢአት ፍጻሜው ይህ አይደል! ሰው በእግዚአብሔር ፊት የእግዚአብሔርን ሕግ ሽሮአልና ምን ብሎ ይናገራል?

ክፋትን በደግነት፣ ጨለማን በሚያስደንቅ ብርሃን መለወጥ የሚቻለው አምላክ ክፉውን ቀን በመልካም ለውጦ ዝምታውን በመናገር ሊለውጠው ዝምታውን ከማሕጸን ጀምሮ ፈታላቸው። ዝምታ ሲጀመር ዓለመ አዳም ገነት፣ ዓለመ መላእክት ሰማያት፣ በዝምታ የተዋጡባት

ያች ሰዓት ከቀኑ ስድስተኛዋ ሰዓት ላይ ነበረች፤ ዛሬ ደግሞ ዝምታ ከማሕጸን ጀምሮ የተወገደበት 6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው። ያን ጊዜ በነቢይ የተነገረው ተፈጸመ "እውነት ከምድር በቀለች ጽድቅም ከሰማይ በቀለች" መዝ 4፥11 6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ኃጢአት የዘጋውን አንደበት የሚከፍት ዘመን በመሆኑ በስድስተኛው ወሩ ጽንሱ ዘለለ። እናቱ ኤልሳቤጥ ስለዚህ ስትናገር "ጸንሱ በማሕጸኔ በደስታ ዘለለ" ስትል የዘለለበትን መንገድ ትገልጸዋለች።

ያኔ የሰው ልጆች ዝም ባሉበት ቀን ምኞቱ ተሳክቶለት በደስታ የዘለለው ጥንተ ጠላታችን ሰይጣን ነበር፤ ዛሬ ደግሞ ተረኛው የሰው ልጅ ሆነና የመካኒቱ ልጅ ዮሐንስ በደስታ ዘለለ። ይህን ተአምር ተከትሎ ያስተማራት ሳይኖር ኤልሳቤጥ የእመቤታችንን ክብር አወቀች በትሕትና ቀለም እንዲህ ስትል መለሰች "የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እኔ ማን ነኝ" አለች ምክንያቱንም ስትገልጽ "እነሆ የሰላምታሽን ድምፅ በሰማሁ ጊዜ ጽንሱ በማሕጸኔ ዘሏልና" ነበር ያለችው።

ወንጌላዊው እንደተናገረው በኤልሳቤጥ ላይ አድሮ ያለ መንፈስ ቅዱስ የእመቤታችንን ክብር ይገልጽ ዘንድ ይህን አደረገ። 6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እስትፋስ ያለው ሁሉ ከታናሽ እስከ ታላቅ ለእመቤታችን ምስጋና እና ስግደትን ማቅረብ የሚገባው መሆኑን ያመላክታል። ማኅደረ እግዚአብሔር ናትና ለልጇ ክብርን የሚሰጡ ሁሉ ለእናቱም ሁሉ ክብርን ሊሰጡ እንደሚገባ የታመነ ነው።

አስኪ ኤልሳቤጥን ተመልከቷት! የጌታየ እናት ወደኔ ትመጪ ዘንድ .... አለች እንጅ ጌታዬን ይዘሽ ትመጪ እንዴት ይሆናል? ያለች አይደለም። ድንግል ማርያም ከሴቶች ሁሉ ልዩ ናትና ራሷን ዝቅ አድርጋ "እኔ ምንድን ነኝ" አለች ከዚህ እንደምንረዳው የእመቤታችን ክብር የመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ መሆኑን ያሳያል።

ያማ ባይሆን ለኤልሳቤጥ እመቤታችን መጽነሷን፣ በዚያውም ላይ የጌታ እናት መሆኗን በምን አወቀች? የሰውን ማንነቱን ሳይነግሩት የሚያውቅ ከእርሱ በቀር ሌላ ማን አለ? ዮሐ 2፥25 አንደበትን የፈጠረ እርሱ በእውነት እርሱ ኤልሳቤጥን መሣሪያ አድርጎ የድንግሊቱን ክብር ተናገረ እንጂ ኤልሳቤጥ ይህን አልተናገረችም። ወንጌላዊው አስቀድሞ "በኤልሳቤጥ ላይ መንፈስ ቅዱስ ሞላ" ብሎ መናገሩ ስለዚህ አይደል? ከዚያም በላይ ስለ እውነት እውነትን መናገር በጀመረበት ጊዜ እኛ የምንናገር አይደለንም፤ የሰማዩ አባታችን ይናገራል እንጂ፤ ወንጌል እንደተናገረ ማቴ 10፥20 በኤልሳቤጥም የሞላው መንፈስ ቅዱስ ድንግሊቱን አመሰገነ፤ አከበረ። እውነት ነው ድንግል የአምላክ ማኅደር ናትና ክብር ይገባታል።

እንግዲህ ምን እንላለን እንደ ሰማይ ከዋክብት ከበዙት የድንግሊቱ ምስክሮች እነዚህ ሦስቱ ዋኖች ናቸው፦

- መላኩ ገብርኤል
- የስድስተኛው ወር ሰው ዮሐንስ
- ኤልሳቤጥ

የእነዚህን ምስክርነት ከተቀበለች በኋላ እሷም የባሪያውን የሔዋንን መዋረዷን፣ በእግረ አጋንንት መጠቅጠቋን ተመለከተ፤ብላ ከፍ ከፍ እንዳደረጋት ተናግራ በእኒህ ሦስት ምስክሮች ተጀመረ እንጂ እስከ ዓለም ፍጻሜ የሚነሳው ትውልድ ብፅዕት ሲላት እንደ ሚኖር ተናግራለች ሉቃ 1፥47-55

በመጀመሪያይቱ ሔዋን በደል የተረገመው ትውልድ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ "አ! ሔዋን ምንተኑ ረሰይናኪ ዘአውጻእከነ እምገነተ ተድላ፣ ሔዋን ሆይ! ተድላ ደስታ ከበዛበት ገነት እንዳንኖር ያስወጣሽን

ምን አደረግንሽ[44]" ሲላት ይኖራል በአንጻሩ እመቤታችንን ግን ብፅዕት ሲላት ይኖራል። ከገነት በወጣንበት እድሜ ዞረን ገብተን ነቀፋውን ወደ ምስጋና የለወጥንበት ዘመን ነው -15ኛው ዓመት የሔዋን እድሜ።

በኤልሳቤጥ ቤት

እመቤታችን ጌታን ከጸነሰች በኋላ ዕለቱን የተጓዘችው ወደ ዘካርያስና ኤልሳቤጥ መንደር ነው የሄደችበት የመንገዷ ምክንያት ሦስት ነገሮች እንደሆኑ ሊቃውንት ይናገራሉ።

- ዘካርያስ ታሟል ብለዋት ለመጠየቅ
- መላኩ የኤልሳቤጥን መጽነስ ነግሯት ነበርና ካረጀች በኋላ የመጽነሷን ነገር ልታይ
- ምስክር ሦስት ለማድረግ (ቅድም የጠቀስናቸውን ምስክሮች ማለት ነው)

በእነዚህ ሦስት ምክንያቶች የሄደችው እመቤታችን በተራራማው የኤፍሬም ሀገር በይሁዳ ከተማ ሦስት ወራትን አሳልፋ ነበር- የተመለሰችው። የኤልሳቤጥ የመውለጃዋ ወራት ሲደርስ ግን በፈቃደ እግዚአብሔር ወደ ቤቷ ተመለሰች። በዚያ ዘመን አራስ ሴት የረከሰች ናትና ንጽሕት የአምላክ እናት ከኦሪት ርኩሰት መሳተፍ ስለሌለባት ነው።

ከዚያ በተጨማሪም ሲጸነስ የተዘጋው የአባቱ አፍ በልጁ ደግነት ቢከፈት ተአምራቱ ልዩ ሆኖ ለዮሐንስ ባልተነገረለት፣ በዚያውም ላይ ባልተደነቀም ነበር፤ ተአምር የሚደንቀው ፈጣሪ ሲያደርገው ሳይሆን ፍጡራን ሲያደርጉት ነውና።

ሌላው በዚህ ዐረፍተ ነገር ውስጥ የምናገኘው ምሥጢር ከሦስት ወር በኋላ፣ ከሦስተኛው ክፍለ ዘመን በኋላ ወደ ቀደመ ቤታችን የሚመልሰን ጌታ ከእርሷ እንደተጸነሰ ያመላክታል።

52. ቅዳሴ ዘአትናቴዎስ

ከ6 ወር በኋላ

ከዘካርያስ ቤት ከተራራማው የኤፍሬም መንደር ከተመለሰች በኋላ እመቤታችን የኖረችው በዮሴፍ ቤት ነበር። በዚህ ወር ማብቂያ ላይ የሮሙ ንጉሥ አውግስጦስ የተባለው ቄሣር በዓለም ያለ ሰው ሁሉ እንዲቆጠር ትእዛዝ ያወጣበት ዘመን ነበር። በሮማ መንግሥት ሥር የሚተዳደር ማንኛውም ሀገር ይህን በአስገዳጅ ሁኔታ እንዲፈጽሙ አስቸኳይ ትእዛዝ ነበር የተሰጠው። የሚገርመው ነገር ጽሕፈቱም የመጀመሪያ ጽሕፈት እንደነበረ ወንጌላዊው አልደበቀንም። ሉቃ 2፥1

ይህ በአውግስጦስ የወጣው የመጀመሪያው የጽሕፈት አዋጅ ዓለሙ ሁሉ በሕይወት መዝገብ ላይ የሚሰፍርበት የምሕረት ዘመን መድረሱን የሚያመላክት ቃል ነው። ዓለማችን የኃጢአት ማኅተሟን ፈትቶ የሕይወትን መጽሐፍ የሚገልጠው ክርስቶስ ሊወለድ በተቃረበበት ወራት የተደረገ ጽሕፈት ነው።

ለሕዝቡ ሁሉ በየርስታቸው እንዲቆጠሩ ፈቃድ ተሰጥቶ ስለነበር ዮሴፍም ከሚኖርበት ከገሊላ አውራጃ ከናዝሬት ከተማ ተነሥቶ ወደ ዳዊት ከተማ ቤተልሔም ተጓዘ፤ ከዳዊት ወገን ነውና። በዚያ ሳሉ የመውለጃዋ ወራት ደረሰ፤ ለማደሪያ የሚሆን እንኳን ቦታ ሳይኖር በዚያው በወጡበት ወደ ሄዱበት ከተማቸው ሳይመለሱ ተወለደ። ሲጀመርም የሄደበት ምክንያት የነቢያት ትንቢት እንዲፈጸም በቤተልሔም መወለድ ስለነበረበት ሲሆን ሚክ 5፥2 አዳም እና ሔዋን ገና ወደ ማደሪያቸው ገነት ሳይመለሱ የመጣ መሆኑን ያመላክታል።

የሰው ዘር በሙሉ ገና ከአዳም ጀምሮ እስከ ዚች ቀን ድረስ በምድረ በዳ እንደሚቅበዘበዝ በግ ተበትነው በነበሩበት ሰዓት የመጣው ጌታ

ሰው በማይኖርበት የእንስሳት በረት ተወለደ። በበረቱ የሚያድሩት እንስሳ አምላክነቱን ተረድተው እስትንፋሳቸውን ሲገብሩለት የሰው ልጆች ደግሞ አልቀበለው ሲሉ ሲያዳኝባቸው ነው ኢሳ 1፥3 እንስሳት ቤታቸውን ከፍተው ሲቀበሉት የሰው ልጆች ግን አልተቀበሉትም፤ እንስሳት የሚሰጉት አሕዛብ ሲያምኑበት እስራኤል አለማመናቸውን ያሳያል።

ከቤት ውስጥ ሆና ሔዋን በጎልዮ ጸንሳ፣ በነቢብ ወልዳ፣ በገቢር ያሳደገችውን ኃጢአት ድንግል ማርያም በጎልዮ፣ በነቢብ፣ በገቢር ንጹሕ ሆና የጸነሰችው እና የወለደችው ንጹሕ አምላክ እስኪወለድ ድረስ እንዲህ ሆኖ መቆየቱ ግድ ነው። ነገሩ ተገልብጦ ነበርና ባርነት የሚገባው ሰይጣን ጌታ ሆነ፣ ጌታ ሲሆን የሚገባው የሰው ዘር ባሪያ ሆኖ ነገሩ ተገልብጦ ነበርና። ምን ይሆናል ዳኛ በሌላት ሀገር።

የተገለበጠውን ታሪካችንን ለማስተካከል የተገለበጠውን ታሪካችንን ተካፈለ፤ እናም የዳዊት ልጅ፣ የሰሎሞን ልጅ በበረት ተወለደ፤ በቤተ መቅደስ ሳለች በዚያው ወልዳው ቢሆን ኖሮ ትሕትናው በምን ይገለጥ ነበር። ሰውን መውደዱስ በምን ይረጋገጣል፤ ቤተ መቅደስ የአባቱ ቤት ነውና በኃጢአት ምክንያት በአባቱ ፊት ለኮበለለው አዳም ሁለተኛ መሆኑንም በዚህ አውቀናል።

አዎ! ቀዳማይ አዳም ስለ ኃጢአት የአባቱን ቤት ለቀቀ፤ ክርስቶስ ግን ስለ ጽድቅ የአባቱን ቤት ቤተ መቅደስን ለቀቀ።

ምዕራፍ ፬

ሦስት ዓመት ከመንፈቅ

ይህ ዘመን እመቤታችን ከኢየሩሳሌም ውጪ የኖረችበት ዘመን ነው፤ ጌታ በተወለደ በሁለት ዓመቱ ሰብአ ሰገል በመጡበት ወራት ከሄሮድስ ቁጣ የተነሣ ድንግል ከነልጇ በስተማ መቀመጥ አልቻለችም። ሰይጣን የሰው ልጆችን የመዳን ሥራ ሲጀመር ሲመለከት ዝም አላለም፤ ገና ይወርዳል፣ ይወለዳል ሲባል ትንቢቱን በመስማቱ እነ ኢሳይያስን በመጋዝ አስተርትሮ፣ በኩላብ አሰቅሎ አስገድሎ ነበር ሲወለድም የተወለደውን ሕጻን ማሳደድ ጀመረ፤

በተለይም ሊወለድ ሃያ አምስት ቀን ሲቀረው መላእክት የሚወለድበትን ሥፍራ ቤተልሔምን ተግተው ይጠብቁ ነበርና አጋንንት በጣዖታት አድረው መመለክ ስለተሳናቸው ጣዖታቱም ወድቀው ወድቀው በማለቃቸው ይህንን ምልክት አድርጎ ዲያብሎስ አዳኝነቱን ጀመረ።

የአባቶቻችን አዳኝ እርሱ በእመ አምላክም ላይ ከሰው እስከ አጋንንት የክፋት ሠራዊቶችን አስከትሎ ለሠልፍ ተነሳ። አስቀድሞ በመጽሐፍ ስለዚች ቀን የተነገረው የመጀመሪያው ትንቢታዊ ቃል በዚህ ጊዜ ተፈጸመ "በአንቺ እና በሴቲቱ መካከል በዘርሽ እና በዘሯም ላይ ጠላትነትን አደርጋለሁ,, ይህ ቃል በገነት ውስጥ ከተነገሩ የወደፊት የሰው ሕይወት ጠቋሚ ቃላት አንዱ ሲሆን እመቤታችንና የቀደመው እባብ ተብሎ በሚጠራው ጥንተ ጠላታችን በሠራዊተ አጋንንት እና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መካከል የሚደረገውን ጦርነት የሚያመላክት ቃል ነው።

እግዚአብሔር የተናገረው ሊፈጸም ግድ ነውና የንጉሠ -ሰማይ ወምድር እናቱ እመቤታችን ድንግል ማርያም የሰይጣን ውጥን ጨራሽ በሆኑ ምድራውያን ነገሥታት ከሀገር ወደ ሀገር ተሰደደች።

ዓለማችን እንዲህ ናት ዓመፀኞች የሚገኙባት፣ እውነት የሚሰደድባት የእሪያ ዓይነት ልማድ ያላት ዓለም ናት። እሪያ አብሮ የሚኖረው መልኩን ላለማየት እውነተኛ መልኩን ያሳየውን እንቁሉ ረግጦ ይሰብረዋል፤ ችግሩ እኮ የመልኩ ክፋነት እንጂ እንቁውማ ያለውን መልኩን ነበር ያሳየው። ዓለማችንም በኃጢአት የበሰበ ፊቷን የሚያሳዩዋት የእውነት መቅረዞችን እንደምንም ተሯሩጣ መርገጥ ትፈልጋለች፤ አሳድዳ የዋጠቻቸው ብዙ ሲሆኑ በለመደችው አሁንም የዋጣትን የኃጢአት ረግረግ ሊያደርቅ የመጣውን ጌታ ለመዋጥ አፏን ከፈተች።

የተከፈተ አንደበቷን ሞት እስኪዘጋው፣ መቃብርም እስኪያትመው ድንግል ከዘንዶው ከሄሮድስ ፊት ሸሸች፤ ከመካከለኛው ምሥራቅ ወደ ምድረ አፍሪቃ ከነልጇ መጣች፤ ከሁለቱ አገልጋዮቿ ከዮሴፍ ከሰሎሜ በቀር ከዘመዶቿ የተከተላት ማንም አልነበረም።

አምላካችን ክርስቶስ ንጉሠ ነገሥት ነውና ከሦስት ነገሥታት ግብርን ተቀበለ ይህን ካደረገ በኋላ ነገሥታቱ ግብራቸውን አቅርበው ሲመለሱ ሰውነቱ ፍጹም እንደሆነ ለማጠየቅ እናቱ ይዛው ተሰደደች በምድር እልፍ እልፍ ሠራዊት የተከተላቸው ሦስት ነገሥታት የሰገዱለት፣ በሰማይ ሥፍር ቁጥር የሌላቸው ሠራዊተ መላእክት የሚገዙለት ሲሆን ተሰደደ።

እመቤታችን ከመልአከ ብሥራቷ ቅዱስ ገብርኤል በተረዳችው መሠረት ወደ ምድረ አፍሪቃ ይዛው ስትመጣ ያን ጊዜ አባቶቿ ነቢያት የተናገሩት ተፈጸመ "ጌታ በፈጣን ደመና ተጭኖ ወደ ግብጽ ይመጣል" ኢሳ 19፥1 የነቢያት ቃል እንዲፈጸም ብቻም ሳይሆን በዓለማችን ልዩ ልዩ ክፍላት ተሰማርተው ጣዖት ያስመልኩ፣ ኃጢአት ያሠሩ የነበሩ አጋንንት፣ ሊቃነ አጋንንት ከምድር ጨርሰው እስኪሰደዱ ጌታ ተሰደደ።

እመብርሃን ድንግል በዚያ ወቅት በብዙ መንገድ ተፈተነች፤ የሄሮድስ ሠራዊቶች ከተማ ለከተማ ይሄዱ፣ ጐዳናውን ይዘው ይከታተሏቸው ነበርና ከዚያ ለማምለጥ ጫካ ለጫካ ይሄዱ ስለነበር በከባድ ረሐብና በታላቅ ውኃ ጥም ተፈተኑ። የእስራኤልን መና፣ የዐለቱን ልብ አላልቶ ውኃን የሚያጠጣውን ጌታ በጀርባዋ ይዛ ተራበች፣ ተጠማች፤

አባቷ አዳም እናቷ ሔዋንን ከዘለዓለማዊ የነፍስ ረሐብና ጥም የሚያድነውን ጌታ ነውና የያዘችው ተራበች፣ ተቸገረች። ከዕለታት በአንድ ቀን እንኳን ወደ መንደር ገብተው ቁራሽ እንጀራ ጥርኝ ውኃ ሲለምኑ የሚሰጣቸው አልነበረም። ዓለም ምን አላትና ሁሉን በእጁ ለያዘው ምን ትሰጠዋለች ጌታ ራሱን እስኪሰጠን ድረስ የምንሰጠው አንዳች ነገር የሌለን ድሆች ነበርን፤ ባለጠጎች የሆንነው ባለጠጋው ጌታ ራሱን የሰጠን ጊዜ ነው። ከረሐቡ ጋር አብሮ የማይረሳው ደግሞ በግብፅ ምድረ በዳ የተደረገው ጉዞ ነው፤ የግብፅ በረሐ በአሸዋ የተሞላ ሰውነትን የሚያሳርፍ ምንም ዓይነት ለምለም ነገር የሌለው፣ አሸዋው እግርን የሚያቃጥል የፀሐዩ ግለት ነፍስን ከሥጋ ለይቶ የሚጥል እሾህ እና አሜካላን የሚያበቅል ምድረ በዳ ነው።

ከአዳም በደል የተነሣ የረከሰችውን ምድር ሊቀድሳት የተረገመችውን ሊባርካት የመጣው ጌታ የሰውን ሕማም በሥጋው መከራን ሲቀበል ዳግማዊት ሔዋን እመቤታችንም እንደ እናቷ ሔዋን ከብርቱ እንባ ጋር መከራን ተቀበለች። ሔዋን በሕማም፣ በምጥ እንድትወልድ ሲፈርድባት ላለቀሰችው እንባ አምሳል የሚሆን እንባ በመውለዷ ጊዜ ይህ ሁሉ ያልደረሰባት እመቤታችን አነባች። ሦስት ዓመት ከመንፈቅ መከራው ያልተለያት ቢሆንም በተለይ አራቱ ፀዋትወ መከራዎቿ ሁል ጊዜ ሲታወሱ ይኖራሉ።

፭ኛ ምጽአተ ዮሳ ወልደ ዮሴፍ

ዮሳ በመጽሐፍ የጌታ ወንድሞች ተብለው አይሁድ ከዘረዘሯቸው ሰዎች አንዱ ሲሆን ማቴ 13፥55 የስደቱ ታሪክ በተጀመረበት ሌሊት አብሮ ከዚህ ታሪክ ተካፋይ ነበር። ጥቂት እንደሄደ ግን ከበረከተ ስደቱ ሊካፈል የማይገባው ሰነፍ ሰው በመሆኑ ከጐዳናው ላይ ተለይቶ ቀረ።

በኋላ ግን ዘመዶችህን ሊያስገድል ሄሮድስ ጭፍራ ሰደደ ሲሉ ቢሰማ እግሮቹ ለበረከት ባይሆንም ለመርገም ፈጣኖች በመሆናቸው ማንም ሳይቀድመው ለስደተኞች የወሬ ስንቅ ተሸክሞላቸው ሮጠ። ሲደርስ ደክመው ጥላ ሥር አርፈው አገልጋይቱ ሰሎሜ ሕጻኑ ኢየሱስ ክርስቶስን ስታጥበው ከወንዝ ዳር ነበር ያገኛቸው። ከመድረሱ ቸር ዋላችሁ፣ ቸር አደራችሁ እንኳን አላለም፤ ይህን ሕጻን ልታስገድሉት ከዚህ ተቀምጣችኋል ሄሮድስ ጭፍሮችን በየሀገሩ አሰማርቷል ሲል እመቤታችን ከሰሎሜ እጅ ሕጻኑን ተቀብላ ይህን ሁሉ መከራ የተቀበልኩት ላላድንህ ነው ብላ ምርር ብላ አልቅሳለች።

፪ኛ ሁለቱ ወንበዴዎች ባገኟት ጊዜ

ጥጦስን እና ዳክርስን ያስተባበራቸው ቃል ኪዳናቸው ውንብድና ነው። ለማንም ላይራሩ ተማምለው ሥራውን ከጀመሩ ሰነባብተዋል። በጥጦስ መምህርነት፣ በዳክርስ ተማሪነት የተጀመረው ይህ ተግባር በድሃውም በባለጠጋውም እንዲጨክኑ አድርጎአቸዋል።

በዚህ ወቅት ነው ድንግል ከነልጇ በዚህ ጫካ ያገኝቻቸው፤ የጠፉትን ፍለጋ የመጣው ጌታችን ግን የራሱ የሆነ ጉዳይ ነበረው ወደ ዚህ በረሐ የመጣበት፤ ከነዚህ ሽፍቶች አንዱ ከደጋጉ ቅዱሳን ከነ አብርሃም፣ ይስሐቅ፣ ያዕቆብ ተቀድሞ ደመ ማኅተሙን ይዞ ገነት የሚገባ ነውና አስቀድሞ ይህን የምሥራች ሊነግረው ወደ ዚህ መጣ።

ሊቀሚቸው እየተሯሯጡ ሲመጡ ሰሎሜ አስቀድማ ልብሷን ጥላ ሸሸች የእመቤታችን መጦናጸፊያውንና የጌታን ሰብአ ሰገል የገበሩለትን የወርቅ ጫማና ቀሚስ ነጥቀው ወሰዱ። አዳም እና ሔዋን የብርሃን መጦናጸፊያቸውን ተገፈው ነበርና ለዚያስ ካሳ እንዲሆን ነው።

እመቤታችንን ያስለቀሳት ግን የልብሱ መነጠቅ ሳይሆን ጥቂት አለፍ ብለው ነገር መጀመራቸው ነው። እነሱ የሚመክሩት የቀሙትን ልብሳቸውን የሚመልሱበትን መንገድ ሲሆን እመቤታችን ደግሞ ሌባ አዩኝ አላዩኝ ብሎ ያገኘውን ዘርፎ ይሄዳል እንጂ እንዲህ የልብ ልብ ተሰምቶት ይቆማልን? እኒህማ ልጀን ሊገድሉ የተላኩት ይሆናሉ ስትል ስለ ልጇ ዳግመኛ አምርራ አለቀሰች። በቅዱሳት እጆቹ የተወደደ ልጇ እንባዋን ከዓይኗ እስከጠረገላት ድረስ በተወደደ ልጇ ደረት ላይ እንባዋን አፈሰሰች።

፫ኛ ቤተ ኮቲባ

አንዳንዱ ቤት ከሰው እስከ ሰማያዊው አምላክ የሚስተናገዱበት፣ የሰማዩ አባታችን የእግዚአብሔር ፈቃድ የሚፈጸምበት ማኅደረ እግዚአብሔር ይሆናል። አንዳንዱ ደግሞ ሰይጣን ጥላውን ይጥልበትና በረከት አልባ፣ ሊተኙበት የሚያባባ፣ ባል እና ሚስትን የማያግባባ፣ አስቸጋሪ ይሆናል ቤተ ኮቲባም እንዲህ ነበር።

በወቅቱ ከነበሩት የምድር ባለጠጎች የአንዱ ቤት ሲሆን ከብዙ ሀብት መካከል ጥቂት ቸርነት ካልተገኘ አስቸጋሪ ነውና እመቤታችን ስመ እግዚአብሔር ጠርታ ስትለምን የተመለከተች የቤቱ ባለቤት ልብን ከመዶሻ ይልቅ የሚሰብር ጨካኝ ቃላትን ተናገረች። የሰነፍ ሰው ንግግር እንደ አሸዋ ከባድ ነው፤ እንደ ፍላፃም ተዋጊ ነው። "አንቺ ሴት ደረቅ ሴት ነሽ መሰለኝ እንጂ እንደ አንች ያለ መልክ መልካም ሴት ከመጋረጃ ይወጣ ነበርን" ስትላት አረጋዊው ዮሴፍ ተቀብሎ "ለለማኝ ቢኖር ይሰጡታል ባይኖር ካለው ያድርስህ ይሉታል እንጅ እንዲህን በነገር ይወጉታል" አላት።

ኮቲባ የተሰኘችው አገልጋይ ደርቡን እያናወጠች ወርዳ ዮሴፍን በጥፊ ቃጥታ ጌታን ከእመቤታችን ጀርባ ነጥቃ ከመሬት ቀላቀለችው፤ ሕጻኑ ትክን ትክን ብሎ ሲያለቅስ እመቤታችንም ጩኸት እና ድንጋጤ የከበበው ብርቱ ለቅሶን አልቅሳለች።

፬ኛ የልጇን ጫማ በወሰዱባት ጊዜ

ከነጥጦስ የተረፈው የጌታችን ጫማ ዲያብሎስ ባስቀመጣቸው የመንደር ምልምሎች ከመወሰድ አልዳነም። ነገሩ እዲህ ነው፡- ከዕለታት አንድ ቀን ቁራሽ ልመና ስትሄድ የልጇን ልብስ እና ጫማ ከአንድ ዋሻ ውስጥ አስቀምጣ ነበር የሄደችው፤ ብትሄድ ሰይጣን እንደ ፈርያን

የሰውን ልብ አፅንቶት ምንም ቁራሽ ሳታገኝ ተመለሰች። እንኳን ቁራሽ እፍኝ ውኃ መስጠትንም ከለከሏት፤ ከዚህም ብትመለስ የልጇን ጫማ አጣች፤ ያን ጊዜ "ለአልክወሙ ማየ ኢወሀቡኒ በሕቅ ወንጦልኩ ለወልድየ አሳዕኖ ዘወርቅ[55]፤ ጥቂትን ውኃን ለመንሁ አልሰጡኝም የልጄን ጫማም አስወሰድኩ" ስትል አምርራ አለቀሰች።

ቤተክርስቲያን በዚህ ዓለም ክርስቶስን ተሸክማ በስሙ ተጠርታ እስከ ዓለም ፍጻሜ የምትሰደደውን መሰደድ ድንግል ጀመረችው። በዚህም በመጻሕፍት ሁሉ ስሟ ሲጠራ እመ ሰማዕታት መዋዕያን፤ ያሸናፊዎች ሰማዕታት እናት እየተባለች ትጠራለች በተሰይም በዘመኑ መጨረሻ ሐሳዊ መሲሕ ነግሦ ቤተክርስቲያንን ለአርባ ሁለት ወራት የሚያሳድዳት መሆኑን አስቀድሞ በሄሮድስ ንግሥና እመቤታችን ለአርባ ሁለት ወራት በመሰደዷ ነገረን።

እመቤታችን የስደቷ መከራ እያንዳንዱ ቢነገር አስገራሚ እና አሳዛኝ ሲሆን ከሦስት ዓመት ከመንፈቅ በኋላ ግንቦት ሃያ ስድት ቀን ተጀምሮ ኅዳር 6 ቀን በድል ተጠናቀቀ። ብዙ ሕጻናትን የፈጀው ሄሮድስ ሐሳቡ ሳይሳካ ግብዓተ መሬቱ ተፈጸመ። የሕፃናቱ ጩኸት፣ የእናቶቻቸውም ለቅሶ እና ዋይታ የተሰማባት ገሊላ ዛሬ ስለ ልጆቿ መጽናናትን እምቢ የምትለዋ ራሔል ሳትሆን የምታለቅስበት የንጉሥ ቤተሰቦች የለቅሶ ስፍራ ናት።

የዚህ ዓለም ደስታ በፈረቃ ነውና ከ1260 ቀናት በኋላ ያዘነችው ድንግል ደስ ይላት ዘንድ በበረሐ ሳለች "መከራዬን አይቶ ይረዳኝ ዘንድ ትጸንሻለሽ ብሎ ያበሠረኝ መላክ ወዴት ነው?" ስትለው የነበረው መላክ ቅዱስ ገብርኤል መጥቶ ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ ነገራቸው።

55. ሰቆቃወ ድንግል

ጌታ ጠላቶቹን መምታት የጀመረው ከሄሮድስ ጀምሮ ነው፤ የመጨረሻው ዲያብሎስ ነው። እንዲህ የሚመስሉ ብዙ የመዳን ተስፋዎችን የያዘው የግብፅ መልሳቸው ከዚህ በላይ የአበው ነቢያት ተስፋ ትንቢትን ፍጹም ያደረገ ቀን ነበር። በትንቢታቸው ቅዱስ መጽሐፍ ከመዘገባቸው ዐበይት እና ደቂቅ ነቢያት ቃለ ትንቢታቸው ተናግረውት እስካልተመዘገበላቸው የቃል ነቢያት ድረስ የመመለሱን ዜና ለዓለም አውጀዋል።

ከነቢያት አንዱ "እምግብፅ ጸዋዕክዎ ለወልድየ፤ ልጄን ከግብፅ ጠራሁት" ሆሴ 11፥1 ብሎ ስለ ግብፁ ስደተኛ ክርስቶስ በባሕርይ አባቱ ዘንድ የታሰበውን ሲገልጽ ሌላው ነቢይ ደግሞ "አንቺ ሱላማጢስ ሆይ ተመለሽ ተመለሽ እናይሽ ዘንድ ተመለሺ" መኃ 7፥1 ሲል ናፍቆቱን ይገልጽላታል።

ከቃል ነቢያት አንዱ ስሙ ያልታወቀ ነቢይም "ልጇ ናዝራዊ ይባላል" ብሎ የተናገረው ሳይደርስ እንደደረስ፣ ሳይደረግ እንደተደረገ አድርጎ የተናገረው እንዲፈጸም ከቦታዎቹ ሁሉ ናዝሬትን መርጠው ተቀመጡ።

ልብ በሉ! የእመቤታችን ወደ ናዝሬት መመለስ የእኛን ወደ ገነት የመመለስ ምሥጢር የያዘ በመሆኑ ነው በነቢያት ሁሉ በናፍቆት ይጠበቅ የነበረው። ይህ ደግሞ የተፈጸመው ነፍስ ገዳዩ ንጉሥ ሄሮድስ ዓለምን ተሰናብቶ ማለቂያ ወደ ሌለው የጨለማ ዓለም ከተዛወረበት በኋላ መሆኑ ከጥንት ጀምሮ በእውነት የማይቆመው ነፍስ ገዳዩ የአባቶቻችን ከሳሽ ዲያብሎስ ከተገደለ በኋላ አማናዊው የሰው ልጆች መዳን የሚፈጸም መሆኑን አመላካች ነው።

ይሄን ሁሉ ምሥጢር መነጽር ሆና ያሳየችን ድንግል ማርያም በገሊላ አውራጃ በምትገኝ የዮሴፍ ደሳሳ ጐጆ ውስጥ ሆና እናታቸውን ያጡ የዮሴፍን ልጆች ጨምራ እናት ሆነቻቸው። እናት አጥቶ በሞት መዳፍ ውስጥ ለወደቀው ዓለም እናት እስክትሆን እናትነቷን በቤተ ዮሴፍ ጀመረች። ብዙ ጊዜ ሕጻኑ ልጇ ከሚያደርጋቸው ልዩ ልዩ ተአምራቶች የተነሣ የአካባቢው ሰዎች ስለ ልጇ ይከሷት እና ይወቅሷት ነበር።

እርሱ በመስኮት ዘልቆ ወደ ቤት በሚገባው የፀሐይ ጨረር ላይ ሲራመድ ሕጻናቱ ሲመለከቱ እንደ እርሱ እናደርጋለን እያሉ ከመስኮት እየወደቁ አንዳንዶቹ ሲሞቱ ከሞት የተረፉት ደግሞ ተሰበሩ፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ ጭቃውን አድበልቡሎ ሕይወትን የሚያድል እስትንፋሱን ሲለግሳቸው በረው በረው ሲሄዱ ሕጻናቱ ተመልክተው በእስትፋሳቸው ሕይወትን እንፈጥራለን ብለው እፍ ሲሉ ዋሉ፤ ሲመሽ ጉሮሮአቸው አበጠ፣ ልባቸው ወለቀ።

ይህንን የተመለከቱ የገሊላ መንደር ነዋሪዎች በእመቤታችን ላይ በጠላትነት ተነሡባት ልጅሽ ልጆቻችንን ገሏል አሏት፤ ሁሉን ቻይ ልጇ የሞቱትን አሥነስቶ በውኑ የገደልኳቸሁ እኔ ነኝን? ብሎ በሕዝቡ መካከል ሙታን ምስክርነትን እንዲሰጡ እስካደረገበት ጊዜ ድረስ የአባቶቻችን ከሳሽ እርሱ ክሱን አላቆመም ነበር።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያድግ እንደ ሁሉም ምድራውያን ሕጻናት ነውና ለእናቱ በነገር ሁሉ ይታዘዝ ነበር፤ ውኃ እንዲቀዳ ስታዘው ውኃውን በወንፊት ቀድቶ ያመጣላት ነበር[56]፤ ውኃውን ቋጥሮ በነፋስ ምስሶ ላይ ሰቅሎ፣ ስሙን ሰማይ ብሎ ለሚጠራው ለእርሱ በወንፊት ውኃን መቅዳቱ ምን ይገርማል።

56. ተአምረ ኢየሱስ

እንጨትም ልቀም ከተባለ ለቅሞ በነፋስ ትክሻ ላይ ጭኖ እያመጣላት ለእናቱ እና ለዘመዶቹ ሁሉ ያገለግል ነበር ሉቃ2÷51። በዚህ ሁሉ ነገር መላእክት እና ሊቃነ መላእክት ይገረማሉ፤ አጋንንት ይደነግጣሉ ባለመታዘዝ የተጀመረውን ኃጢአት በመታዘዝ ሊሽር መጥቷልና፤

ይህን አገልግሎቱን ሲያዩ መላእክት በመገረም ዝም ይላሉ ሊያገለግሉት እንጅ ሊያገለግል የማይገባው ሆኖ ሳለ በፈቃዱ ይህን አድርጓልና። በነገር ሁሉ እንደ ሕጻናት ሆነ እንጂ ከሕጻናት የተለየበት ምንም መንገድ አልነበረም። ሁለት የሰው ልጅ ሊያልፍባቸው የሚችሉ ሕግጋትን ፈጸመ[47]።

❖ <u>ሕግ ጠባይዓዊ</u> :- በተፈጥሮ የተሰጠ የፍጥረት ሕግ ሲሆን በቀዳማዊው ልደቱ ይህ አልነበረበትም፤ በደኃራዊ ልደት ከድንግል ሲወለድ ግን ይህን የተፈጥሮ ሕግ ሳያዛባ ከማሕጸን ጀምሮ በየጥቂቱ አሳደገችው እንጂ አምላክ ነኝና ዕለቱን ተወልጄ ዕለቱን ልደግ አላለም።

❖ <u>ሕግ መጽሐፋዊ</u>:- ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ሕግ ሥር እንዲያልፍ እድሜው ለትምህርት ሲደርስ እመቤታችን ወስዳ ለገማልያል አስተምርልኝ ብላ ሰጠችው። ሰው የሚሆነውን ለመሆን ይህን አደረገው እንጂ የመምህራን መሪያቸው፣ የአዋቂዎች እውቀታቸው እርሱ እኮ ነው።

እናቱ ድንግል ማርያም ግን ነገሮችን ሁሉ በልብዋ እየጠበቀች ታስቀምጥ ነበር ለበዓል በኦሪታውያን ልማድ ወደ ቤተ መቅደስ የወጣችም እንደሆነ አስከትላው ትሄድ ነበር፤ ወደ ቤተ መቅደስ መሄድን የጀመረው ልክ አስራ ሁለት ዓመት ሲሞላው እንደነበር መጽሐፍ ይመሰክራል።ሉቃ

57. መቅ. ወንጌል

በሌሎች ሌዋውያን ከሃያ ዓመት በታች እንዳይወጡ ሥርዓት ተሠርቶባቸዋል እርሱ ግን የሚወጣው በሊቃውንቱ መካከል ተገልጦ ለማስተማር ነውና በዚህ ታናሽ እድሜ ወጥቷል።ዘሌ

እመቤታችን በእለተ ዐርብ

ዕለተ ዓርብ ከሰማይ እስከ ምድር፣ ከአድማስ እስከ አድማስ በሚኖሩ ፍጡራን ላይ በማለዳዋ ኀዘን የታወጀባት፣ ሲመሽ ወደ ማታ ደግሞ በአጸደ ሥጋ፣ በአጸደ ነፍስ ተድላ ደስታ የበዛባት ልዩ የመዳናችን ቀን ናት።

በዚህች ዕለት ግዕዛን ያላቸው እና የሌላቸው ልዩ ልዩ ሥነ ፍጥረታት አንገታቸውን ደፍተው በተሰበረ ልብ ሐዘናቸውን ገልጠዋል። ሐዘናቸው ወደ ደስታ እስኪለወጥ የመከራ እንባን አንብተዋል። አንዳንዶቹ የሚደርሱበትን አጥተው ብር ብር ሲሉ ነው የዋሉት፣ በተለይም ደቀ መዛሙርቱ መድረሻ ለሌለው የሰው ዘር መድረሻ ሊሆን ጌታ በመስቀል ላይ ነውና እስከዚያው ድረስ ሁሉም መድረሻ አጥተው ተቸገሩ።

ኀዘን ሲበዛ ከባድ ነውና ምድር ሳትቀር ከኀዘኑ ከባድነት የተነሣ መሸከም አቅቷት ተንገፈገፈች፣ ይህም ምሬቷ ደግሞ በአሕዛብ መንደር ሳይቀር ተሰማ፣ እንዲያውም በአቴና ባለቸው አርዮስፋጎስ በተሰኘው ሥፍራ ቆሞ ይሰብክ ለነበረው ታላቅ የጥበብ ሰው ቅዱስ ዲዮናስዮስ ወደ ክርስትና መመለስ አንድ ምክንያት የሆነው የምድር መናወጧ፣ የፀሐይም መጨለም፣ የጨረቃም ደም መሆን፣ የዓለማችን በጨለማ መዋጥ እና እነዚህን የመሳሰሉ የሥነ ፍጥረታት የሐዘን መግለጫዎች ናቸው።

ዕለቲቱ አንገት ካስደፋቻቸው፣ ሐዘን ልባቸውን ከሰበረባቸው ሰዎች አንዷ እመቤታችን ድንግል ማርያም ናት። አስቀድሞ ከሰላሳ ዓመት በፊት ሕጻኑን በቤተ መቅደስ የታቀፈው ሽማግሌው ስምዖን እንደተናገረው ልቧን የሚከፋፍል የመከራ ሰይፍ በነፍሷ አለፈ ሉቃ 2፥35 ጌታም እናቷ ሔዋን በሲኦል የምትቀበለውን መከራ እንድትቀበል ፈቃዱ ነውና ለአዳም እና ለሔዋን ልጃቸው አቤል በሞተ ጊዜ የሚያጽናና መላክ እንደላከላቸው ልጇ በመከራ ተይዞባት ለምታለቅሰዋ ሴት ለእመቤታችን የሚያጽናና መልአክ የላከላት አይደለም።

ቀኑን ሙሉ በመከራ እንድታሳልፍ ዝም ብሏታል እንጂ። እርሷም የልጇን በአይሁድ እጅ መያዝ ከሰማችበት ጊዜ ጀምሮ አንድ ጊዜ ከድንጋይ፣ ሌላ ጊዜ ከመሬት እየወደቀች አለቀሰች። ሲወለድ ጀምሮ በስደት፣ በረሐብ፣ በብዙ መከራ የተፈተነችለት ልጇ ሲያዝ እንደምን አታለቅስ፣ ታለቅሳለች እንጂ።

በስደቱ ስለ እርሱ ራሳቸውን ለሞት የሰጡ ምድራዊ ሕይወታቸውን በዘለዓለማዊ ሕይወት የለወጡ ብዙ ሕጻናት ነበሩ። ዛሬ ግን ስለ እርሱ መከራን ለመቀበል የደፈረ ማንም የለም። አብረውት የነበሩት ሁሉ ክደተዋል፣ የባሰባቸው አናውቅም ብለው ምለው ሸሽተዋል። እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘንብሏል። አብረውት ሊሞቱ ቃል የገቡት ሁሉ ከአጠገቡ ሲታጡ መንገደኛው ስምዖን ቀሬናዊ / አፍሪካዊው ሰው/ ሸክሙን ተጋራው።ዓለምን ከነበረባት ሸክም ሊያሳርፍ "እናንተ ሸክማችሁ የከበዳችሁ ወደ እኔ ኑ" ማቴ 11፥28 ብሎ የጠራንን ጌታ ስምዖን አንድ ለአንድ ምዕራፍ አሳረፈው።

ምሥጢሩ ግን መስቀሉን ከክርስቶስ ተቀብላ ቤተ ክርስቲያን ልትሸከመው እንደሚገባት የሚያሳይ እንጂ የሚያሳርፈንን ጌታ

ለማሳረፍ የተደረገ አልነበረም። ፍጡርማ የፍጡራንን ሽክም መሸከም ቢችል ኖሮ ይሄን ያክል ዘመን ከነነውራችን ባልቆየንም ነበር፤ ጌታ እኮ የተሸከመው ነውራችንን ነው። ከደቀ መዛሙርቱ ተሰይቶ የመከራውን ጉዞ መጀመሩስ ለዚህ አይደል፤

ደቀ መዛሙርቱም ተሳታፊዎች ሆነው ቢሆን ኖሮ በክርስቶስ የቤዛነት ሥራ የፍጡራንም እገዛ አለበት በተሰኘ ነበር። እርሱ ግን በመጀመሪያው ተፈጥሮአችን ከማንም ጋር ሳይመክር በገዛ ፈቃዱ ብቻውን ሆኖ በልብነቱ አስቦ በቃልነቱ "ሰውን እንፍጠር" ብሎ ተናግሮ በሕይወትነቱ ሕያው አድርጎ እንደፈጠረን ዛሬም በሐዲስ ተፈጥሮ ሲፈጥረን የማንንም እርዳታ ሳይሻ ብቻውን ፈጠረን።

የመጀመሪያው እና በነፍስ ሕያው የሆነው ሰው ሞትን ወደ ዓለም ሲያመጣ ፣ለኃጢአትም መሠረት ሲሆን ብቻውን ነበር፤ ሁለተኛው እና ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ የሆነው ሰውም ጽድቅን ሲመሠርት እና ሕይወትን ወደ ዓለም ሲያስገባ ብቻውን ሆኖ ነው።

በዚህ ጊዜ ከሁሉም በላይ የመረረውን ሐዘን ገፈት ቀማሽ እናቱ ድንግል ማርያም ናት። ምክንያቱም እናቷ ሔዋን መርገም በእርሷ ስለተጀመረ ክፉኛ ልቧ በሐዘን ነደ፣ ተስፋዋም ተወግዶ የመጀመሪያውን ሐዘን የቀመሰችው እርሷ ናትና በእናቷ ፈንታ የተፈጠረችው አዲሲቱ ሔዋን እመቤታችን የእናቷን የተጀመረ ሐዘን ለማደማደም መሪር እንባን አነባች።

የሔዋን ለቅሶ ስለ ራሷ የተለቀሰ ስለነበር ለዚህ ዓለም የጠቀመው አንዳች ነገር የለም፤ ልጆቿ ሁሉ በምጥ በጭንቅ ሲወልዱ እየተቀባበሉ ይዘውላት ቆይተዋል እንጂ። ሊቁ አትናቴዎስ ያኔ የነበረውን ለቅሶ

ሲገልጸው "አ! ሔዋን ምንተኑ ረሰይናኪ ዘአምጻእኪ ፍትሐ ሞት ላዕሌነ ይበክያ ኩሎን አዋልድኪ እለ ይወልዳ በሕማም ወበጻዕር፤ ሔዋን ሆይ የሞት ፍርድን ያመጣሽብን ምን አደረግንሽ ልጆችሽ በሕማም በጻዕር ሲወልዱ ዛሬም ያለቅሳሉ[58]" በሚል አሳዛኝ ቃል ነው።

የሔዋን ለቅሶ ነፍሰ ገዳዩንና አስለቃሹን ሰው ቃኤልን አስገኝቷል። የእመቤታችን ለቅሶ ግን የስሙ ትርጓሜ ፍሥሓ ወሐሴት የሆነውን ዮሐንስን በልጅነት አስገኝቷል። ከዚያም አልፎ ሁላችንን ጠቅሟል፤ እንዴት ከተባለ የሙት ልጆች እንዳንሆን ድንግሊቱን እናት አድርጉልናልና ነው። አባቶቻችን እንደነገሩን እነኂት እናትህ ማለት በዮሐንስ ግብር ጸንተው ለሚኖሩ እስከ እለተ ምጽአት ለሚነሱ ደቀ መዛሙርት የተገባ ቃል ኪዳን ነውና።

በጌታ ያመኑ ከቃሉ ግሩምነት የተነሣ መቀበል አቅቶአቸው ሕዝቡ በሸሹ ጊዜ "አቤቱ ወደ ማን እንሄዳለን" ብለው የቀሩት ደቀ መዛሙርቱ ላይ በሙሉ ሐዘን ድባቡን ጥሎባቸው ነው የዋለው፤ ምክንያቱም ይህ ቀን አይሁድ የፋሲካ በዓልን አክብረው ታላቅ ተድላ ደስታን የሚያደርጉበት ቀን በመሆኑ የክርስቲያኖች ፋሲካ ከአይሁድ ፋሲካ የተለየ መሆን ስላለበት ነው። ከእንግዲህ በኋላ ፋሲካችን ክርስቶስ እንጂ ሙሴ ያዘዘው የአንድ ዓመት ጠቦት አይደለም ሲሉ ሲያዝኑ ነው የዋሉት፤ ከነዚያ አንዷ እመቤታችን ናትና።

ሊቁ አባ ሀርያቆስ ሐዘኗን ሲገልጠው ከታላቁ ያዕቆብ ሐዘን ጋር ያመሳስለዋል። "ተሐደሰ ዮም ብካዩ ለያዕቆብ፤ ዛሬ የያዕቆብ ሐዘን ታደሰ" ሲል ድርሳኑን መጻፍ ይጀምራል።

58. ቅዳ. አትናቴዎስ

በእርግጥም የድንግል ለቅሶ ከያዕቆብ በእጅጉ ይልቃል፤ ያዕቆብ ምንም እንኳን በዘመኑ ከባድ ሐዘን የገጠመው ቢሆንም ዮሴፍና ሌሎች አስራ አንድ ወንዶች፣ አንዲት ሴት ልጅ ለማጽናናት ያሉት አይደለምን?እመቤታችን ግን ከአንዱ ልጇ በቀር ሌላ ማን አላት? ለያዕቆብ የሚያጽናኑ አራት ሚስቶች ብዙ ዘመዶች ያሉት አይደለምን? ለድንግል ግን የሚያጽናናት ዘመድ የላትም። እናቷ ሐና እንዳታጽናናት ያረፈችው እመቤታችን በቤተ መቅደስ ሳለች ነው፤ በስደቷ ጊዜ ያጽናናት ያገለግላት የነበረው አረጋዊው ሰው ዮሴፍ እንኳን ዛሬ በምድር የለም በሞት ወደ ፈጣሪው ተወስዷልና።

ያዕቆብ የልጁን ሞት በወሬ ሰምቶታል እንጂ በዓይኑ አላየውም፤ ድንግል ግን ልጇ የተቀበለውን መከራ በዓይኖቿ አይታለች። ያዕቆብ የልጁን የዮሴፍን ዕርቃን አላየም፤ የተቀደደ ልብሱን በበግ ደም ለውሰው አምጥተው ልጅህን አውሬ በላው ብለው ዜና ሞቱን አረዱት እንጂ። እመቤታችን ግን በበግ ደም ሳይሆን በልጇ ደም የተነከረ ልብሱን፣ ከድካሙ ብዛት የተነሣ በወዝ የረጠበ መጐናጸፊያውን አይሁድ ሲገፉት ሲካፈሉት ተመልክታለች፤

ያዕቆብ የልጁ ደም ሳይፈስ እንደፈሰሰ ሰምቶ አለቀሰ፤ ድንግል ግን የልጇ ደም በቆመችበት መሬት ያለገደብ ሲፈስ እየተመለከተች እንባዋ የለ ማቋረጥ እንደምን አይፈስ! መሬቱ በልጇ በክርስቶስ ደም ሲርስ የእናቱም ጕንጮቿ በመሪር እንባ ረሰረሱ።

ያዕቆብ ልጁን ዮሴፍን ወንድሞቹ ለሃያ ብር ሲሸጡት፣ እየተቀባበሉም ሲደበድቡት፣ ከመሬቱ ከድንጋዩ ሲጥሉት አላየም፤ ድንግል ይህን ሁሉ ግፍ በዓይኖቿ በልጇ ላይ ሲፈጸም ተመለከተች።

ወንድሞቼ ብሎ ከሚጠራቸው ደቀ መዛሙርት አንዱ ይሁዳ ለ30 ብር ሲሸጠው፣ አይሁድም ከእጁ ተቀብለው አንድ ጊዜ ከመሬት ሌላ ጊዜ ከድንጋይ ሲጥሉት ስትመለከት የድንግል ሐዘን ከያዕቆብ ሐዘን ይልቅ በረታ።

በሐዘኗ ጊዜ እስከ ልጇ የመስቀል ሥፍራ እንዲከተሏት ብትፈልግም ከደቀ መዛሙርቱ አንዱን እንኳን ማግኘት አልቻለችም። ስለ እያንዳንዳቸውም ጠየቀች ስለ ጴጥሮስ ብትጠይቅ ከአይሁድ ፍርሀት የተነሣ ስለ እርሱ ብሎ ሚስቱን፣ቤቱን፣ መረቡን የተወለትን ጌታ አላውቀውም ብሎ እንደ ካደው ነገሯት።

ስለ ታላቁ ያዕቆብ ብትጠይቅም ጌታ በተያዘበት ሥፍራ በፍርሀት ልብሱን ጥሎ እንደሸሸ ነገሯት፣ ስለ እንድርያስ፣ ስለ ቶማስ መረመረች ከእርሱ ጋር ወደ ከተማ እንዳልገቡ ነገሯት። ስለ በርተሎሜዎስ፣ ስለ ፊልጶስ በጠየቀችም ጊዜ በርተሎሜዎስ ከሁሉም ደቀ መዛሙርት አስቀድሞ እንደሸሸ እና ፊልጶስም የአይሁድ ጭፍሮች መብራት ይዘው ሲመጡ ባየ ጊዜ ደንግጦ እንደጠፋ ሰማች አንድም እንኳ ተስፋ የሚሆናት ሰው አጣች።

የዮሐንስ ወንድም ስለሆነው ያዕቆብ፣ ስለ ማቴዎስም ጠየቀቻቸው፤ አንድም ጊዜ እንኳን አብረውት እንዳልቆሙና ይልቁንም ማቴዎስን ባቀረጥ ምክንያት አጥብቀው ይጠሉት ስለነበር በጨለማ ወጥቶ እንደተሰወረ ሰማች። ስለ ሁሉም ጠየቀች፤ ከዮሐንስ በቀር ካጠገቧ የቆመ አንዳች ደቀ መዝሙር የለም።

ከእጁ በረከትን የቀመሱት፣ በተአምራቱ በትምህርቱ ያደነቁት ሁሉ ዛሬ ከእርሱ ጋር የሉም፤ በዚህ ጊዜ ድንግል ሐዘኗ እጅግ ጸና።

ስለተወደደው ልጇ ሙሾ እያወጣች አለቀሰች፤ ፋሲካዬ ወደ ለቅሶ፣ ደስታዬ ወደ ሐዘን ተለወጠ አለች።

ምን ታድርግ! ራሔል መቃብራቸውን ላላየቻቸው ልጆቿ ካለቀሰች ድንግል የልጇን መቃብር እያየች እንዴት ዝም ትበል ማቴ 2፥18 ራሔል ላልወለደቻቸው ልጆቿ መጽናናትን እንቢ ካለች ድንግል በድንግልና ጸንሳ፣ በድንግልና ለወለደቻቸው ልጇ እንዴት አታለቅስ?

በከባድ ሐዘን ውስጥ ሆና በዮሐንስ ቤት ሳለች ዮሐንስ ወደ ቀራንዮ እንዲወስዳት ደጋግማ ጠየቀችው፤ የሳምንቱ መጨረሻ ቀን በመሆኑ ዮሐንስ እየመራት ሰሎሜን እና ሌሎችንም ቅዱሳት አንስት አስከትላ በአደባባዩ መሐል ስትሄድ ወደ ገበያ የሚወጣው ሕዝብ በደም ግባቷ ይደነቃል፤ በሐዘኗ ይገረማል፤ አንዳንዶቹ ግን በእርሷ ልጅ ምክንያት ሄሮድስ ልጅ አልባ አድርጉናል ሲሉ በመከራዋ ደስ ተሰኙ።

ወደ ቀራንዮ እየተጠጉ ሲሄዱ የአይሁድ ድንፋታቸው ከሩቅ ይሰማል አንዳንዶቹ ፊቱን በሻሽ ሸፍነው "መኑ ጸፍአከ" እያሉ በጥፊ ይመቱታል ሌሎች ደግሞ ራሱን በዘንግ እየደበደቡ "መኑ ኰርአከ" ይሉታል።

ድንግል መስቀሉ ወደ ተተከለበት ስፍራ በደረሰች ጊዜ በቀደመው ሰው በአዳም እንደተደረገው ልጇ ክርስቶስ ዕርቃኑን በመስቀል ላይ ሆኖ አገኘችው፤ በቀሚሱ ፈንታ የደም ቀሚስ አጥልቀውለታል፤ ስለ መጐናጸፊያውም በቁስል አስጊጠውታል፤ ከሊቶስጥራ እስከ ቀራንዮ፣ ከሀና ቤት እስከቀያፋ፣ ከጲላጦስ እስከ ሄሮድስ ለ18 ሰዓት በተቀበለው መከራ መልኩ ተለውጧል።

በመጽሐፍ "ከሰው ልጆች ይልቅ ደም ግባትህ ያምራል መዝ 44፥2 ተብሎ የተነገረለት እርሱ ደም ግባት አልባ ሆኗል፤ ይህ ሊሆን

አስቀድሞ በነቢይ ተነግሮ ነበርና ኢሳ 53፥2 ታዲያ በዚህ ጊዜ ሰማያውያኑ መላእክት ከፍርሀት የተነሣ ቀና ብሎ ማየት ተስኗቸው ሁሉም በዐውደ መስቀል እንደሻሽ ተነጽፈዋል።

የሰው ልጆች አባት አዳም ክብሩን ያጣው፤ በሰይጣን ቅንዓት ደም ግባቱና ውበቱ የተለወጠው፤ በተፈጸመው ስሕተት ምክንያት ከሰማይ እስከ መሬት ባሉት ፍጡራን ፍርሀትና መንቀጥቀጥ የታየው በዚህ ዕለት፤ በዚህ ሰዓት ነበር። በዚያን ጊዜ አንተ አቡነ ወአንተ እምነ የሚባል ጌታ ስለ ልጁ አዳም በሐዘን ወደ ገነት ገባ።

ዛሬ ደግሞ የዳግማይ አዳም ኢየሱስ ክርስቶስ እናቱ እመቤታችን ስለ ልጇ አለቀሰች፤ በእናቷ በሔዋን ላይ አጋንንት እንደተጠቃቀሱባት በእመቤታችንም የአጋንንት ወኪሎች ጸሐፍት ፈረሳውያን ተጠቋቀሙባት። እርሷ ግን ከሰማችው የአይሁድ ሽሙጥ ይልቅ የልጇ መከራ በዝቶ ስላገኘችው አምርራ አለቀሰች።

በመስቀሉ ዙሪያ የነበሩ መላእክትን ጠየቀቻቸው፤ እንዲህም አለቻቸው፤ ደቀ መዛሙርቱስ ሥጋውያን፤ ደማውያን በመሆናቸው ፍርሀት አሸሻቸው እናንተም እንደነሱ ፈራችሁን? በፈጣሪያችሁ ላይ ይህ ሲደረግ ዝም ትላላችሁን?

ገብርኤል ሆይ! ወንድ ልጅ ትወልጃለሽ ያልከኝ ለዚህ ነበርን? ምነው ወንድ ልጅ ትወልጃለሽ ብለህ በነገርከኝ ዕለት ሞቴን በነገርከኝ አለች። ስህተቱ በተፈጸመባት በመጀመሪያዋ ዓርብ የመከራው ባለቤቶች አዳም እና ሔዋን ብቻ እንደነበሩ፤ ድኅነት በተጀመረባት በዚህችኛዋ ዓርብም የመከራው ባለቤቶች እናቱ ድንግል ማርያም እና ልጇ ክርስቶስ ነው። የቀደሙትን ፍጥረታት በመከራቸው ወቅት በመገረም ከበው መላእክቱ

ይመለከቷቸው እንደነበሩ ሁሉ ዛሬም በስደቷ ወቅት ይመራት የነበረው ኡራኤል፣ ከልጅነቷ ጀምሮ ጠባቂ መላኳ ሆኖ የተሾመው ቅዱስ ሚካኤል፣ መልአከ ብሥራቷ ቅዱስ ገብርኤል ዙሪያውን ከበው ይመለከታሉ።

ዑራኤል በአምሳለ ዲያቆናት የብርሃን ጽዋውን ይዞ ከእጁም ከጎኑም የሚፈሰውን ደም ይቀበላል፤ ሚካኤል በተደሞ ቆሞ የእግዚአብሔርን ትዕግሥት ያደንቃል፤ ገብርኤል በቁጣ የመዘዘውን ሰይፍ የአብ ምሕረቱ፣ የወልድ ትዕግሥቱ፣ የመንፈስ ቅዱስ ቸርነቱ ስለ ከለከለችው የቤተ መቅደሱ መጋረጃ እስኪቀደድ ወደ ምድር ወርውሮታል (ሃይ.አበ ዘአትናቴዎስ)

እንደ ቤተ መቅደሱ ሁሉ አማናዊት የሰማያዊ ምሥጢር መጋረጃ እመቤታችንም ልብን የሚከፋፍል ብርቱ የሐዘን ሰይፍ በነፍሷ አለፈ አረጋዊው ስምዖን በቤተ መቅደሱ በር አስቀድሞ ነገራት ትንቢታዊ ቃል ይደርስ ይፈፀም ዘንድ ይህ ሁሉ ሆነ ሉቃ 2÷35።

ሰዓቱ ሄደ፣ ነጐደ፤ በምድር ላይ ጨለማ እና ብርሃን ያለ ወትሮአቸው ተፈራረቁባት፤ የተፈጸመው ግፍ ዜናው እስከ ሲኦል ዘልቆ ተሰማ፤ የሁሉም ነገር ፍጻሜ ከመሆኑ በፊት ግን በፊቱ ለምታለቅስ እናቱ ጌታ አንድ ነገር ተናገረ "እነሆ ልጅሽ" አላት። የመሞቱ ዓላማ ይህ ነበርና።

እናቱ ሔዋንን በሞት ለተነጠቀው ዓለም እናቱን እንደመለሰለት ለማጠየቅ በዮሐንስ አማካኝነት ለክርስቲያኖች ሁሉ እናት አደረጋት። ስለ አንዱ ልጇ ስታለቅስ ሳለች በቁጥር ለማይታወቁ እስከ ዓለም ፍጻሜ የሚነሡ ልጆችን ሰጣት። በመከራ ቀን ያጣናትን እናታችንን በመከራ ቀን ዳግም አገኘናት። በመጀመሪያዋ ዓርብ ያጣናትን ሔዋንን በመጀመሪያዋ ዓርብ አገኘናት፤ ከዕፀ በለስ ሥር አጣናት ከዕፀ መስቀል ሥር እንደገና ተረከብናት። ከዚህች ሰዓት ጀምሮ ያ ደቀ መዝሙር

ወደ ቤቱ ወሰዳት፤ ከዚያ እስከ ዛሬ ድንግል የሁሉ እናት ሆና "ይእቲ ማርያም እምነ" ስትባል ትኖራለች።

ከ9:00-11:00 ድንግል በዮሐንስ ቤት ቆየች ስለ ልጇ ፋንታ ዮሐንስ ልጅ ሆኖ የተሰጣት ቢሆንም በመስቀል ላይ ያየችውን የልጇን መከራ መርሳት አምቢ አለች። በግርፋት የተበጣጠሰ ሰውነቱ፣ በመከራ የተለወጠው ደም ግባቱ፣ በደም የወየበ ፊቱ፣ በትዕግሥት ዘንበል ያለው አንገቱ ሁሉም እየተፈራረቁ በፊቷ ላይ ድቅን አሉባት።

ታዲያ እንደምን ዝም ትበል!። አንድ ልጇን የሾህ አክሊል ደፍቶ እያየችው እንደምን ሐዘኗን ትርሳ። በመቃብር የነበሩ ሙታን ተፈተው ሲመላለሱ የድንግል ልብ በሐዘን ታሰረ፤ በሲኦል ለነበሩ ነፍሳት ዕረፍት ሲሰጥ እመቤታችን ግን አላረፈችም።

ዳግመኛ የነገሩን ፍጻሜ ለማየት የዓለመ· የሕይወት ምንጭ ወደ ፈለቀበት ቅዱስ ተራራ ወደ ቀራንዮ ከቅዱስ ዮሐንስ ጋር ሄደች። አሁን ሊቃነ ካህናቱ የሉም፤ ቅድስት ነፍሱ ከክብርት ሥጋው ስትለይ ምድር በመንቀጥቀጡ ከፍርሀት የተነሣ የአይሁድ ባለሥልጣኖቻቸው ፈርተው ተደብቀዋል።

ሁለት ሰዎች ብቻ እርሱን ያገኘ ያገኘናል ሳይሉ ከጲላጦስ ፈቃድ ጠይቀው ከመስቀሉ አውርደው ሲገንዙ እመቤታችን መጣች። ከነፍሱ እንጂ ከመለኮቱ ያልተለየ በድነ ሥጋውን እየዞረች ምርር ብላ አለቀሰች። ወደ መቃብር ከመውረዱ አስቀድሞ በላዩ ላይ እየወደቀች አለቀሰች፤ የከበረ እንባዋ በተወደደ ልጇ ላይ ፈሰሰ። ይህ የመጨረሻው ልጇን ያየችበት ሰዓት ነበር።

ከዚህ በኋላ በትንሣኤው እስክታገኘው ድረስ ላታየው ወደ መቃብር ዮሴፍ እና ኒቆዲሞስ አወረዱት። በትንሣኤው በሐዲስ ሥጋ ሞትን

በሥልጣኑ ሸሮ ተነሥቶ ስታገኘው ልጄ ሆይ! ተነሣህን! ብላ በደስታ አቅፋ ሳመችው፤ ይሆን አስመልክቶ ደራሲው «ወልድየ ብህልኪኦ ተንሣእክኑ እሙነ ወሰዐምኪ በአፉኪ አፉሁ ቁርባነ፤ ልጄ ሆይ በእውነት ተነሣህን ብለሽ አፉን ሳምሽ» ሲል ያወድሳታል ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ለ15 ዓመታት ድንግል በቤተ ዮሐንስ ኖረች።

እመ አምላክ በቤተ ዮሐንስ

ከትንሣኤ በኋላ በጌታ ላመኑ ደቀ መዛሙርት የመጽናናት ወቅት አልነበረም፤ ምክንያቱም ከሙታን ተለይቶ ተነሣ የሚለውን ዜና ለዓለም እንዳያዳርሱባቸው በመስጋት አይሁድ ሊያጠፏቸው ይዝቱባቸው ነበርና። በቀንም በሌሊትም ጽርሐ ጽዮን በተሰኘው የሐዋርያው ማርቆስ እናት ቤት ለሃምሳ ቀናት ተቀመጡ። በዝግ ደጆች እየገባ ከሚጠይቃቸው ጌታ በቀር ሌላ ማንም ወደ እነርሱ አልመጣም።

በዚህ አስጨናቂ የደቀ መዛሙርቱ ኑሮ ውስጥ እመቤታችንም ነበረችበት፤ በበዓለ ሃምሳ ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ሲቀበሉ እመቤታችንን በመካከላቸው እንደ ታቦት አድርገዋት እንደነበር ታሪክ ምስክር ነው። እንደ ጌታችን ቃል ዓመት ወደ ሌላው የዓለም ክፍል ለስብከት ሳይወጡ በጎብረት ኢየሩሳሌምን ያስተምሩ በነበረበትም (መቅድመ ወንጌል) ጊዜ እመቤታችን ከእነርሱ አልተለየችም። እርሷ ለበቃቸው ምሥጢር እነርሱ አልበቁምና የተሰወረውን ትገልጥላቸው ያልሰሙትን ታስረዳቸው ነበር፤

ከዕለታት አንድ ቀን ግን የማይገባቸውን ጥያቄ አቅርበውላት እንደነበር በታሪክ ድርሳናት ተመዝግቧል፤ ጌታችን ይነገረናል ስንል ሳይነግረን

ዐረገ፤ ሰማይና ምድር የማይችሉትን አምላክ ከቶ እንደምን ቻልሽው? እስኪ ንገሪን? አሏት፤ እርሷም ይሄንንስ እኔም ልናገረው እናንተም ልትሰሙት አይቻላችሁም አለቻቸው፤ እነርሱ ግን ነገሩ ቢገርማቸው ደጋግመው ጠየቋት፤

ከቤተ እግዚአብሔር ወሰዷት፤ የማያውቀው መላክ ቀርቶ የማላውቀው ግሩም መላክ መጣ፤ ቀኝ ክንፉን ቢባርከው ጎበስተ ሕይወት ሆነ፤ በልቶ አበላኝ፤ ግራ ክንፉንም ባረከው፤ የሕይወት መጠጥ ሆነ ጠጥቶ አጠጣኝ። ብላ ወደ ዋናው ምሥጢር እገባለሁ ስትል ጊዜው የካፊያ ስለነበር መላኩ የመብረቅ የነጐድጓድ ድምፅ አሰምቶ ገስጾአቸዋል፤ ልትመረምሩት አይገባችሁም ሲል ነው።

በዚህም ዓለም ያልደረሰበት የመለኮቱ መዝገበ ምሥጢር እንደሆነች ታወቀ ተረዳ።

ሁሉም ደቀ መዛሙርት የጠፉትን በጐች ፍለጋ ዕጣ ወደ ደረሳቸው ክፍለ- ዓለም ሲሰማሩ እመቤታችን ቀሪ ዘመኗን ያሳለፈችው ጌታ ይወደው ከነበረው ደቀ መዝሙር ቤት ነው። ያደራ እናቱ ናትና ከቀራንዮ እስከ ጌቴሴማኒ በፍጹም ፍቅር አገለገላት። ቀን ቀን ሀገረ ስብከቱ ኤፌሶን ነበረችና ወንጌልን ሲሰብክ ውሎ ማታ ማታ በደመና ከቤቱ ገብቶ ያድር ነበር።

እመቤታችንም ነፍስ ከሥጋዋ እስከተለየችበት ቀን ድረስ ወደ ልጇ የመቃብር ስፍራ መሄዷን አታቋርጥም ነበር፤ እኒያ ርጉማን አይሁድ አዘውትራ ወደ ልጇ መቃብር መሄዷን ሲሰሙ ጊዜ ጠባቂዎችን ሾመውባት ነበር እርሷ ግን ከመሄድ አላቋረጠችም፤ እነርሱም

አላዩአትም፤ የልጇ የጥበቡ መጋረጃ ሰውሮአት ነበርና[60]። በአጸደ ሥጋ ሳለች ከተገቡላት ሁለት ቃል ኪዳኖች መካከል አንዱ በዚህ ስፍራ ቆማ ስትጸልይ ሳለች በየካቲት 16 ቀን የተገባላት ነው።

በዓለመ- ሥጋ ሳለች ዓለመ ነፍሳትን የጐበኘችውም በዚሁ በዮሐንስ ቤት ሳለች ነው። የሮመ ንጉሥ ጢባርዮስ የጌታን በግፍ መገደል ሰምቶ ያዘን ነበርና እርሱ ሞቶ ተነሥቶ ወደ ሰማይ ያረገ ቢሆንም እናቱ በምድር ያለች አይደለምን? ለምን አታስመጣትምና አንተ ወንድ ባሪያ፤ እኔ ገረድ ሆነን እርሷን ከዙፋን አስቀምጠን አናገለግላትም፤ የሚል በጐ ቃልን ከሚስቱ በመስማት ሊያስመጣት ሠራዊቱን በላከበት ቀን መላእክት በክንፎቻቸው ተሸክመው ወስደው ዓለመ ነፍሳትን አስጐበኙት።

በገነት የሚኖሩ ነፍሳትንም ዛቲ ይእቲ ሕይወትክሙ ኪያሃ ሰብሑ፤ ሕይወታችሁ እርሷ ናትና እርሷን አመስግኑ ብለው ሰጧቸው፤ እነርሱም ተቀብለው "የተሸከመችሽ ማሕጸን ብፅዕት ናት፤ አንችን ያጠባች ጡት የተባረከች ናት፤ የእኛም አንቺን ያዩ ዓይኖቻችን ንጹሐን፤ ክቡራን ናቸው" እያሉ ከአዳም ጀምሮ እስከዚያችኛዋ ቀን የሞቱ ሰዎች ነፍሳት ይህን ዝማሬ እየተቀባበሉ አመሰገኗት። የወሰዳት መላክ መልሶ ወደ ቦታዋ እስካደረሳት ጊዜ ድረስ በልጇ ቤዛነት የተዋጁት ሁሉ ዘመሩላት።

ይህ የሆነው ጌታ የእናቱን ተድላ ነፍሷን እንጂ ተድላ ሥጋዋን ስለማይሻ ነው፤ ከሮም ቤተ መንግሥት ለሚበልጥ ክብር ያጫት እናቱን ክብሯ በምድራዊ ዙፋን እንዲገለጽ አይፈልግምና ይልቁንም በሰማይ ባለችው መንግሥቱ በቀኙ በተዘረጋው ዙፋን ተቀምጣ በክብር ልትገለጥ ነው እንጅ።

60. ተአምረ ማርያም

ምዕራፍ ፭

ጊዜ ዕረፍታ ለሶልያና

ዮሐንስ እያገለገላት እርሷም እንደ እናት እያጽናናችው ለ15 ዓመት ቆየች፤ ከዚህ በኋላ ለሰው ሁሉ እንደታዘዘ በተወለደች በ64 ዓመት ጥር 21 ቀን 49 ዓ.ም በሞት ወደ ወዲያኛው ዓለም ተወሰደች።

መላው ዘመኗ ሲሰላ እንዲህ ነው፤ ጌታን ሳትጸንስ 15 ዓመት ማለትም 3 ዓመት ከእናት ከአባቷ ቤት 12 ዓመት በቤተ መቅደስ፤ ጌታን ጸንሳ ሳለች 9 ወር ከ5 ቀን ጌታን ከወለደች በኋላ 33 ዓመት ከሦስት ወር ጌታ ካረገ በኋላ 15 ዓመት ሲደመር 3+12+9 ወር+33 ዓመት ከሶስት ወር =64 መላው ዘመኗ ይህ ሆኖ ሳለ ጌታን ከመውለዷ አስቀድሞ 15 ዓመት ጌታን ከወለደች በኋላ ወላዲተ አምላክ ተብላ እየተጠራች 49 ዓመት በምድር ቆይታለች።

በዚህም 15 ዓመት ሲሆናት ለአምላክ እናትነት መታጨቷ የሔዋን ደኅንነቷን ዳግማዊት ሔዋን እርሷ መሆኗን ሲያጠይቅ ነው። ቀዳማዊ አዳም ሔዋንን ያጫት በዚህ እድሜዋ ነበር፤ ሔዋን የሕያዋን እናት የሚለውን መጠሪያ ስም የወጣላት ለመጀመሪያይቱ ሔዋን በዚህ እድሜዋ ነበር በትክክልም የሕያዋን እናት መባል የሚገባት እመቤታችን እንጂ ሔዋን አልነበረችም፤ የነ ቃኤል እናት ናትና። ስለዚህም በዚህ እድሜዋ ለቀዳማዊው አዳም ለክርስቶስ ታጨች።

ጌታንም ከወለደች በኋላ የቆየችው 49 ዓመት መሆኑ አንድ ኢዮቤልዩ ነው ይህም ማለት ሰባት ሱባዔ ማለት ሲሆን በዚህም እመቤታችን

በነቢያት ትንቢት በአበው ሱባዔ የተገኘች የአባቶቻችን የጸሎት ውጤት መሆኗን እንረዳለን

የእመቤታችን ምሳሌ የሆነችው ሐመረ ኖኅ እድሜዋ በኢዮቤልዩ ቁጥር ነው የተሰላ። ከዚያን ጀምሮ 64 ቁጥር ታላቅ ቁጥር ሆነ፤ እነ ቅዱስ ኤፍሬም ጸሎተ ማርያምን ያደርሱ የነበረው በዚህ ልክ ነበር፤ በኋላም ውዳሴዋን የደረሱላት እርሷም ፈቃዷ ሆኖ ያስደረሰችው በዚህ ልክ ነው፤ ዛሬም በበረሐ የወደቁ መናንያን ለመታሰቢያ በዚህ ቁጥር ልክ ይጸልያሉ።

ዘመኑ ጥቂት ቢሆንም በመከራ የተፈጸሙ ዓመታት ናቸው ከዚህ የመከራ ዓለም ሲያሳርፋት ልጇ በግርማ መለኮት፤ በቅዳሴ መላእክት እርሷ ወደነበረችበት ቤት ወደ ዮሐንስ ቤት ወረደ። ጌታን የመጽነሷን ዜና በቤተ ዮሴፍ ሰማች፤ የልጇን ሞት በቤተ ዮሐንስ፤ ዛሬ ደግሞ የእርሷን ሞት በዚሁ ስፍራ ተነገራት።

ስለ ክብሯ ሊቀበላት የወረደው ጌታ ሐዋርያትን ከየ አህጉረ ስብከታቸው በፈጣን ደመና ሰበሰባቸው። እመቤታችንን እንዲሰናበቷት አዘዛቸው፤ ከዚህ በኋላ በአጸደ ሥጋ አይገናኙምና ሁሉም ደቀ መዛሙርት ዝቅ እያሉ ተሰናበቷት፤ በረከቷን ተቀበሏት፤ ወደ ፈጣሪ እንድታሳስብላቸው አደራ አሏት። ከዚህ በኋላ አባቷ ዳዊት ንግሥቲቱ በቀኝህ ትቀመጣለች..... የሚለውን መዝሙር እየዘመረላት ሰሎሞን ንዒ ርግብዬ እያላት ሌሎችም ነቢያት እያወደሷት፤ የሰማይ መላእክት ማንም ሊሰማው በማይችለው የምስጋና ቃል እየጠሯት ሳሉ በልጇ ቃል ቅድስት ነፍሷ ከሥጋዋ ተለይታ በተወደደ ልጇ

እቅፍ ላይ ተቀመጠች። ቀኑ ልዩ ነበር በአጸደ ሥጋ የነበሩ ሐዋርያት በአጸደ ነፍስ ከነበሩ ነቢያት ጋር መሬታውያን ከሰማያውያን ጋር አንድ ሆነው የዘመሩበት ነውና።

ነፍሷ ወደ ፈጣሪ ከተመለሰች በኋላ ሐዋርያት ሥጋዋን ገንዘው ለመቅበር ወደ ጌቴሴማኒ ይዘዋት ሔዱ። "ከእንግዲህስ ዕረፉ" ብሎ ጌታችን በመከራው ምሽት ለመጀመሪያ ጊዜ በእርሱ ድካም ሰው እንዲያርፍ የተናገረባት፤ "አባት ሆይ ቢቻልስ ይህች ጽዋዕ ከእኔ ትለፍ" ብሎ በመጸለይ የሞትን ጽዋ ከሰው ያሳለፈባት ቦታ ናት
የሁሉ ነገራችን መነሻም እመቤታችን በመሆኗ ወደ ዚህ ሥፍራ ለመቃብር ወሰዷት። ጌቴሴማኒ ከመድረሳቸው በፊት ግን አይሁድ ከጕዳና ላይ በጠላትነት ተነሡባቸው በእሳት አቃጥለን በድንጋይ ቀጥቅጠን እናጠፋለን ወደ መቃብር እንዳትደርስ እናደርጋታለን አሉ። በሕይወት ሳለች ያነሡ እንደነበር ከሞተችም በኋላ ተቃውሞአቸው አላቆመም። ቅዱሳን እንደማይሞቱ በዚህ ይታወቃል ቢሞቱማ ኖሮ የሞተን ሰው ምን ይሠራል ብሎ ማን ይቃወመዋል።

በክርስቶስ የሚሞቱት ግን ያንቀላፉት ለዕረፍት እንጂ ለሞት አይደለምና ከሞቱም በኋላ ሥራ ይሠራሉ፤ ጠላታቸውን ይጎዳሉ ወዳጆቻቸውን ይጠቅማሉ ከዚህም የተነሣ አጋንንት ሰዎችን እያሥነሡ ሲጣሏቸው ይኖራሉ።

የልጇን ትንሣኤ እንደሰማን የእርሷንም ትንሣኤ ልንሰማ አይደለም? ብለው በመፍራት እናጠፋለን ብለው የቀረቡትን አይሁድ በመቅጣት የእግዚአብሔር መላክ ዮሐንስን ጨምሮ እሳተ መለኮትን በመሸከም

የከበረ ሥጋዋን በገነት ካሉት ዕፀዋት መካከል አስቀመጠው፤ ዮሐንስ በሕይወት ዘመኗ እንዳገለገላት ከሞተች በኋላም ማዕጠንቱ ወርቁን ይዞ በማጠን አገለገላት።

ከጥር 21 እስከ ሐምሌ 30 በየአህጉረ ስብከታቸው የነበሩ ሐዋርያት ከነሐሴ አንድ ጀምሮ በጋራ ስለ እመቤታችን ከፊታቸው መሰወር ሱባዔ ገቡ፤ ካንዱ ከዮሐንስ በስተቀር ያለችበትን የሚያውቅ አልነበረምና። ሁለት ሱባዔ እንደ ጸሙ ቀኑ ነሐሴ 14 ቀን 49 ዓ.ም ዕለቱ ዕለተ እሁድ ነበር የእግዚአብሔር መላክ አምጥቶ ሰጥቶአቸው እነሱም ደስ ብሎአቸው ተቀብለው ዕለቱን ቀብረዋታል የተነሳችውም እነሱ ቀብረዋት ከሄዱ በኋላ ነሐሴ 14 ቀን 49 ዓ.ም በዚሁ ዕለት በዕለተ እሁድ ነው አልዋለችም አላደረችም።

ከመ ትንሣኤ ወልዳ የሚል ንባብ ይገኛልሳ ያሉ እደሆነ ይህ ስለ ሁለት ነገር ነው።

1ኛ በዕለተ እሁድ መነሣቷን ሲያይ ነው ልጇ የተነሣው በዕለተ እሁድ ነውና።

2ኛ በሐዲስ ሥጋ (ዳግመኛ ሞት የማያሰጋው ሥጋ) መነሣቷን ያጠይቃል ከፍጡራን መካከል ዳግም ሞት የሌለበት አማናዊ ትንሣኤ የተነሣ ከእመቤታችን በቀር ሌላ ፍጡር የለምና። ትንሣኤዋ ከነ አልአዛር ትንሣኤ ልዩ መሆኑን ለማስረዳት ከመትንሣኤ ወልዳ ተብሏል እንጂ በሦስተኛው ቀን ተነሣች ለማለት አይደለም።

በሦስተኛው ቀን መነሣቷ የሚያመጣው ችግር

በአንዳንድ የመጻሕፍት ትርጓሜ ትምህርት ቤቶች እስካሁንም ድረስ በወንበር የሚነገረው እመቤታችን ሦስት ቀን ሦስት ሌሊት በከርሰ መቃብር እንደቆየች ነው። ምን አልባት በዚህ ነገር ልዩ ሊሆን የሚችለው የዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ጉባኤ ነው። ነገር ግን በየገዳማትና አድባራት ያሉት ሊቃውንት እንደገና እንዲያዩት እያሳሰብሁ ሦስተኛውን ቀን እኔም ሆንሁ ያስተማሩኝ መምህር ለምን እንደማንቀበለው ጥቂት ነገር ልናገር፤

በሦስተኛው ቀን ተነሣች ከተባለ የእሁድ ሣልስቱ ማክሰኞ ነው፤ ማክሰኞ ደግሞ እንደነ አልአዛር ዓይነት ትንሣኤ ካልሆነ አማናዊ ትንሣኤ አይደረግም አማናዊ ትንሣኤ የሚደረገው በዕለተ እሑድ ብቻ ነው። ምክንያቱም ትንሣኤ ዘጉባኤ የሚደረግበት በዕለተ እሁድ ስለሆነ ነው። ስለዚህ በዕለተ ሠሉስ ተነሣች ማለት ትንሣኤዋ በብሉይ ሥጋ ነው ማለት ነውና መጠንቀቅ ያስፈልጋል።

እንዲያውም መምህር ማዕበል ፈጠነ ‹‹ልሳነ ሊቃውንት›› በተባለው ያልታተመ መጽሐፉ የዚህን ዓለም ፍጻሜ ሲገልጽ ከሰኞ እስከ ቅዳሜ ያሉ ዕለታት ዕለተ ሙታን ናቸው ።በመጨረሻ ዘመን የማታልፍ ዕለተ እሁድ ብቻ ናት ።በአቡሻክር ቀመርም ሲቀመሩ ዕለታቱ ሁሉ ተገድፈው ሲያልቁ እሁድ ብቻ ትቀራለች። ይህችም አልፋና ያሜጋ ትባላለች ይህችም ዕለት ለኖርነው ዓለም መጀመሪያ እንደ ሆነች ወደ ፊት ለሚመጣው ዓለም ለመንግሥተ ሰማይም ቀዳሚት ናትና ከትንሣኤ ዘጉባኤ በኋላም ትኖራለች ።ለው ዳግም ሞት እንደሌለበት ይታወቅ ዘንድ በዚች ዕለት አዲስ ሕይወት ይጀምራል ይላል ።

እመቤታችንም በሐዲስ ተፈጥሮ ለተፈጠረው ትውልድ የመጀመሪያ ሆና በእግዚአብሔር ፊት በመገኘቷ ተስፋ ለምናደርጋት ዓለማችን መንግሥተ ሰማያትም የመጀመሪያ አደርጎ ነፍስና ሥጋ ተዋሕደው በአንድነት በሚኖሩበት መንግሥተ ሰማያት እንድትኖር አደረጋት።

እኛ ግን በተረዳ ነገር አበው መምህራነ ቤተክርስቲያን በነገሩን መሠረት የተነሳችው ነሐሴ 14 ቀን 49 ዓ.ም በዕለተ እሁድ እንደሆነ እናምናለን። የአዳም ባሕርይ የአምላክን ባሕርይ ገንዘብ ያደረገባት ሰማያዊው መሬታዊ ሲሆን መሬታዊው ደግሞ ሰማያዊ የሆነባት በኋላም በጌታ ትንሣኤ የሰው ልጆች ባሕርይ ትንሣኤ ከተረጋገጠበት ከዕለተ እሁድ በቀር ሌላ ቀን የለምና የሰው ልጆች ባሕርይ ደግሞ የእመቤታችንም ባሕርይ መሆኑን ልብ ይሏል።

ምን አልባት ዛሬ ለምንድን ነው ፍልሰተ ሥጋዋን ነሐሴ በገባ በ16ኛው ቀን የምናከብረው የሚል ጥያቄ ከተነሣብም ነገሩ ሌላ ነው፤ ምሥጢሩ እንዲህ ነው፤ ቀደም ሲል በጠቀስነው እና እመቤታችን በተነሣችበት ዕለት ከደቀ መዛሙርቱ መካከል ከቶማስ በስተቀር ያያት ማንም አልነበረም። ቶማስ ብቻ ከሀገረ ስብከቱ ወደ ኢየሩሳሌም በደመና ተጭኖ ሲመለስ እመቤታችንን መላእክት በብርሃን ሠረገላ ሲያሳርጓት አገኛት።

የመግነሟን ሰበን ለምልክት ለምስክርነትም ቢሉ ሰጥታው ነበርና በዓመቱ ማለትም በ50 ዓ.ም ከነሐሴ አንድ ቀን ጀምረው ሁሉም ሐዋርያት ከቶማስ በጆሯቸው የሰሙትን ዜና ትንሣኤዋን በዓይናቸው ለማየት እንደገና ሱባዔ ጀምረዋል፤ ነገርን ሁሉ በጊዜው ውብ አድርጉ የሚሠራው ጌታ በ16ኛው ቀን ከእናቱ ከቅድስት ድንግል ማርያም

ጋር በክብር ተገልጾ ቀድሶ እንዳቆረባቸው እና እንደባረካቸው የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ፤ ስለዚህም አባቶቻችን ሐዋርያት ትንሣኤዋን ያዩበትን ቀን ፍልሰተ ሥጋሃ ብለን እናከብራለን፤ እናም የነሐሴ አስራ ስድስተኛው ቀን ትንሣኤዋ የተገለጠበት ቀን እንጅ የተነሣችበት ቀን አይደለም።

ነቢዩ ዳዊት በትንቢት እንደተናገረው ጌታ ከሙታን መካከል ከአብ ቀኝ ለመቀመጥ ማለትም በክብር በአብ ዕረና ለመኖር እንደተነሣ እናቱ ድንግል ማርያምም ዳግመኛ ሞት በማያስፈራው ትንሣኤ በልጇ ቀኝ ለመቀመጥ ተነሣች። "ተንሥእ እግዚኦ ውስተ ዕረፍትከ አንተ ወታቦተ መቅደስከ፤ አቤቱ ምዕመናን ወደ ምታሳርፍበት ወደ መንግሥተ ሰማያት ተነሥ አንተ እና የታቦትህ መቅደስ" መዝ 131፥8 በዚህ ዐረፍተ ነገር ውስጥ ነቢዩ የተናገረው ስለ ጌታ እና ስለ እመቤታችን ትንሣኤ ነበር፤ መቅደስ የተባለች ኢየሩሳሌም ስትሆን ታቦት የተባለች ደግሞ ማኅደረ እግዚአብሔር ድንግል ማርያም ናት።

ከዚያች ዕለት ጀምሮ ለዘለዓለም በሰማዕትነቷ ከሰማዕታት፤ በትሕትናዋ በትዕግሥቷ ከጻድቃን፤ በድንግልናዋ ከደናግል በነቢይነቷ ከነቢያት የምትቆጠረው እመ ሰማዕታት/ ምክሐ ደግናል ማኅደረ ንጹሐን አክሊለ ጻድቃን ተብላ የምትጠራ እመቤታችን ድንግል ማርያም በእግዚአብሔር ፈቃድ በተሰጣት ሥልጣን በቀኙ ተቀምጣ ትኖራለች። ያ ማለት በመንግሥተ ሰማያት ማለት ነው። ለእግዚአብሔር ቀኝ እና ግራ የለውምና።

ሰአሊለነ ቅድስት አሜን

ዋቢ መጻሕፍት

1ኛ ፱ወ፩ መጽሐፍ ቅዱስ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት የ1980 ዕትም
2ኛ አንድምታ ወንጌል ትንሣኤ ዘጉባኤ
3ኛ የጳውሎስ መላዕክታት ትርጓሜ ትንሣኤ
4ኛ ትርጓሜ ወንጌል (ግእዝ በግእዝ) ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንደተረጎመው
5ኛ የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክታት ትርጓሜ (ግእዝ በግእዝ)
ፊሎጎስ እንደተረጎመው
6ኛ ድርሳነ ቂርሎስ እና ጰላድዮስ አንድምታ (የእጅ ጽሑፍ)
7ኛ ሃይማኖተ አበው ንባቡና ትርጓሜው ትንሣኤ ዘጉባኤ 19....ዕትም
8ኛ ሃይማኖተ አበው አንድምታ (የእጅ ጽሑፍ)
9ኛ አሪት ዘፍጥረትና ዘፀአት አንድምታ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት የታተመ
10ኛ ሠለስቱ መጻሕፍተ ሐዲሳት ትንሣኤ ዘጉባኤ ፰፻፯ ዕትም
11ኛ ነገረ ማርያም ታላቁ የብራና
12ኛተአምረ ማርያም ንባብና ትርጓሜው
13ኛ ገድለ ቅድስት ሐና ያልታተመ
14ኛ ውዳሴ ማርያም ምስለ ቅዳሴ ማርያም አንድምታ የእጅ ጽሑፍ(የዲማ አብነት)
15ኛ መጽሐፈ ምሥጢር ንባብና ትርጓሜው በመ/ር ሕሩይ ኤርምያስ
ተተርጉሞ በአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫና በአባ በጸሎተ ሚካኤል አንድነት
ገዳም የታተመ
16ኛ ዜና ዮሐንስ መጥምቅ ያልታተመ
17ኛ ዜና እስክንድር ንጉሥ የብራና
18ኛ ፫ቱ የቅዱስ ያሬድ ፀዋትዎ ዜማዎች ድጓ፣ ጸመ ድጓ፣ምዕራፍ፣
ዝማሬና መሥዋዕት
19ኛ ልሳነ ሊቃውንት ያልታተመ በመምህር ማዕበል ፈጠነ
20ኛ ኩሉሐ ሃይማኖት (አድማሱ ጀምበሬ መላከ ብርሃን)
21ኛ መድሎተ አሚን (አድማሱ ጀምበሬ መላከ ብርሃን)

ሕይወተ ማርያም ድንግል በሚል ርዕስ የተጠቀሰው መጽሐፍ እመቤታችን ከፅንሰቷ ወራት ጀምሮ እስከ ዕለተ እረፍቷ የተንዘፍዝፈበትን የሕይወት መስመር በምሥጢራዊ አገላለጥ ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ መጽሔተ ብርሃን ሆኖ አግኝቼዋለሁ፤ አቀራረቡም ትምህርተ አበውን የተከተለ፣ በትርጓሜ የበሰለ፣ ትውፊተ አበውን አጉልቶ የሚያሳይ ቅዱስ መጽሐፍን መሠረት ያደረገ በመሆኑ እውነተኛ የቤተ ክርስቲያኒቱን ልጆች ያስተምራል ብዬ አምናለሁ፤ በጸሐፌውም መንፈሳዊ ኩራት ይሰማኛል፤ ብዙዎች ስለ እመቤታችን መስበክና መዳፍ እንደ ነውር ተቆጥሮባቸው በተፈተኑበት ዘመናችን በቋንቋ አጠቃቀሙ በአቀራረቡ የተዋሕዶ ልጆችን የሚያበረታታ ጽሑፍ በመዳፋቸው አደንቃቸዋለሁ፤ ለወደፊቱም ብዙ እጠብቃለሁ፤ አነሣስቶ ሳስጀመራቸው፣ አስጀምሮም ሳስፈጸማቸው ለልዑል እግዚአብሔር ክብርና ምስጋና ይሁን።

ስባ አብርሃም

የምዕራብ ጎጃም ሀገረ ስብከት ሲቀ ጳጳስ

ደራሲው ከዚህ በፊት ያዘጋጇቸው መጻሕፍት

ዕኛ አረኛ ወይስ ምንደኛ?

ፀኛ በሞት የተገለጠ ፍቅር

ወደ ፊት የሚታተሙ

ዕኛ ታዕደኮስ

ፀኛ የሰው ሕይወቱ.....?

ለእግዚአብሔር የተሰጠ ሕይወት በማጎፀን ውስጥ እንዳለ ሕፃን ነው።

ከቡራን አንባብያን ሆይ! በዚህ መጽሐፍ ላይ የተመዘገቡ ቃሳትን ካነበባችሁ በኋላ በቀጣይ ስሚዘጋጀው ‹‹ታዕደኮስ›› ስተሰኘውና በነገረ ማርያም ላይ ስሚነሡ ጥያቄዎች መልስ ስሚሰጠው መጽሐፍ ዝግጅት ያግዘን ዘንድ በእመቤታችን ላይ የሚነሣ ማንኛውንም ጥያቄዎችንና አስተያየቶች በተከታዩ አድራሻ ብትክልን በምስጋና የምንቀበል መሆኑን እንገልጻለን።

E-mail:- simakonemelak@gmail.com

Mobile:- +2519 12 17 88 51

ይክን-ሰነ አታሚዎች 0911 19 89 28

ዋጋ : 40.00